www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍተ ፡ መነኰሳት ።

ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ።



ፈለኽስዩስ

ገብረ ፡ ክርስቶስ

ከቀድሞ ፡ አባቶች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡
ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ ንባባቸውንና ፡ ትርጓሜያቸውን ፡
በአንድነት ፡ አድርጐ ፡ ተስፋ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
ዘሀገረ ፡ ቡልጋ ፡ አዘጋጀው ።

በተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት
፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

መ ግ ለ ጫ ።

ይህ ፡ ፈ ል ነ ባ ህ ይ ስ ፡ የ ተ ባ ለ ፡ መ ጽ ሐ ፍ ከ ጥ ን ት ፡ የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ፡ ሊ ቃ ው ን ት ፡ የ ጸ ፉ ት ና ፡ የ ተ ረ ጐ መ ት ፡ የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ፡ ቅ ር ስ ፡ እ ን ዳ ይ ጠ ፋ ፡ ቤ ተ ፡ ክ ር ስ ቲ ያ ን ፡ በ መ ጽ ሐ ፍ ፡ እ ጦ ት ፡ እ ን ዳ ት ች ገ ር ፡ የ ተ ለ መ ደ ው ፡ ጸ ሎ ት ፡ እ ን ዳ ይ ታ ጐ ል ፡ መ ነ ኰ ሳ ት ፡ ዘ ወ ትር ፡ እ የ መ ረ መ ሩ ፡ እ ን ዲ ጠ ቀ ሙ በ ት ፡ ታ ተ መ ።

ከ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ. ም ጀ ም ሮ ፡ የ ት ም ህ ር ት ና የ ጸ ሎ ት ፡ መ ጻ ሕ ፍ ት ፡ አ ዘ ጋ ጅ ና ፡ አ ከ ፋ ፋ ይ ተ ስ ፋ ፡ ገ ብ ረ ፡ ሥ ላ ሴ ፡ ዘ ሀ ገ ረ ፡ ቡ ል ጋ ።

ሥርዓተ ፡ ብሕትውና ፡ በጳውሊ ፤ ሥርዓተ ፡ ምንኵስና ፡ በእንጦኒ ፡ ተዝምሯል ። የጳውሊ ፡ አባቱ ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ነበረ ። ሲሞት ፡ ገንዘቡን ፡ በታላቅ ፡ ወንድሙ ፡ እጅ ፡ አድርጎ ፤ ኋላ ፡ መጠነ ፡ አካል ፡ ሲያደርስ ፡ ከፍለህ ፡ ስጠው ፡ ብሎ ፡ ተናዘ ፡ አረፈ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሰ ፡ ጊዜ ፤ ያባትን ፡ ሞቱን ፡ አይወዱ ፤ ረጀቱን ፡ አይሰዱ ፡ እንዲሉ ፤ ደረስሁ ፡ ልጅ ፤ ፈላሁ ፡ ጠጅ ፤ ያባቴን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍለህ ፡ ስጠኝ ፡ አለው ። አይሆንም ፡ አለ ፤ ምነው ፡ ቢለው ፤ ታበላሻለህ ፡ እንጂ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለ ። አላበላሽም ፡ ስጠኝ ፡ አለው ። ግድግ ፡ ካልኸኝ ፡ ብሎ ፤ ብዙውን ፡ አስቀርቶ ፡ ጥቂቱን ፤ መልካካሙን ፡ አስቀርቶ ፡ ተራ ፡ ተራውን ፡ ሰጠው ። እሱም ፡ በዚህ ፡ ተናዶ ፡ ዳኛ ፡ አወጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲሔድ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ያለ ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ሙቶ ፡ እኮሉ ፡ ሲያለቅሱ ፤ እኮሉ ፤ ሲፈቱ ፡ አገኘ ። ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ። ባለ ፡ ጸጋ ፡ ነበረ ፤ ሙቶ ፡ ይለቀሳል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ከነዚያ ፡ አንዱን ፡ እስኪ ፡ ምከረኝ ፤ ከወንድሜ ፡ ጋራ ፡ በገንዘብ ፡ ተጣልቼ ፡ ዳኛ ፡ አወጣለሁ ፡ ብዬ ፡ መጥቼ ፡ ነበረ ፡ ቢለው ፤ አባትህ ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ነበር ፡ ጥሎት ፡ ሞተ ። ይኸም ፡ የምታየው ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ነበር ፤ ጥሎት ፡ ሞተ ። አንተስ ፡ ብታመጣው ፡ ነግ ፡ ጥለኸው ፡ ትሞት ፡ የለምን ፡ ተወው ፡ ይቅርብህ ፡ አለው ። እውነትህ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ትቶት ፡ ተመልሷል ፡ ይላሉ ። ቦ ፡ እንዲያው ፡ እሱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲለቀስ ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲፈታ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፤ አባቱ ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ነበረ ፤ ጥሎት ፡ ሞተ ። እኔስ ፡ ጥዬው ፡ ልሞት ፡ አይደለምን ፡ ልተወው ፡ ይቅርብኝ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፤ ወንድሜ ፡ ገንዘቡ ፡ አንተን ፡ ይምሰል ፡ ትቼልሃለሁ ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ላባቱ ፡ ወንጌል ፡ ዮሐንስ ፡ ነበረችው ፤ ይህችን ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ ያችን ፡ ብቻ ፡ ይዘ ፡ ሄደ ። ምጣላል ፡ ቦታ ፡ ፈልጎ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ከዚያ ፡ ገብቶ ፡ አደረ ። ጌታም ፡ ለፈተና ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ምግብ ፡ ነሣው ። ያችን ፡ ወንጌል ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ፡ ጎልጎታ ፡ ከወሀ ፡ ላይ ፡ እየ ፡ ደገመ ፡ ጠበሉን ፡ እየ ፡ ቀመሰ ፡ ምክንያት ፡ ሁኖት ፡ አጽንቶት ፡ ሰነበተ ። በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ መንፈቀ ፡ ሳብስት ፡ ወርዶለት ፤ ፈጽሞ ፡ ሳይለዩ ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፤ ፈጽሞ ፡ ቢለዩማ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ተአምራት ፡ በተደረገ ፡ ብሎ ፤ አናብስት ፤ አናምርት ፤ አክይስት ፤ አቃርብት ፡ ካሉበት ፤ ነቅዐ ፡ ማይ ፤ ልምላሜ ፡ ዕፅ ፡ ከሌለበት ፤ ድሩክ ፡ ለተዓቅቦ ፡ ይለዋል ፤ ዘር ፡ ተክል ፡ ከማይገኝበት ፡ ከጽኑ ፡ በረሃ ፡ ሄደ ። የዚህን ፡ የጳውሎስን ፡ ታሪክ ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ ለመጨረስ ፡ እናመጣዋለን ።

ይኸም ፡ እንጦንዮስ ፡ አባቱ ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ነበረ ። አገሩንም ፡ ጽሚድ ፡ ዘአምፈለገ ፡ አቅበጣ ፡ ይላታል ፡ ስንክሳር ። ግን ፡ በተለየ ፡ ስሟን ፡ ቅማ ፡ ይላታል ፤ ቅምንም ፡ ቅማንም ፡ ይላል ። ይህችም ፡ ወሀ ፡ ገብ ፡ ናት ፤ በቀሐ ፡ አጠገብ ፡ ልደታ ፡ እንዳለች ፡ ሁሉ ፡ የወሀ ፡ አጸገብ ፡ ናትና ። ሾላው ፤ ወርክው ፡ ዛፉ ፡ ሁሉ ፡ ነበረባት ። ዋሻም ፡ ክዚያው ፡ አለባት ። እሱም ፡ በሕግንቱ ፡ ከትምርት ፡ ቤት ፡ ሄደ ። ባገራቸው ፡ ቅዳሴ ፡ ለመስማት ፡ ለጸሎት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍጹም ፡ ትምርት ፡ እጅግ ፡ አይማሩምና ፤ ቶሎ ፡ ተምሮ ፡ መጣ ። ሲመለስ ፡ አባቱ ፡ ሕግ ፡ ግባ ፡ አለው ፤ አይሆንም ፡ አለ ። ምነው ፡ ቢሉ ፤ ፈቃዱ ፡ እንደ ፡ ቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ እንደነ ፡ ኤልያስ ፤ እንደ ፡ ኋላ ፡ ሰዎች ፡ እንደነ ፡ ዮሐንስ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፤ ከሴት ፡ ርቆ ፡ በድንግልና ፡ መኖር ፡ ነውና ። ግድ ፡ አለው ፤ ግድግ ፡ ካልኸኝ ፡ አንተስ ፡ ባልኸው ፤ እኔስ ፡ ባልሁት ፡ ይሆናልን ፡ ፍቀድልኝኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አመልክቼ ፡ ልምጣ ፡ እንጂ ፡ አለ ። ደግ ፡ አመልክተህ ፡ ና ፡ አለው ። ሂዶ ፡ ከዚያች ፡ ዋሻ ፡ ገባ ። ወዲያው ፡ አባትህ ፡ ታመመ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፤ ቢሔድ ፡ አርፎ ፡ አገኘው ። ገንዘቡን ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ አስቀድሞ ፡ ይመጸውታል ። መገመሪያ ፤ ያባቱ ፡ በድኑ ፡ ከመቃብር ፡ ሳይከተት ፡ መብሉ ፡ በከርሠ ፡ ርኁባን ፤ መጠጡ ፡ በጕርሜ ፡ ጽሙዓን ፤ ልብሱ ፡ በዘባነ ፡ ዕሩቃን ፡ ይከተት ፡ ብሎ ። ሁለተኛ ፡ ወዲያ ወርድ ፡ ምስሌሁ ፡ ኵሉ ፡ ክብረ ፡ ቤቱ ፡ ያለውን ፡ የነቢዩን ፡ ቃል ፡ ያውቃልና ። ሦስተኛ ፤ የሚመኝን ፡ ነውና ፡ ልብ ፡ እንዳይቀረው ። ሲመጸውትም ፡ አይቱ ፡ ኃይልከ ፤ አይቱ ፡ አእምሮትከ ፤ አይቱ ፡ ፍጥነትከ ፡ እያለ ፡ መጽውቶታል ። ኃይልከ ፡ ማለቱ ፤ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ሥራ ፡ ልሥራ ፡ ቢል ፡ አይቸግረውምና ፤ ይህ ፡ ወዲት ፡ አለ ። አእምሮትከ ፡ ማለት ፤ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ከብቱን ፡ ቁጥሮ ፤ በደብዳቤ ፡ ጽፎ ፤ ዐውቆ ፡ ዐውቆ ፡ ያኖራልና ፤ ይህ ፡ ወዲት ፡ አለ ። ፍጥነትከ ፡ ማለ

www.ethiopianorthodox.org

ት ፤ ባለ ፣ ጸጋ ፣ ያሰበው ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ ፈጥኖ ፣ ይደ
ረጋልና ፤ ይህ ፣ ወዴት ፣ አለ ፣ እያለ ፣ ጨርሶ ፣ መጽ
ውቶ ፤ አባቱን ፣ አስቀብሮ ፣ ሲያበቃ ፣ ቅዳሴ ፣ ለመ
ስማት ፣ ከቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ገብቶ ፣ ቆመ ። ቂሱ ፣
ወንጌል ፣ ብሎ ፣ ወጥቶ ፣ ሲያነብ ፤ እመሰ ፣ ፈቀድከ ፣
ትኩን ፣ ፍጹመ ፣ ሚጥ ፣ ሁሎ ፣ ንዋየከ ፣ ወሀብ ፣ ለነ
ዳያን ፤ ወነሳ ፣ ትልወኒ ፣ ያለውን ፣ ቃል ፣ ሰማ ። አ
ባ ፣ ለትጹን ፣ ዘገደፋ ፣ ያለውን ፤ ስምዖን ፣ ዘዓምድ ፣
ምንት ፣ ይበቍዖ ፣ ለሰብእ ፣ ያለውን ፣ እንደ ፣ ሰማ ።
ይኸ ፣ አዋጅ ፣ የተነገረ ፣ ለኔ ፣ እንጂ ፣ ነው ፣ ብሎ ፤
እሳት ፣ ነበረችው ፤ ከደብረ ፣ ደናግል ፣ አስጠግቶ ፣
ሂዶ ፣ ፊት ፣ ከነበረባት ፣ ዋሻ ፣ ገብቶ ፣ ተቀመጠ ።

ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ወለተ ፣ አረሚ ፣ ሠና
ይተ ፣ ላህይ ፣ ይላታል ፤ ከደንገጡሮቿ ፣ ጋራ ፣ በቀት
ር ፣ ጊዜ ፣ መጥታ ፣ ከዛፉ ፣ እግር ፣ ከወሀው ፣ ጻር ፣
አረፈች ። ፊት ፣ እሲን ፣ አጸቢት ፣ ኋላ ፣ እስበሳቸው ፣
ይተጻጸቡ ፣ ገርመር ። እሱም ፣ ዕርቃናቸውን ፣ እንዳያ
ይ ፣ ዓይነ ፣ ሥጋውን ፣ ወደ ፣ ምድር ፤ ዓይነ ፣ ነፍሱ
ን ፣ ወደ ፣ ሰማይ ፣ አድርጎ ፣ ሲጸልይ ፣ ቆየ ። ያበቃ
ሉ ፣ ቢል ፤ የማያበቁለት ፣ ሆኑ ። ኋላ ፣ ደግሞ ፣ ቆይ
ተው ፣ ነገረ ፣ ጎፊር ፣ እያነሳሡ ፣ ይጨነዋወቱ ፣ ገርመ
ር ። ምነው ፣ እንግዲህማ ፣ አያበቃችሁም ፣ አትሒዱ
ምን ፣ አላቸው ። አ እንጦኒ ፤ አ እንጦኒ ፣ ለእመ ፣ ከ
ንከ ፣ መነኮሰ ፣ ሐር ፣ ጎበ ፣ ደብር ፤ መነሡሴ ፣ እን
ደ ፣ ሆንህ ፣ ከዚህ ፣ ምን ፣ አስቀመጠህ ፣ ከበረሃ ፣ አ
ትሒድምን ፣ አለችው ። ከዚያ ፣ አስቀድሞ ፣ መነሡ
ሴ ፣ አልነበረ ፤ መነ ኮስ ፣ ማለትን ፣ ከምን ፣ አምጥ
ታ ፣ ተናገረች ። ቢሉ ፤ ጌታ ፣ ለአበው ፣ ትምርት ፣ የ
ሚሆነውን ፣ ነገር ፣ በማናቸውም ፣ ባልበቃ ፣ ሰው ፣
አድሮ ፣ መናገር ፣ ልማዱ ፣ ነው ። ከዚያ ፣ ሁሉ ፣ አ
ንድ ፣ ካህን ፣ ዓረሚ ፤ ካህን ፤ ዓረምም ፣ ይለዋል ፣ ከአ
ንድ ፣ ሰው ፣ ጋራ ፣ ሲጫወቱ ፤ እናንት ፣ መነኰሳት ፣
ምሥጢር ፣ የማይገልጽላችሁ ፣ ከንጽሐ ፣ ልቡና ፣ እ
ንጂ ፣ ባትደርሱ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ እንደ ፣ ተናገረ ። አሁ
ን ፣ እሱ ፣ በምን ፣ ዐውቆ ፣ ነው ፣ ይላሉ ። አባ ፣ መቃ
ርስም ፣ አርድእቱን ፣ አስከትሎ ፣ ሲሔድ ፣ ሕፃናት ፣
ሲጫወቱ ፣ አገኘ ። እንደምን ፣ ቢሉ ፤ ቡድን ፣ ቡድን ፣
አለው ፤ ምን ፣ አለህ ፣ ቢለው ፤ አንድ ፣ ባለ ፣ጸጋ ፣ አ
ለ ፤ እሱ ፣ ይወደኛል ፤ እኔ ፣ እጸላዋለሁ ። ደጳሞ ፣ አ
ንድ ፣ ምስኪን ፣ አለ ፤ እሱ ፣ ይጠላኛል ፤ እኔ ፣ እወ

ደዋለሁ ፣ አለ ። ወአንከረ ፣ አባ ፣ መቃራ ፣ ይላል ፤
ሰምቶ ፣ አደነቀ ። አባታችን ፤ አሁን ፣ ከሊህ ፣ ሕ
ት ፣ ምን ፣ ፍሬ ፣ ነገር ፣ ሰምተህ ፣ ታደንቃለህ ፣ አ
ት ። ልጆቼ ፤ እንዲህ ፣ እንጂ ፣ አይደለም ፤ ባለ ፣
ጋ ፣ የተባለ ፣ ጌታ ፣ ነው ። እሱ ፣ ይወደኛል ፣ እኔ ፣
ጸላዋለሁ ፣ ማለት ፤ እሱ ፣ የኛን ፣ ድኅነት ፣ ይሻል ፤ እ
ኛ ፣ የሱን ፣ ፈቃድ ፣ አንፈጽምለትም ። ምስኪን ፣
ተባለ ፣ ዲያብሎስ ፣ ነው ። እሱ ፣ ይጠላኛል ፤ እኔ ፣
እወደዋለሁ ፣ ማለት ፤ እሱ ፣ የኛን ፣ ጥፋት ፣ ይወ
ል ፤ እኛ ፣ የሱን ፣ ፈቃድ ፣ እንፈጽምለታለን ፣ ማ
ት ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ እንደ ፣ ነገራቸው ። ቦ ፤ መነ ኰስ
ማለት ፤ ዘርሕቀ ፣ እምዓለም ፤ ወተፈልጠ ፣ እምሰ
እ ፣ ምውት ፣ ማለት ፣ ነውና ። ቦ ፤ እንዲያው ፣ እሱ
ከመነኰሰ ፣ ፈት ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ የማይገባ ፣ ነገ
ጎፈር ፣ ትናገሪያለሽን ፣ አላት ። ከሱ ፣ ሰምታ ፤ አ
ንጦኒ ፤ አ እንጦኒ ፣ እመሰ ፣ ከንከ ፣ መነኰሰ ፣ ሐር ፣ ጎበ
ገዳም ፣ አለችው ። ከዚህ ፣ አስቀድሞ ፣ ምንኩስና ፣
ለ ፣ እሱስ ፣ ቢሆን ፣ ከምን ፣ አምጥቶ ፣ ተናገረው ፣ ቢ
ሉ ፤ የሷን ፣ ሐተታ ፣ ለሱ ፣ ሰጥቶ ፣ መናገር ፣ ነው ።

ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ይኸው ፣ ምክር ፣ ተግሣጽ ፣ ሠ
ኖት ፣ አ እንጦኒ ፤ አ እንጦኒ ፣ እመሰ ፣ ከንከ ፣ መነኰ
ሰ ፣ ሐር ፣ ውስተ ፣ ደብር ፣ እያለ ፣ ራሱን ፣ እየ ፣ ገ
ሠጸ ፤ ፊቱን ፣ እየ ፣ ጸፋ ፤ ጽሕሙን ፣ እየ ፣ ነጨ ፣
ከዚያ ፣ ተነሥቶ ፣ አናብስት ፤ አናምርት ፤ አክይስት ፤
አቃርብት ፣ ካሉበት ፤ ነቅዐ ፣ ማይ ፤ ልምላሜ ፣ ዕዕ ፣
ከሌለበት ፤ ድሩክ ፣ ለተዓቅቦ ፣ ይላል ፤ ዘር ፣ ተክል
ከማይገኝበት ፣ ገዳመ ፣ አትፊህ ፣ ሐዲ ። የዚህ ፣ ሠ
ንገዱ ፣ ፍለጋ ፣ የለውም ፤ አሸዋ ፣ ላሸዋ ፣ ነው ። ነጋ
ድያን ፣ ሲጓዙ ፣ የወደቀውን ፣ ያህያና ፣ የግመል ፣ ፋ
ንድያ ፣ እያዩ ፣ በዚያ ፣ ምልክት ፣ ይሔዳሉ ። በረሃነ
ቱም ፣ ጽኑ ፣ ነው ። ከሐሩሩ ፣ ጽናት ፣ የተነሣ ፣ በቀት
ር ፣ ጊዜ ፣ ከደንጊያ ፣ ላይ ፣ ተልባ ፣ ቢያሰጡ ፣ ይቄላ
ል ። እሱም ፣ ከዚያ ፣ ሂዶ ፣ ሲጋደል ፣ አጋንንት ፣ ዖ
ር ፣ አጸኑበት ። አ ሕጹጸ ፣ መዋዕል ፣ እፎ ፣ ደፈርከ ፣
ዝየ ። ከዚህ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ደፍረህ ፣ መጣህ ፤ አባ
ም ፣ ከወጣበት ፣ ገነት ፣ እንጂ ፣ እገባ ፣ ብሎ ፣ ነው ፣
ብለው ፣ ዘበቱበት ። እሱም ፣ በትሕትና ፣ ይዋጋቸዋ
ል ። መሆንማ ፣ ይሆን ፣ ብላችሁ ፣ ነውን ፤ እናንት ፣
ብዙ ፤ እኔ ፣ አንድ ፣ ብቻዬን ። እናንት ፣ ረቂቃን ፤ እ
ኔ ፣ ጻዙፍ ። እናንት ፣ ኃያላን ፤ እኔ ፣ ደካማ ፤ በኃይ
ል ፣ እግዚአብሔር ፣ ብችላችሁ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ያለዚ
ያስ ፣ አልችላችሁም ፣ እያለ ፣ በትሕትና ፣ ሲዋጋቸው ፣
ኖረ ። እነሱም ፣ እንዲህ ፣ እያሉ ፣ ያር ፣ አጸኑበት ።

ከዕለታት ፣ ባንድ ፣ ቀን ፣ ይኸን ፣ ያር ፣ አልቻ
ልሁትም ፤ ልሒድ ፣ እንጂ ፣ ብሎ ፣ ሲያስብ ፣ አደረ ።
ማለዳ ፣ በትረ ፣ ሆሣዕና ፣ ነበረችው ፤ ያችን ፣ ይዞ ፣
ከደጃፉ ፣ ላይ ፣ ቁሞ ፤ እንዳይቀርም ፣ ያሩ ፣ ትዝ ፣ ት
ዝ ፣ እያለው ፤ እንዳይሔድም ፣ በዓቱ ፣ እየ ፣ ናፈቀ
ው ፤ አንድ ፣ እግሩን ፣ ከውሥጥ ፤ አንድ ፣ እግሩን ፣
ከአፍአ ፣ አድርጎ ፣ ሲያወጣ ፣ ሲያወርድ ፤ መልአኩ ፣
የሰሌን ፣ ቆብ ፣ ደፍቶ ፤ የሰሌን ፣ መዋረፊያ ፣ ለብሶ ፣
የሰሌን ፣ መታጠቂያ ፣ ታጥቆ ፤ ብትን ፣ ሰሌን ፣ ይዞ ፣
መጣ ። ምን ፣ ሊያደርግ ፣ ይሆን ፣ ሲል ፤ ፊቱን ፣ ወ
ደ ፣ ምሥራቅ ፣ መልሶ ፣ ቆመ ። ወዲያው ፣ ጸሎቱ ፣
ወንጌልን ፤ ነአኩቶን ፤ ተሠሀለኒን ፣ ደግሞ ፤ መዠመ
ሪያ ፣ ለሥላሴ ፣ ሥስት ፣ ጊዜ ፣ እጅ ፣ ነሣ ። ከዚያ ፣
በኋላ ፣ አንድ ፣ አቡነ ፣ ዘበሰማያት ፣ አድርሶ ፣ ሦስት ፣
ጊዜ ፣ ደግሞ ፣ ሰገደ ። እንዲህ ፣ እያለ ፣ ዓሥራውለ
ት ፣ አቡነ ፣ ዘበሰማያት ፤ ሠላሳ ፣ ስድስት ፣ ሰጊድ ፣ አ
ድርሶ ፣ በመጨረሻ ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ እጅ ፣ ነሥቶ ፣
ተቀመጠ ። መጨረሻውንና ፣ መዠመሪያውን ፣ ያዛ
ውሩታል ። ያን ፣ አንድ ፣ ያሉ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤ ይኸን ፣
ሦስት ። ይኸን ፣ ሦስት ፣ ያሉ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤ ያን ፣ አ
ንድ ፣ ይሏል ። ወዲያው ፣ ያን ፣ ብትን ፣ ሰሌን ፣ አቅ
ርቦ ፣ ይታታ ፣ ገርመር ። እንጦንዮስም ፣ እንግዲህማ ፣
የዚህን ፣ ፍጻሜ ፣ ሳላይ ፣ እሔዳለሁን ፣ ብሎ ፣ ተቀም
ጦ ፣ ይመለከተው ፣ ገርመር ። ሠለስት ፣ ሲሆን ፣ ደጳ
ሞ ፣ ተነሥቶ ፣ አቡነ ፣ ዘበሰማያቱንም ፣ ሰጊዱንም ፣
ያንኑ ፣ ያህል ፣ አደረሰ ። የቀሩትንም ፣ የሰዓቱንም ፣ የ
ሠርኩንም ፣ እንደዚሁ ፣ አድርጎ ፣ አሳየው ። በሠር
ክ ፤ አ እንጦኒ ፣ ከመ ፣ ከመ ፣ ዝ ፣ ግበር ። ወለእመ ፣
ገበርከ ፣ ዘንተ ፣ ትድኅን ፣ እምጸብአ ፣ አጋንንት ፣ አ
ለው ። ስለ ፣ ምን ፣ አምስቱን ፣ ጊዜያት ፣ ብቻ ፣ አሳ
የው ፣ ቢሉ ፤ ባምስቱ ፣ ኪዳናት ፣ ምሳሌ ። ኪዳነ ፣ አ
ዳም ፤ ኪዳነ ፣ ኖኅ ፤ ኪዳነ ፣ አብርሃም ፤ ኪዳነ ፣ ሙ
ሴ ፤ ኪዳነ ፣ ሐዲስ ፣ ሕግ ። ቦ ፣ ባምስቱ ፣ ገባዕተ ፣
ሠርክ ፤ ባምስቱ ፣ ሕዋሳት ። ቦ ፣ እንዲሠሩ ፣ ለማጠ
የቅ ። ባምስቱ ፣ አዕማደ ፣ ምሥጢር ፣ አምሳል ። የን
ዋሙን ፣ የመንፈቀ ፣ ሌሊቱን ፣ ግን ፣ እርሱ ፣ ጨም
ሮታል ። ሰባቱን ፣ ጊዜያት ፣ መጠበቅ ፣ ስለ ፣ ምን ፣
ነው ፣ ቢሉ ፤ በነግህ ፣ ያደሩበትን ፣ የሚያሳርግ ፣ መ
ልአክ ፣ አለና ፤ ያደረውን ፣ ለማበርከት ። በሠርክ ፣
የዋሉበትን ፣ የሚያሳርግ ፣ አለና ፤ የዋለውን ፣ ለማበ
ርከት ። ቦ ፤ በነግህ ፣ የመዓልቱን ፣ ለማስባረክ ። በሠ
ርክ ፣ የሌሊቱን ፣ ለማስባረክ ። ቦ ፣ በነግህ ፣ ከበደ ፣ ን
ዋምን ፣ ያሳለፍህልን ፤ በሠርክ ፣ ከሥራሐ ፣ መዓል
ት ፣ ያሳረፍኸን ፣ ብሎ ፣ ነው ። ቦ ፣ ነግህ ፣ አዳም ፣ ከ
ገነት ፣ የወጣበት ። ሠለስት ፣ ገነትን ፣ ያጠነበት ። እ
መቤታችን ፣ ብሥራት ፣ መልአክን ፣ የሰማችበት ። ለ
ሐዋርያት ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ የተሰጠበት ፣ ነው ።
ቦ ፣ ነግህ ፣ ጌታ ፣ ከጲላጦስ ፣ ፊት ፣ የቆመበት ፤ ሠለስ
ት ፣ የተገረፈበት ፤ ቀትር ፣ የተሰቀለበት ፤ ሰዓት ፣ ነፍ
ሱን ፣ ከሥጋው ፣ የለየበት ፤ ሠርክ ፣ መቃብር ፣ የወረ
ደበት ፤ ንዋም ፣ የጸለየበት ፤ መንፈቀ ፣ ሌሊት ፣ የተ
ያዘበት ፣ ነውና ። ይኸም ፣ እንዲገባ ፣ አስቀድሞ ፣ በ
መጻሕፍት ፣ ታውቋል ። ለነግሁ ፤ በጽባሕ ፣ እቀውሙ ፣ ቅድሜክ ፣ ወአስተርኢ ፣ ለከ ። ለሠለስቱ ፤ ጊ
ዜ ፣ ሠለስቱ ፣ ሰዓት ፣ ጸለየ ፣ ዳንኤል ፤ ወአርኅወ ፣
መሳክዘ ፣ ቤቱ ። ለቀትሩ ፤ ሠርክ ፣ ወነግሀ ፣ ወመዓ
ልተ ፣ እነግር ። ለሰዓቱ ፤ ጊዜ ፣ ተስዓቱ ፣ ሰዓት ፣ ያዐ
ርጉ ፣ መላእክት ፣ ምግባሮ ፣ ለሰብእ ፣ ጎበ ፣ ክርስቶ
ስ ። ለሠርኩ ፤ እንሥእ ፣ እደውየ ፣ መሥዋዕተ ፣ ሠር
ክ ። ለንዋሙ ፤ በሌሊት ፣ እንሥኡ ፣ እደዊክሙ ፣ በ
ቤተ ፣ መቅደስ ። ለመንፈቀ ፣ ሌሊቱ ፤ መንፈቀ ፣ ሌ
ሊት ፣ እትነሣእ ፣ ተብሎ ። ቦ ፤ ይህን ፣ ሁሉ ፣ አን
ድ ፣ አድርጎ ፣ ዳዊተ ፤ ስብዐ ፣ ለዕለትየ ፣ እሴብሐከ ፣
ብሏል ።

ከዚያ ፣ አስቀድሞ ፣ ዓሥር ፣ ዓመት ፣ ነው ፣ ቢ
ሉ ፤ ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ኻያ ፣ ዓመት ። ከዚያ ፣ አስቀድ
ሞ ፣ ኻያ ፣ ዓመት ፣ ሁኖት ፣ ነበር ፣ ቢሉ ፤ ከዚያ ፣ በ
ኋላ ፣ ዓሥር ፣ ዓመት ፣ ኑሮ ፣ ሠላሳ ፣ ዓመት ፣ ሲመ
ላው ፣ ጌታ ፣ በዕለተ ፣ ዓርብ ፣ የለበሰውን ፣ ልብስ ፣
አልብሶታል ። ማየት ፣ ከመልአክ ፤ መቀበል ፣ ከአም
ላክ ፣ እንዲሉ ። በሠላሳ ፣ ዓመት ፣ መሆኑ ፣ ስለ ፣ ም
ን ፣ ነው ፣ ቢሉ ፤ አዳም ፣ የሠላሳ ፣ ዓመት ፣ ጕልማ
ሳ ፣ ሁኖ ፣ ተፈጥሮ ፣ ልጅነትን ፣ ተቀብሏል ። ዮሴፍ
ም ፣ በሠላሳ ፣ ዓመት ፣ ምስፍና ፣ ተሹሟል ። ዳዊት
ም ፣ በሠላሳ ፣ ዓመት ፣ ተቀብቶ ፣ ነግሧል ። ጌታም ፣
በሠላሳ ፣ ዓመት ፣ ተጠምቆ ፣ ማስተማር ፣ ገሥጾል ፤
በዚያ ፣ አምሳል ። ይኸም ፣ ምሳሌ ፣ ነው ። ቆቡ ፣ የአ

www.ethiopianorthodox.org

ክሊለ ፡ ሦክ ፤ ቀሚሱ ፡ የከለሜዳ ፤ ቅናቱ ፡ የሀብል ፤ ሥጋ ፡ ማርያም ፡ የሥጋ ፡ ማርያም ፤ አስኬማ ፡ የሰውነት ፤ ወተመሰለን ፡ በአስኬማሁ ፡ እንዲል ። ቦ ፤ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ልብስ ፡ አምሳል ፤ የብሉዩ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በውሥጥ ፡ እጀ ፡ ጸቢብ ፤ በላይ ፡ እጀ ፡ ሰፊ ፤ በዚያ ፡ ላይ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይለብሳል ። ከዚያ ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ መብርሂያት ፡ ያለ ፡ ይደርባል ። ይኸን ፡ ለብሶ ፡ አፍአዊ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውዶ ፡ አፍአዊ ፡ ጎጢአት ፡ ያስተሰርይ ፡ ነበር ። እሊህ ፡ መነኰሳት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፤ ውጣዊ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውተው ፡ ውጣዊ ፡ ጎጢአትን ፡ ያስተሰርያሉና ። እመቤታችንም ፡ ብሥራት ፡ መልአክን ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ነበር ። ይኸን ፡ ለብሳ ፡ ብሥራተ ፡ መልአክን ፡ ሰምታ ፡ ጌታን ፡ በድንግልና ፡ ጸንሳ ፡ ወልዳለች ። እሊህም ፡ መነኰሳት ፡ ይኸን ፡ ለብሰው ፡ ምእመናንን ፡ በትምርት ፡ ይወልዳሉና ። እሥራኤልም ፡ ከግብጽ ፡ ሲወጡ ፡ ሑፈት ፡ ይፍተው ፤ በሎታ ፡ ይዘው ፡ ዝናር ፡ ታጥቀው ፤ ጫማ ፡ አዝበው ፡ ወጥተዋል ። እሊህም ፡ መነኰሳት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በምናኔም ፡ ቢሉ ፤ በሞትም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይለያሉና ። ሥጋወ-ያን ፡ አርበኞችም ፡ ሑፈት ፡ አርገው ፤ ዝናር ፡ ታጥቀው ፤ ጋሻ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፤ ሥጋዊ ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ የመጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገሥታት ፡ መኳንንት ፡ ካባ ፡ ላንቃ ፡ ያለብሷቸዋል ። እሊህም ፡ ይኸን ፡ ለብሰው ፡ ረቂቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥላሴ ፡ የብርሃን ፡ ካባ ፡ ላንቃ ፡ ያለብሷቸዋል ። ይህም ፡ አንድ ፡ መነኰሴ ፡ እንዳየው ፡ ነው ። ሦስት ፡ የብርሃን ፡ ካባ ፡ ላንቃ ፡ ሲወርድ ፡ አየ ፤ ምንድር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መልአኩን ፡ ጠየቀው ። አንዱ ፡ ባሕታዊ ፡ ዘበጎድዓት ፤ አንዱ ፡ ድውይ ፡ ዘበአ ኰቴት ፤ አንዱ ፡ ረድእ ፡ ዘበጥብዓት ፡ የሚያገኘው ፡ ክብር ፡ ነው ። ከሦስተኛው ፡ ላይ ፡ ከመጨረሻው ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ረዋት ፡ ያለ ፡ ትርፍ ፡ አየበት ። ይህ ፡ ትርፉ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ቢለው ፤ ይኸስ ፡ ረድእ ፡ ዘበጥብዓት ፡ በጎዲገ ፡ ልማድ ፡ በመቲረ ፡ ፈቃድ ፡ የሚያገኘው ፡ ትርፍ ፡ ክብሩ ፡ ነው ፡ ብሎታል ። ቦ ፤ በልብሰ ፡ ምውታን ፡ አምሳል ፤ ቆቡ ፡ የሰበን ፤ ቀሚሱ ፡ የመጐናጸፊያ ። ቅናት ፡ የመግነዝ ፤ አስኬማ ፡ የትንሣኤ ፡ ሙታን ። ቦ ፤ ከዚያ ፡ ከመግነዙ ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንደ ፡ ማኅተም ፡ ያለ ፡ አለበትና ፤ የዚያ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ይኸ ፡ ለእንጦንዮስ ፡ የተሰጠው ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ደገኛው ፡ ለሐዋርያት ፡ የተሰጠው ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅናትን ፡ በንጽሐ ፡ ሥጋ ፤ ቀሚስን ፡ በንጽሐ ፡ ነፍስ ፤ ቆብን ፡ በንጽሐ ፡ ልቡና ፡ መዓርግ ፡ ሁነው ፡ ይቀበሉታል ። አስኬማን ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይላሉ ። ይኸስ ፡ አይደለም ፤ አስኬማከኒ ፡ አስኬማ ፡ መላእክት ፡ ይላልና ፤ ደገኛው ፡ ኋላ ፡ ለእንጦንዮስ ፡ የተሰጠው ፡ ነው ። ለሐዋርያት ፡ የተሰጠው ፡ ግን ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቅናትና ፡ ቀሚስን ፡ በንጽሐ ፡ ሥጋ ፤ ቆብን ፡ በንጽሐ ፡ ነፍስ ፤ አስኬማን ፡ በንጽሐ ፡ ልቡና ፡ መዓርግ ፡ ሁነው ፡ ይቀበሉታል ። አስኬማከኒ ፡ አስኬማ ፡ መላእክት ፡ እንዲል ። የሰሬን ፡ መሆኑሳ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ የሰሬን ፡ ፍሬው ፡ በሾህ ፡ የተከበበ ፡ ነው ፤ እሳት ፡ ስንኳ ፡ አይበላውም ። ይኸም ፡ ትእምርተ ፡ ኃይል ፡ ትእምርተ ፡ መዊእ ፡ ይሆናልና ። ቦ ፤ አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ በወለደ ፡ ጊዜ ፤ ከሰዶምንሞርን ፡ ድል ፡ በነሣ ፡ ጊዜ ፡ ይኸን ፡ ይዘ ፡ አመስግኑዋል ። እስራኤልም ፡ ባሕሩን ፡ በተሻገሩ ፡ ጊዜ ፡ ይኸን ፡ ይዘው ፡ አመስግነዋል ። ዮዲት ም ፡ ሆለሆርኒስን ፡ በገደለች ፡ ጊዜ ፡ ይኸን ፡ ይዘው ፡ አመስግነዋል ። ኢሳይያስም ፡ ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡ ወልደ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ይኸን ፡ ይዘ ፡ አመስግኑዋል ። ጌታም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አዕሩጓ ፡ ሕፃናት ፡ ይኸን ፡ ይዘው ፡ እያመሰገኑ ፡ ተቀብለውታልና ፤ ስለዚህ ፡ ነው ።

እርሱም ፡ ይኸን ፡ ተቀብሎ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለሁ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ነኝን ፡ ሌላም ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመልክተ ። ጌታም ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተራምዶ ፡ ሁለተኛውን ፡ ሳይደግም ፤ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ዓለመ ፡ ሁሉ ፡ ቢሰበሰብ ፡ የማይሠራው ፤ በጸሎቱ ፡ ዝናም ፡ የሚያዘንም ፤ ፀሐይ ፡ የሚያወጣ ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ወዳጅ ፡ አለኝ ፤ አለው ። ልሒድን ፡ ልቅር ፡ ቢለው ፤ ሒድ ፡ አለው ፤ መልአኩ ፡ እየ ፡ መራ ፡ አደረሰው ። ጳውሎስም ፡ ከበዓቱ ፡ ወጥቶ ፡ ፀሐይ ፡ ሲሞቅ ፡ ነበር ፤ ሲመጣ ፡ አይቶ ፡ ከበዓቱ ፡ ገብቶ ፡ ወወደየ ፡ ማዕያ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ በዓቱ ፡ ይላል ፤ ዘጋበት ። ከደጃፉ ፡ ቁሞ ፡ አውሎግሶን ፡ አውሎግሶን ፡ አለ ። ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ክፈትልኝ ፡ ክፈትልኝ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሰው ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ ጓባ ፡ ብሎ ፡ ከፈተለት ። ገብቶ ፡ ማን ፡ ይሉሃል ፡ አለው ። ስሜን ፡ ሳታውቅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ መጣህ ፡ አለው ። እርሱም ፡ ፍጹም ፡ ነውና ፡ አያጽረውም ፤ ቢያመለክት ፡ ወዲያው ፡ ተገለጸለት ። ጐድጐድኩ ፡ ወተርኅወ ፡ ሊተ ፤ ጎሠሥኩ ፡ ወረከብኩ ፡ ጳውሎስሃ ፡ ገዳማዊ ፡ አለው ። ጳውሎስ ፡ ትባላለህ ፡ ቢለው ፡ አደነቀ ። ተጨዋውተው ፡ ሲያበቁ ፡ ባጠገቡ ፡ ለብቻው ፡ በዓት ፡ ሰጠው ፤ ከዚያ ፡ ሁኖ ፡ ጉዳዩን ፡ ሲያደርግ ፡ ዋለ ። ወትሮ ፡ መንፈቀ ፡ ሳብስት ፡ ይወርድለት ፡ የነበረ ፡ ማታ ፡ ምሉእ ፡ ሳብስት ፡ ወረደለት ። በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መምጣቱን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አወቀው ። ወዲያው ፡ ያን ፡ ሳብስት ፡ ከሁለት ፡ ገምሶ ፡ እሡሌታዉን ፡ አስቀርቶ ፡ እሡሌታዉን ፡ ሰጠው ። ያን ፡ ተመግበው ፡ ሌት ፡ ሁሉም ፡ በየ ፡ ሥራቸው ፡ ክብራቸው ፡ ተገልጾ ፡ ሲተያዩ ፡ አድረዋል ። ጳውሎስ ፡ ዓሥር ፡ ጣቶቹ ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ሁነው ፡ እያበሩለት ፡ አራቱን ፡ ወንጌል ፡ ሲያደርስ ። እንጦንዮስም ፡ እንደ ፡ ዓምደ ፡ ብርሃን ፡ ተተክሎ ፡ ሲያበራ ፡ ተያይተዋል ። በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ከዚያች ፡ ቦታ ፡ ጨለማ ፡ ጠፍቶ ፡ አድሯል ። በነጋው ፡ እንዲህ ፡ ሠለስት ፡ እሳፈ ፡ ሲሆን ፡ ጉዳያቸውን ፡ አድርሰው ፡ ሲያበቁ ፡ ተግናኝተው ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ቆቡን ፡ አይቶ ፡ ይህን ፡ ከማን ፡ አገኘኸው ፡ አለው ። እርሱ ፡ ባለ ፡ ቤቱ ፡ ሰጠኝ ፡ አለ ። እርሱም ፡ የጌታን ፡ ቸርነት ፡ ያደንቅ ፡ ገሥመረ ። ቀድሞ ፡ ሰውን ፡ ይጠቀም ፡ ብሎ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ፈጠረው ። በዚያ ፡ መጠቀም ፡ ባይሆንለት ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ሠራለት ። ኋላ ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ መጽደቅ ፡ ባይቻለው ፤ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወርዶ ፤ ከመቤታችን ፡ ተወልዶ ፤ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ ሠራ ፤ ሥጋዉን ፡ ደሙን ፡ ሰጠ ። ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ለሰው ፡ መጽደቂያ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ምክንያተ ፡ ድኂን ፡ አመጣ ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ ቸርነት ፡ ብሎ ፡ አደነቀ ። እስኪ ፡ በኔ ፡ ብቻ ፡ የሚቀር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሌላም ፡ የሚያልፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመልክትልኝ ፡ አለው ፤ አመለከተ ፤ ወዲያው ፡ ተገለጸለት ። ወአክሞሰሰ ፡ ይላል ፤ ደስ ፡ አለው ። ምን ፡ አየህ ፡ ቢለው ፡ ጽዕድዋን ፡ አርጋብ ፡ በጠፈር ፡ መልተው ፡ አንተ ፡ እየ ፡ መራሃቸው ፡ ተከትለውህ ፡ ሲሔዱ ፡ አየሁ ፡ አለ ። ምንድር ፡ ነው ፡ ቢለው ፡ አሊህማ ፡ በዚህ ፡ በቆቡ ፡ የምትወልዳቸው ፡ ንጹሓን ፡ ጻድቃን ፡ ልጆችህ ፡ ናቸው ፡ አለው ። ሁለተኛ ፡ አመልክትልኝ ፡ አለው ፤ አመለከተ ። ወደመነ ፡ ገጹ ፡ ይላል ፤ አዘነ ። ምነው ፡ ቢለው ፡ ከክንፋቸው ፡ ጥቂር ፡ ተቀላቅሎባቸው ፡ አየሁ ፡ አለ ። ምንድናቸው ፡ ቢለው ፡ ጽድቅና ፡ ጎጢአት ፡ እየ ፡ ቀላቀሉ ፡ የሚሠሩ ፡ ልጆችህ ፡ ናቸው ፡ አለው ። ሦስተኛ ፡ አመልክትልኝ ፡ አለው ፤ አመለከተ ። ገወረ ፡ ወበከየ ፡ ይላል ፤ ቃሉን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ጮኸ ። ምነው ፡ አለው ፤ አርጋብ ፡ ኣርጋብ ፡ ናቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ቁራ ፡ ጠቁረው ፡ አየኋቸው ፡ አለ ። ምንድር ፡ ናቸው ፡ ቢለው ፡ ጎሣሥያነ ፡ ሚመት ፤ መፍቀርያነ ፡ ንዋይ ፤ አለ ፡ ይሠርው ፡ በነግህ ፡ ማዕደ ፡ ምስለ ፡ መኳንንት ፡ ይላቸዋል ፤ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ የሚነሡ ፡ ጎጥአን ፡ ልጆችህ ፡ ናቸው ፡ አለው ። ያለ ፡ ንስሓ ፡ ባይጠራቸው ፡ እስኪ ፡ አመልክትልኝ ፡ አለው ፤ አመለከተ ። የዚህ ፡ ምላሽ ፡ አልመጣለትም ፡ ይላሉ ። መምር ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ ጳን ፡ መጥሎታል ፤ አልጠራቸው ፡ ብሎታል ፡ ይላሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንግዲህ ፡ ይኸን ፡ ከራስህ ፡ ያደረግኸውን ፡ ለኔ ፡ ስጠኝ ፡ ላንተ ፡ ሌላ ፡ ሠርተህ ፡ አድርግ ፡ አለው ። ይኸንንስ ፡ እንዳልሰጥህ ፡ ከባለቤቱ ፡ ተቀብየዋለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሥራዉን ፡ ለምጂዋለሁ ፡ ሌላ ፡ ሠርቼ ፡ ላምጣልህ ፡ አለው ። እንኪያስ ፡ አትዘግይ ፡ ቶሎ ፡ ሠርተህ ፡ አምጣልኝ ፡ አለው ። ጊዜው ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አውቆታልና ፡ ይላሉ ። ሠርቶ ፡ ይዘ ፡ ሲመጣ ፡ አርፎ ፡ ነፍሱን ፡ መላእክተ ፡ ብርሃን ፡ ይዘዋት ፡ ሲያርጉ ፡ አየ ። ማነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፤ ያ ፡ ሰው ፡ አርፏልና ፡ ሒደህ ፡ ቅበረው ፡ አሉት ። ይህንሳ ፡ የያዝሁትን ፡ ልተወውን ፡ አላቸው ፤ አትተው ፡ አድርግለት ፡ ብለዉታል ። ከምንዙስና ፡ አስቀድሞ ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ እንዳይደለ ፡ ለማጠየቅ ፡ ነው ። ቢሔድ ፡ መጽሐፉን ፡ ታቅፎ ፤ አጽፉን ፡ ተጐናጽፎ ፤ ከበዓቱ ፡ አርፎ ፡ አገኘው ። ከራስጌው ፡ ቁሞ ፡ አርበዕተ ፡ ወንጌል ፡ አድርሶ ፡ ኤልያስን ፡ ልበልህ ። መጥምቁ ፡ ዮሐንስን ፡ ልበልህ ። ጳውሎስን ፡ ልበልህ ፡ እያለ ፡ ሲያለቅስ ፡ ሁለት ፡ አናብስት ፡ መጡ ። የመቃብሩን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ላደርግ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፤ ሲጨነቅ ፡ በእጃቸው ፡ እንደ ፡ መዋቀስ ፡ አድርገው ፡ አሳዩት ። ልኩን ፡ ለክቶ ፡ ሰጣቸው ፡ ቆፈሩለት ።

www.ethiopianorthodox.org

እሱን ፡ ቀብሮ ፡ እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። ጌታ ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ በሱ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አላይበትምና ፡ አይሆንልህም ፡ ሒድ ፡ አለው ፤ አጽፉንና ፡ መጽሐፉን ፡ ይዘ ፡ ሒዶ ፡ እስክንድርያ ፡ ሲደርስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ አትናቴዎስ ፡ ወደት ፡ ሒደህ ፡ ነበር ፡ አለው ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ልጠይቅ ፡ ሒጂ ፡ ነበር ፤ አርፎ ፡ አግኝቹ ፡ ቀብሬው ፡ መጣው ፡ አለ ። ልሒድና ፡ ከዚያ ፡ ልኑር ፡ አለው ። እንደሆንልህም ፡ አትሒድ ፤ እኔም ፡ አስቤ ፡ ነበር ፤ የማይሆንልኝ ፡ ሁኖ ፡ መጣሁ ፡ እንጂ ፡ አለው ። ባይሆን ፡ ለበረከት ፡ ያህል ፡ አጽፌቱን ፡ ጥለህልኝ ፡ ሒድ ፡ ብሎት ፡ ትቶለት ፡ ሔደ ። መዓርግ ፡ ሲሰጥ ፡ ሥጋዉን ፡ ደሙን ፡ ሲለውጥ ፡ በውሥጥ ፡ ያችን ፡ ይለብስ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ቆብ ፡ እንጠንዮስ ፡ መቃርስን ፤ መቃርስ ፡ ጳዙሚስን ፤ ጳዙሚስ ፡ ጳላሞንን ፤ ጳላሞን ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሮማዊ ፡ አረጋዊን ፡ ይወልዳሉ ። አረጋዊንስ ፡ ራብዕ ፡ እምእንጠንዮስ ፡ ይለዋልና ፡ አራተኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንጠንዮስ ፡ መቃርስን ፤ መቃርስ ፡ ጳዙሚስን ፤ ጳዙሚስ ፡ አረጋዊን ፡ ይላሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መነኰሳት ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ በዝተው ፡ ተነሥተዋል ። ይሩማሊስ ፡ ጳላድዮስ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ሊቃውንት ፡ መነኰሳት ፡ ከግብጽ ፡ ተነሥተው ፡ አገር ፡ ላገር ፡ እየ ፡ ዞሩ ፡ የአበውን ፡ ዜና ፡ ያሉትን ፡ ከቃላቸው ፤ የሞቱትን ፡ ከአርድእቶቻቸው ፡ እየ ፡ ጠየቁ ፡ ጽፈዋል ። መጽሐፋንም ፡ ሲጽፉት ፡ ቃለ ፡ አቡው ፤ ዜና ፡ አበው ፡ ክልእ ፤ ዜና ፡ ሣልስ ፤ ዜና ፡ ራብዕ ፡ እያሉ ፡ ጽፈውታል ። እንዲያውም ፡ ሁሉን ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ መጽሐፈ ፡ ገነት ፡ ብለዉታል ። በገነት ፡ ብዙ ፡ ጣዕም ፤ መዓዛ ፡ እንዲገኝ ፡ በዚህም ፡ በመጻፉ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ብዙ ፡ ምሥጢር ፡ ይገኝበታልና ። ቦ ፤ ዕውቀት ፡ ያለበት ፡ ማለት ፡ ነው ። አበዊሃ ፡ ይሰምይዎ ፡ ለብርሃነ ፡ አእምሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገነተ ፡ እንዲል ። ቦ ፤ ገነተ ፡ መጽሐፍ ፡ ብሎ ፡ ይገኛል ። መጽሐፍ ፡ የተባሉ ፡ አበው ፡ ናቸው ፤ የአበው ፡ ዕውቀት ፡ ሲል ፡ ነው ።

ኋላ ፡ ግን ፡ አበው ፡ ቢያልፉ ፡ ውሉድ ፡ ቢተርፉ ፡ ተመልሶ ፡ ሳለ ፡ ያልተመለሰ ፤ ተተርጕሞ ፡ ሳለ ፡ ያልተተረጐመ ፡ መስሏቸው ፡ አዝነዋል ። እንዲያውም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያልተተረጐመ ፡ እንደ ፡ ጥሬ ፡ ያለ ፡ ነበርና ፡ ያን ፡ እያዩ ፡ መተርጕም ፡ ማነን ፡ ባገኝን ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኑረዋል ። ቋንቋ ፡ ያወቀ ፡ የተማረ ፡ ቢሆን ፤ ግብር ፡ ያልገ ፡ ይሆናል ። ግብር ፡ የገባ ፡ ቢሆን ፡ ቋንቋ ፡ የማያወቅ ፡ ያልተማረ ፡ ይሆናል ። ኋላ ፡ ግን ፡ ቋንቋ ፡ ያወቀ ፤ የተማረ ፤ ግብር ፡ የገባ ፡ ይኸ ፡ ፈልክስዩስ ፡ ተነሥቶ ፡ ተርጕሞላቸዋል ። እሊህሳ ፡ የወዲት ፡ ናቸው ፡ ቢሉ ፤ የሶርያ ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ። ምነው ፡ ሶርያማ ፡ የተማረ ፡ ግብር ፡ የገባ ፤ ቋንቋ ፡ ያወቀ ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ አል ነበረምን ፡ ቢሉ ፤ የግብጽ ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ። ግብጽስ ፡ ቋንቋ ፡ ያወቀ ፡ የተማረ ፤ ግብር ፡ የገባ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አልነበረምን ፡ ቢሉ ፤ ጊዜው ፡ ባይገጥማቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሶርያ ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ። የተረጐመላቸውም ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ከብሉይ ፡ አየ ፡ ጠቀሰ ፡ እያመጣ ፡ ያልተመሰለውን ፡ አየ ፡ መሰለ ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ አጕልቶ ፡ አብርቶ ፡ ተርጕሞላቸዋል ። ሲተረጕምም ፡ እንዲረዳቸው ፡ ብሎ ፡ አድልፍዩስ ፡ የሚባል ፡ ከነጽሮ ፡ የደረሰ ፡ አንድ ፡ ፍጹም ፡ ነበረ ። እሱን ፡ ከመከከላቸው ፡ አስቀምጦ ፡ በሱ ፡ ፊት ፡ ተርጕሞላቸዋል ። እርሱም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከአኃው ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከመተርጕም ፡ እየ ፡ ሆነ ፡ ነገር ፡ ያቀናል ። በውሥጡም ፡ አረጋዊ ፡ አረጋዊ ፡ እያለ ፡ የሚያመጣው ፡ የእርሱ ፡ ነው ። ታሪክ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ይህሳ ፡ ወደ ፡ ሀገራችን ፡ የተመለሰ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ፈልክስዩስ ፡ ባፄ ፡ ድልነዓድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሰይፈ ፡ አርዓድም ፡ ይላሉ ። መላሹም ፡ ንውስ ፡ ሰላማ ፡ ብርሃነ ፡ አዜብ ፡ ካህነ ፡ አዜብ ፡ ይለዋል ፤ እርሱ ፡ ጳብረ ፡ ሕማማትን ፡ ጨምሮ ፡ መልሶ ታል ። አረጋዊ ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ ተመልሷል ። መላሹ ፡ ጨ ፡ ሚካኤል ፣ ጳብጻዊ ፡ ማርቆስ ፡ ይላሉ ። የማር ፡ ይስሐቅ ፡ ጊዜው ፡ አልታወቀም ። ቦ ፡ ታሪክ ፡ አገኘነ ፡ ብለው ፡ ባፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ይላሉ ። መላሹን ፡ ግን ፡ ሰሊክ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ይለዋል ። የተድባበ ፡ ማርያም ፡ መነኵሴ ፡ ነው ። አቡሻኽርን ፡ ጨምሮ ፡ መልሶታል ። ፈልክስዩስ ፡ ዜናቸውን ፡ ታሪክቸውንም ፡ ቢሉ ፡ ይናገራል ። አረጋዊ ፡ ጣዕማቸውን ፡ ጸጋቸውንም ፡ ቢሉ ፡ ይናገራል ። ማር ፡ ይስሐቅ ፡ ያራቸውን ፡ ጳብራቸውንም ፡ ቢሉ ፡ ይናገራል ። ታሪክ ፡ እስከዚህ ፡ ነው ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ። እዌጥን ፡ በኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሥን ፡ ሀብቱ ፡ ጽሑፈ ፡ እስተጋብኦ ፡ ዝ ፡ መጽሐፍ ።

በአብ ፡ ስም ፡ አምጜ ፡ አብን ፡ ወላዲ ፤ በወልድ ፡ ስም ፡ አምጜ ፡ ወልድን ፡ ተወላዲ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አምጜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሠራፂ ፡ ብዬ ፤ ለአጠይቆ ፡ አካላት ፡ ሶስት ፡ ስላልሁ ፤ ዘበሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አምጜ ። ጽሑፈ ፡ ዝ ፡ መጽሐፍ ፤ እስትጉቡዕ ፡ ሲል ፡ ነው ። የተሰበሰበ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ መጻፍን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አጋዥ ፡ ሀብቱን ፡ መልክ ፡ ጌጽ ፡ በማድረግ ፡ እጀምራለሁ ። በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ አለ ፤ እግዚአብሔርን ፡ አጋዥ ፡ ካላደረጉ ፡ እማር ፡ አስተምር ፤ አነብ ፡ እተረጕም ፡ ቢሉ ፡ አይሆንምና ። ኩላኬ ፡ ፍድፋዴ ፡ እንተ ፡ ይገብራ ፡ ብእሲ ፡ ኢትተዓገም ፡ ዘእንበለ ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለእግዚእነ ፤ ወዘእንበሌየሰ ፡ ኢትክሉ ፡ ገቢረ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ብሎ ፡ እንዲያመጣው ። አንድም ፡ ወልድን ፡ አጋዥ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መልክ ፡ ጌጽ ፡ በማድረግ ፡ እጀምራለሁ ። ሀብትኬ ፡ ሠናይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲል ። ሐተታ ፤ አብን ፡ ቅዱስ ፡ ይላል ፤ ወልድንም ፡ ቅዱስ ፡ ይላል ፡ ከዚህ ፡ ለይቶ ፡ ስለምን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፤ ከወላዲውና ፡ ከተወላዲው ፡ አካል ፡ ሠራፂውን ፡ አካል ፡ ሲለይ ። አንድም ፡ ነፍሳትን ፡ ነፋሳትን ፡ መላእክትንም ፡ አጋንንትን ፡ ቅሉ ፡ መንፈስ ፡ ይላቸዋልና ፤ ከፍጡራን ፡ ባሕርይ ፡ የፈጣሪን ፡ ባሕርይ ፡ ሲለይ ። አንድም ፡ ከልዕና ፡ ካባት ፡ ሲለይ ። ልጅ ፡ ምንም ፡ ካባት ፡ ቢገኝ ፡ ልዩ ፡ ነው ። እሱ ፡ ግን ፡ መለየት ፡ የለበትምና ። እንዲያውስ ፡ ከሶስት ፡ ዝማም ፡ ወርቅ ፡ አሁን ፡ አንዱን ፡ ኸከውር ፡ ቢያገቡት ፡ ተለየ ፡ ይባላልን ፡ ልዩም ፡ አይደል ። አንድም ፡ ጽሑፈ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘአስተጋብአ ፡ ሲል ፡ ነው ። ጳላድዮስ ፡ የሰበሰበውን ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ መጻፍን ። አንድም ፡ ጽሑፈ ፡ ዘአስተጋብአ ፡ ዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ሲል ፡ ነው ። ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሰበሰበውን ፡ ምሥጢር ፡ መጻፍን ፡ እጀምራለሁ ። ራእይ ፡ ዘርእየ ፡ ኢሳይያስ ፤ ራእይ ፡ ዘርእየ ፡ ኤርምያስ ፤ ራእይ ፡ ዘርእየ ፡ ዕንባቆም ፡ እንዲል ።

ወውእቱ ፡ ክፍል ፡ ቀዳሚ ፡ እምተስእሶታት ፡ ዜናሆሙ ፡ ለአበው ፡ መኰሳት ፡ ግብጻውያን ።

ሁለተኛ ፡ ሶስተኛ ፡ የሚጽፍ ፡ ነውና ፡ ቀዳማዊ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ የግብጽ ፡ መነኰሳት ፡ የሚሆኑ ፡ የአበውን ፡ ዜና ፡ አኃው ፡ ከጠየቁት ፡ የመጣ ፡ መጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ምነው ፡ የግብጽን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የጠየቁት ፡ የሁሉንስ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፤ በበዛው ፡ መናገር ፡ ነው ። አናብስተ ፡ መስዕ ፤ ተዅላተ ፡ ዓረብ ፤ ከዋክብተ ፡ ጽባሕ ፡ ይላል ፤ ከሌላ ፡ የሌለ ፡ ሁኖ ፡ ነውን ፡ በበዛው ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ዘ ፡ የቀረው ፡ ነው ። የግብጽ ፡ መነኰሳት ፡ እነ ፡ ጳላድዮስ ፤ እነ ፡ ይሩማሊስ ፡ የአበውን ፡ ዜና ፡ ከጠየቁት ፡ የሚቀድም ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘጸሐፎ ፡ ቅዱስ ፡ ፈልክስዩስ ፡ ሶርያዊ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘመንበሮ ።

ፈልክስዩስ ፡ የጸፈው ። ፈልክስዩስ ፡ ማለት ፡ ጉበረ ፡ ክርስቶስ ፡ ማለት ፡ ነው ። አንድም ፡ መፍቀሬ ፡ አኃው ፡ ማለት ፡ ነው ። ፈልጰስ ፡ ፈላታዖስ ፡ ፈልሳዳርስ ፡ ማለት ፡ መፍቀሬ ፡ አኃው ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ። ሶርያ ፡ ሀገሩ ፤ መንበግ ፡ የተሾመበት ፡ ነው ።

ክፍል ፡ ቀዳማዊ ።

ተስእሎ ፡ ፩ ።

በእንተ ፡ ዘከመ ፡ ይኄይስ ፡ ሥርዓተ ፡ ብሕትውና ፡ እምሥርዓተ ፡ ማኅበር ፡ ይቤሉ ፡ አኃው ።

በማኅበር ፡ ሁኖ ፡ ከሚሠሩት ፡ በተባሕትዎ ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ እንዲበልጥ ፡ ዘጸሐፎ ። አንድም ፡ ይቤሉ ፡ አኃው ፡ እምንብረተ ፡ ማኅበርም ፡ ይላል ። በማኅበር ፡ ከመኖር ፡ በተባሕትዎ ፡ መኖር ፡ እንዲበልጥ ፡ ከጻፈው ። አንድም ፡ እንዲበልጥ ፡ ይቤሉ ፡ አኃው ፡ በእንተ ፡ ሥርዓተ ፡ ተባሕትዎ ፡ እምሥርዓተ ፡ ማኅበርም ፡ ይላል ። በእንተ ፡ ንብረተ ፡ ተባሕትዎ ፡ እምንብረተ ፡ ማኅበርም ፡ ይላል ።

ንዌጥን ፡ እምጥንቱ ፡ ለግብር ።

መጽሐፈ ፡ ገነት ፡ የሚጀምረው ፡ በውሉደ ፡ ነጋዲ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥንቱ ፡ ለመጽሐፍ ፡ ለነገር ፤ በመጽሐፈ ፡ ገነት ፡ ከተነገረው ፡ ከተጻፈው ፡ ጀ

www.ethiopianorthodox.org

ምረን ፡ እንጠይቃለን ። መጽሐፈ ፡ ገነትስ ፡ የሚጀ
ምረው ፡ በነ ፡ አሞንዮስ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
ጥንቱ ፡ ለፈቃድ ፤ መጠየቅ ፡ ከሚያሻው ፡ ከምንሻ
ው ፡ ነገር ፡ ጀምረን ፡ እንጠይቃለን ።

ወለዉ ፡ ክልዔቱ ፡ አኃው ፡ ውስደ ፡ ብእሲ ፡ ኑጋዲ ።
ይተርክል ፤ ያንድ ፡ ነጋዲ ፡ ልጆች ፡ ሁለት ፡ ወንድማ
ማች ፡ ነበሩ ።

ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አቡሆሙ ፡ ተካፈሎ ፡ ርስቶ ።
አባታቸው ፡ ሙቶ ፡ ገንዘብ ፡ ሲካፈሉ ።

ወኮነ ፡ ለበኵር ፡ እምኔሆሙ ፡ በበ ፡ ሃምሳ ፡ ምዕት ፡ ዲናር ።
ከነሱ ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ ገንዘቡ ፡ እልፍ ፡ ሁኖ ፡
አምሳ ፡ አምሳ ፡ ወሰደ ፡ ያረሰው ። አዕረፈ ፡ አለ ፤ በ
ጎ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በነውን ፡ ዕረፍት ፡ ያርፋል ።
ክፋም ፡ ቢሆን ፡ ቅሉ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሃር ፡ ጋር ፡
ያርፋልና ። ዕረፍተ ፡ ሞት ፡ ይኄሩ ፡ ሊተ ፡ እምሃዕ
ራቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ፡ እንዲል ። ርስት ፡ ያለው ፡ ገ
ንዘብን ፡ ነው ። አባ ፡ ሀበኒ ፡ መክፈልተ ፡ ርስትየ ፡
ዘይረክበኒ ። አንተ ፡ ወሲባ ፡ ትትካፈሉ ፡ ርስቶ ፡ ለሳ
አል ፡ እንዲል ። አንድም ፡ በቁሙ ፡ ርስት ፡ ነው ። እ
ልፍ ፡ አውጥቶ ፡ አምሳ ፡ አምሳ ፡ ደረሰቸው ። ምን
ው ፡ ርስት ፡ ያለው ፡ አይነግድ ፡ ይል ፡ የለምን ፡ ቢ
ሉ ፤ ሁሉ ፡ ሥርዓት ፡ ያጸናልን ፡ ፈርሶ ፡ ቢገኝ ፤ ያ
ውስ ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚያወጣ ፡ ርስት ፡
ይገኛልን ፡ ቢሉ ፤ በሀገራቸው ፡ ባሕሩ ፡ ብዙ ፡ የብ
ሱ ፡ ጥቂት ፡ ነውና ፡ ያወጣል ።

ወሀለዩ ፡ በልቦሙ ፡ ክመ ፡ ያሥምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጽድት ፡
ፍጹም ።
ሁሉም ፡ በልቡናቸው ፡ ፍጹም ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡
ጌታን ፡ ሊያገለግሉት ፡ ወደዱ ።

ወዘረወ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ መክፈልቶ ፡ ላዕለ ፡ አብየተ ፡ ክርስቲ
ያናት ፡ ወምኔታት ፡ ወምስኪናን ፡ ወመፍቅዳውያን ።
አንዱ ፡ ከወንድሙ ፡ የተካፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለአብ
ያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ለገዳማት ፤ ምስኪናን ፡ የለት ፡
ምግብ ፡ የሌላቸው ፡ መፍቅዳውያን ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡
የተያዘላቸው ፤ አንድም ፡ ምስኪናን ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡
የተያዘላቸው ፡ መፍቅዳውያን ፡ ክመቃለል ፡ መጠቃ
ለል ፡ ብለው ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ሥጋቡ ፡ ጽምዕ ፡
የሚበገብጋቸው ፤ አንድም ፡ ያለተገብር ፡ ተባሕትዎ ፡
ለማይፈጸምላቸው ፡ ሰጠው ፡ መሪወተው ።

ወተምሕረ ፡ ኪን ፡ እድ ፡ ለሰላየ ፡ ዕለቱ ።
የለት ፡ ምግብ ፡ ሊሆነው ፡ እንቅብ ፡ መስፋት ፡ ሰሌ
ን ፡ መታታት ፡ ተማረ ።

ወአዝለፈ ፡ ጎድአተ ።
በበዓት ፡ መከተትን ፡ ወደደ ፤ ላይዓት ፡ የሚለው ፡
ባሕታውያን ፡ ከዘጉ ፡ በኋላ ፡ በመስኮተ ፡ ቤት ፡ ዘል
ቆ ፡ ብርሃነ ፡ ፀሐይ ፡ አለማየት ፡ ቆብ ፡ ቅናት ፡ ቀሚ
ስ ፡ አለማውለቅ ፡ ገላ ፡ አለመዳሰስ ፡ ነው ።

ወጸሎተ ።
እንደ ፡ አብርሃም ፡ ጸሎተ ፡ ሥጋን ፡ እንደ ፡ ኤልያስ ፡
ጸሎተ ፡ ነፍስን ፡ ተማረ ፤ መነኩሴውስ ፡ እንደ ፡ አ
ብርሃም ፡ ልጅ ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ አይጸልይም ፡ ብለህ ፡
ጸሎተ ፡ ሥጋን ፡ ጸሎተ ፡ ነፍስን ፤ ጸሎተ ፡ ልብን ፡
ተማረ ፤ ጸሎተ ፡ ሥጋ ፡ በአንስሐስሐ ፡ ከናፍር ፡ ጸ
ሎተ ፡ ነፍስ ፡ ያለ ፡ አንስሐስሐ ፡ ከናፍር ፡ የሚጸለ
ይ ፡ ነው ፡ ጸሎተ ፡ ልብ ፡ ካልደረሰበት ፡ አይታወቅ
ም ።

ወጸመ ።
ጾም ፡ የሚለው ፡ ውሎ ፡ ውሎ ፡ መብላት ፡ ሲርብ ፡
መተው ፡ ምግብ ፡ አለማሻሻል ፡ ጊዜ ፡ አለመለዋወ
ጥ ፡ ነው ።

ወክልውኒ ፡ ሐንጸ ፡ ምኒተ ፡ ወአበተጋብአ ፡ ጎቤሁ ፡ አኃው ።
ሁለተኛው ፡ ገዳም ፡ አቅንቶ ፡ አኃውን ፡ ሰብስቦ ፡ ኖረ ።

ወኮነ ፡ ይትቁበል ፡ ነግዳን ።
እንግዳ ፡ ሲቀበል ፡ ኖረ ።

ወንዳያን ፡ ወአዕፍን ፡ ወድውያን ፡ በፍሥሓ ።
ዋልድቦች ፡ ከሽሬ ፡ ከሰራዬ ፡ የመጣውን ፡ እንግዳ ፡
ሲቀበሉ ፡ እንደነበረ ፡ ነዳያንን ፡ ምስኪናንን ፡ ሽማግ
ሎችን ፡ ደውያንን ፡ በፍሥሓ ፤ ደስ ፡ ብሎት ፡ ደስ ፡
አሰኝቶ ።

ወለዮስ ፡ በዘይደሉ ፡ ያወርርመ ።
ለሁሉም ፡ በሚገባ ፡ የሚሹ ፡ የሚሹትን ፡ እየሰጠ ፡ ያ
ሳርፋቸው ፡ ነበር ።

ወከመገ ፡ ዘረወ ፡ ሀሎ ፡ ንዋየ ።
ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ መጸወተ ።

ወኮኑ ፡ መንፈቀ ፡ አኃው ፡ ያኄይሱ ፡ ግብረ ፡ አሐዱ ።
እነሱሉቶቹ ፡ አኃው ፡ ያንዱን ፡ የታላቁን ፡ ሥራ ፡ አ
በለጡ ፡ ይበልጣል ፡ አሉ ።

ወመንፈቆሙ ፡ ያኄይሱ ፡ ሥርዓተ ፡ ክልኤ ።
እነሱሉቶቹ ፡ ደግሞ ፡ የሁለተኛውን ፡ የታናሹን ፡ ሥ
ራ ፡ አበለጡ ፡ ይበልጣል ፡ አሉ ።

ወተስእልዎ ፡ ሰብዑዕ ፡ አባ ፡ ባዎሳ ።
አባ ፡ ባምዋን ፡ ጠየቁት ።

ወይቤልዎ ፡ አይ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምክልኤሆሙ ።
ከሁለቱ ፡ ማናቸው ፡ ይበልጣል ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ወይቤሎሙ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ፍጹማን ፡ እሙንቱ ።
ሁሉም ፡ ፍጹማን ፡ ናቸው ።

እስመ ፡ ቀዳሚሁ ፡ ገብረ ፡ ክመ ፡ ሥርዓተ ፡ ኤልያስ ።
አንዱ ፡ ታላቁ ፡ እንደ ፡ ኤልያስ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ሠር
ቷልና ።

ወክልውኒ ፡ ገብረ ፡ ክመ ፡ ሥርዓተ ፡ አብርሃም ።
ሁለተኛው ፡ ታናሹ ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡
ሠርቷልና ።

ወይቤሉ ፡ መንፈቆሙ ፡ እፎ ፡ ይትኄረዩ ።
እነሱሉቶቹ ፡ በምን ፡ ይተካከላሉ ፡ እንደምን ፡ ይተካ
ከላሉ ።

ቀዳሚሁሰ ፡ ፈጸመ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚእነ ፡ እንተ ፡ ለፍጹማን ፡ ዘይብ
ል ፡ እመስ ፡ ትፈቅድ ፡ ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሚጥ ፡ ሀሎ ፡ ንዋየከ ፡ ወሀ
ብ ፡ ለምስኪናን ፡ ወንኅ ፡ ትልወኒ ። (ማቴ ፲፱ ፡ ፳፩) ።
አንዱ ፡ ታላቁ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ ለፍጹማን ፡
ያዘዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽሟልና ፡ እንደምን ፡ ይተካ
ከላሉ ፡ አሉ ።

ወክልዓንኒ ፡ ተሠጥዉ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ።
ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

እስመ ፡ ክልኤ ፡ ውእቱ ፡ ብዑዕሰ ፡ በክመ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ መኑ ፡
ውእቱ ፡ መጋቢ ፡ ጠቢብ ፡ ወምዕመን ፡ ዘይሠይሞ ፡ እግዚኡ ፡ ላዕለ ፡
ሀሉ ፡ ቤቱ ፡ ክመ ፡ የዐዩሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ በበጊዜሁ ፡ ብዑዕ ፡ ውእቱ ፡
ገብር ፡ ዘመጺኦ ፡ እግዚኡ ፡ ይረክቦ ፡ እንዘ ፡ ክመግ ፡ ይገብር ፤ አማ
ን ፡ እብለክሙ ፡ ክመ ፡ ዲበ ፡ ሀሉ ፡ ንዋዩ ፡ ይሠይሞ ። (ማቴ ፳፬ ፡
፵፭ ፡ ፵፯) ።
እንደ ፡ ጌታ ፡ አኔጋገር ፡ የሚበልጠውስ ፡ ታናሹ ፡ ነ
ው ፡ አሉ ።

ወይቤ ፡ ተዓገሡኒ ፡ እንከ ፡ ሕቀ ።
ጥቂት ፡ ቆዩኝ ፡ ቀን ፡ ስጡኝ ።

እስክነ ፡ አእምር ፡ እምእግዚአብሔር ።
ከእግዚአብሔር ፡ አግኝቼ ፡ እስካስረዳችሁ ፡ ድረስ ፡
አላቸው ፡ ቀን ፡ ሰጡት ። ምነው ፡ ፍጹም ፡ አይደለ
ምን ፡ ቢሉ ፡ ፍጹም ፡ ቢሆን ፡ ፍጡር ፡ ካልተገለ
ጸለት ፡ አያውቅምና ፡ በይገለጽለት ፤ አንድም ፡ ሁሉ
ም ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ ይዘው ፡ ጠይቀውታል ፡ ከጌ
ታ ፡ አግኝቶ ፡ ለማስረዳት ፤ አንድም ፡ ባለሚልኑቱን ፡
ለማጠየቅ ።

ወእምድኅረ ፡ ኀዳጥ ፡ መዋዕል ፡ መጽኡ ፡ ኀቤሁ ።
ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ መጥተው ፡ ጠየቁት ።

ወይቤሎሙ ፡ ርኢክዎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
ሁለቱንም ፡ ከጌታ ፡ ፊት ፡ በባለሚልኑት ፡ ቀርበው ፡
አየኋቸው ።

ውስተ ፡ ገነተ ፡ ዔደም ።
ኤዶም ፡ በምትባል ፡ ገነት ። አንድም ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡
ኤዶም ፤ በምቹ ፡ ሥፍራ ፡ በገነት ፤ አንድም ፡ ውስ
ተ ፡ ገነት ፡ አዳም ፤ ባማረ ፡ በተወደደ ፡ ቦታ ፡ በገነ
ት ፤ አንድም ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ አዳም ፤ አዳም ፡ ሰባ
ት ፡ ዓመት ፡ በነበረበት ። አንድም ፡ በአዳም ፡ ዕው
ቀት ፡ በስምንተኛው ፡ ማዕርግ ፡ ሲል ፡ ነው ። አበዊነ
ሂ ፡ ይሰምይዎ ፡ ለብርሃነ ፡ አእምሮተ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ገነተ ፡ እንዲል ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ በሕሊናስ ፡ ኮኑ ፡ መሳርያነ ።
መተርጉም ፡ ያለው ፡ ፊልክስዩስ ፡ ነው ። በምን ፡ ይ
ተካከላሉ ፡ ብለው ፡ ታልና ፤ መተካከላቸውስ ፡ በሕሊ
ና ፡ ነው ፡ አላቸው ።

እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ሐሰዩ ፡ ክመ ፡ ያሥምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በክ
መ ፡ አእመረ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ክመ ፡ ውእቱ ፡ ያበጽ
ሕ ፡ ሰንበ ፡ ፍጹም ፡ ሥምረተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወፈቃዱ ።
ከነሱ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ መተዉ ፡ ጌታ ፡ ወደሚወ
ደው ፡ ነገር ፡ ፊጽሞ ፡ ፈቃዱን ፡ ወደ ፡ መፈጸም ፡ እ
ንዲያደርሰው ፤ ይበጽሕ ፡ ቢል ፡ ሰውየው ፡ ገንዘቡን ፡
በመተው ፡ ፈቃዱን ፡ ወደ ፡ መፈጸም ፡ እንዲደርስ ፡
እንዳወቀ ፡ መጠን ፡ ሁሉም ፡ ጌታን ፡ ሊያገለግሉ ፡
ወደዋልና ።

በሥርዓትሰ ።
የሄዱበትን ፡ መንገድ ፡ የቆሙበትን ፡ ዓጸድ ፡ ቢመረ
ምሩት ፡ ግን ።

እስመ ፡ ዘገደፈ ፡ ሀሎ ፡ ወተሰዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ሥርዓቱ ፡ ትሩፍ ።
ሁሉን ፡ ጥሎ ፡ ጌታን ፡ የተከተለ ፡ ሥራው ፡ ፍጹም ፡
ነው ።

እስመ ፡ መተረ ፡ ግብራተ ፡ ድድቃት ፡ ዘያርሕቃ ፡ እምእግዚአብሔር ።
መከራት ፡ የሚመጡባቸው ፡ ንዋያትን ፡ ትቷልና ።
ዘያርሕቃ ፡ ብሎ ፡ ለንዋያት ፡ ቀጠለ ። አንድም ፡ ጎ
ብራት ፡ ድቀታት ፡ ይላል ፤ ኃጣውኢ ፡ የሚሠሩባቸ
ው ፡ ንዋያትን ፡ ትቷልና ። ዘያርሕቃ ፡ ከእግዚአብሔ
ር ፡ የሚለዩ ፡ ብሎ ፡ ለኃጣውኢ ፡ ቀጠለ ።

ወኢያስተገበረ ፡ ሕሊናሁ ፡ በምንትኒ ፡ ዘይክልኦ ፡ አስተባጽሖ ፡ ኀበ ፡
እግዚአብሔር ።

www.ethiopianorthodox.org

ሕሊናውንም ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ከመሆን ፡ የሚ
ለየውን ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አላሠራውምና ።

ወሥርዓት ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ለክልኤ ፡ ክፍል ።
እንኪያስ ፡ የምንሁስና ፡ ሥራ ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ ናት።

ሥርዓተ ፡ ኄራን ።
አንዱ ፡ የወጣንያን ፡ ሥራ ።

ወሥርዓት ፡ ፍጹማን ።
ሁለተኛው ፡ የፍጹማን ፡ ሥራ ።

ሥርዓተ ፡ ፍጹማንሰ ፡ ውእቱኬ ፡ ሥርዓተ ፡ ኤልያስ ፡ ወማቴዎስ ፡ ወ
ሐና ፡ ወማርያም ፡ እኅተ ፡ ማርታ ።
የፍጹማን ፡ ሥራስ ፡ የኤልያስ ፡ የማቴዎስ ፡ የሐና ፡
የማርያም ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ወሥርዓተ ፡ ኤልያስ ፡ ወማቴዎስ ፡ ይኄይስ ፡ እምሥርዓተ ፡ አብርሃ
ም ፡ ወዘኬዎስ ።
የኤልያስ ፡ ከአብርሃም ፤ የማቴዎስ ፡ ከዘኬዎስ ፡ ሥራ ፡
ይበልጣል ።

ወምግባረ ፡ ሐና ፡ ወማርያም ፡ ይኄይስ ፡ እምግባረ ፡ ሳራ ፡ ወማርታ ።
የሐና ፡ ከሳራ ፡ የማርያም ፡ ከማርታ ፡ ሥራ ፡ ይበልጣ
ል ።

አኮ ፡ በሕሊና ፡ አላ ፡ በሥርዓት ።
መብለጡም ፡ በሥራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሕሊና ፡ አይደ
ለም ።

እስመ ፡ አብርሃም ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ በሕሊናሁ ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮ ፡ እ
ግዚአብሔር ፡ ወበብኅ ።
አብርሃም ፡ በሕሊናው ፡ ሰውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በ
መውደድ ፡ ፍጹም ፡ ነበርና ።

በእንሶስዎቱ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ እየኖረ ።

ወእግዚአብሔር ፡ ፈቀደ ፡ ዘንተ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ መኖሩን ፡ ጌታ ፡ ወዶለት ፡ ነው ።

እስመ ፡ ሀለዎ ፡ ይኩን ፡ ክርስቶስ ፡ እምዝርው ።
ክርስቶስ ፡ ከወገኑ ፡ ይወለድ ፡ ዘንድ ፡ አለውና ።

ወከማሁ ፡ ዳዊትኒ ፡ ንኑሥ ፡ ኮነ ፡ ትሑተ ።
ዳዊትም ፡ ትሑት ፡ ነበረ ። አንሰ ፡ ዕዴ ፡ ወአከ ፡ ሰብ
እ ፡ ይላልና ።

ወጸድቀ ።
እውነተኛ ፡ ነበር ። አነ ፡ ዐቀብኩ ፡ ፍናወ ፡ ዕፁባተ ፡
ይላልና ።

ወባሕቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ኤልያስ ፡ ኮነ ፡ ይኄይስ ፡ እምሥርዓታቲሆሙ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከዳዊት ፡ ከአብርሃም ፡ ሥራ ፡ የኤልያስ ፡
ሥራ ፡ ይበልጥ ፡ ነበረ ።

ወሶበ ፡ ተሰእሎ ፡ አሐዱ ፡ እኁሁ ፡ ለአባ ፡ ይስቲር ፡ (ይስሪን) ።
ይስቲር ፡ የተባለ ፡ መጣዕ ፡ (ሊባኖስ) ፡ ነው ። አንድ ፡
መነኰሰ ፡ አባ ፡ ይስቲርን ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ። እንደ
ምን ፡ ቢሉ ፡ ማዕሠረ ፡ ተዋስቦን ፡ ማዕሠረ ፡ ምንዅ
ስና ፡ እንደ ፡ ፈታው ፤ ማዕሠረ ፡ ምንዅስናንም ፡ ማ
ዕሠረ ፡ ተዋስቦ ፡ የሚፈታውና ፡ የሚጠቅመው ፡ መ
ስሎት ፡ ይጠይቃል ፡ ይላሉ ። መነኰሴውስ ፡ እንደ ፡
አብርሃም ፡ ሚስት ፡ አግብቼ ፡ ልኑር ፡ ብሎ ፡ አይጠ
ይቅም ፡ ብለህ ።

በእንተ ፡ ሥርዓት ፡ ዘይሠራዕ ፡ ቦቱ ።
የሚኖርበትን ፡ ያናዋፉን ፡ ነገር ፡ በርድናን ፡ ልኑር ፡
በተባሕትዎ ፡ ብሎ ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ።

ይቤሎ ፡ ጽሑፍ ።
ጽሑፍ ፡ አለ ።

እስመ ፡ አብርሃም ፡ ያፈቅር ፡ ነግደ ።
አብርሃም ፡ እንግዳ ፡ መቀበልን ፡ ይወድ ፡ እንደነበረ ።

ወእግዚአብሔር ፡ ሀሎ ፡ ምስሌሁ ።
እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ እንዳደረበት ።

ወዳዊትኒ ፡ ኮነ ፡ ትሑተ ።
ዳዊትም ፡ ትሑት ፡ እንደ ፡ ነበረ ።

ወሀሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሁ ።
እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ እንዳደረበት ።

ወኤልያስኒ ፡ ኮነ ፡ ያወትር ፡ ጎድዓተ ፡ ወብሕቃዊ ።
ያፈቅር ፡ ሲል ፡ ነው ። ኤልያስም ፡ ከሰው ፡ መለየት
ን ፡ ብቸኝነትን ፡ ይወድ ፡ እንደ ፡ ነበረ ።

ወእግዚአብሔር ፡ ሀሎ ፡ ምስሌሁ ።
እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ እንዳደረበት ።

ወዮሎክ ፡ ግብረ ፡ ዘይክውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ግበር ።
የምትሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ሥ
ራው ።

ወይሄሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌክ ።
እንዲህ ፡ ያደረግህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጌታ ፡ በረድኤት ፡
አድሮብህ ፡ ይኖራል ፡ አለው ፡ እንጂ ።

ወኢይቤሎኪ ፡ ግባእ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።
ወደ ፡ ዓለም ፡ ተመልሰህ ።

ወእውስብ ፡ ወተሰእክ ፡ ለንግድ ፡ ክመ ፡ አብርሃም ።
እንደ ፡ አብርሃም ፡ ሚስት ፡ አግብተህ ፡ እንግዳ ፡ ተ
ቀበለህ ፡ ኑር ።

ወቲተሐት ፡ ክመ ፡ ዳዊት ፡ ለዘትርእስ ፡ ላዕሌሁ ።
እንደ ፡ ዳዊትም ፡ ገባር ፡ ለሆንኸው ፡ ሰው ፡ ተዋርደ
ህ ፡ ለዘትንዕስ ፡ ቢል ፡ በፈቃድ ፡ ለምታንሰው ፡ ትሕ
ትና ፡ ሠርተህ ፡ ኑር ፡ አላለውም ።

አላ ፡ ፈቀደ ፡ ክመ ፡ ይሠራዕ ፡ ውስተ ፡ ምንሁስና ፡ ምስለ ፡ ገቢር ፡ እ
ምግብሬት ፡ እንተ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ከሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡
ትሩፋት ፡ ከመሥራት ፡ ጋራ ፡ በምንሁስና ፡ ግብር ፡
ተወስኖ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ተባሕትዎን ፡ ወደደለት ፡
እንጂ ፡ ኢይቤሎ ፡ ግባዕ ። ምስለ ፡ ገቢር ፡ አለ ፤ ተ
ባሕትዎ ፡ ያገኙ ፡ ብሎ ፡ ከዋሸ ፡ ቢከተቱ ፡ ሥራ ፡
ከልሰሩ ፡ እንዳሸከከ ፡ መወተፍ ፡ ነውና ፤ ሐተታ ፡ ይህ ፡
ሰው ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ አውቆታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡
መነኰሴውን ፡ እንደምን ፡ ሚስት ፡ አግባ ፡ እለዋለ
ሁ ፡ አታግባስ ፡ ብለው ፡ ያለልቡናው ፡ ይሆናል ፡ ብ
ሎ ፡ አማኸይ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ነግሮታል ።

እስመ ፡ ሥርዓተ ፡ ምንሁስና ፡ በኀበ ፡ አበው ፡ ለኀበ ፡ ወለስቱ ፡ ክፍል ።
እንኪያስ ፡ የምንሁስና ፡ ሥርዓት ፡ በአበው ፡ ዘንድ ፡
ሶስት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ከሶስት ፡ ይከፈላል ።

ጎድዓት ፡ ምስለ ፡ ተጋድሎ ።
አንዱ ፡ ባሕታዊ ፡ ዘበጎድዓት ፡ ነው ።

ወደዌ ፡ ምስለ ፡ አኰቴት ።
አንዱ ፡ ድውይ ፡ ዘበአኰቴት ፡ ነው ።

ወተልእኮ ፡ ምስለ ፡ ፍሥሓ ፡ ወጥብኅት ።
አንዱ ፡ ረድዕ ፡ ዘበጥብዓት ፡ ነው ። አንዱ ፡ ባሕታ
ዊ ፡ ዘበጎድዓት ፡ ነውና ። አንዱ ፡ ድውይ ፡ ዘበአኰ
ቴት ፡ ነውና ፡ የኤልያስን ፡ ነገር ፡ ነገረው ። አንዱ ፡
ረድዕ ፡ ዘበጎድዓት ፡ ነውና ፡ የዳዊትን ፡ የአብርሃም
ን ፡ ነገር ፡ ነገረው ።

ወዘሰ ፡ ውስተ ፡ ጎድዓት ፡ ይጸመድ ፡ ተሐይጦ ።
በተባሕትዎ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የሰይጣንን ፡ ነገር ፡ ይወቅ ፡
ያስተውል ፤ አንድም ፡ ተሐይጦ ፡ በዝ ፤ ለሰይጣን ፡
የተሸነገለ ፡ መስሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገልግል ።

ወያርስን ፡ ልቦ ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክመ ፡ ኤልያስ ።
እንደ ፡ ኤልያስ ፡ ልቡን ፡ በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡
ያናድ ።

ወይጹም ፡ ወይጸሊ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርዓት ።
ሁሌጊዜ ፡ ይጹም ፡ ይጸልይ ።

ወይትዓገሥ ፡ ስተቃትሎተ ፡ ሰይጣናት ፡ ዘኀቡዕ ፡ ወክሡት ።
በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ የሚመጣ ፡ የሰይጣንን ፡ ጦር ፡
ይታገሥ ። ኅቡዕ ፤ አንበሳ ፡ ዘንዶ ፡ መስለው ፤ ክሡት ፡
ኅሡም ፡ ገጹን ፡ ጽሉም ፡ ራዕዩን ፡ ገልጾ ፡ የሚመጸ
ውን ።

ወይግበር ፡ ውኂተ ፡ ግብረ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኮ ፡ በእንተ ፡
ሰብእ ።
ሰው ፡ ያመስግነኝ ፤ አንድም ፡ ሰውነቴ ፡ ይጠቀም ፡ ብ
ሎ ፡ ያይደለ ፡ ሥራውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ይ
ሥራው ።

ወዘኒ ፡ ውስተ ፡ ደዌ ፡ ዘለዓለም ፡ ይትመሰሎ ፡ ለዳዊት ፡ ውስተ ፡ አስ
ተስርዮቱ ።
በደዌ ፡ ዳኛ ፡ ባልጋ ፡ ቁራኛ ፡ ተይዘ ፡ የሚኖርም ፡ ኃ
ጢአቴን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ በማለት ፡ ዳዊትን ።

ወበእንተ ፡ አንሶ ፡ መንፈስ ፡ በትዕግሥቱ ፡ ለኢዮብ ፡ ወአኰቴቱ ፡ ሰ
እግዚአብሔር ።
ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ አላፊ ፡ ሁኖ ፡ መከራ ፡ በመታገ
ሥ ፡ ጌታን ፡ በማመስገን ፡ ኢዮብን ፡ ይምሰለው ።

ወኢይትዓንተል ፡ ላዕለ ፡ ላዕኩ ፡ ወኢእምን ፡ ኃጢአ ፡ ዘይሰንዓዎ ።
የሚስማማውን ፡ ምግብ ፡ ከማጣቱ ፡ የተነሣ ፡ በረዱ ፡
አይበጻበጽ ፤ በገዳም ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ አይገኝምና ፤
አንድም ፡ በረዱ ፡ አይበጻበጽ ፤ ወእምን ፡ ኃጢአ ፡ የ
ሚስማማው ፡ ረድዕ ፡ ከማጣቱ ፡ የተነሣ ፡ አይበጻበጽ ፤
አንድም ፡ የድውይ ፡ ጸሎት ፡ ይጠቅማልና ፡ ይጸል
ይ ፡ ቸል ፡ አይበል ።

ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እኁኑ ፡ ዘኢይክል ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ጎድዓት ።
በተባሕትዎ ።

ወኢውስተ ፡ ደዌ ፡ ዘዘልፍ ።
በደዌ ፡ መኖር ፡ የማይቻለው ፡ ቢሆን ፤ ምነው ፡ ደዌ
ማ ፡ የግድ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ እንደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡
ግብር ፡ ገበተው ፡ የሚያመጡት ፡ የፈቃድ ፡ ደዌ ፡ አ
ለና ።

በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ይትለአክ ፡ ለእኁኑ ፡ ድውይ ፡ ወበአረጋዊ ፡ ድኩም ።
ስለዚህ ፡ ድውዩን ፡ አረጋዊዉን ፡ ይርዳ

አው ፡ ለእኁኑ ፡ ዘበውስተ ፡ ጎድኣት ፡ ዘዘልፍ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ባሕቲቱ ፡ ወአኮ ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ ምድራዊ ።
እበላበት ፡ እጠጣበት ፡ ብሎ ፡ ያይደለ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ ተባሕትዎ ፡ የያዘውን ፡ ሕፃኑን
ም ፡ መነኰሴ ፡ ቢሆን ፡ ይርዳው ፤ አንድም ፡ ይትለአ
ክ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ ለእግዚ
አብሔር ፡ ብሎ ፡ ይርዳው ፤ ወአከ ፤ ሰውነቴ ፡ ይጠቀ
ም ፡ ብሎ ፡ አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

አላ ፡ ይምትር ፡ ፈቃደ ፡ ወይግበር ፡ ሥምረቶ ፡ ለዘይትአአኮ ።
የሱን ፡ ፈቃድ ፡ ትቶ ፡ የሚረዳውን ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽምለት ፡ እንጂ ፤ አንድም ፡ የሱን ፡ ፈቃድ ፡ ለ ዚያ ፡ ለሚረዳው ፡ ሰው ፡ ያድርግ ፤ አንድም ፡ ጌታ ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ ይሥራለት ።

በአፍቅሮ ፡ ወፍሥሓ ፡ ወአኮ ፡ በመንኖ ፡ ወአንጉርጉሮ ።
በማቃለል ፡ ያይደለ ፡ በፍቅር ፤ በማዘን ፡ ያይደለ ፡ በ ደስታ ።

አላ ፡ ይትለአክ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወአኮ ፡ በእንተ ፡ ሰብእ ።
ለሰው ፡ ብሎ ፡ ያይደለ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ ይርዳ ው ፡ እንጂ ።

እሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂሮ ፡ ኵሉ ፡ ክመጣ ፡ ይክውኑ ፡ እሙንቱ ፡ ዕሩያን ፡ ፍጹይ ።
እሊህ ፡ ሶስቱ ፡ በሥራ ፡ ቢተካከሉ ፡ በዋጋም ፡ የተካ ከሉ ፡ ይሆናሉ ።

በክመ ፡ ቀደመ ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ ክልኤቱ ፡ አኃው ።
የውሉደ ፡ ኃጋዲ ፡ መተካከል ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ።

እስመ ፡ ኮኑ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ፍጹማን ፡ በሥርዓቶሙ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ማዕርግ ፡ አሐዱ ፡ ዘበጽሙና ፡ ወክልኤኒ ፡ ዘበመልእክት ።
ባሕታዊና ፡ ረድእ ፤ አንድም ፡ ኤልያስና ፡ አብርሃም ፤ አንድም ፡ ሙሉዩ ፡ ኃጋዲ ፡ አንድ ፡ በምታደርጋቸው ፡ በማዕዝ ፡ ርትዕ ፡ ሁነው ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ሁሉ ም ፡ ፍጹም ፡ ናቸውና ።

ሐተታ ፤ አሁን ፡ ዛሬ ፡ ያንድ ፡ ጨዋ ፡ ልጆች ፡ ሁለት ፡ ሁነው ፡ ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ ይገባሉ ። አንዱ ፡ መከዳ ፡ አቃፊ ፤ ዙፋን ፡ ቤት ፡ አንጣፊ ። አንዱ ፡ ቋ ሚ ፡ ለጓሚ ፡ ቢሆን ፡ ሁሉም ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሉ ፤ የንጉሥ ፡ ባለሟል ፡ ናቸው ፡ እንዲባሉ ። ሁለ ት ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ አሐዱ በፍኖት ፡ መጕንድይ ፡ ይላል ። በዙሪያ ፡ መንገድ ፤ አንዱ ፡ በስርጥ ፡ መንገ ድ ፡ ወጥተው ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ እን ዲታዩ ፤ ባሕታውያንም ፡ ፍጹማኑ ፡ ከንጽሐ ፡ ልብ ፡ ደርሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጌታን ፡ ቢያዩ ፤ ወጣንያን ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳያዩ ፡ ቢቀሩ ፤ ኋ ላ ፡ በመንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ጌታን ፡ በማየት ፡ አንድ ፡ ናቸውና ።

ወበእንተገ ፡ ይቤ ፡ አባ ፡ ባምዋ ።
የሚተካከሉ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ዖበ ፡ አኮ ፡ ጸሙ ፡ ለአሐዱ ፡ ወጸሎቱ ፡ እምኢበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ምሕረት ፡ ወተልእኮተ ፡ ካልኡ ።

የባሕታዊ ፡ ጸሙ ፡ ጸሎቱ ፡ በግዕዝ ፡ ርትዕ ፡ ባይሆ ን ፡ ጸሙ ፡ እርድናውን ፤ ጸሎቱ ፡ ምጽዋቱን ፡ ባልተ ካከለውም ፡ ነበር ። በግዕዝ ፡ ርትዕ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ይ ተካከላል ፡ አለ ።

ወዖበ ፡ አኮ ፡ ተልእኮተ ፡ ካልኡ ፡ በግዕዝ ፡ ርትዕ ፡ እምኢኮነ ፡ ይትዔ ረዮ ፡ ለዘውእቱ ፡ ውስተ ፡ ጎድኅት ።
የረዱም ፡ ርድናው ፡ ምጽዋቱ ፡ በግዕዝ ፡ ርትዕ ፡ ባይ ሆን ፤ ርድናው ፡ ጸሙን ፡ ምጽዋቱ ፡ ጸሎቱን ፡ ባል ተካከለውም ፡ ነበር ፤ በግዕዝ ፡ ርትዕ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ይተካከለዋል ፡ አለ ።

ወናሁ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓዊ ፡ እንጦንስ ።
ንዕድና ፡ ያለው ፡ እንጦንስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

እመቦ ፡ እንኑ ፡ ዘይነብር ፡ በበዓቱ ፡ በጎድባት ፡ ዓመታተ ፡ ብዙኀ ።
ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ በበዓቱ ፡ ተከቶ ።

ወኢየአምር ፡ እፎ ፡ ንብረት ፡ ውስቴታ ፡ አሐደኒ ፡ ዕለተ ።
ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ከበዓት ፡ ተከቶ ፡ መኖሩን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ስንኳ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ።

ዘውእቱ ፡ ኢየሐስብ ፡ ነፍሶ ፡ ክመ ፡ ኃጥኣ ፡ ወስዑን ፡ ወኢብድ ፡ አላ ፡ ያጸድቅ ፡ ነፍሶ ፡ ወያነውሮሙ ፡ ለካልኣን ።
ይኸውም ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ነው ። ንጹሕ ፡ ጻድቅ ፡ ነኝ ፡ ቢል ፡ አይተካከለውም ። ኃጥአ ፡ ነኝ ፤ ስውን ፡ ነኝ ፡ ቢል ፡ ይተካከለዋል ፡ አለ ።

ወጎድኣትሰ ፤ ፍጹም ፡ ውእቱክ ፡ ሥርዓት ፡ ትፋፍ ።
እንኪያስ ፡ ከርድና ፡ ሥራ ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ይ በልጣል ፤ ይህም ፡ ፍጹም ፡ ሥራ ፡ ነው ። አንድም ፡ ሥርዓተ ፡ ትሩፍ ፤ የፍጹም ፡ ሥራ ፡ ነው ።

በክመ ፡ መንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይኄይስ ፡ እመላእክት ፡ መንረሳው ያን ፡ ቅዱሳን ።
ከመላእክት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲበልጥ ፡ ከረድ ፡ ባሕታዊ ፡ ይበልጣል ። ባሕርየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከባ ሕርየ ፡ መላእክት ፡ እንዲበልጥ ፤ ከርድና ፡ ሥራም ፡ የተባሕትም ፡ ሥራ ፡ ይበልጣል ።

እስመ ፡ ሖረ ፡ ካልኣ ፡ እምን ፡ አኃው ፡ ኀበ ፡ አርሳንዮስ ።
ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ ከአኃው ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አ ርሳንዮስ ፡ ሄደ ።

ወኢተወክፎ ።
አልተቀበለውም ።

ወኢያዕረፎ ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮቱ ፡ ጎድኦተ ፡ ወብሕትውና ።
ተባሕትዎን ፡ ስለ ፡ ወደደ ፡ ደስ ፡ አላሰኝውም ።

ወሖረ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ሙሴ ።
ደጓሞ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ ሄደ ።

ወተወክፎ ፡ በፍሥሓ ፡ ወበእክሞስዶ ።
ደስ ፡ ብሎት ፡ ስቆ ፡ ተቀበለው ። እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ እየዘረ ፡ አበውን ፡ የሚጠይቅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። መጥቶ ፡ ከአኃው ፡ አንዱን ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አር ሳንዮስ ፡ ውሰደኝ ፡ አለው ። ይዞት ፡ ሄደ ። ተባሕት ዎን ፡ ይወዳልና ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ ። እስኪ ፡ ካባ ፡ ሙሴ ፡ ዘንድ ፡ ውሰደኝ ፡ አለው ፤ ይዞ ት ፡ ሄደ ፤ ስቆ ፡ ተቀበለው ። ያ ፡ የወሰደው ፡ ሰው ፡ ናሁ ፡ አብጻሕኩከ ፡ ኀበ ፡ ትሩፍ ፡ ሮማዊ ፤ ውኀበ ፡ ጽሙድ ፡ ግብጻዊ ፤ መነ ፡ ታኄይስ ፡ እምእሉ ፡ አለ ው ። ያን ፡ ፍቅረ ፡ ገምድል ፡ አባ ፡ አርሳንዮስን ፡ አ አትበለኝ ፤ መነሑሰ ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ እንጂ ፡ ብሎታ ል ።

ወዖበ ፡ ሰምዐ ፡ ክልዕ ፡ እምአኃው ።
ይህን ፡ ሲለው ፡ ከአኃው ፡ አንዱ ፡ አብስልዲስ ፡ በሰ ማ ፡ ጊዜ ።

ይቤ ፡ እግዚኦ ፡ እፎኑ ፡ ይጐይይ ፡ እምዕብኣ ፡ አሐዱ ፡ በእንቲአክ ።
አቤቱ ፡ አንዱ ፡ ላንተ ፡ ብሎ ፡ ከሰው ፡ ይለያል ።

ወክልኤ ፡ ይትዋከፍ ፡ ዕብኣ ፡ በእንቲአክ ።
አንዱ ፡ ላንተ ፡ ብሎ ፡ እንግዳ ፡ ይቀበላል ፤ ይህ ፡ እ ንደምን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ አመለከተ ።

ወርእየ ፡ እንከ ፡ ክልኤተ ፡ አሕማረ ፡ ውስተ ፡ ፈሰጣ ፡ ዐቢይ ።
ከወባይ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ መርከቦች ፡ ሲሄዱ ፡ አየ ። ወ ባይ ፡ ላይ ፡ መርከብ ፡ ያስጥላልን ፡ ቢሉ ፤ አዎን ፡ ከሪ ፍ ፡ እስከ ፡ እስክንድርያ ፡ ያስጥላል ።

ወአርሳንዮስ ፡ ውስተ ፡ አሐዱ ፡ እምእሉሙ ፡ በጎድኣት ።
አርሳንዮስ ፡ ከሁለቱ ፡ በንዱ ፡ መርከብ ፡ ሁኖ ፡ ብፓ ውን ።

ወመንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሁ ።
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠበት ። እንደም ፡ እሳት ፡ ሁኖ ፡ ተውሕዶት ።

ወአባ ፡ ሙሴ ፡ ውስተ ፡ ካልእታ ።
አባ ፡ ሙሴ ፡ በንዱ ፡ መርከብ ፡ ሁኖ ።

ወመላእክት ፡ ቅዱሳን ፡ ምስሌሁ ።
መላእክት ፡ አብረዉት ፡ ሁነው ።

ወእሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ያበልዕዎ ፡ መኃረ ፡ እምጸቃውዕ ።
ዕሜት ፡ ፍቅሩን ፡ ጸቃውዕ ፡ መዓር ፡ ሲመላበት ፡ አ የ ።

ሥርዓተ ፡ ጎድኣት ፡ ይኄይስኬ ።
እንኪያስ ፡ ከርድና ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ይበልጣ ል ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ልዑል ፡ እምሁሉ ፡ ፍጥረተ ፡ እንለ ፡ እመሕያው ።
ከሰው ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ነው ፡ አለ ፤ አይሠራውምና ።
አንድም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ይበል ጣልና ። አንድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመላእክት ፡ እንዲበልጥ ፤ ከረዱ ፡ ባሕታዊ ፡ ይበልጣል ፤ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ነውና ።

ወውእቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ትፋፍ ።
ይኸውም ፡ የፍጹማን ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ዘዝንሓውያን ።
የናባ ፡ አጋቶን ።

ወፈላስያን ፡ ክልኤቱ ።
ከሎንያ ፡ ከአስክንድርያ ፡ ተወጻጽተው ፡ የሄዱ ።

ወገዳማውያን ፡ ወባሕታውያን ።
የናባ ፡ ሲሶይ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፪ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ወለምንትኑ ፡ ይቤ ፡ አባ ፡ ባምዋ ፡ ዖበ ፡ አኮ ፡ ጸ ሙ ፡ ለአሐዱ ፡ እምኢተዓረየ ፡ ለምሕረተ ፡ ካልኡ ።
አባ ፡ ባምዋ ፡ የባሕታዊ ፡ ጸሎቱ ፡ በግዕዝ ፡ ርትዕት ፡ ካልሆነ ፡ ጸሙ ፡ ምጽዋቱን ፡ ጸሎቱ ፡ እርድናውን ፡ አይተካከለውም ፤ በግዕዝ ፡ ርትዕት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ይ ተካከለዋል ፡ ያለው ።

ወዖበ ፡ አኮ ፡ መልእክቱ ፡ ለካልኡ ፡ ዘበግዕዝ ፡ ርትዕት ፡ እምኢተዓረ ዮ ፡ ለእንጉሁ ፡ ዘውስተ ፡ ጎድኣት ።
እርድናው ፡ ምጽዋቱ ፡ በግዕዝ ፡ ርትዕት ፡ ካልሆነ ፡ ምጽዋቱ ፡ ጸሙን ፤ እርድናው ፡ ጸሎቱን ፡ አይተካከ ለውም ፤ በግዕዝ ፡ ርትዕት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ይተካከለ ዋል ፡ ያለ ፡ ከምን ፡ አምጥቶ ፡ ነው ፡ ከመጽሐፍን ፡ አላገኙቶ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ከልቡ ፡ አንቅቶ ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ፤ እሊህ ፡ ጥያቄ ፡ አቅንተዋል ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፡ በእንተ ፡ ዘቀደመ ፡ ተጽሕፎቱ ፡ እምርትዓቱ ፡ ስ ለ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓቱ ፡ ከመ ፡ ዝሂሎቱ ።
ከነዚህ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ከቅንነቱ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ቸ ፡ ለው ፡ ባሚሠራው ፡ ሥራ ፡ የመተካከላቸው ፡ ነ ገር ፡ እኒ ፡ ስለ ፡ ቀደመ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ካባ ፡ በምዋ ፡ ጽሑፍ ፡ ቀድሞ ፡ አይደለም ፤ የውሉደ ፡ ኃጋዲ ፡ ነገ

www.ethiopianorthodox.org

ር ፡ በመጽሐፈ ፡ ገነት ፡ ከታወቀ ፡ ብሎ ፤ አንድም ፡ በወንጌል ፡ የተነገሩ ፡ ገባዕተ ፡ ነግህ ፡ መሠርክ ፡ የባሕ ታውያን ፡ ምሳሌ ፡ ከሆኑ ፡ ብሎ ፤ አንድም ፡ ሁለቱን ም ፡ ብፁዕ ፡ ብሏቸዋልና ፤ አንድም ፡ በሕሊናሰ ፡ ከ ኑ ፡ መሻርያነ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትበሀል ፡ በክ ።

የርድና ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ ሊባል ፡ አይገባም ።

እስመ ፡ ዅሉ ፡ ዘይርኅቅ ፡ ኦምዅሉ ፡ ኀዋዩ ።

ከገንዘብ ፡ የሚለይ

ወይኑበር ፡ ውስተ ፡ ጎድኣት ።

በተባሕትዎ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ።

ወለእመ ፡ ኢይጸውም ፡ ለዓለም ፡ ወኢይጼሊ ፡ ዘንባለ ፡ ጾርዓት ።

ሁለጊዜ ፡ ካልጸመ ፡ ካልጸለየ ።

ኢይትኄረዮ ፡ ለዘሶቱ ፡ ጥፊት ፡ ወምሕረት ፡ ወመልእክት ፡ ፍጽምት ።

ገንዘብ ፡ ያለውን ፡ የሚረዳ ፡ የሚመጸውተውን ፡ አይ ተካከለውምና ፡ የርድና ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ አይባልም ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዘውስተ ፡ ጎድኣት ።

እመኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ምንም ፡ በተባሕትዎ ፡ ቢኖር ፡ አይተካከለውምና ፡ ኢይደሉ ፡ ይትበሀል ፡ በክ ።

ለእመ ፡ ኮነ ፡ ድውይ ፡ ዘየአኵት ።

ድውይ ፡ ዘበአኰቴትም ፡ ቢኖር ።

ወኢይክል ፡ በእንተ ፡ ደዌሁ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ጻዋሚ ፡ ወይጸሊ ፡ ለዓ ለም ።

በደዌው ፡ ምክንያት ፡ ይጸም ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ የማ ይቻለው ፡ ቢሆን ።

ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘውስተ ፡ ዓለም ፡ ዝክቱ ፡ እጉ ፡ ኀአክ ፡ ወመሐሪ ።

በዓለም ፡ ያለ ፡ ረድም ፡ ቢኖር ፤ የሚረዳ ፡ የሚመጸው ትም ፡ ቢሆን ።

ወሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ወውሉድ ።

ሚስት ፡ ልጅ ፡ ያለው ፡ ቢሆን ።

ወውእቱ ፡ ይገብር ፡ መልእክተ ፡ ወምሕረተ ፡ በአምጣነ ፡ ይክል ፡ እን ዘ ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ወውሉድ ።

በዓለም ፡ እየኖረ ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ እያለው ፡ እንደተቻ ለው ፡ ቢረዳ ፡ ቢመጸውት ፡ ልጁን ፡ ሚስቱን ፡ ጥሎ ፡ ካልሄደ ፡ አይተካከለውምና ፡ የርድና ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ ሊባል ፡ አይገባም ፤ ከዓለማዊ ፡ ረድ ፡ ገዳማዊ ፡ ረድ ፡ ይበልጣል ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥ ራ ፡ ከንቱ ፡ ሊባል ፡ አይገባም ፤ ከገንዘቡ ፡ የሚለይ ፡ በተባሕትዎ ፡ የሚኖር ፡ ካልጸመ ፡ ካልጸለየ ፡ ገንዘብ ፡ ያለውን ፡ የሚረዳ ፡ የሚመጸውተውን ፡ አይተካከለ ውምና ፤ ቢጸም ፡ ቢጸልይ ፡ ግን ፡ ይተካከለዋልና ፤ የ ተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ ሊባል ፡ አይገባም ፤ እመ ሰ ፡ ዘውስተ ፡ ጎድኣት ፡ ኮነ ፡ ድውየ ፡ ዘየአኵት ። በተ ባሕትዎ ፡ ያለው ፡ ድውይን ፡ ቦ ፡ ሆን ፡ ግን ፡ በደዌ ፡ ምክንያት ፡ መጸም ፡ መጸለይ ፡ ባይቻለው ፡ እንዳለፈ ው ፡ ተርጕም ፤ ሚስቱን ፡ ልጁን ፡ ጥሎ ፡ ቢሄድ ፡ ይ ተካከለዋልና ፤ ልጁን ፡ ሚስቱን ፡ ጥሎ ፡ ባይሄድ ፡ አ ይተካከለውምና ፤ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ ሊባል ፡ አይገባም ፤ አንድም ፡ የርድና ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ ሊባል ፡ አይገባም ፤ ከገንዘቡ ፡ የሚለይ ፡ ከገ ንዘቡ ፡ ተለይቶ ፡ በተባሕትዎ ፡ የሚኖር ፡ ሁለጊዜ ፡ ካ ልጸመ ፡ ከልጸለየ ፡ ገንዘብ ፡ ያለውን ፡ የሚረዳ ፡ የሚ መጸውተውን ፡ አይተካከለውምና ፤ ምንም ፡ በተባሕት ዎ ፡ ቢኖር ፡ አይተካከለውም ፤ የርድና ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ አይባልም ፤ ድውይ ፡ ዘየአኵትም ፡ ቢኖር ፡ በደዌ ፡ ምክንያት ፡ መጸም ፡ መጸለይ ፡ የማይቻለው ፡ ቢሆን ፡ በዓለም ፡ ያለ ፡ ረድ ፡ ቢኖር ፡ የሚረዳ ፡ የሚመጸው ት ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እ የኖረ ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ እያለው ፡ የሚረዳ ፡ የሚመጸው ት ፡ ቢሆን ፡ ልጁን ፡ ሚስቱን ፡ ጥሎ ፡ ካልሄደ ፡ እንዳ ይተካከለው ፡ ሚስቱን ፡ ልጁን ፡ ጥሎ ፡ ቢሄድ ፡ እንዲ ተካከለው ፤ ያም ፡ ካልጸመ ፡ ካልጸለየ ፡ አይተካከለው ምና ፤ ቢጸም ፡ ቢጸልይ ፡ ግን ፡ ይተካከለዋልና ፤ የርድ ና ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ኢይተበሀል ፡ በከ ፤ አንድም ፡ ይቤ ፡ አባ ፡ በምዋ ፡ ይተካከላሉ ፡ አለ ።

እምኢኮኑ ፡ አበው ፡ ያዴርዩ ፡ ግብሮ ፡ ወፍዳዮ ፡ ምስለ ፡ እጉ ፡ ዘው ስተ ፡ ጎድኣት ፡ ወብሕትውና ፡ በክመ ፡ ኢያበተዐደዩ ፡ ሥርዓተ ፡ ወዕ ሜተ ፡ ማቴዎስ ፡ መጸብሓዊ ፡ ምስለ ፡ ሥርዓተ ፡ ዘዜዎስ ፡ ሊቀ ፡ መ ጽብሓን ።

ማቴዎስ ፡ ከዘዜዎስ ፡ ጋራ ፡ በሥራ ፡ በዋጋ ፡ እንዳይ ተካከል ፤ በርድና ፡ ያለው ፡ በተባሕትዎ ፡ ያለውን ፡ አይተካከለውምና ፤ ኢይተበሀል ፡ በከ ፤ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ከንቱ ፡ አይባልም ።

ወክልኤሆሙ ፡ ፈቀዱ ፡ ክመ ፡ ያሥምርዎ ፡ ለእግዚእብሔር ። ክልኤሆሙ ፡ ውሉደ ፡ ነጋዲ ። አንድም ፡ ዘኬዎስና ፡ ማቴዎስ ። አንድም ፡ ረድና ፡ ባሕታዊ ፡ ጌታን ፡ ሊ ያገለግሉት ፡ ወደዱ ።

ወበአምጣነ ፡ ንጽሕ ፡ ግዕዝኬ ፡ ወሥርዓት ፡ ዘበእንተ ፡ ምግባረ ፡ ት ሩፋት ፡ ትክውን ፡ ፍዳ ።

እንኪያስ ፡ ትሩፋት ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ የሚሰጥ ፡ ዋጋ ፡ እ ንደ ፡ ሕሊና ፡ ቅንነት ፡ ሥራ ፡ መጠን ፡ ነው ።

ወናው ፡ የዐርቅ ፡ ብእሲ ፡ እምዅሉ ፡ ጥሪት ፡ ወይሠራዕ ፡ ለጎድኣት ፡ ወብሕትውና ።

የሚነቀፍማ ፡ ምን ፡ ታጥቶ ፡ እነሆ ፡ ከገንዘቡ ፡ ተለይ ቶ ፡ ከበዓት ፡ ተከቶ ፡ በተባሕትዎ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ አለ ።

በጸም ፡ ወበጸሎት ።

እየጸመ ፡ እየጸለየም ፡

ወባሕቱ ፡ በግዕዝ ፡ ዘኢኮነት ፡ ርትዕት ።

ነገር ፡ ግን ፡ በግዕዝ ፡ ርትዕት ፡ አላደረገውም ።

እስመ ፡ ይክውንኬ ፡ ውእቱ ፡ ንግኒ ፡ ስብሐተ ፡ ሰብእ ።

ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ይፈልጋልና ።

ወናሁ ፡ ይክውን ፡ ኅዕበ ፡ ዘርቱዐ ፡ ግዕዝ ፡ ወሥርዓቱ ፡ ጕደሎ ።

ይግሞ ፡ ሕሊናው ፡ የቀና ፡ ሁኖ ፡ ሥራ ፡ የጐደለበ ት ፡ አለ ።

በእንተ ፡ ልህላሄ ፡ ሕሊናው ።

ሕሊናው ፡ ደካማ ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

አኮሰ ፡ በእንተ ፡ ድካመ ፡ ሥጋሁ ።

ሰውነቱ ፡ ደክሞ ፡ አይደለም ።

ወክግሣሁ ፡ ይመጽእ ፡ ኅልእኒ ፡ ምስለ ፡ ጥሪቱ ፡ ለጎበ ፡ ብሕትውና ።

ሌላም ፡ ገንዘቡን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ የሚመጣ ።

ወያየውርሙ ፡ ለመፍቅዳውያን ።

የሚሹ ፡ የሚሹትን ፡ እየሰጠ ፡ የሚያሰርፋቸው ፡ አ ለ ።

ወባሕቱ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ስብሐተ ፡ ሰብእ ።

ሰው ፡ ያመስግነኝ ፡ ብሎ ፡ አይደለም ።

ወናሁ ፡ ይገብር ፡ ውእቱ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ይሠራዋል ፡ እንጂ ።

ወባሕቱ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ኀሩቱ ፡ ወአኅቅሮቱ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ።

ኀሩት ፡ ይሁንልኝ ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ ወዶ ፡ አይደለ ም ።

አላ ፡ በእንተ ፡ ዘክመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ክመ ፡ ያገብር ፡ ነፍሶ ፡ በእንተ ፡ ዕዕበተ ፡ ጎድኣት ።

ረድኖ ፡ ተባሕትዎ ፡ ይይገዝ ፡ ዘንድ፡ የርድና ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ጭንቅ ፡ ስለ ፡ ሆነበት ፡ ሰውነቱን ፡ ለርድ ና ፡ ሥራ ፡ ያገብር ፡ ዘንድ ፡ የሚቻለው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ። እንደ ፡ አዛኝ ፡ ያዕቆብ ፤ ገንዘባቸው ን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ዋልድባ ፡ ገብተው ፡ ማኅበሩን ፡ አ ነሣ ፡ ገንዘቤ ፤ ይህን ፡ ይዛችሁ ፡ እርዱኝ ፤ ሥጋው ም ፡ ጠጅም ፡ አይኮደልብኝ ፡ ብለዋል ፡ ይላሉ ።

ተስእሎ ፡ ፫ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፡ ንፈቅድ ፡ ክመ ፡ ታዘይን ፡ ለን ፡ ስምዓታተ ፡ እፎኑ ፡ ዘኢይክውን ፡ ድልወ ፡ ዕርየት ፡ ምስለ ፡ ባሕታውያን ፡ ውስተ ፡ ፍድየ ት ፡ ዘውእቱ ፡ ዘውስተ ፡ ዓለም ።

በዓለም ፡ ያለ ።

ወሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ወውሉድ ።

ሚስት ፡ ልጅ ።

ወጥሪት ።

ገንዘብ ፡ ያለው ።

ወሥርዓተ ፡ ሠናይ ።

የሚሰጥ ፡ የሚመጸውት ። አንድም ፡ ጥሪት ፡ ባሪያ ፡ ያለው ፤ ወሥርዓቱ ፡ ሠናይ ፡ ባሮቹን ፡ እንደ ፡ ልጆቹ ፡ አርጎ ፡ የሚኖር ።

ወይመጸውት ፡ ላዕለ ፡ ምስእናን ።

ለነዳያን ፡ የሚመጸውት ።

ወያድኅኖሙ ፡ ለመሳቲሐን ።

በግፍዕ ፡ የታሠሩትን ፡ አንድም ፡ የሚከፍሉት ፡ አጥ ተው ፡ የታሠሩትን ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡ የሚያስፈታ ።

ወያግዕዝ ፡ ቅኑያን ።

ባሮቹን ፡ አጥተው ፡ የሚገዙትን ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡ ነ ፃ ፡ የሚያወጣ ።

ወያየውርሙ ።

የሚያሰርፋቸው ።

ወያስብጠሙ ፡ ለዕሙግን ።

ሸፋጭ ፡ ተነሥቶባቸው ፡ ዳኛ ፡ አድልቶባቸው ፡ የተ በደሉትን ። አንድም ፡ በረዶ ፡ መቶባቸው ፤ አንበጣ ፡ በልቶባቸው ፡ የተቸገሩትን ፡ የሚያስታርብ ።

ወያክብሮሙ ፡ ለጻድቃን ።

ጻድቃንን ፡ የሚያከብር ። ዘያከብሮሙ ፡ ለፈራሀያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

ወያረትዕ ፡ በውስተ ፡ ፍትሕ ፡ ማዕከለ ፡ ድኩማን ፡ ወኃያላን ።

በፍርድ ፡ ጊዜ ፡ በደካማውና ፡ በኃይለኛው ፡ መካከ ል ፡ ፍርድ ፡ የሚያቀና ፡ የነገር ፡ ብርቱ ፡ የነገር ፡ ደካ ማ ፡ አለና ። አንድም ፡ በቁመ ፡ የጐልበት ፡ ብርቱና ፡ ደካማ ፡ አለና ፤ ማዕከለ ፡ ድኩማን ፡ ወኃያላን ፡ አለ ።

ወኢይነሥኣ ፡ ህልያነ ፡ በውስተ ፡ ፍትሕ ።

በፍርድ ፡ ጊዜ ፡ መማለኛ ፡ የማይቀበል ፤ በፍርድ ፡ ጊዜማ ፡ እንደምን ፡ ቢሉ ፤ ጣቱን ፡ አገልቆ ፡ ያሳያል ና ። አንድም ፡ ኀላ ፡ ትሰጠኛለህ ፡ ብሎ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወኢለመፍቅዱ ፡ ርደ ።
ፈቃዱን ፡ ለመፈጸም ፡ አራጣ ፡ የማይቀበል ፤ ወዘኢ
ለቅሐ ፡ ወርቀ ፡ በርዴ ፡ እንጂ ፡ ይላል ፡ ብሎ ።
ወየሐፅን ፡ እጓለ ፡ ማውታ ።
እናት ፡ አባት ፡ የሌለውን ፡ ድሀውን ፡ የሚያሳድግ ፤
ጌታን ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ ለእጓለ ፡ ማውታ ፡ ይለዋል ፡ ብሎ ።
ወይቀውም ፡ ለመዓብ ።
ማን ፡ ተበደለ ፡ ብሎ ፡ የሚቆም ፤ ወመኰንኖን ፡ ለዕ
ቤራት ፡ እንጂ ፡ ይላል ፡ ብሎ ።
ወይሔውጽ ፡ መቁሓሳ ፡ ወድውያን ።
የታሠሩትን ፡ የሚጠይቅ ፤ ተሞቃሕኩ ፡ ወኢነበብከ
ሙኒ ፡ እንጂ ፡ ይላል ፡ ብሎ ።
ወይትቀንይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእምጣነ ፡ ኃይሉ ።
እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ በተቻለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የ
ሚያገለግል ፡ ሰው ፡ ከበሕታውያን ፡ ጋራ ፡ በሥራ ፡
በዋጋ ፡ እንደምን ፡ እንዳይተካከል ፡ ከመጻሕፍት ፡ ም
ስክር ፡ አምጥተህ ፡ ልታስረዳን ፡ እንወዳለን ፡ አሉት ።
ይቤ ፡ መተርጉም ፤ ዕውቅ ፡ ዝ ፡ እምታሳት ፡ እግዚእነ ።
ይህስ ፡ ጌታ ፡ ከተናገረው ፡ ቃል ፡ የተነሣ ።
ወሥርዓተ ፡ አበው ።
አበውም ፡ ከሠሩት ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ የታወቀ ፡ የተ
ረዳ ፡ ነው ። ሁለት ፡ አርእስት ፡ ነው ፤ ያመጣዋል ።
ወባሕቱ ፡ ለመድመ ፡ እግዚእ ፡ ለቅዱሳን ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ።
ጌታ ፡ ቅዱሳንን ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።
ወለመዮሙ ፡ ክዕበ ፡ ለዓለማውያን ፡ ውሉደ ፡ ዓለም ።
ዓለማውያንን ፡ ውሉደ ፡ ዓለም ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።
እስመ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ውሉደ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ይጠበቡ ፡ እምኵሉ
ደ ፡ ብርሃን ፡ በትውልደመ ፡ ዝንቱ ። (ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፰) ።
ምንም ፡ ይጠበቡ ፡ ቢል ።
እስመ ፡ ትራፍመ ፡ ጽድሕት ፡ ግብር ።
የዓለማውያን ፡ ትሩፋታቸው ፡ የማታስቸግር ፡ ናትና ።
እስመ ፡ ይእቲ ፡ ውጽኣት ፡ እምአርእስቲሆመ ።
ራሰቸውን ፡ ከመስጠት ፡ በአፍአ ፡ ስለ ፡ ሆነች ።
ወትራፎመ ፡ ለውሉደ ፡ ብርሃን ፡ ዕፅብት ፡ ለገቢር ።
የጸድቃን ፡ ግን ፡ ትሩፋታቸው ፡ ሊሠሯት ፡ ጭንቅ ፡
ናትና ።
እስመ ፡ ይእቲ ፡ በሕሊናተ ፡ ነፍሳቲሆመ ።
በልቡናቸው ፡ አስበው ።
ወበአባለ ፡ ሥጋቲሆመ ።
ሰውነታቸውን ፡ ለረኃብ ፡ ለጽምዕ ፡ ሰጥተው ፡ የሚሠ
ሯት ፡ ስለ ፡ ሆነ ።
እስመ ፡ እመንፍስኬ ፡ ያቂርቡ ፡ ነፍሳቲሆመ ፡ ሞጻሕተ ፡ ነባቢተ ፡ ወ
ቅድስተ ።
ባሕታውያንስ ፡ ሰውነታቸውን ፡ በረኃብ ፡ በጽምዕ ፡
ሠውተው ፡ ለጌታ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ያቀርባ
ሉ ።
በከመ ፡ ትእዛዙ ፡ ለሐዋርያ ።
ረስዩ ፡ ነፍስተክሙ ፡ መሥዋዕተ ፡ ነባቢተ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ እንዳለ ።
ወገባሪያን ፡ ለትእዛዘ ፡ እግዚእነ ፡ ዘይብል ፡ ለእመሰ ፡ ትፈቅድ ፡ ከመ ፡
ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሚጥ ፡ ሑሶ ፡ ንዋየከ ፡ ወሀብ ፡ ለምስኪናን ። (ማ
ቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩) ።
እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሠሩ ፡ ናቸው ።
ወውር ፡ መስቀሰከ ፡ ወትልወኒ ።
እንዲህ ፡ አለ ።
ዘውእቱ ፡ ተሰእከኒ ፡ ዘርእስከ ፡ አኮ ፡ በዘውጹእ ፡ እምኔከ ።
ይኸውም ፡ ከንተ ፡ አፍአ ፡ ባለ ፡ ገንዘብህ ፡ ያይደለ ፡
አንተ ፡ ራስህ ፡ አገልግለኝ ።
ወመኑት ፡ እምፍትወታቲሁ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ወእስተሐምሞቱ ።
ከማሰቡ ፡ ከማንኰርኰሩ ፡ ከማገለባበጡ ፡ ተለይ ፡ ማ
ለቱ ፡ ነው ።
ወእሱስኬ ፡ ጎሠሙ ፡ መልእክተ ፡ እግዚእ ፡ ባሕቲቶ ።
እሊህስ ፡ ጌታን ፡ ማገልገል ፡ ብቻ ፡ ወደዱ ።
በጎበ ፡ ዘኢይክልኦሙ ፡ እምኔሃ ፡ ግብራት ፡ ዓለማዊት ።
ጌታን ፡ ከማገልገል ፡ ዓለማዊ ፡ ሥራ ፡ በማይከለክላቸ
ው ፡ በገዳም ፡ ሁነው ።
ተላውያን ፡ ለጎበ ፡ ቃሉ ፡ ዘይቤ ፡ ጎበ ፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፡ ሀየ ፡ ይሄሉ ፡
ከማየ ፡ ዘይትለአክኒ ፤ ወለዙይትለአክኒ ፡ ያክብሮ ፡ አብ ።
እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ይዘው ።
አፍቀርዎክ ፡ ለባሕቲቱ ፡ እግዚእ ።
ጌታን ፡ ብቻ ፡ ወደዱ ።
ውነይጉ ፡ አፍቅሮተ ፡ ክልኡ ።
ፍቅረ ፡ ዓለምን ፡ ፍቅረ ፡ ንዋየን ፡ ተዉ ።
በእንተ ፡ ቃሉ ፡ ዘይቤ ፡ ዘያፈቅር ፡ አበ ፡ ወእመ ፡ አው ፡ ብእሲተ ፡
አው ፡ ውሉደ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ፤ ተፈልጡኩ ፡ እ
ምዘመደመ ።
እንዲህ ፡ ስላለ ፡ ከወገናቸው ።
ወእብደቲሆመ ።
ከገንዘባቸው ፡ ተለዩ ።
ወተቃወመ ፡ ፈቃዳቲሆመ ።
ፈቃደ ፡ ሥጋቸውን ፡ ተቃወሙ ።

ክመ ፡ ይፈጽሙ ፡ ሥምረቶ ።
የጌታን ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ።
በእንተ ፡ ቃሉ ፡ ዘይቤ ፡ ዘኢጸልዐ ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ ወአኀዊሁ ፡ ወአ
ኀቲሁ ፡ ወብእሲቶ ፡ ወውሉደ ፡ ወእስከኑ ፡ ነፍሱ ፡ ኢይክል ፡ ክመ ፡
ይኩን ፡ ሊተ ፡ ረድኡ ።
እንዲህ ፡ ስላለ ።
ገደፉኩ ፡ ነፍሳቲሆመ ።
ሰውነታቸውን ፡ ናቁ ።
ወተወገሙ ፡ መናስወ ፡ ሰይጣናዊተ ።
የሰይጣንን ፡ ያር ።
ወዕውባተ ፡ ፍጥረታዊተ ።
የባሕርይን ፡ ያር ፡ ታገሡ ።
በእንተ ፡ ቃሉ ፡ ዘይቤ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይትልወኒ ፡ ይጽልዓ ፡ ለነፍሱ ፡ ወ
ይውር ፡ መስቀሎ ፡ ሑሶ ፡ ዕለተ ፡ ወይትልወኒ ።
እንዲህ ፡ ስላለ ።
ወዘተ ፡ ቃሳተ ፡ ይቤ ፡ ኪያሆን ፡ እግዚእ ፡ ለእለ ፡ ጎደጉ ፡ ዓለመ ።
ጌታ ፡ ይህን ፡ የተናገረ ፡ ዓለሙን ፡ ለተዉ ።
ውነሥሥዎ ፡ ለባሕቲቱ ።
እሱን ፡ ብቻ ፡ ለሚሹ ፡ ሰዎች ፡ ነው ።
እንዘ ፡ ይትዓገሡ ፡ በእንተ ፡ መጽብብ ።
በወንጌል ፡ ያለውን ፡ መከረ ፡ ታግሠው ። አንድም ፡
ጌታ ፡ ባዑ ፡ እንተ ፡ ጸባብ ፡ አንቀጽ ፡ ስላለ ። አንድ
ም ፡ ዕዝራ ፡ ካያት ፡ መንገድ ፡ ለመዳን ።
እስክን ፡ መሞትኒ ፡ ፍሡሓኒሆመ ፡ ለቀራብ ፡ ጎበ ፡ እግዚእነ ።
ደስ ፡ ብሏቸዉ ፡ እስከ ፡ መሞት ፡ ደርሰው ። አንድ
ም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ለመቅረብ ።
ወለዓለማውያን ፡ ሎሙኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ።
ዓለማው ያንንም ፡ ጌታ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ።
ንሥኡ ፡ ለክሙ ፡ አዕርክተ ፡ እምንኖየ ፡ ዐመፃ ፡ ክመ ፡ ሶበ ፡ ኀልቀ ፡
ይትወክፉክሙ ፡ ውስተ ፡ ምጽላላቲሆሙ ፡ ዘለዓለማዊት ። (ሉቃ ፲፮ ፡
፱) ።
በማታልፍ ፡ ቤታቸው ፡ ይቀበሏችሁ ፡ ዘንድ ።
ዘውእቱ ፡ በአምጣነ ፡ ታብውዕዎሙ ፡ ለገዳፍያን ፡ ዓለም ፡ መምለክያ
ን ።
ይኸውም ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ የተዉትን ፤ መምለክያን ፤
ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ አጋንንትን ፡ የሚገዙትን ፡ ለሥላሴ ፡
የሚገዙትን ።
እስ ፡ አልቦሙ ፡ ምንትኒ ።
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሌላቸው ፡ በሕታው
ያንን ፡ ለማስታረቅ ፡ ለተራድኦ ፡ በሃይማኖት ፡ ምክ
ንያት ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ የተቀበላችኋቸው ፡ ያህል ።
ክማሁ ፡ ያበውውክሙ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።
ምክንያት ፡ ሁነው ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያገ
ቧችኋል ፡ ማለት ፡ ነው ።
በእንተ ፡ ዘገበርክምዎ ፡ ምስሌሆሙ ።
ለመመ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ሠራችሁላቸው ፡ በጎ ፡
ሥራ ።
ወበእንተ ፡ ዓለማውያንመ ፡ ነሳሕያን ፡ ወገዳፍያን ፡ መምለክያን ።
እንዳለፈው ።
ይቤ ፡ እግዚእ ፤ እንተሰ ፡ ጎ ፡ አወልድየ ፡ ሀሎክ ፡ ምስሌየ ፡ ኵሎ ፡ ጊ
ዜ ፤ ወኵሉ ፡ ዘዚአየ ፡ ዚአከ ፡ ውእቱ ፡ ወይደሉ ፡ ለነ ፡ ክመ ፡ ትትፈ
ሣሕ ። በእንተ ፡ እንኁክ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ምውተ ፡ ወሐይወ ።
ንስሓ ፡ ስለ ፡ ገቡ ፡ ስለ ፡ ዓለሚውያን ፡ ጌታ ፡ እንዲ
ህ ፡ አለ ።
ወለወልድ ፡ ዘየዐቢ ፡ አመረ ፡ ኪያሁ ፡ ለጎበ ፡ ገዳፍያን ፡ መምለክያን ።
ወልድ ፡ ዘየዐቢ ፡ ያለው ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ የተዉ ፡
ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ ፍጹማንን ፡ ያስረዳ
ል ።
እስ ፡ እመንፁ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምንዕዶሙ ፡ እስክ ፡ ተፍ
ጻሜቶመ ።
እለ ፡ ህም ፡ ከሕፃንነት ፡ ጀምረው ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡
ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ የኖሩ ፡ ናቸው ።
ወመንግሥቲኒ ፡ ስመ ።
መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ገንዘባቸው ፡ ናት ።
ወለወልድኒ ፡ ንዑስ ፡ አመረ ፡ ኪያሁ ፡ ለጎበ ፡ ተመደያዊያን ፡ ጎበ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ እምነ ፡ ዓለማውያን ።
ወልድ ፡ ዘይንዕስ ፡ ያለው ፡ ከዓለማውያን ፡ ወገን ፡ በ
ንስሓ ፡ የተመለሱ ፡ ወጣንያንን ፡ ያስረዳል ።
ሎሙኒ ፡ ክፍል ፡ ውናይ ፡ እመንግሥት ።
ከመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ አላቸው ።
በክመ ፡ ተነበየ ፡ በወንጌል ። (ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩-፳፫) ።
አምጽኡ ፡ አልባሰ ፡ ቅድዋተ ፡ ወአልብስዎ ፤ አምጽ
ኡ ፡ ሳልቀተ ፡ ወደዩ ፡ ውስተ ፡ አፃብኢሁ ፤ አምጽ
ኡ ፡ ላህመ ፡ ንጥብሑ ፡ ወንብልዖ ፡ ወንትፈሣሕ ፡ በ
ቱ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ።
ወገ ፡ ውሑድ ፡ እምነ ፡ ብዙኅ ፡ እምታሳት ፡ እግዚእነ ።
ጌታ ፡ ከተናገረው ፡ እኛ ፡ የተናገርነው ፡ ጥቂት ፡ ነ
ው ፤ አንድም ፡ ለፍጹማን ፡ ከተናገረው ፡ ለወጣንያ
ን ፡ የተናገረው ፡ ጥቂት ፡ ነው ።
ወናሁ ፡ ተበየነ ፡ በውስቴታ ፡ ትራፈ ፡ ገዳፍያን ፡ ወመምለክያን ።
በሕታውያን ፡ ከዓለማውያን ፡ እንዲበልጡ ፡ እነሆ ፡
ታመቀ ፡ ተረዳ ።

www.ethiopianorthodox.org

(ወልድ ፣ ዘይንዕስ)

ወበእንተሰ ፣ ተበይኖ ፣ ውእቱ ፣ እምሥርዓታተ ፣ ገጸት ።
ከመጸሕፍት ፣ ከያንቀጹ ፣ አምጥተሀ ፣ አስረዳን ፣ ስላ ላችሁኝ ። አንድም ፣ ታወቀ ፣ ተረዳ ፣ ብለሀ ፤ ወበእንተሰ ፤ ከሥራ ፣ በማናቸውም ፣ ሥራ ፤ ከነገር ፣ በማ ናቸውም ፣ ነገር ፣ እገሌ ፣ ከእገሌ ፣ ይበልጣል ፣ ብ ሎ ፣ የማስረዳት ፣ ነገር ፣ እንዲህ ፣ ነው ።

እስመ ፣ ዘኬዎስ ፣ መኰንን ፣ መጸብሓን
የመጸብሓን ፣ አለቃ ፣ ዘኬዎስ ።

ዘብጹሕ ፣ ውስተ ፣ ትሩፍ ።
ወደ ፣ ፍጹምነት ፣ የደረሰ ።

ወወህበ ፣ እስክ ፣ መንፈቀ ፣ ንዋየ ፣ ለምስኪናን ።
መንፈቀ ፣ ንዋይየ ፣ እሁብ ፣ ያለ ፣ ዘኬዎስ ።

ወለዘተወገሎሂ ፣ ምንተኒ ፣ ወህቦ ፣ ህየንተ ፣ አሐዱ ፣ ትርብዕተ ፣ በትፍሥሕት ፣ ወበጥብዓት ። (ሉቃ ፲፱ ፣ ፰-፣) ።
ወእመኒ ፣ በ ፣ ዘተዓገልክዎ ፣ እፈድዮ ፣ ህየንተ ፣ አሐ ዱ ፣ ትርብዕተ ፣ ያለ ፣ ዘኬዎስ ።

እስክ ፣ ቦአ ፣ እግዚእነ ፣ ውስተ ፣ ቤቱ ።
ጌታ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ እስክ ፣ መግባት ፣ ድረስ ፣ ደርሶ ።

ዘብጹሕ ።
ወደ ፣ ፍጹምነት ፣ የደረሰ ፣ ዘኬዎስ ።

ወረሰየ ፣ ሎቱ ፣ ድልወተ ፣ መድኃኒት ።
ዮም ፣ ክነ ፣ ሕይወት ፣ ለሰብአ ፣ ገዝቱ ፣ ቤት ፣ ብሎ ፣ ጌታ ፣ የተናገረለት ፣ ዘኬዎስ ።

ኢኮነ ፣ ጽድቁ ፣ ወዐስቡ ፣ ዕፍየ ፣ ምስለ ፣ ጽድቁ ፣ ወዐስቡ ፣ ለማቴዎ ስ ፣ መጽብሓዊ ።
ሥራው ፣ ከማቴዎስ ፣ ሥራ ፤ ዋጋው ፣ ከማቴዎስ ፣ ዋ ጋ ፣ የተካከለ ፣ አይደለም ።

ወኢገብረኒ ፣ ከማሁ ።
ዘኬዎስ ፣ እንደ ፣ ማቴዎስ ፣ ያለ ፣ ሥራ ፣ አልሠራም ።

ዘገብረሰ ፣ አሐዱ ፣ ግብር ፣ (አሐደኬ ፣ ግብረ) ።
ማቴዎስ ፣ የሠራውስ ፣ ሥራ ፣ አንድ ፣ ነው ፤ ያመጣ ዋል ። አንድም ፣ አንድ ፣ ሥራ ፣ የሠራ ፣ ማቴዎስ ፣ እንደ ፣ ዘኬዎስ ፣ ያለ ፣ ሥራ ፣ አልሠራም ።

በከመ ፣ ሰምዐ ፣ መጽሐፍ ፣ ወውእቱኬ ፣ እስመ ፣ ጸውዖ ፣ እግዚእ ።
እሱስ ፣ ወንጌል ፣ እንደ ፣ መሰከረ ፣ ጌታ ፣ ትልወኒ ፣ ባለው ፣ ጊዜ ።

ኀደገ ፣ እምኔሁ ፣ ኵሎ ፣ ወተለዎ ። (ማቴ፱ ፣ ፱) ።
ሁሉን ፣ ጥሎ ፣ እሱን ፣ ተከትሎ ፣ ሄደ ።

ወሐይወ ፣ ምስሌሁ ፣ ሕይወተ ፣ መጽብዓተ ።
ከሱ ፣ ጋራ ፣ መከራ ፣ እየተቀበለ ፣ ጭንቅ ፣ አናወር ፣ ኖረ ።

ወወህበ ፣ ነፍሶ ፣ በእንተ ፣ ፈቃዱ ።
የጌታን ፣ ፈቃድ ፣ ለመፈጸም ። አንድም ፣ እሱ ፣ ወ ዶ ፣ ሰውነቱን ፣ ለሞት ፣ አሳልፎ ፣ ሰጠ ።

ወከማሁ ፣ ማርታኒ ፣ ኮነት ፣ ድሙተ ፣ በእንተ ፣ መልእክተ ፣ እግዚእ ፣ ወአርዳኢሁ ።

ማርታም ፣ ጌታን ፣ ሐዋርያትን ፣ ለመርዳት ፣ ዝባጁ ፣ ነበረች ።

ወማርያምሰ ፣ ኮነት ፣ ንብርተ ፣ ወትሰምዕ ፣ ቃለ ፣ እግዚእ ።
ማርያም ፣ ግን ፣ ተቀምጣ ፣ ጉባዔ ፣ ትሰማ ፣ ነበረ ።

ወኢተገበረት ፣ ምንተኒ ፣ እምዘኢምኔሁ ።
ማርታ ፣ ትሠራው ፣ ከነበረ ፣ ከርድና ፣ ሥራ ፣ ወገን ፣ ምንም ፣ ምን ፣ አልሠራችም ።

አላ ፣ ኀደረት ፣ ግብራቲሁ ፣ ለገ ፣ ዓለም ።
የዚህን ፣ ዓለም ፣ ሥራ ፣ ትታ ።

ወመጽአት ፣ ምስለ ፣ ኵለንታሃ ፣ ለኀበ ፣ ዓለም ፣ ካልእ ፤ ዘውእቱ ፣ ክርስቶስ ።
ፈጤርሳ ፣ ወደ ፣ ሌላ ፣ ዓለም ፣ መጣች ፣ እንጂ ፤ ይኸ ውም ፣ ክርስቶስ ፣ ነው ።

ወሶበ ፣ ሰአለት ፣ ማርታ ፣ እምእግዚእነ ፣ ከመ ፣ ይበላ ፣ ለማርያም ፣ እኅታ ፣ ታርድኣ ። (ሉቃ፲፩ ፣ ፵፩) ።
ማርታ ፣ ጌታን ፣ ኢያጽዕቀከኑ ፣ እግዚአየ ፣ እንዘ ፣ ተ ኃድገኒ ፣ እኅትየ ፣ ባሕቲትየ ፣ በላኬ ፣ ታርድአኒ ፣ ብ ለችው ፣ ጊዜ ።

ይቤላ ፣ እስመ ፣ ማርያምሰ ፣ ጎርየት ፣ ላቲ ፣ መክፈልተ ፣ ሠናየ ፣ ዘኢ ይትነሥድ ፣ እምኔሃ ።
ማርያምስ ፣ ውዳሴ ፣ ከንቱ ፣ የማያስቀርባት ፣ በጎ ፣ እ ድል ፣ ትምርትን ፣ መረጠች ፣ አላት ። በትምርት ፣ ውዳሴ ፣ ከንቱ ፣ የለምና ።

በከመ ፣ ኮነት ፣ ማርታ ፣ ዘኢተአምር ፣ ሥርዓተ ፣ ማርያም ፣ እኅታ ።
ማርታ ፣ የማርያምን ፣ ሥራ ፣ አታውቀው ፣ እንደ ፣ ነበረ ፤ የልቡና ፣ ነውና ። አንድም ፣ አትሠራው ፣ እን ደ ፣ ነበረ ።

ከማሁ ፣ ዓለማውያንኒ ፣ እለ ፣ ይገብሩ ፣ ትፍፋተ ፣ ክሡታተ ፣ በሥጋቲሆሙ ፣ ወበንዋያቲሆሙ ።
በሰውነታቸው ፣ በገንዘባቸው ፣ ትፍፋት ፣ አፍአ ፣ የ ሚሠሩ ፣ ዓለማውያንም ።

ኢየአምሩ ፣ ሥርዓተ ፣ ጎቡአ ፣ ዘለዓለማውያን ፣ ዘውስተ ፣ ጎድአት ።
ባሕታውያን ፣ የሚሠሩትን ፣ ትፍፋት ፣ ነፍስ ፣ አያው ቁትም ፤ የልቡና ፣ ነውና ።

ወከመ ፣ በውስተ ፣ ፍጥረት ፣ ትኄይስ ፣ ነፍስ ፣ እምሥጋ ።
ከተፈጥሮተ ፣ ሥጋ ፣ ተፈጥሮተ ፣ ነፍስ ፣ እንዲበልጥ ፤ እንደምን ፣ ቢሉ ፤ ነፍስ ፣ የምታውቀው ፣ የምትሠራ ው ፣ በገንዘቢ ፣ ነው ፤ ሥጋ ፣ ግን ፣ በነፍስ ፣ ነውና ። አንድም ፣ ነፍስ ፣ አርአያ ፣ እግዚአብሔር ፣ አርአያ ፣ መላእክት ፣ ናት ፤ ሥጋ ፣ ግን ፣ አርአያ ፣ እንስሳ ፣ ነ ውና ።

ከማሁ ፣ ሥርዓት ፣ ክቡታዊ ፣ መንፈሳዊ ፣ ይኄይስ ፣ እምነ ፣ ሥርዓ ት ፣ ግሁድ ፣ ሥጋዊ ።
ከትፍፋት ፣ ሥጋም ፣ ትፍፋት ፣ ነፍስ ፣ ይበልጣል ።

ወበከመ ፣ ምግባረ ፣ መላእክት ፣ መንፈሳውያን ፣ ይትሌዐል ፣ እምግባ ረ ፣ እጓለ ፣ እመሕያው ።
ከሰው ፣ ሥራ ፣ የመላእክት ፣ ሥራ ፣ እንዲበልጥ ።

ወአፍቅሮ ፣ እግዚአብሔር ፣ ይኄይስ ፣ እምአፍቅሮ ፣ ፍጡራን ።
ፍጡራንን ፣ ከመውደድ ፣ እግዚአብሔርን ፣ መውዴ ድ ፣ እንዲበልጥ ።

ከማሁ ፣ ምግባረ ፣ ባሕታውያን ፣ ይትሌዐል ፣ ወይፈደፍድ ፣ እምን ፣ ምግባረ ፣ ዓለማውያን ።
ካለማውያን ፣ ሥራ ፣ የባሕታውያን ፣ ሥራ ፣ ይበልጣ ል ።

ወአፍቅሮተ ፣ ዓለማውያን ፣ ክፍልት ፣ ካዕበ ።
የዓለማውያን ፣ ፍቅራቸው ፣ ሁለት ፣ ወገን ፣ ናት ። አ ንድም ፣ የተከፈለች ፣ ናት ።

በእንተ ፣ እንስቲያሆሙ ፣ ወውስደሙ ።
ሚስት ፣ ልጅ ፣ ስላላቸው ።

ወመጥርየታቲሆሙ ።
ባሪያ ፣ ስላላቸው ፤ መጥርየ ፣ እንዲል ፣ ትግሬ ።

ወክንታቲሆሙ ።
ጥበብ ፣ ስላላቸው ።

ወዘርዐ ፣ ትፍፋቲሆሙ ፣ ሕኑት ፣ ዘክመ ፣ ቃለ ፣ እግዚእነ ፣ በምክ ፣ ዝ ፣ ዓለም ።
ትፍፋታቸውም ፣ ጌታ ፣ ንንደ ፣ ተናገረው ፣ በዚህ ፣ ዓ ለም ፣ ግብር ፣ የተያዘ ፣ ነው ።

ዘውእቱ ፣ ሐልዮቱ ።
ይኸውም ፣ ዓለሙን ፣ ማሰብ ፣ ነው ።

ወአስተሐምሞቱ ።
ማንኰርኰሩ ፣ ማገለባበጡ ፣ ነው ።

ብሑትሰ ፣ ጎደገኬ ፣ አፍቅሮታ ፣ ለሥላ ፣ ፍናዋት ።
ባሕታዊ ፣ ግን ፣ የዚህን ፣ ዓለም ፣ ፍቅር ፣ ተወ ።

ወሶቱስ ፣ አሐቲ ፣ አፍቅሮት ።
የሱስ ፣ ፍቅር ፣ አንዲት ፣ ናት ።

ዘበእንተ ፣ አፍቅሮተ ፣ አሐዱ ፣ ወውእቱኬ ፣ ክርስቶስ ፣ ፈጣሪ ።
ይኸውም ፣ አንድ ፣ ክርስቶስን ፣ መውደድ ፣ ነው ።

ወእልክቱስ ፣ ይፈርሁ ፣ እምብዙኅ ፣ ግብራት ።
ዓለማውያን ፣ ግን ፣ የልጅ ፣ የወዳጅ ፣ ፍቅር ፣ ይፈርስ ብናል ፣ ብለው ፣ በብዙ ፣ ወገን ፣ ይፈራሉ ።

ወዝሰ ፣ ይፈርሀ ፣ እምገዝቱ ፣ ዘዋሕድ ፣ ባሕቲቱ ።
ባሕታዊ ፣ ግን ፣ ያንድ ፣ የጌታ ፣ ፍቅር ፣ ብቻ ፣ ይፈርስ

www.ethiopianorthodox.org

ብኛል ፡ ብሎ ፡ ይፈራል ።

ወኢይትፈሣሕ ፡ በክልኡ ።

በዓለሙ ፡ ፍቅር ፡ ደስ ፡ አይለውም ።

ወበእንተ ፡ ተበይኖ ፡ ፍድፋዲ ፡ ባሕታውያን ፡ ዘእምትምሕርተ ፡ አበው ።

ባሕታውያን ፡ ከዓለማውያን ፡ እንዲበልጡ ፡ አበው ፡ ከስተማሩት ፡ ትምርት ፡ አምጥዶ ፡ የማስረዳት ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ብሎ ፡ ማንሻ ። አንድም ፡ የማስረዳት ፡ ነገር ።

ናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ ገንት ።

ወይኩን ፡ ውስተ ፡ ዘይክል ፡ ኅዕሉው ፤ ወይርባሕ ፡ በውስቴታ ።
ሊሠራው ፡ በሚቻለው ፤ በሚጠቀምበት ፡ ጣብር ፡ ጸንቶ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ።
ወእግዚእነሂ ፡ ሰምዐ ፡ ጸሎቶ ፡ በእንተ ፡ ክልኤቱ ፡ ግብራት ።
ጌታም ፡ ልመናውን ፡ ሰማው ። አንድም ፡ የሰማው ፡ ስለ ፡ ሁለት ፡ ነገር ፡ ነው ።
አሐዱ ፤ እምኔሆሙ ፡ ለረባሑ ።
አንዱ ፤ እሱ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ነው ።
ወነዕበኒ ፤ ከመ ፡ ይትገኝሥ ፡ ድፍረቱ ፡ ለአብድ ፡ ጽንዕ ፡ እምኀሚሠ ፡ ሚመተ ፡ ክህነት ፡
ሁለተኛም ፤ ያልተማረ ፡ ሰው ፡ ድፍረቱ ፡ ሹመት ፡ ከመሸት ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ።
ወከመ ፡ ያእምር ፡ ሥምረተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለስብእ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ውስተ ፡ ዘሰቱ ፡ ረባሕ ፡ ውስቴቱ ።
ጌታ ፡ ለሰው ፡ የሚወደው ፡ ነገር ፡ ረብሕ ፡ ጥቅም ፡ ባለበት ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ ሊኖር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፲፮ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ጸሐፈ ፡ ገነት ፡ ይቤ ፡ ብፁዓዊ ፡ አስጣቴዎስ ።
ጳላድዮስ ፤ ልዕልና ፡ ስላለው ፡ አስጣቴዎስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
ከመ ፡ አይበሰ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋው ፡ እምጸዎ ፡ ወትጋህ ፡ እስክነ ፡ ኮነት ፡ ዐሐይ ፡ ታስተርኢ ፡ እማእክለ ፡ አዕዕምተ ፡ ገበዋቲው ።
ፀሐይ ፡ በጎኑ ፡ መካከል ፡ ገብታ ፡ እስክ ፡ መቃየት ፡ ደርሳ ፤ ሰውነቱ ፡ በትሳርምት ፡ በትጋህ ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ያረቀ ፡ ተናገረ ። ሰው ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ ይደርሳልን ፡ ብለው ፡ ያጠይቃሉ ።
ይቤ ፡ መተርጕም ፡ እንሰ ፡ ርኢክዎ ፡ ለአሐዱ ፡ ቅዱስ ።
ልማድ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ አንድ ፡ ፍጹም ፡ አይቻለሁ ።
ወውእቱ ፡ ኃያል ።
ኃያል ፡ ነበረ ።
ወየሐውርኒ ።
ይሄዳልም ።
ያብስ ፡ ሥጋው ፡ እምብዝኀ ፡ ትህርምት ።
ከትህርምት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሰውነቱ ፡ ደርቆ ፡ ነበረ ።
እስክን ፡ ይትሔዘብዎ ፡ ከመ ፡ ዘአልቦ ፡ ልብ ፡ ውስተ ፡ ክርሡ ፡ ወኢ ፡ ጣፍያ ።
ያዩት ፡ ሰዎች ፡ ከሰውነቱ ፡ ውሥጥ ፡ ልብ ፤ ጣፊያ ፤ የለውም ፡ እስኪሉት ፡ ድረስ ።
ወፈድፋደሰ ፡ ታስተርኢ ፡ አዕዕምተ ፡ ገበዋቲው ፡ እምታሕተ ፡ ማዕሰ ፡ ጎፍይ ።
ይልቁንም ፡ የገሎና ፡ የገሉ ፡ አጥንት ፡ ከገላው ፡ ውስጥ ፡ ትታይ ፡ ነበረ ፤ በቅቷልና ፡ ተመስጦ ፡ አለውና ፡ ሳፉይ ፡ አለ ።
ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ መቃርዮስ ።
ይኸን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ መቃርዮስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
በከመ ፡ ያየብስ ፡ እሳት ፡ ርጥበተ ፡ ዕፅ ፡ ወያውዕዮ ።
እሳት ፡ እርጥቡን ፡ እንጨት ፡ እንዲያደርቀው ፡ እንዲያቃጥለው ።
ክግሁ ፡ ፍርሃተ ፡ እግዚአብሔርኒ ፡ እምከመ ፡ ኃደረት ፡ ውስተ ፡ ብእሲ ።
ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሰው ፡ ያደረች ፡ እንደ ሆነ ።
ታየብስ ፡ ሥጋው ፡ ወታጸመሂ ፡ አዕዕምቲው ።
ሰውነቱ ፡ ይደርቃል ፡ አጥንቱ ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ይላል ።
መተርጕምኒ ፡ ብፁዓዊ ፡ ይቤ ፡ በውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሥርዓት ፤ በእንተ ፡ ክልኤቱ ፡ አኃው ፡ በፍጥረት ፡ ባሕታውያን ፡ ዘየኃድሩ ፡ ውስተ ፡ አንጸክያ ።
መተርጕም ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ከበዓት ፡ ተከቶ ፡ መኖር ፡ እንዲገባ ፡ በተናገረበት ፡ መጽሐፍ ፤ በአንጸክያ ፡ የሚኖሩ ፡ አኃው ፡ በፍጥረት ፡ በሥጋ ፡ ወንድማማች ፡ የሚሆኑ ፡ የሁለቱን ፡ ባሕታውያን ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ መክሲሞስ ፡ ደማቴዎስ ፡ ናቸው ።
እምድኅረ ፡ ብሂሎቱ ፡ እስመ ፡ ነድኡ ፡ ቃል ፡ ይስዕን ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ ፍጹሞሙ ፡ እመንፍቱ ፡ በእንተ ፡ ትኅርምቶሙ ፡ ወድክሞሙ ።
ተንራምያን ፡ ስለሆኑ ፡ በትሩፋት ፡ ስለ ፡ ደከመ ፤ የፍጹምነታቸውን ፡ ሥራ ፡ አንደበት ፡ ሁሉ ፡ መናገር ፡ አይቻለውም ፡ ከለ ፡ በኋላ ።
ደግደገ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወተጸምዖየየ ።
ሰውነታቸው ፡ ደረቀ ፡ ጸወለገ ።

እስክ ፡ ዘርእየ ፡ ሰብእ ፡ ነቢሆሙ ፡ ይትሔዘብ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይሬኢ ፡ ምትሐተ ፡ ወአኮ ፡ ሰብእ ፡ በእግኔ ።
ያያቸው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ አይደሉም ፡ ምትሐት ፡ ነው ፡ እስኪል ፡ ድረስ ።
ጳላድዮስሂ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ እኁኑ ፡ ዘክነ ፡ የኃድር ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ።
ጳላድዮስም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ መነኩሴ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
ከመ ፡ ውእቱ ፡ ያስተርኢ ፡ ከመ ፡ ጽሳሎት ፡ በእንተ ፡ ሥርዓተ ፡ ምግባሩቲው ።
ትሳርምቲ ፤ ትሩፋቱ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ ጥላ ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ እንደነበረ ፡ ተናገረ ፤ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ማዕርግ ፡ እንደምን ፡ ይደርሳል ፡ ብለው ፡ ተጠራጥረውበት ፡ ነነበርና ።
ወይደሉ ፡ ኀእመን ፡ ዘይትበሃል ፡ በእንተ ፡ ቅዱሳን ፡ እምዜናውያን ፡ ወጽዱቃውያን ።
ዜና ፡ አበውን ፡ ከሚነግሩ ፡ ከሚያስረዱ ፡ ከነጳላድዮስ ፡ ስለ ፡ ቅዱሳን ፡ የተነገረውን ፡ ነገር ፡ አምኖ ፡ መቀበል ፡ ይገባል ።
ለእመኒ ፡ ኢየሐሊ ፡ በእግማኒነ ።
ጸሐፎቺ ፡ እነጳላድዮስ ፤ አንድም ፡ ይህ ፡ የተነገረላቸው ፡ ፍጹማኑ ፡ ምንም ፡ በዘመናችን ፡ ባይኖሩ ።
ተፈጸመ ፡ ክፍል ፡ ቀዳሚ ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ።
መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።
ወነገረ ፡ ከመ ፡ ተኃጥኣ ፡ እምቀዳሚው ፡ ፵ ፡ ተስእሎታት ።
ከመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ አርባ ፡ ጥያቄ ፡ እንደቀረ ፡ ተናገረ ። ሐተታ ፤ እነሱም ፡ መጽሐፍ ፡ ይዘው ፡ ጠይቀውታል ፡ እሱም ፡ መጽሐፍ ፡ ይዞ ፡ ተርጕሞላቸዋልና ፡ ከመጻፋቸው ፡ የሌለውን ፡ የናንት ፡ መጻፍ ፡ አርባ ፡ ጥያቄ ፡ ጐድሎታል ፡ አላቸው ፤ የነሱ ፡ መጻፍ ፡ ጐደሎ ፡ የሱ ፡ መጻፍ ፡ ሙሉ ፡ ነው ። አንድም ፡ መጽሐፍ ፡ በአርእስቱና ፡ በሳዳጉ ፡ ይጽፋልና ፡ በአርእስቱና ፡ በሳዳጉ ፡ የተጻፈውን ፡ ትተው ፡ ቢጠይቁት ፡ አርባ ፡ ጥያቄ ፡ ቀረ ፡ አላቸው ። አንድም ፡ ሊጠይቁት ፡ አስበው ፡ ዘንጊተው ፡ ቢተዉት ፤ የረሱትን ፡ ምነው ፡ ይኸ ፡ ቀረ ፡ አላቸው ። አንድም ፡ ጥያቄ ፡ እንዲያሻቸው ፡ አውቆ ፡ ሊነግራቸው ፡ ቢሻ ፤ አርባ ፡ ጥያቄ ፡ ቀረ ፡ አለ ። አንድም ፡ ጳላድዮስ ፡ ጠይቆ ፡ ሳይጽፈው ፡ የቀረ ፡ ነው ፤ የኔም ፡ የናንተም ፡ መጻፍ ፡ አርባ ፡ ጥያቄ ፡ ጐድሎታል ፡ አላቸው ። አንድም ፡ በውስጡ ፡ አረጋዊ ፡ አረጋዊ ፡ አያለ ፡ የሚያመጣው ።

ክፍል ፡ ካዕብ ።

እምክፍል ፡ ካዕብ ።
ከሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የመጣ ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፲፯ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ተርጕም ፡ ስን ፡ ቃለ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ቀሲስ ።
የቄሱን ፡ ያባ ፡ መቃርስን ፡ ነገር ፡ ተርጕምልን ።
ዘይቤ ፡ አንሰ ፡ ኢያቅረብክዎ ፡ ግሙራ ፡ ለማርቆስ ፡ ዘየዓቢ ።
ማርቆስ ፡ ዘየዓቢን ፡ እኔ ፡ አላቄረብኩትም ።
አላ ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ይሜጥዎ ፡ በእይሁ ፡ እምሥዋዕ ።
መልአኩ ፡ ካዓሕሉ ፡ ከጽዋው ፡ አንሥቶ ፡ ያቄርበው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ያለውን ፡ ተርጕምልን ፤ ምነው ፡ እሱ ፡ ባያቄርበው ፡ ሌላ ፡ አያቄርበውም ፤ እሱስ ፡ ይህን ፡ ማየቱ ፡ በዓይን ፡ ሥጋ ፡ ነውን ፡ በዓይነ ፡ ነፍስ ፤ ያስ ፡ ከዚህ ፡ መዓርግ ፡ የደረሰበት ፡ ትሩፋቱ ፡ ምን ድር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ።
ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ በቀዳሚ ፡ አዝማን ፡ በውስተ ፡ ገዳማተ ፡ ግብጽ ፡ ኮነ ፡ ዘይሰፍን ፡ ምኔተ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘይቄድስ ፡ ቅዳሴ ፡ እስክነ ፡ ጊዜ ፡ ፍልሰቱ ።
ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በግብጽ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ቀድሶ ፡ የሚያቄርበው ፡ ገዳሙን ፡ የተሾመው ፡ ብቻ ፡ ነበርና ።
በክመ ፡ ይቤ ፡ ጳላድዮስ ።
ጳላድዮስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ።
እስመ ፡ ኗቱ ፡ ቀዳውስት ፡ ኮኑ ፡ ይሠርው ፡ ምኔተ ፡ እልባርኑግ ።
እልበርኑግ ፡ በሚባል ፡ ገዳም ፡ ስምንት ፡ ቊሳውስት ፡ ተሹመው ፡ አንዳቸው ፡ ሲሞቱ ፡ አንዳቸው ፡ እየተተኩ ፡ ቀድሰው ፡ ያቆርቡ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ።
ወአምጣነ ፡ ሀሎ ፡ ቀዳሚሁ ፡ ሕያወ ፡ ኢይትከሀን ፡ አሐዱኒ ፡ እምኔሆሙ ።
ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ የፊተኛው ፡ ሳለ ፡ ቀድሶ ፡ አያቆርብም ፡ ነበር ፤ ሲሞት ፡ እየተተኩ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

www.ethiopianorthodox.org

ለባሕታውያንኒ ፡ ዘውስተ ፡ በዓታተ ፡ እንጽና ፡ ኮን ፡ አሐዱ ፡ ቀሲስ ፡ ይፈጽም ፡ ሎሙ ፡ መልእክተ ፡ ክህነት ።

እንጽና ፡ በሚባል ፡ ገዳም ፡ ያሉ ፡ ባሕታውያንንም ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ ቀድሶ ፡ ያቆርባቸው ፡ ነበር ።

ወውስተ ፡ ክልኣትኒ ፡ መክናት ፡ ኮን ፡ አሐዱ ፡ ቀሲስ ፡ ወአሐዱ ፡ ዲያቆን ፡ ይትለአኩ ፡ ዓመተ ፡ ፍጽምቶ ።

በሌሎችም ፡ ገዳማት ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ አንድ ፡ ዲያቆን ፡ ሁነው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ቀድሰው ፡ ያቆርቡ ፡ ነበር ።

ቀሲስኒ ፡ መቃርዮስ ፡ ኮን ፡ ይቄድስ ፡ ባሕቲቶ ።

በዚህ ፡ ልማድ ፡ መቃርዮስም ፡ ብቻውን ፡ ይቀድስ ፡ ነበር ።

ወኮነ ፡ ይፌኢ ፡ እደ ፡ መልእክቱ ፡ ውሻጤው ፡ ማእክሌሁ ፡ ወማእዘለ ፡ ማርቆስ ።

ውሣጤሁና ፡ ማእከሌሁ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ዓረብ ፡ መከከል ፡ ሲል ፡ ውሥጥ ፡ ይላል ። በሱና ፡ በማርቆስ ፡ መካከል ፡ የመልአኩን ፡ እጅ ፡ ያይ ፡ ነበር ። አንድም ፡ ውሣጤሁ ፤ በዓይን ፡ ነፍስ ፡ ያይ ፡ ነበር ። አንድም ፡ በሱና ፡ በማርቆስ ፡ መካከል ፡ የመልአኩን ፡ እጅ ፡ በውሥጥ ፡ ሁኖ ፡ ያይ ፡ ነበር ።

በከመ ፡ ገብረ ፡ አሐዱ ፡ እምሱራፌል ።

ከሱራፌል ፡ አንዱ ፡ እንዳደረገው ።

ሶበ ፡ ነሥአ ፡ እምዲበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ፍሕመ ፡ እሳት ፡ ወወደየ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ።

ፍሙን ፡ ከምሥዋው ፡ እንሥቶ ፡ ኢሳይያስን ፡ እንዳቆረበው ። ሐተታ ፤ መልኡኩ ፡ የቄስ ፤ ጕጠቱ ፡ የሥልጣን ፤ ፍም ፡ የሥጋው ፡ የደሙ ፤ ኢሳይያስ ፡ የምእመናን ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ወኮነ ፡ መልአክ ፡ ይገብር ፡ ከመዝ ።

መልአኩ ፡ እንዲህ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

እስመ ፡ አልቦሙ ፡ ሥልጣን ፡ ለመላእክት ፡ ክመ ፡ ይቀድሱ ፡ ቅዳሴ ፡ ወየሀብዎ ፡ ለስብእ ።

መላእክት ፡ ቀድሰው ፡ ያቆርቡ ፡ ዘንድ ፤ ሥጋዉን ፡ ደሙን ፡ ለሰው ፡ ያቀብሉ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ መሣርያ ፡ የላቸውምና ።

ወበእንተ ፡ ዕበየ ፡ ንጽሕ ፡ ለማርቆስ ።

የማርቆስም ፡ ንጽሕናው ፡ ደግ ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ወትሕትናሁ ።

ትሑት ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ክመ ፡ ይትመሰል ፡ ኪያሁ ፡ ካልኣ ፡ ሰምዖት ፡ ገድሉ

ሌላው ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ገድሉ ፡ መሰከረች ።

ክመ ፡ ኮነት ፡ ዐቱ ፡ አርዓዕቱ ፡ ትሩፋት ።

አራት ፡ ትሩፋት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ።

እንተ ፡ በጽሐ ፡ ኀቤሃ ።

እሱ ፡ የሠራት ።

ወአልቦ ፡ ዘበጽሐ ፡ ኀቤሃ ፡ ካልዑ ፡ በእንተ ፡ ተጋድሎቱ ።

በትሩፋት ፡ ምንም ፡ ቢጋደል ፡ ሌላው ፡ ያልሠራት ። አንድም ፡ በትሩፋት ፡ ስለ ፡ ተጋደለ ፡ እሱ ፡ የሠራት ።

ወእመ·ንቱኒ ፡ ንጽሑ ፡ ዘውስተ ፡ ነፍሱ ፡ ወሥጋሁ ።

[illegible] ፡ ናቸው ። ንጽሑ ፡ ሥጋና ፡

ወትሕትናሁ ፡ ዐቢይ ።

ሁለተኛው ፡ ፍጹም ፡ ትሕትና ፡ ነው ።

ወክልኤቱ ፡ ሀብት ፡ እምእግዚአብሔር ።

ሁለቱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚሰጡ ፡ ሀብታት ፡ ናቸው ።

ወእመ·ንቱኒ ፡ አጽንዖ ፡ ብሲት ፡ ወሐዲስ ፡ በውስተ ፡ ልቡ ።

ይኸውም ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ በልቡና ፡ አጽንቶ ፡ መያዝ ፡ ነው ።

ወአእምሮ ፡ ትርጓሜሆሙ ።

ትርጓሜያቸውን ፡ ማወቅ ፡ ነው ።

ዘበአማናዊ ።

እንደባለቤቱ ፡ ሁኖ ።

ወነሢኦቱ ፡ ቍርባን ፡ እምእደ ፡ መልአክ ።

**አራተኛው ፡ ከመልአኩ ፡ እጅ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ መቀበል ፡ ነው ፤ ይኸማ ፡ መሣርያ ፡ ጸጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መኾ ፡ መሣርያ ፡ ትሩፋት ፡ ነዋ ፡ ብሎ ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ አንድ ፤ ንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ሁለት ፤ ትሕትና ፡ ሶስት ፤ ወክልኤቱ ፡ ሲል ፡ ካልዑኒ ፡ ብለሀ ፡ አቅና ፤ አራተኛው ፡ ብሉይ ፡ ሐዲስ ፡ ማጽናት ፡ ነው ። ዓላውያን ፡ ነገሥታት ፡ መኳንንት ፡ ተነሥተው ፡ መጻሕፍትን ፡ ሁሉ ፡ ያቃጠልዋቸው ፡ እንደሆነ ፡ አብነት ፡ ይታጣል ፡ ብሎ ፡ በቃል ፡ አዋንቶ ፡ ይዘ ፡ ብሉይ ፡ ሐዲስ ፡ አጽፍዋልና ፤ ነሢኦቱሰ ፤ ከመልአኩ ፡ እጅ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ መቀበሉ ፡ ሳን ፤ በእንተ ፡ ዕበየ ፡ ንጽሑ ፡ ብለሀ ፡ ሳጠም ፤ ንጽሕናው ፡ ደግ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

ወገሠጸቱ ፡ ማርቆስ ፡ ዮናናዊ ፡ ግብጻዊ ።

ይኸውም ፡ ማርቆስ ፡ ዘዮናኒ ፡ ግብጻዊ ፡ ነው ፤ ዮናኒ ፡ ሀገሩ ፤ ግብጽ ፡ የመነኰሰበት ።

ወአልቦ ፡ ዘከነ ፡ በውስተ ፡ ዝኩ ፡ ግብጽ ፡ ዘማእምር ፡ እምኔሁ ።

በግብጽ ፡ ሁሉ ፡ ከሱ ፡ ይልቅ ፡ እንደርሱ ፡ አዋቂ ፡ የሆነ ፡ የሌለ ።

ወእምኵሎሙ ፡ ባሕታውያን ፡ በአእምሮ ፡ ወሥርዓት ።

ከባሕታውያን ፡ ሁሉ ፡ በውቀት ፡ በሥራ ፤ አንድም ፡ አናቦ ፡ ሥርዓት ፡ በማወቅ ፡ እንደሱ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የሌለ ፡ ማርቆስ ፡ ነው ፤ አልነበረም ፡ ብትልም ፡ ይሆናል ።

ወውእቱ ፡ ዘገብረ ፡ መጽሐፈ ፡ በእንተ ፡ ተሠዋዎ ፡ በበይን ፡ ዘይቤሉ ፡ ክመ ፡ መልክ ፡ ጴጥቅ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ።

**ይኸውም ፡ መልክ ፡ ጴጥቅ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ላሉት ፡ ምላሽ ፡ መጻፍ ፡ የጻፈ ፡ ነው ፤ ዘአልቦቱ ፡ አብ ፡ ወእም ፡ ያለውን ፡ ይዘው ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ብለዋል ። እሱን ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፤ የነገደ ፡ ክም ፡ ትውልዳቸው ፡ ነገዳቸው ፡ በአሪት ፡ ባይጸፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እናት ፡ አባት ፡ አሉት ። ሐሰል ፡ ሳሴምን ፤ ሳሴም ፡ ሜልኪን ፤ ሜልኪ ፡ ደሳሞ ፡ ሜልኪንና ፡ መልክ ፡ ጴጥቅን ፡ ይወልዳል ፤ እናታቸው ፡ ሰለ·ማ ፡ ትባላለች ። አባታቸው ፡ ጣዖት ፡ ያመልክ ፡ ነበርና ፡ መልክ ፡ ጴጥቅን ፡ ጠርቶ ፡ ከበጎቹ ፡ መርጠህ ፡ ለጣዖት ፡ የምን ሰዋው ፡ በግ ፡ አምጣልኝ ፡ አለው ፤ አባቱ ፡ ይኸ ፡ ጣዖት ፡ ምን ፡ ይረባናል ፡ አለው ፤ እምቢ ፡ ብለህ ፡ እንደሆነ ፡ አንተን ፡ እሰዋሀለሁ ፡ ብሎ ፡ ያዘው ። እናቱ ፡ ትወደው ፡ ነበርና ፡ ባይሆን ፡ በዕፃ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ልጄን ፡ አትሠዋብኝ ፡ አለችው ፤ ዕፃ ፡ ቢጥል ፡ በታላቁ ፡ ወጣበት ፡ ሊሠዋው ፡ ይዞት ፡ ሄደ ። እናቱ ፡ አይታ ፡ ወንድምህን ፡ ሲወስድብህ ፡ ገዝ ፡ ትላለህን ፡ አለችው ፤ ወደ ፡ ጌታ ፡ ቢያመለክት ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ ወርዶ ፡ አባቱንም ፡ ወንድሙንም ፡ በልቷቸው ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ቀረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጥቷል ፡ ብሎ ፡ ነሳርዋቸዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ወኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ማርቆስ ፡ ዖርያዊ ፡ ዘከነ ፡ ይሰመይ ፡ ቀዲሙ ፡ ማልክስ ፡ ወፈጸመ ፡ ሕይወቶ ፡ በውስተ ፡ ዖርያ ።

ተራኪ ፡ ይኸም ፡ አይደል ፤ ይኸም ፡ አይደል ፡ ማለት ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቀድሞ ፡ ማልክስ ፡ ይባል ፡ የነበረው ፤ ዘመኑን ፡ በሶርያ ፡ የፈጸመው ፡ ማርቆስ ፡ ሶርያዊ ፡ አይደለም ።

ወኢሂ ፡ ውእቱ ፡ ማርቆስ ፡ ዘይንዕስ ፡ ረድኡ ፡ ለስልዋኖስ ።

የስልዋኖስ ፡ ረድእ ፡ የነበረው ፡ ማርቆስ ፡ ዘይንዕስም ፡ አይደለም ።

ተስእሎ ፡ ፲፰ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ጸሐፈ ፡ ገነት ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ቀሲስ ፡ ዘደብረ ፡ ናጥሮን ።

ናጥሮን ፡ ያገር ፡ ስም ። አንድም ፡ አምቦ ፡ ነው ፤ የቄሱን ፡ ያባ ፡ ቆሮስዮስን ፡ ነገር ፡ ጸላኤዮስ ፡ እንዲህ ፡ ለ ።

ሶበ ፡ ወረደ ፡ ኀበ ፡ ምኔት ፡ ዘእምአዕዋደ ፡ አለእስክንድርያ ፡ ረከበ ፡ ሙ ፡ ለአኃው ፡ ጉቡኣን ፤ በእርብዓው ፡ ለአሐዱ ፤ ወበሣልሱ ፡ ለካልኡ ።

**ከአስክንድርያ ፡ ባጠገብ ፡ ወዳሉ ፡ ገዳማት ፡ ቢወርድ ፡ ለአውላጋ ፡ አርባ ፡ ለገልጉስ ፡ ሣልስት ፡ ሁኖ ፡ አኃውን ፡ ተሰብስበው ፡ ሲፈቱ ፡ አገኛቸው ፡ አለ ፤ ይህ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ አሉት ። ይህ ፡ አውላጋ ፡ ዓለማዊ ፡ ረድኡ ፡ ነበረ ፤ ለተልእኮ ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፡ ዝልጉስን ፡ ካደባባይ ፡ ወድቆ ፡ አገኘው ። አትሑሮ ፡ አትሑሮ ፡ ያየው ፡ ጀመር ፤ አትሑረኝ ፡ አትሑረኝ ፡ አየኸኝ ፡ አለ ፤ ደዌህ ፡ እንጂ ፡ ቢያጽረኝ ፡ አለው ። የኔ ፡ ደዌ ፡ ይደንቅሃልን ፤ ላህያዬ ፡ ሣር ፡ ስንኳ ፡ የሚጥልለት ፡ የለም ፡ አለው ። የሚረዳኝ ፡ የለም ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ከሌላውማ ፡ ይኸን ፡ ብረዳ ፡ ይልቅ ፡ ይጠቅመኝ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ ከቤቱ ፡ ወስዶ ፡ ይረዳው ፡ ጀመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድውይ ፈ ብጽብጸኛ ፡ ነው ፡ ና ፡ ይበጻበጻል ፤ ግብሩን ፡ የማይችለው ፡ ሆነ ። ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ ከተግባሩ ፡ ውሎ ፡ ሲገባ ፤ አንተ ፡ ሰው ፡ ጥቂት ፡ ይዘኸ ፡ ትወጣለኸ ፤ ብዙ ፡ ይዘኸ ፡ ትገባለኸ ፤ በዚህ ፡ በደዌዬ ፡ እንዳልጠቀምበት ፡ ታደርገኝ ፡ መሰለኝ ፡ አለው ። ቢጸናበት ፡ ይህ ፡ ቆሮስዮስ ፡ የነፍስ ፡ አብቱ ፡ ነውና ፡ ሂዶ ፡ ነገረው ። በነፍስ ፡ ይጠቅመኛል ፡ እረዳዋለሁ ፡ ብዬ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አምጥቼ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ሳን ፡ ግብሩን ፡ የማልችለው ፡ ሆነ ፤ እንዴት ፡ ላድርግ ፡ ትለኛለኸ ፡ አለው ። ክርስቶስን ፡ ከቤትኸ ፡ አግብተኸ ፡ ስታበቃ ፡ አውጥተኸ ፡ ትጥላለኸን ፡ አይሆንም ፤ ታሳሠኸ ፡ እርዳው ፡ አለው ። የሱ ፡ ነገር ፡ ባይረዳው ፡ እስኪ ፡ ደግሞ ፡ ከዓረጋዊ ፡ አባ ፡ እንጦንስ ፡ ዘንድ ፡ ምክር ፡ ቢያክፍለኝ ፡ ልሂድ ፡ ብሎ ፡ ሄደ ። እንጦንዮስም ፡ ከሩቅ ፡ ሲ

www.ethiopianorthodox.org

መጣ ፡ አይቶ ፡ የመጣበቱ ፡ ነገር ፡ ተገልጸለት ፡ አውላጋ ፡ አውላጋ ፡ ብሎ ፤ ኢትትፋለጡ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ቀርበ ፡ ፍጥነትክሙ ፤ ጊዜ ፡ ሞታችሁ ፡ ቀርቧልና ፡ አትለያዩ ፡ አለው ። ተመልሶ ፡ ዓረጋዊ ፡ እንጠንስም ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ለቆሮስዮስ ፡ ነገረው ፤ ባይረዳኝ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ ነግሬኝ ፡ አልነበረምን ፡ በል ፡ ሂድ ፡ እኔም ፡ እጠይቃችኋለኹ ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድካሙን ፡ ለማሳወቅ ፡ አስቀድሞ ፡ አር�ፋል ። እሱ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ሲሆነው ፡ ዝልጉስ ፡ ደግሞ፡ አር�ፋል ። ይህ ፡ ቆሮስዮስም ፡ ልጠይቃቸው ፡ ብሎ ፡ ቢሄድ ፡ ለአውላጋ ፡ ዓርባ ፤ ለዝልጉስ ፡ ሣልስት ፡ ሁኑዋቸው ፡ ሲፈቱ ፡ ደርሷልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ እስመ ፡ ቅዱስ ፡ እንመንኖስ ፡ ይቤ ፡ ለአውላጋ ፡ ወለቢጹ ፡ ዝልጉስ ፡ ኢትትፋለጡ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ቀርበ ፡ ፍጥነትክሙ ። እንጠንየ፦ስም ፡ አውላጋንና ፡ ባልንጀራውን ፡ ዝልጉስን ፡ ጊዜ ፡ ሞታችሁ ፡ ቀርቧልና ፡ አትለያዩ ፡ አላቸው ።

ወዖበ ፡ በጽሐ ፡ ቅዱስ ፡ ኀበ ፡ መካናሙ ፡ ረክቦሙ ፡ ጉቡኣን ፡ በአርብዓው ፡ ለአውላጋ ፡ ወበሣልሱ ፡ ለዝልጉስ ።

ቆሮስዮስም ፡ ሊጠይቃቸው ፡ ቢሄድ ፤ ለአውላጋ ፡ አርባ ፤ ለዝልጉስ ፡ ሣልስት ፡ ሁኖት ፡ አኃው ፡ ተሰብስበው ፡ አገኛቸው ።

ተስእሎ ፡ ፲፱ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ውስተ ፡ ገድሉ ፡ ለአባ ፡ ሙሴ ፡ ጸሊም ፡ ጽሑፍ ።

በአባ ፡ ሙሴ ፡ ገድል ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ተጽፍዋል ።

ከመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ በካልእት ፡ አመዋዕል ፡ እንዘ ፡ ያንዕሱ ፡ ምስለ ፡ አብያጺሁ ፡ ፈያት ፡ ውስተ ፡ ዘይትበርዖ ፡ እምእክያት ። በጽሐቆ ፡ ሕሊና ፡ ወናይት ።

ከዕለታት ፡ በንዱ ፡ ሌቦች ፤ ወንበዶች ፡ ከሚሆኑ ፡ በልንጀሮቹ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ ወደሚሠሩት ፡ ወደ ፡ ስርቆት ፤ ወደ ፡ ቅሚያ ፡ ሲሄዱ ፡ በጎ ፡ ሕሊና ፡ እንደ ፡ ታሰበችው ፡ ተነግሯል ።

ወበእንቲኪ ፡ ክህለት ፡ ሕሊናሁ ፡ ታድኅኖ ፡ እምልግፍት ፡ እኩያት ፡ ወእምአብያጺሁ ፡ ወእምሰይጣናት ።

ሕሊናው ፡ ከክፉ ሥራ ፡ ታድነው ፡ ዘንድ ፤ ከባልንጀሮቹም ፤ ከሰይጣናትም ፡ ተለየው ፡ ዘንድ ፡ እንደምን ፡ ተቻላት ።

ወለእመ ፡ ኮን ፡ እምጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፤ አው ፡ እምኔሁ ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነትም ፡ ቢሆን ፤ እሱ ፡ አስቦም ፡ ቢሆን ።

ወለምንትኒ ፡ ዘኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ እምቅድም ፡ ወባሕቱ ፡ ኮነ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ።

በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ተደረገ ፡ እንጂ ፡ አስቀድሞ ፡ ያልተደረገ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ አሉት ። ታሪክ ፤ የዚህ ፡ የሙሴ ፡ ጸሊም ፡ ጌቶቹ ፡ ዐሐይ ፡ ፍኬረቃ ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ፤ እነዚያ ፡ መ·ተው ፡ ለልጆቹ ፡ ይገዛል ፤ ልጆቹም ፡ ዐሐይ ፡ ፍኬረቃ ፡ ያመልካሉ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ጋራ ፡ ሊሠርቁ ፡ ሊቀሙ ፡ በረኃ ፡ ለበረኃ ፡ ሰጊዱ ፡ ዋዕየ ፡ ዐሐይ ፡ ጸናባቸው ፡ ከጥላ ፡ አርፈው ፡ ሳለ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ዐሐይን ፡ ስትባክን ፡ አይቶ ፡ አሁን ፡ ይች ፡ ዐሐይ ፡ ምን ፡ አምላክ ፡ ናት ፤ አምላክስ ፡ የኔ ፡ ጌቶች ፡ ናቸው ፡ በል ተው ፡ ጠጥተው ፡ ከጥላ ፡ አርፈው ፡ የሚውሉ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ አሻግረው ፡ አይተው ፡ አምላክ ፡ አምላክ ፡ ትላለህ ፡ አምላክማ ፡ ከፈለገህ ፡ ያባ ፡ ኤስድሮስ ፡ ገዳም ፡ ያውልህ ፡ አትሂድምን ፡ አሉት ፤ ወዳያው ፡ ተነሥቶ ፡ ሂደ ፤ ከገዳሙ ፡ ቢደርስ ፡ ግብሩን ፡ ያውቃሉና ፡ ማኅበሩ ፡ ተሸበሩ ፤ አበ ፡ ምኔቱ ፡ አባ ፡ ኤስድሮስ ፡ ነው ፤ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርታ ፡ አምጥታዋለችና ፡ ይልቅ ፡ ተቀበሉት ፡ አሳቸው ፤ ተብለው ፡ አገቡት ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ልጇ ፡ ምን ፡ አመጣህ ፡ አለው ፤ ትመክረኝ ፡ ብዬ ፡ አለ ። መከረው ፡ አስተማረው ፤ አመነ ፡ ተጠመቀ ፤ ደግ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ አመንኩሰታል ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፡ ሶሱ ፡ ፍድፋዲ ፡ ብእሲ ፡ ዘይትበራ ፡ በረድኡት ፡ እግዚአብሔር ፡ ትትፈጸም ።

ሰው ፡ የሚሠራት ፡ ትሩፋት ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ትፈጸማለች ።

ከመ ፡ ታሰ ፡ እግዚእነ ፡ ወዘእንበለዮሰ ፡ አልቦ ፡ ዘትክሱ ፡ ትግበሩ ፡ እምግባራተ ፡ ሠናይ ።

እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ እንደተናገረ ።

ወትስሕብ ፡ ጸጋ ፡ ስብእ ፡ ኀበ ፡ ፍድፋዲ ፡ በእንተ ፡ ሠላስ ፡ ግብራት ።

ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ትሩፋት ፡ ትስበዋለች ፡ አንድም ፡ የምትስበው ፡ ስለ ፡ ሶስት ፡ ነገር ፡ ነው ።

በእንተ ፡ ሕሊና ።

አንዱ ፡ እሱ ፡ አስቦ ፡ ነው ።

ወበእንተ ፡ ትምህርት ።

ሁለተኛው ፡ ተምሮ ፡ ነው ።

ወበእንተ ፡ አንብቦ ።

ሶስተኛውም ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልክቶ ፡ ነው ።

ወምግባራት ፡ ኄራት ፡ ትትፈጸም ፡ እንክ ፡ እምጸጋ ።

በጎ ፡ ሥራም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ የተነሣ ።

ወጎርየተ ፡ ፈቃደ ፡ ብእሲ ።

ከሰውም ፡ ከበጎ ፡ ፈቃድ ፡ የተነሣ ፡ ይፈጸማል ።

ወእምቅድመ ፡ ትጽንኀ ፡ ሕሊናሁ ፡ ለብእሲ ፡ ለኀፍሩ ፡ ወለእክይ ።

ሕሊናው ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ለክፉ ፡ ነገር ፡ ሳይጸን ፤ እንድም ፡ ኀበ ፡ ኀሩት ፤ ሕሊናው ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ሳትሳብ ።

ኢትረድኦ ።

ጸጋ ፡ ሰውን ፡ አትረዳም ።

ወኀበ ፡ እክይ ።

ወደ ፡ ክፉ ፡ ነገርም ፡ ሳይሳብ ።

ኢትርሕቅ ፡ እምኔሁ ።

ጸጋ ፡ ሰውን ፡ አትለየውም ።

ወአብ ፡ አብርሃምኒ ፡ ዖበ ፡ መንኖት ፡ ሕሊናሁ ፡ ክህደ ፡ አበዊሁ ።

አብርሃምም ፡ ያባቱን ፡ ጣዖት ፡ ሕሊናው ፡ በናቀችለት ፡ ጊዜ ።

ወፈተወት ፡ ነፍሱ ፡ አእምሮ ፡ ጽድቅ ።

ልቡናው ፡ እውነተኛን ፡ ሃይማኖት ፡ ማወቅ ፡ ወደ ደች ፤ በወደደች ፡ ጊዜ ።

ወበጊዜሃ ፡ አብርሀት ፡ ጸጋ ፡ ሕሊናሁ ። (ዘፍ ፲፪ ፡ ፩-፫) ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ጸጋ ፡ ሕሊናውን ፡ ብሩህ ፡ አደረገችለት ፤ ዕውቀት ፡ ገለጸችለት ።

ወክማሁ ፡ አባ ፡ ሙሴኒ ፡ ዖበ ፡ ጸንት ፡ ሕሊናሁ ።

አባ ፡ ሙሴም ፡ እንደሱ ፡ ሕሊናው ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ብትሳብ ።

ዖቤሃ ፡ አርድአቶ ፡ ጸጋ ።

ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አገኛችው ፤ አዋቂ ፡ አደረገችው ።

ተስእሎ ፡ ፳ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ፡ ይሠርዑን ፡ በሎሱ ፡ ጊዜ ፡ ውስተ ፡ ገቢረ ፡ ፍድፋዲ ፡ ወተጸብየ ፡ ሕማማት ፡ ወዕይጠ ፡ ናት ።

አበው ፡ ቅዱሳን ፡ ሁለጊዜ ፡ ትሩፋት ፡ ሥሩ ፡ ኃጣውእን ፡ አጋንንትን ፡ ሁለጊዜ ፡ ተዋጉ ፡ ብለው ፡ ያዙናል ።

ወቀሲስ ፡ አባ ፡ ኤስድሮስ ፡ ለአባ ፡ ሙሴ ፡ ይቤሎ ፡ ኢትዕግመቅ ፡ ላዕለ ፡ ለዕይጠናት ።

አባ ፡ ኤስድሮስ ፡ ግን ፡ ለሙሴ ፡ ጸሊም ፤ ሰይጣናትን ፡ ደረት ፡ ለደረት ፡ እጋፋቸዋለሁ ፡ አትበል ።

እስመ ፡ ምግባራት ፡ ወሥርዓት ፡ በዓቅም ።

ሥራ ፡ በዕጦጠን ፡ ነውና ፡ አለው ። ይህ ፡ ሙሴ ፡ ጸሊም ፡ ኃይለኛ ፡ ወንበዴ ፡ ነበር ፤ ኃይሉም ፡ አንበሳ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ እንዳያመልጠው ፡ በእጁ ፡ ይዘ ፡ የሚገል ፡ ነው ፤ ውሀም ፡ የመላበት ፡ እንደሆነ ፡ ደረት ፡ ለደረት ፡ ተጋፍቶ ፡ ዋኝቶ ፡ የሚሻገር ፡ ነው ፤ በጣ ፡ እንደ ፡ ሽንኩርት ፡ ልጦ ፡ የሚበላ ፡ ነው ። ፊቀን ፡ ጠጅ ፡ አንስቶ ፡ ይዘ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠጣ ፡ ነው ፤ ሰውም ፡ ገድሎ ፡ በጦር ፡ አንሥቶ ፡ ለአዕዋፍ ፡ ለአንስርት ፡ የሚያበላ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደዚያ ፡ መስሎት ፡ አጋንንትን ፡ በሥራዬ ፡ በጉልበቴ ፡ ድል ፡ እነግለው ፡ ብሎ ፡ በብዙ ፡ ትሩፋት ፡ ይጋደል ፡ ጀመር ፤ አጋንንትም ፡ ይህን ፡ ዓውቀው ፡ ያር ፡ አጽንተውበታል ፤ ለአባ ፡ ኤስድሮስ ፡ እንዴት ፡ ላድርግ ፡ ያር ፡ ጸናብኝ ፡ ብሎ ፡ ቢነግረው ፡ ከሰንነት ፡ ላይ ፡ ይዘ ፡ ወጥቶ ፡ መላእክትን ፡ በምሥራቅ ፡ አጋንንትን ፡ በምዕራብ ፡ ተሰልፈው ፡ የሚዋጉ ፡ አስመስሎ ፡ አሳይቶታል ፤ ምንድር ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ያልከ ፡ እንደሆነ ፡ እሊህ ፡ ይረዱሃል ፤ በኃይሉ ፡ በጉልበቱ ፡ ያልክ ፡ እንደሆነ ፡ እሊያ ፡ ይዋጉሃል ፡ አለው ። በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡ ድል ፡ ነሥቷቸዋል ፤ አኃው ፡ ጣን ፡ ተጣይ ፡ ቃል ፡ መስሏቸው ፡ ይህን ፡ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ እስመ ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ ኮነ ፡ በውጥኑ ፡ የሐዝብ ፡ ክመ ፡ ውእቱ ፡ እምብዝኃ ፡ ምግባሩቲሁ ፡ ወድካማቲሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይትኄየል ፡ ላዕለ ፡ ሰይጣናት ።

አባ ፡ ሙሴ ፡ በወጣኒነቱ ፡ በብዙ ፡ ትሩፋት ፤ በሱ ፡ ድካም ፡ ብቻ ፡ አጋንንትን ፡ ድል ፡ እነግለው ፡ ይመስለው ፡ ነበር ።

ወዖበ ፡ አእመሩ ፡ እምኔሁ ፡ ዘንተ ።

እነሱም ፡ ይህን ፡ ትዕቢቱን ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ።

አልሐሙ ፡ በእንተ ፡ ተጽብያቱ ።

ያር ፡ አጸኑበት ። አልቦ ፡ ዘበቍጣ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአል

www.ethiopianorthodox.org

ሐማ ። አርዌ ፡ ምድር ፡ ይልሕም ፡ እከየ ፡ እንዲል ። ክ፡ት ።

አንበሳ ፤ ዘንዶ ፡ መስለው ። ወገሃደ ።

ሕሡም ፡ ገጻቸውን ፡ ጽሉም ፡ ራእያቸውን ፡ ገልጸው ፡ እየመጡ ።

ወፈቀደ ፡ አባ ፡ ኤስድሮስ ፡ ክመ ፡ ያወይቆ ፡ ትሕትና ።

አባ ፡ ኤስድሮስም ፡ ትሕትናን ፡ ሊያስረዳው ፡ በወደ ፡ ጊዜ ።

ወያአምሮ ፡ ክመ ፡ ፃማ ፡ ባሕቲታ ፡ ኢትረድኦ ፡ ለብእሲ ፡ ዘእንበለ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንተ ፡ ትወረይ ፡ በጥምቀት ፡ ወተመዋም ፡ ሞኖባን ፡ ቅዱስ ።

በጥምቀት ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በመቀበል ፡ የምትገኝ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ ናት ፡ እንጂ ፤ የራሱ ፡ ድካም ፡ ብቻ ፡ ለሰው ፡ እንዳትረባው ፡ ሊያሰው ቀው ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፤ ኢትትዐማመቅ ፡ አለው ።

ክመ ፡ ለዘይውይ ፡ ውእቱ ፡ በሥጋው ፡ ይኤዝዞ ፡ እንከ ፡ ጠቢብ ፡ ዕት የ ፡ ፈውስ ።

በሥጋ ፡ የታመመ ፡ ሰውን ፡ ባለ ፡ መድኃኒት ፡ መድኃኒት ፡ ጠጣ ፡ ብሎ ፡ እንዲያዘው ።

ወይኤዝዞ ፡ ክመ ፡ ይትከላዕ ፡ እምኀሊም ።

አትተኛ ።

ወሰትየት ።

ያልሆነ ፡ አትጠጣ ።

ወሰሲት ።

ያልሆነ ፡ እትመገብ ።

ወትቀጥዕት ።

አትቆጣ ፡ ብሎ ፡ እንዲነግረው ።

ወሶሎ ፡ ግብረ ፡ ዘበትየተ ፡ ፈውስ ።

መድኃኒት ፡ የመጠጣት ፡ ግብር ፡ ሁሉ ፡ እንዲያስተምረው ።

ወኢይጠረይ ፡ እንከ ፡ ተፈውሶ ፡ እምዝቲ ፡ ምግባር ፡ ወባሕቱ ፡ በፈውስ ፡ ይጠረይ ።

መድኃኒቱን ፡ ቢያደርገው ፡ ይድናል ፡ እንጂ ፤ በመነገሩ ፡ ብቻ ፡ ድኅነት ፡ እንዳይገኝ ።

ከማሁ ፡ ዘይክውንኒ ፡ ድውየ ፡ በመንፈሱ ፡ ኢይትፈወስ ፡ በሥርዓቱ ፡ ለመንፈሱ ።

በነፍሱ ፡ ድውይ ፡ የሆነ ፡ ሰውም ፡ እሱ ፡ በሠራው ፡ በትሩፋቱ ፡ ብቻ ፡ ድኅነት ፡ አያገኝም ።

በምግባሩ ፡ ዘእምጸም ፡ ወጸሶት ።

ከጸም ፡ ከጸሎት ፡ ወገን ፡ በሠረው ፡ ሥ

ወአርምሞ ፡ ወትጋህ ፡ አው ፡ እምቅኔ ።

ከተባሕትዎና ፡ ከርድና ፡ ወገን ፡ በሠራው ፡ ሥራ ።

አው ፡ ምጽዋት ፡ ወትሕትና ።

ከምጽዋትና ፡ ከትሕትና ፡ ወገን ፡ በሠራው ፡ በትሩፋት ፡ ብቻ ፡ ድኅነት ፡ አያገኝም ።

ወባሕቱ ፡ በጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመውዖ ፡ ለሰይጣን ፤ ወይትፈወስ ።

በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ድኅነት ፡ ያገኛል ፡ እንጂ ።

ዘሰ ፡ ይጸባዕ ፡ ምስለ ፡ ሰይጣናት ።

ከሰይጣናት ፡ ጋራ ፡ የሚዋጋ ፡ ሰውስ ።

ያፍቅር ፡ እንክ ፡ ክመ ፡ ይግበር ፡ ትእዛዘተ ፡ እግዚእነ ።

ወሰሎ ፡ ዘአዘገከክሙ ፡ ገቢረክሙ ፡ በሉ ፡ አግብርት ፡ ጽሩዓን ፡ ንሕነ ። ወዘእንበሌየሰ ፡ ኢትክሉ ፡ ገቢረ ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ ያዘዘውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይውደድ ። (ሉቃ፲፯ ፡ ፲ ። ዮሐ፲፫ ፡ ፲፭) ።

ወኢይርኢየ ፡ ኀበ ፡ ጽያሕ ፡ ዘገቢሮቱ ፡ ባሕቲቱ ።

በሥራዬ ፡ ብቻ ፡ እጠቀማለሁ ፤ ድል ፡ እነግለሁ ፡ አይበል ።

ባሕቱ ፡ ኀበ ፡ ኃይል ፡ ዘበእግኁ ፡ እምጸጋ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ።

ከጌታ ፡ በሚሰጥ ፡ ኃይል ፡ ይበል ፡ እንጂ ።

« ቅኔ ፤ ቦኑ ፡ ፍልጠት ፡ ማእከለ ፡ ፈላሲ ፡ ወ መንጎግው » ። ቅኔ ፡ ማለት ፡ የተስእሎና ፡ የተሠጥዎ ፡ ማቅኛ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የተዛባውን ፡ ንባብና ፡ ምሥጢር ፡ ለማቅናት ፡ መምህራን ፡ ከመጾሐፈ ፡ ገነት ፡ እየመጡ ፡ እንደ ፡ ጥቅስ ፡ በቃል ፡ ይነገሩታል ። ሲጻፍም ፡ የአኀውና ፡ የፊልክስዩስ ፡ ቃል ፡ የሚረጋዊው ፡ የአድልፍዩስ ፡ ባህል ፡ ስላልሆነ ፡ እንደ ፡ ምልክት ፡ በጻር ፡ ቤገጽ ፡ ይጣፋል ፡ እንጂ ፡ ከሙሥጥ ፡ ገብቶ ፡ ከንባብ ፡ ጋራ ፡ ተዘንቆ ፡ አይጣፍም » ።

(፩) ይቤ ፡ አረጋዊ ፡ ክዕበ ፡ ፍልጠት ፡ ማእከለ ፡ ፈላሲ ፡ ወመንጎግው ።

ሚረጋዊን ፡ ሙተርጉም ፡ ቢሉ ፡ ክዕበ ፡ ለጸላድዮስ ። ሚረጋዊን ፡ አድልፍዩስ ፡ ቢሉ ፡ ክዕበ ፡ ለመተርጉም ። በፈላሲና ፡ በመንጎግው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አለ ፡ ልዩ ፡ ናቸው ።

አበመ ፡ ፈላሲ ፡ የዐውሮ ፡ ውስተ ፡ ምኔታት ፡ ክመ ፡ ይርባሕ ፡ ወያር ብሕ ፡ ግብራት ፡ መንፈሳዊት ።

ፈላሲ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ ተቀብለው ፡ ራሱን ፡ አ

ስቀብሎ ፡ ሌላውን ፡ ይጠቅም ፡ ዘንድ ፡ ካንዱ ፡ ገዳም ፡ ወደንዱ ፡ ገዳም ፡ የሚል ፡ ነው ።

መንጎግውስኒ ፡ ይርባሕ ፡ ግብራተ ፡ ሥጋዊተ ።

መንጎግው ፡ ግን ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ከወይዛዝር ፡ ከመኳንንት ፡ የሚዞር ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፸፩ ።

ይቤሉ ፡ አኀው ፡ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ አበው ፡ ባሕታውያን ፡ ይሰፍሑ ፡ እያዊሆሙ ፡ በውስተ ፡ ጸሎት ።

ባሕታውያን ፡ አበው ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ እኝቸውን ፡ ይዘረጋሉ ፤ ትች ።

ወያሴልልዎ ፡ መንገለ ፡ ሰማይ ።

ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይሰቅሉታል ፤ ስለምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ በእንተ ፡ ቃሰ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንሰ ፡ እፈቅድ ፡ ክመ ፡ ይጸልዩ ፡ ዕደው ፡ በነሶሱ ፡ መካን ፡ እንሚአመሙ ፡ እደዊሆሙ ፡ በንጹሕ ። (፩ጢሞ፪ ፡ ፰) ።

ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተናገረ ፡ ነው ፡ አለ ። ዘእንበለ ፡ ነገርጓር ፡ ወዕከይ ፡ ያለውን ፤ ዘእንበለ ፡ መዓት ፡ ወሕሊና ፡ ዕኩይ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ።

ተስእሎ ፡ ፸፪ ።

ይቤሉ ፡ አኀው ፡ በእንተዝ ፡ ይቤ ፡ መተርጉም ፡ እስመ ፡ እንሥኦ ፡ እደው ፡ ውእቱ ፡ አልዕሎ ፡ ሕሊና ፡ ኀበ ፡ ሰማይ ፡ ኀበ ፡ እግዚእ ፡ በአፍቅሮ ፡ ወንጽሕ ።

ይህንማ ፡ መተርጉም ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ጳውሎስ ፡ እንሥኦ ፡ እደው ፡ ያለው ፡ በፍቅር ፡ በንጽሕና ፡ ሁኖ ፡ ሕሊናን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መስቀል ፡ ነው ፡ ብሎት ፡ የለምን ፡ አሉት ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፡ ኢይትበሀል ፡ ዝንቱ ፡ ለብዙኃንኒ ፤ ወይትበሀል ፡ ባሕቱ ፡ ለባሕታውያን ፡ ፍጹማን ።

ሰቂለ ፡ ሕሊና ፡ ለፍጹማን ፡ ይነገራል ፡ እንጂ ፤ ለወጣንያን ፡ አይነገርም ። አንድም ፤ ኢይትከሀል ፤ ሰቂለ ፡ ሕሊና ፡ ለፍጹማን ፡ ይቻላል ፡ እንጂ ፤ ለወጣንያን ፡ አይቻልም ።

ወእሳ ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘያሴዕሰ ፡ አላ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ወእደዊሆሙኒ ።

የሚሰቅሉትም ፡ ሕሊናቸውን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ዓይናቸውንም ፤ እኝቸውንም ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ለመብዝኀነቶሙሰ ፡ ይሰፀናሙ ፡ አልዕሎ ፡ ሕሊናት ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይትክህሶሙ ፡ አልዕሎ ፡ አዕዳውሰ ፡ ወአዕይንት ፡ ኀበ ፡ ሰማይ ።

ለወጣንያን ፡ ግን ፤ ሕሊናቸውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መስቀል ፡ አይቻላቸውም ። ወደ ፡ ሰማይ ፡ እኝቸውን ፡ መዘርጋት ፤ ዓይናቸውን ፡ መስቀል ፡ ይቻላቸዋል ፡ እንጂ ።

ወሶሶሙ ፡ ይትመሰልዎሙኬ ፡ ለንቢያት ።

ሁሉም ፡ ነቢያትን ፡ መሰሏቸው ፤ ይመስሏቸዋል ።

ወለክርስቶስ ፡ ለሙ ፡ ስብሐት ።

ክርስቶስን ፡ መሰሉት ።

ወለሐዋርያትሂ ፡ ወለትጹሳኒሆ ።

ሐዋርያትንም ፤ ቅዱሳንንም ፡ መሰሏቸው ፤ ይመስሏቸዋል ። አርእስት ፡ ነው ፤ ያመጣዋል ።

አስመ ፡ ይብል ፡ ዳዊት ፡ ሰፋሕኩ ፡ እደውየ ፡ ኀቤከ ፤ ወይኩን ፡ አን ሥኦ ፡ እደውየ ፡ ክመ ፡ መሥዋዕተ ፡ ሠርክ ። (መዝ፻፵) ።

ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ፤ ሰፈሐ ፡ እደው ፡ ላለው ።

ወይብል ፤ ኀቤክ ፡ እግዚኦ ፡ አንቃዕደያን ፡ አዕይንተን ። (መዝ፻፳፪) ።

ሰቂለ ፡ አዕይንት ፡ ላለው ።

ወክመዝ ፡ ጎበረ ፡ ሙሴኒ ፡ ነቢይ ፡ ውስተ ፡ ወብወ ፡ አማሌቃውያን ።

ሙሴም ፡ አማሌቃውያንን ፡ ወግተኽ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ኢያሱን ፡ በሰያይደው ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አደረገ አለ ። አሮንና ፡ ሆር ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ደግፈውት ፡ እጁን ፡ ሰቅሎ ፡ ውሏል ። ሙሴ ፡ እጁን ፡ ሲያነሣ ፡ አማሌቃውያን ፡ ድል ፡ ይሆናሉ ። እሱ ፡ እጁን ፡ ሲያወርድ ፡ እሥራኤል ፡ ድል ፡ ይሆናሉ ። ኋላ ፡ የማይሆንላቸው ፡ ቢሆን ፤ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ደንጊያ ፡ ተክለዉለት ፡ እጁን ፡ እንደ ፡ ሰቀለ ፡ ውሎ ፡ አጥፍቷቸው ፡ መጥቷልና ፤ እንዲህ ፡ አለ ። (ዘፀ፲፯ ፡ ፰—፲፮) ።

ክርስቶስኒ ፡ ጊዜ ፡ አልዐለ ፡ እደዊሁ ።

ክርስቶስም ፡ እጁን ፡ የዘረጋበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

ወጊዜ ፡ አንቃዕደወ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ወሕሊናቲሁ ። (ዮሐ፲ ፡ ፮) ።

ዓይኑን ፡ ሕሊናውን ፡ የሰቀለበት ፡ ጊዜ ፡ አለና ፤ ክርስቶስ ፡ ላለው ።

ወጸወሎስኒ ፡ ይቤ ፤ ጎሠ ፡ ዘላዕሉ ፡ መካነ ፡ መንበሩ ፡ ለክርስቶስ ። (ቈላ፫ ፡ ፩) ።

ጳውሎስም ፡ ላሡ ፡ ብሏልና ፤ ሐዋርያት ፡ ላለው ።

ላሡ ፡ አለ ፡ እንጂ ፤ ሠራውን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፤ ሐዋርያት ፡ ያልሠሩትን ፡ ሥሩ ፡ ብለው ፡ አያስተምሩምና ።

አበውኒ ፡ ያሴዕሉ ፡ አደዊሆሙ ፡ ወአዕይንቲሆሙ ፡ ኀበ ፡ ሰማይ ፡ አር ድኦ ፡ ለአንሥኦ ፡ ሕሊናቲሆሙ ፡ ለንበ ፡ እግዚአብሔር ።

አበውም ፡ ሕሊናቸውን ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ለመስቀል ፡

www.ethiopianorthodox.org

አጋዥ ፡ ሊሆናቸው ፡ ዓይናቸውን ፤ እጃቸውን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይሰቅሉ ፡ ነበርና ፤ ቅዱሳን ፡ ላለው ።

እስመ ፡ ናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ክመ ፡ አባ ፡ ሲዶያ ፡ ተብያሳዊ ፡ ኮነ ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ ጸሎት ።

ከአበው ፡ አንዱ ፡ ሲዶያ ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ይቆም ፡ እንደ ፡ ነበረ ።

ወይሰፍሕ ፡ እደዊሁ ።

እጁን ፡ ይዘረጋ ፡ እንደ ፡ ነበረ ።

ወይትመሰጥ ፡ ልቡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነዋኅ ፡ ጊዜ ።

ልቡናው ፡ በተመሥጠ ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ሂዶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይቆይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ተነግሯል ።

ወእምኀበ ፡ [illegible]

እስከ ፡ ይገብኦ ፡ ልቡ ።

ከሰውም ፡ አንዱ ፡ ቢመጣ ፡ ግን ፡ ልቡ ፡ እስኪመለስ ለት ፡ ድረስ ፡ እጁን ፡ ያወርድ ፡ ነበር ።

ወዛቲሰኩ ፡ ግብር ፡ መድኀኒት ፡ ጥቅ ።

ሰፈሐ ፡ አእዳው ፤ ሰቂለ ፡ አዕይንት ፤ ወጣንያንን ፡ አጋንንትን ፤ ሰቂለ ፡ ሕሊና ፡ ፍጹማን ፤ አጋንንትን ፡ ፈጽማ ፡ የምታደክም ፡ ናት ።

ተስእሎ ፡ ፸፫ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ እምገዳማውያን ፡ ይቤ ፡ አቡነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለእጉ ። (ተስፋ፯) ።

እምኔሆሙና ፡ እምገዳማውያን ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ከገዳማውያን ፡ አንዱ ፡ መቃርዮስን ።

ይቤ ፡ ለእመ ፡ ኮንክ ፡ ዘኢትክል ፡ ክመ ፡ ትኩን ፡ ፈላሴ ፡ ክማን ፤ ንበር ፡ ውስተ ፡ በዓትክ ።

እንደኛ ፡ ፈላሲ ፡ መሆን ፡ ባይቻልህ ፡ በበዓት ፡ ተከተህ ፤ ትሩፋት ፡ ሠርተህ ፡ ኑር ።

ወብኪ ፡ በእንተ ፡ ኃጢኦትክ ።

ኃጢአትህን ፡ አስበህ ፡ አልቅስ ።

ወትክውን ፡ እንክ ፡ ክማን ።

እንደኛ ፡ ትሆናለህ ፡ ያለው ፡ ስለምን ፡ ነው ፡ አሉት ። (ታሪክ) ፤ አባ ፡ መቃርስ ፡ አበውን ፡ ዙረህ ፡ ጠይቅ ፡ የሚል ፡ ሕሊና ፡ ታሰበው ። ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ ይሆንን ፡ ወይስ ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ኖረ ። ኋላ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ አውቆ ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ። ገዳማውያን ፡ ያላቸው ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ከሎንያ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ተወጻጽተው ፡ ሂደው ፡ በባሕር ፡ ቁመው ፡ ይኖራሉ ። በረኃ ፡ ለበረኃ ፡ ሲዘር ፡ ከባሕር ፡ ቁመው ፡ አያቸው ። ቢፈራ ፡ ከሩቅ ፡ ሁኖ ፡ ይመለከታቸው ፡ ጀመር ። ሰው ፡ እንደ ፡ ሆንሀ ፡ ና ፡ አሉት ፤ ቀረበ ። ከዚህ ፡ እንደምን ፡ ትኖራላችሁ ፡ አላቸው ፡ እንደምታየን ፡ አሉት ። አሰንብቶ ፡ አለን ፡ አላቸው ፡ ዕረፍት ማለት ፡ ነው ፡ የለም ፡ አሉት ። ምን ፡ ትመገባላችሁ ፡ አላቸው ፡ ከባሕሩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ያለ ፡ አለ ፡ ይህን ፡ እንመገባለን ፤ ሰውነታችን ፡ ብትወድ ፡ ትቀበለዋለች ፤ ባትወድ ፡ ትተወዋለች ፡ አሉት ። ስንት ፡ ዘመን ፡ ሆናችሁ ፡ አላቸው ፤ አርባ ፡ ዘመናችን ፡ ነው ፡ አሉት ። እነሱም ፡ ዓለሙሳ ፡ እንደ ፡ ወትሮ ፡ አለን ፡ ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ይወጣል ፡ ይወርዳልን ። ክረምትና ፡ በጋ ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ፡ ይፈራረቃልን ፡ አሉት ፤ አዎን ፡ አላቸው ። ንጉሥም ፡ ይነግሣል ፤ ጳጳስም ፡ ይሾማል ፡ አሉት ፤ አዎን ፡ አላቸው ፤ ያደንቁ ፡ ጀመር ።

እኔን ፡ እስቲ ፡ ምክሩኝ ፡ አላቸው ፡ እንደኛ ፡ ሁነህ ፡ ኑር ፡ አሉት ፤ እንደናንተ ፡ ሁኖ ፡ መኖርስ ፡ አይቻለኝም ፡ አላቸው ። እንኪያስ ፡ በበዓትህ ፡ ሁነህ ፡ ኃጢአትኅን ፡ እያሰብህ ፡ አልቅስ ፡ እንደኛ ፡ ትሆናለህ ፡ አሉት ። ከዚያ ፡ ኑሮ ፡ ሲመለስ ፡ አርድእቶቹ ፡ ጠፍታቸው ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፡ ሊቀበሉት ፡ መጥተው ፡ አባታችን ፡ መጣህልን ፡ እንዳንተ ፡ አንጂ ፡ ያለ ፡ መነኮሴ ፡ የለም ፡ ይሀን ፡ ያህል ፡ ቀን ፡ በረኃ ፡ ለበረኃ ፡ አሉት ። እሱም ፡ ሂዶ ፡ ያያቸውን ፡ መነኮሰማ ፡ ምን ፡ እኔ ፡ እሊያ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ። ደራሲ ፡ መቃርዮስኒ ፡ እንዘ ፡ መነኰስ ፤ መነኮሰ ፡ ኢኮነ ፡ መቃርስ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፡ እስመ ፡ ዘርኅቀ ፡ እምኀለም ።

ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የራቀ ።

ወመተረ ፡ እምኔሁ ፡ ፍትወተ ፡ ሕማማት ፡ በውስተ ፡ ብሕትውና ።

በተባሕትዎ ፡ ሁኖ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ፍቅረ ፡ ኃጢአትን ፡ ከሱ ፡ የለየ ።

ወአሰረ ፡ ሕሊናሁ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕሊናውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ።

ውእቱኒ ፡ ክመ ፡ ፈላስያን ።

እንደ ፡ ፈላስያን ፡ ይሆናል ።

« ቅኔ ፤ ይቤሎ ፡ እኁ ፡ ለአረጋዊ ፡ እስመ ፡ እፈቅድ ፡ አሥምሮቶ ፡ ለአምላኪየ ፡ በተባሕትዎ ፤ ወበሕዝቡ ፡ እፈርሀ ፡ ሰሚዕየ ፡ ጽንዐ ፡ ጸብአ ፡ ተቃትሎቶሙ ፡ ለሰይጣናት ። ወይቤሎ ፡ አረጋዊ ፡ ኢትዜክር ኑ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ። ወይቤሎ ፡ እሮ ፡ ውእቱ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር » ።

(፱) ይቤ ፡ አረጋዊ ፡ እስመ ፡ መልአክ ፡ ዘበመትሕ ፡ ሠጠጠ ፡ ክርሦ ፡ ለፈላሲ ።

ምትሐት ፡ መስሎ ፡ የመጣ ፡ መልአክ ። አንድም ፡ ዘበመትሕ ፡ ሠጠጠ ፡ ከርሦ ፡ ለፈላሲ ። ሳይሰማው ፡ የጠሞቱዎስን ፡ አካሉን ፡ ሠንጥቆ ።

ወአርአየ ፡ ሕማመ ፡ ልቡ ።

የነፍሱንም ፡ ቢሉ ፡ የሥጋውንም ፡ ቢሉ ፡ ያሩን ፡ እንደ ፡ እንገዝገ ፡ ያለ ፡ አውጥቶ ፡ አሳየው ።

ወአግብኦ ፡ በክመ ፡ ሀሎ ።

መልሶ ፡ ቀድሞ ፡ እንደነበር ፡ አደረገው ።

ወክግሀሁ ፡ ሠጠቱ ፡ መላእክት ፡ እስክቶ ፡ ለማር ፡ ኤልያስኒ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ መነኮሳይያት ፡ ዖበ ፡ ኮነ ፡ ምስሌሁ ፡ በሀየ ፡ ፍትወት ።

የመነኰሳይያት ፡ አባት ፡ የነበረ ፡ የማር ፡ ኤልያስንም ፡ አባለ ፡ ዘሩን ፡ ሰንጥቀው ፡ መላእክት ፡ እንደ ፡ አለቅት ፡ ያለ ፡ አውጥተው ፡ ጣሉለት ። ከማሁ ፡ አለ ፤ የሥጋውን ፡ ቢሉ ፡ የተመቸ ፡ አያሳትትም ፤ የነፍሱን ፡ ቢሉ ፡ መሳሪያው ፡ አንድ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ ከማሁ ፡ አለ ። የማር ፡ ኤልያስ ፡ ታውቋል ፤ የጠሞቱዎስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ከከተማው ፡ አጠገብ ፡ ገዳም ፡ አቅንቶ ፡ በዓት ፡ አበጅቶ ፡ ይኖራል ፤ ልብስ ፡ ምግብ ፡ እየሰጠ ፡ የሚረዳው ፡ ዓለማዊ ፡ ወዳጅ ፡ ነበረው ፤ እሳት ፡ አለችው ፡ ዘማ ፡ ናትና ፡ ምነው ፡ ተዪ ፡ አትላትምን ፡ አለው ፡ አንተ ፡ ተመክራት ፡ እንደሆነ ፡ እንጂ ፡ እኔንስ ፡ በጅም ፡ አትለኝ ፡ አለው ፤ ይዘኻት ፡ ና ፡ አለው ፡ ይገዛዋት ፡ ሄደ ። ምነው ፡ ይኸን ፡ ነገር ፡ አትተይምን ፡ እንዲህ ፡ እንደሆኑ ፡ መቅረት ፡ የለ ፡ አላት ። አባቴ ፡ ሳብሩን ፡ ወድጇው ፡ መስሎሃልን ፡ የማ ድርበት ፡ እንጂ ፡ ባጣ ፡ ነው ፡ አለችው ፤ ይህስ ፡ እውነኒ ፡ ነው ፡ አንተም ፡ ዕርዳት ፡ እኔም ፡ ሰሌን ፡ ሰርቼ ፡ ዕረዳታለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲረዳት ፡ ኖረ ። ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ ቀን ፡ ያ ፡ ሰው ፡ መንገድ ፡ ሊሄድ ፡ ተነሥቶ ፡ እኔ ፡ እስክመለስ ፡ ምግብህን ፡ ብታመጣልህስ ፡ አለው ፤ አይሆንም ፡ አለ ፤ እንኪያ ፡ ትሞት ፡ የለም ፡ ባይሆን ፡ እያመጣች ፡ በአፍአ ፡ እያኖረችልህ ፡ ትሂድ ፡ እንጂ ፡ አለው ፡ ይሁና ፡ አለው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እያመጣች ፡ በአፍአ ፡ እያኖረችለት ፡ ስትሄድ ፡ ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ ድክሙ ፡ ከልቀረልኝ ፡ ገብቼ ፡ በረከት ፡ ተቀብዬ ፡ ብሄድ ፡ ምኔው ፡ አለችው ፡ ግቢያ ፡ አላት ፤ ገባች ፡ ተላመዳ ፡ መንፈቅ ፡ አብረው ፡ ኖሩ ፤ ኋላ ፡ የቀድሞ ፡ ክብሩን ፡ የኋላ ፡ ኃሣሩን ፡ አስቦ ፡ ሂዶ ፡ ከበረኃ ፡ ወድቆ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተጋደለ ። ያ ፡ ገሙት ፡ ሁኖ ፡ የተዋጋው ፡ ሰይጣን ፡ እንደ ፡ እንገዝገ ፡ ሁኖ ፡ ድቂ ፡ አሳደረበት ፤ መልአኩ ፡ አካሉን ፡ ሰንጥቆ ፡ አውጥቶ ፡ አሳይቶታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ አረጋዊ ፡ ወሶሉ ፡ ሰብእ ፡ በአምጣነ ፡ ኃይለ ፡ ተጋድሎቱ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዳቅሙ ፡ እንደገሉበቱ ፡ እንደ ፡ መጋደሉ ፡ እንደ ፡ ትሩፋቱ ።

ወሥርዓቱ ፡ ወትዕግሥቱ ።

እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ትዕግሥቱ ፡ መጠን ።

ይክውን ፡ አምጣነ ፡ ተጋድሎቱ ፡ ሰይጣናት ፡ ሎቱ ።

ሰይጣናት ፡ ይዋጉታል ።

እስመ ፡ አባ ፡ ጽላ ፡ ዖበ ፡ ሰእሎ ፡ እሑዱ ፡ ክመ ፡ ይንበር ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ።

አባ ፡ ጽላን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በገዳም ፡ አብሬህ ፡ ልኑር ፡ ባለው ፡ ጊዜ

ይቤሎ ፡ ኢትክል ፡ ትትዓገሥ ፡ ለመክራተ ፡ ሰይጣናት ።

ያጋንንትን ፡ ያር ፡ መታገሥ ፡ አይቻልህም ፡ አለው ።

ወዖበ ፡ አገበሮ ።

ግድ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ።

ነሥኦ ፡ ምስሌሁ ።

ይዘት ፡ ሄደ ።

ወኃደረ ፡ ውስተ ፡ በዓት ፡ ኀበ ፡ ገቦሁ ።

ባጠገቡ ፡ በዓት ፡ አበጅቶ ፡ ኖረ ።

ወመጽአዎ ፡ ሰይጣናት ፡ በሌሊት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰይጣናት ፡ በሌሊት ፡ መጥተው ።

ወበቀዳሚሁ ፡ አርኩሱ ፡ ሕሊናቲሁ ።

በመጀመሪያው ፡ ሕሊናውን ፡ ለመጡት ።

ወበደኃሪኒ ፡ ፈቀዱ ፡ ክመ ፡ ያፍርህዎ ።

በሁለተኛው ፡ አስፈራሩት ።

ወመጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ አባ ፡ ጽላ ።

ድምጽ ፡ አሰምቶት ፡ አባ ፡ ጽላ ፡ መጣ

ወረሰየ ፡ ዓውደ ፡ በኣቱ ፡ ማዕተበ ፡ መስቀል ፡ ዓውደ ።

አውደና ፡ አውዶ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከበዓቱ ፡ አጠገ

www.ethiopianorthodox.org

ብ ፡ አማተበለት ፤ አንድም ፡ ከበዓቱ ፡ አጠገብ ፡ በ ዙሪያው ፡ መስቀል ፡ ተከለለት ፡ አንድም ፡ ዓዊዶ ። ከበዓቱ ፡ አጠገብ ፡ አዙሮ ፡ መስቀል ፡ ተከለለት ።

ወሶቤሃ ፡ ክህለ ፡ ክመ ፡ ይጎድር ፡ ውስቴታ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብፅውን ፡ ማደር ፡ ተጀለው ።

ወበክመ ፡ ኢተበውሀ ፡ ሶሎሙ ፡ ሐዋርያት ፡ ክመ ፡ ያውዕኦ ፡ ስይጣ ናተ ፡ ሶሎ ።

ሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡ ጋኔን ፡ ማውጣት ፡ እንዳልተጀላ ቸው ።

ክማው ፡ ወኢሶሎሙ ፡ ባሕታውያን ፡ ዘይክሉ ፡ ይጽንው ፡ ለተጻብያ ፡ ሰ ይጣናት ፡ ኃያላን ፡ ወእኩያን ።

ባሕታውያንም ፡ ሁሉ ፡ እኩያን ፡ ኃያላን ፡ አጋንንት ን ፡ ጸንቶ ፡ መዋጋት ፡ የሚቻላቸው ፡ አይደለም ።

ወዘይክልሰ ፡ ጎዕለ ፡ ውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ትሑተ ።

ጸንቶ ፡ መዋጋት ፡ የሚቻለው ፡ ፈጽሞ ፡ ትሑት ፡ የ ሆነ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ተስእሎ ፡ ፶፬ ።

ይቤሉ ፡ እኃው ፡ ወበእንተ ፡ ምንትኑ ፡ ክልኤቱ ፡ እኃው ፡ እለ ፡ ኃይ ሩ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ መቃራ ፡ ውስተ ፡ አስቄጥስ ፡ ሠለስተ ፡ ዓመታተ ፡ ዘኢ ሖሩ ፡ ኀቤሁ ።

ከአባ ፡ መቃራ ፡ ገዳም ፡ የነበሩ ፡ ሁለቱ ፡ እኃው ፡ በአስቄጥስ ፡ ሶስት ፡ ዓመት ፡ ሲኖሩ ፡ አንዳቸው ፡ ስንኳ ፡ ወደሱ ፡ ያልሄዱ ።

ወኢክልኡኒ ።

ታላቁ ፡ ባይሄድ ፡ ታናሹ ፡ ለትምርት ፡ ያልሄደ ፡ ስለ ምን ፡ ነው ፡ አባትን ፡ መጠየቅ ፡ አይገበምን ።

ዘውእቶሙ ፡ ይቄጥ ፡ ንጉሥ ።

እሊሁም ፡ የንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። አንድም ፡ የንጉ ሥ ፡ ልጆች ፡ ነኑ ፡ ብለው ፡ ነውን ። (ታሪክ) ። መክሲሞስ ፡ ዱማቴዎስ ፡ ይባላሉ ፡ አባታቸው ፡ የሮም ፡ ንጉሥ ፡ ነ ው ፡ ልጎንድዮስ ፡ ይባላል ። በሕፃንነት ፡ ክትምርት ፡ ቤት ፡ ሰደዳቸው ፡ ብሉይ ፡ ሐዲስ ፡ አውቀዋል ፡ ሥ ርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጥንተዋል ። ሲመለሱ ፡ ሕግ ፡ ግቡ ፡ አላቸው ፡ አባታችን ፡ የተማሩትን ፡ እ ንጂ ፡ ካልተመለከቱ ፡ ይጠፋል ፡ እንዳይገሠፈን ፡ እን መልክት ፡ አሉት ፡ ተመልከቱ ፡ ብሏቸው ፡ ሲመለከ ቱ ፡ ሰነበቱ ። ሰንብቶ ፡ ደኅሞ ፡ ሕግ ፡ ግቡ ፡ አላቸ ው ፡ ግድስ ፡ ካልኸን ፡ አንተም ፡ ባልከው ፡ እኛም ፡ ባልነው ፡ አይሆንም ፡ አሉት ። ኒቅያ ፡ ሠለስቱ ፡ ም ዕት ፡ በአርዮስ ፡ ሥላው ፡ ሁኖ ፡ የነበረ ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ የነሡበት ፡ ነውና ፡ ከዚያ ፡ ሂደን ፡ እናመልክ ት ፡ ፍቀድልን ፡ አሉት ፤ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ሰደዳቸው ። ኒቂያ ፡ ሂደው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱን ፡ አመንዝሰን ፡ ቢሉ ት ፡ የንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ያለፈቃድ ፡ አመነዝሰለሁን ፡ አ ይሆንም ፡ አሳቸው ። አንጸኪያ ፡ ከአባ ፡ አጋቦስ ፡ ሂ ዱ ፡ እሱ ፡ አመነኰሳቸው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በቂ ፤ ም ባባቸውም ፡ ተድባበ ፡ ሐመር ፡ እየሠሩ ፡ ነበር ፤ ስ ማቸውን ፡ ከዚያው ፡ ላይ ፡ ይጽፉታል ። ኑጋድያን ፡ በባሕር ፡ ሲሄዱ ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ የተነሣባቸው ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ አምላክ ፡ መክሲሞስ ፡ ሲሉት ፡ ጸ ጥ ፡ ይላል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያባታቸው ፡ አሽከር ፡ በ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሲሄድ ፡ ስማቸውን ፡ ኀዚያ ፡ ተጽሮ ፡ አየው ፤ ነገድያን ፡ ደግሞ ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ ቢነሣ ባቸው ፡ ስለ ፡ አምላክ ፡ በክሲሞስ ፡ ጸጥ ፡ በልልን ፡ ብለው ፡ ጸጥ ፡ ሲያደርጉት ፡ አየ ። እሊህ ፡ ሰዎች ፡ ወዴት ፡ ይኖራሉ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፡ አንጸኪያ ፡ ከአባ ፡ አጋቦስ ፡ ዘንድ ፡ አሉልህ ፡ አሉት ። አባታቸ ው ፡ ጠፍተውት ፡ ሲያዝን ፡ ነበርና ፡ ሂዶ ፡ ነገረው ፡ እናታቸውን ፡ እኔ ፡ እንዳልሄድ ፡ ብመንላሥት ፡ ያለ ው ፡ ነኝ ፡ አይመቸኝምና ፡ ሂደሽ ፡ ጠይቂያቸው ፡ ብ ሎ ፡ ሰደዳት ። ሂዳ ፡ ኑ ፡ ልገናኛችሁ ፡ መጥቻለሁ ፡ ብላ ፡ ላከችባቸው ፡ እኛስ ፡ ከብርሃን ፡ ወደ ፡ ጨለ ማ ፡ ከሰፊ ፡ ወደ ፡ ጸባብ ፡ መውጣት ፡ አይቻለንም ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ አልዋት ። እያለቀሰች ፡ ተመልሳ ፡ ሂዳለች ፡ አባ ፡ አጋቦስም ፡ እኔ ፡ ከሞትኩ ፡ በኋላ ፡ ከ ዚህ ፡ ቦታ ፡ አትገኙ ፡ ብሏቸው ፡ አረፈ ። ከዚህ ፡ በ ኋላ ፡ አባታቸው ፡ ያለበት ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ሞ ተ ፡ ክህናት ፡ ተሰብስበው ፡ ሂደው ፡ ፍቀድልን ፡ ክ ልጆችህ ፡ መርጠን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ እንሹም ፡ አሉት ። እኔ ፡ በማፊ ፡ ያተኰሉ ፡ ብዙ ፡ ነበር ፡ ክልሆነ ፡ ባያቸ ው ፡ እጠላለሁን ፡ አምጡና ፡ ሹመዋቸው ፡ አላቸው ። እናመጣለን ፡ ብለው ፡ ሲሄዱ ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔ ር ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ ልቀቁ ፡ ብሎ ፡ አሥጎሳቸው ፡ ወጥ ተው ፡ መንገድ ፡ ጀመሩ ፡ ባገድል ፡ ተቀጥቅጠው ፡ ኑረዋልና ፡ መሄድ ፡ የማይቻላቸው ፡ ሆነ ፤ ዝቅጥቅ ጥ ፡ ቢሉ ፡ ይመና ፡ ጠቅሳ ፡ ወስዳ ፡ አስቄጥስ ፡ አደረ ሰቻቸው ። ክአባ ፡ መቃርስ ፡ የደረሱለት ፡ አንድ ቀን ፡ ተገናኝተው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሳይገናኙ ፡ ኑረው ፡ በ ኛ ፡ ዓመት ፡ በጥር ፡ አርፈዋልና ፡ ይህን ፡ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፡ እስመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘየዓቢ ።

ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ታላቁ ፡ አለመሄዱ ።

ኦኅ ፡ ልቡበ ፡ ፍጹመ ፡ ወየዋሐ ።

ደግ ፡ ሰው ፡ ፍጹም ፡ አዋቂ ፡ ነበርና ።

ወሶበ ፡ ሖረ ፡ ኀቤሁ ፡ እምተክሥተ ፡ ፍጽምናሁ ፡ ወእምተሰብሐ ።

ወደዚያ ፡ ብሄድ ፡ ፍጹምነቱ ፡ ይገለጽና ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ይሆንብኛል ፡ ብሎ ፡ ፈርቶ ፡ ነው ።

ወዘይኅዕስኒ ፡ ኦኅ ፡ ዘይትሜህር ፡ እምን ፡ ዘየዓቢ ።

ታናሹም ፡ ለትምርት ፡ አለመሄዱ ፡ ከታላቅ ፡ ወንድ ሙ ፡ ይማር ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። አንድም ፡ ው ዳሴ ፡ ከንቱ ፡ እንዲገዳ ፡ ታላቅ ፡ ወንድሙ ፡ ያስተም ረው ፡ ነበርና ፤ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ፈርቶ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፶፭ ።

ይቤሉ ፡ እኃው ፡ እስመ ፡ ገድሉ ፡ ለአባ ፡ ይስሪን ፡ ትሰምዕ ፡ ክመ ፡ ውእቱ ፡ ኦኅ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወኢሮቢር ፡ የኃድር ።

የአባ ፡ ይስሪን ፡ ገድል ፡ በዱር ፡ በተራራ ፡ ይኖር ፡ እ ንደነበረ ፡ ትናገራለች ።

ወበጽሐ ፡ ውእቱ ፡ በካልእ ፡ እመዋዕል ፡ ኀበ ፡ ምኔት ።

ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ መጣ ።

ወተቀመጠ ፡ ኀበ ፡ ደዲዮ ።

ከአደባባይ ፡ ተቀመጠ ።

ወበክየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ።

እንዲህ ፡ እያለ ፡ አለቀሰ ።

እስመ ፡ ረክቡኒ ፡ ፈያት ፡ በውስተ ፡ ባሕር ።

ወንበዶች ፡ በባሕር ፡ አገኙኝ ።

ወተንሥኡ ፡ ላዕሌየ ፡ ዓውሎታት ።

ነፋሳት ፡ ተነሡብኝ ።

ወመዋግድ ፡ ተሰዐሉ ፡ ላዕሌየ ።

ማዕበላቱ ፡ ሰለጠኑብኝ ።

ወተፈለጥኩ ፡ እንክ ፡ እምጥፊተ ፡ ቤትየ ፤ ወኀጣእኩ ፡ እምአበ ውየ ፡ ብለህ ፡ አቅና ። ከናት ፡ ካባቶቼ ፡ ተለየሁ ፤ ገ ንዘቤንም ፡ አጣሁ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ ። ገንዘቡ ፡ ከባሕ ር ፡ የሰጠመበት ፡ ነጋዴ ፡ መስሎ ፡ ነው ። ያወቁት ፡ በንድ ፡ ተቀምጠው ፡ ያለቅሳሉ ፤ ያላወቁት ፡ በጠፋ ፡ ይተክህ ፡ እያሉት ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፡ አመረ ፡ ባሕረ ፡ ለኀበ ፡ ሥርዓተ ፡ ብሕትውና ።

ባሕር ፡ ያለው ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ወኀውሎታተ ፡ ለኀበ ፡ መከራ ፡ ነው ።

ዓውሎ ፡ ያለው ፡ መከራ ፡ ነው ።

ወማዕበላተ ፡ ለኀበ ፡ ሕማማት ።

ማዕበል ፡ ያለው ፡ ኃጢአት ፤ ያር ፡ ነው ።

ወፈያተ ፡ ለኀበ ፡ ሰይጣናት ።

ወንበደም ፡ ያላቸው ፡ አጋንንት ፡ ናቸው ።

ወአበዊሁኒ ፡ ለኀበ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

አበውም ፡ ያላቸው ፡ ሥላሴ ፡ ናቸው ።

ፀዳ ፡ አምላክ ።

አንድ ፡ አምላክ ፡ የሚሆን ።

ዘበአርኣያሁ ፡ ወአምሳሊሁ ፡ ንሕን ።

እኛ ፡ በሱ ፡ አርአያ ፡ የተገኘንበት ። ክነ ፡ ቢል ፤ የተ ፈጠርንበት ። ድኅነ ፡ ቢል ፤ የዳንበት ።

(ዘክመ ፡ ፈጠሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ፡ ወለሰሉ ፡ ዘውስቴቱ)

www.ethiopianorthodox.org

በከመ ፥ ይቤ ፥ በውስተ ፥ ኦሪት ።

አብ ፥ ላለው ፤ አኮኑ ፥ ዝንቱ ፥ አብ ፥ ፈጠረከ ። ለሶስትነቱ ፤ አነ ፥ ውእቱ ፥ አምላከ ፥ አብርሃም ፤ ወአምላክ ፥ ይስሐቅ ፤ ወአምላከ ፥ ያዕቆብ ። አሐዱ ፥ ላለው ፤ ስማዕ ፥ እሥራኤል ፥ አሐዱ ፥ ውእቱ ፥ አምላክ ከ ። በአርአያሁ ፥ ወበአምሳሊሁ ፥ ላለው ፤ ንግበር ፥ ሰብአ ፥ በአርአያነ ፥ ወበአምሳሊነ ፥ ብሎ ፥ በአሪት ፥ እንደ ፥ ተናገረ ።

ወበክመ ፥ ቃለ ፥ እግዚእነ ፥ በውስተ ፥ ወንጌል ፥ ኩኑ ፥ ፍጹማን ፥ ከመ ፥ አቡክሙ ፥ ሰማያዊ ፤ እስመ ፥ ፍጹም ፥ ውእቱ ። (ማቴ፭፥፵፰) ።

ጌታ ፥ እንዲህ ፥ እንዳለ ።

ወጥሪተ ፥ ቤቱኒ ፥ ይእቲኬ ፥ ጥሪተ ፥ ነፍሱ ፥ እንተ ፥ ነበረት ፥ እምፍጥረታ ።

ጥሪተ ፥ ቤትም ፥ ያላት ፥ በተፈጥሮ ፥ የምትገኝ ፥ አእምሮ ፥ ጠባይዕ ፥ ናት ።

ወእምጸጋ ፥ እምላክዊት ።

በጌታ ፥ ቸርነት ፥ የምትሰጥ ፥ አእምሮ ፥ መንፈሳዊም ፥ ናት ።

ወእንተሰ ፥ እምፍጥረታ ፤ ይእቲኬ ፥ እንተ ፥ ተክላ ፥ ፈጣሪ ።

በተፈጥሮ ፥ የምትገኘው ፥ ፈጣሪ ፥ ያሳደራት ፥ ናት ።

ወይእቲ ፥ ፍትወት ፥ ወሥምረት ።

በግብሯ ፥ ፍትወት ፥ ሥምረት ፥ አላት ፤ ይህችውም ፥ አስባ ፥ ወዳ ፥ የምትሠራ ፥ ናት ።

ወክሂል ፥ ለአእምሮ ፥ አግን ፥ ወገቢረ ፥ ጽድቅ ።

ከአእምሮ ፥ መንፈሳዊ ፥ ለመድረስ ፤ ትሩፋት ፥ ለመሥራት ፥ የሚቻላት ፥ ናት ።

ወጎርየታ ፥ ለዛቲ ።

ይህችን ፥ መውደድ ፥ ነው ።

ወይእቲ ፥ እንተ ፥ ይቤ ፥ ነቢይ ፤ እስመ ፥ ብእሲ ፥ ዘኢያጠፍዕ ፥ ኪያሃ ፥ ሰብእ ፥ ውእቱ ፥ እምክሙ ፥ ሀሎ ፥ ውስተ ፥ ክብር ።

ለአእምሮ ፥ ጠባይዕ ፥ የማይሰማማ ፥ ሥራ ፥ ባይሠራ ፥ ሰብእሰ ፥ እንዘ ፥ ክቡር ፥ የተባለው ፥ ይህ ፥ ነው ።

ወዖበ ፥ አዕበዳ ፥ ውእቱኬ ፥ አምላስ ፥ እንስሳ ፥ እንተ ፥ አልባቲ ፥ ልብ ።

ለአእምሮ ፥ ጠባይዕ ፥ የማይሰማማ ፥ ሥራ ፥ ቢሠራ ፥ ኢያእመረ ፥ ወከነ ፥ ከመ ፥ እንስሳ ፥ የተባለው ፥ ይህ ፥ ነው ።

ወእንተሰ ፥ እምጸጋ ፥ ይእቲ ፥ ጥምቀት ፥ ወሀብታት ፥ መንፈሳዊት ።

በእግዚአብሔር ፥ ቸርነት ፥ የምትሰጠውም ፥ ጥምቀት ፥ ልጅነት ፥ ናት ።

ወናሁ ፥ ተጽሕፈ ፤ እስመ ፥ ሃይማኖት ፥ ዘእንበለ ፥ ምግባረ ፥ ሠናይ ፥ ምውት ፥ ውእቱ ። (ያዕ፪ ፥ ፲፯) ።

ምግባር ፥ የሌለው ፥ ሃይማኖት ፥ ሥራ ፥ አይሠራም ፥ ተብሎ ፥ በያዕቆብ ፥ ተነግሯል ።

ወዘዘአልቦቱ ፥ ዘኒ ፥ ቦቱ ፥ ይትነሣእ ፥ እምኔሁ ። (ማቴ፳፭ ፥ ፳፱) ።

በወንጌልም ፥ እንዲህ ፥ ተብሏል ።

ዘውእቱ ፥ ለዘአልቦቱ ፥ ምግባረ ፥ ሠናይ ፥ ሃይማኖት ፥ ይትነሣእ ፥ እምኔሁ ።

ይኸውም ፥ ምግባር ፥ የሌለው ፥ ሰው ፥ ሃይማኖቱ ፥ ብቻ ፥ ሥራ ፥ አይሠራለትም ፥ ማለት ፥ ነው ።

ወያኤምር ፥ ክመ ፥ ኢይክውን ፥ ባተ፦ ፀ ፥ ቦቱ ።

በሃይማኖቱ ፥ ብቻ ፥ እንዳይጠቀም ፥ ያስረዳል ።

በክመ ፥ ዘአልቦቱ ፥ ሃይማኖት ።

ሃይማኖት ፥ የሌለው ፥ በምግባር ፥ ብቻ ፥ እንዳይጠቀም ።

ወጥሪተ ፥ አበዊሁኒ ፥ ይእቲ ፥ ትሩፋት ፥ እንተ ፥ ተመስልኖ ፥ ባቲ ፥ ለአቡን ፥ ሰማያዊ ፤ ወረሰየን ፥ ጎኩን ፥ ወራስያን ፥ መንግሥቱ ።

ጥሪተ ፥ አበውም ፥ ያላት ፥ ጌታን ፥ የምንመስልባት ፤ መንግሥተ ፥ ሰማያትን ፥ እንድንወርስ ፥ የምታደርገን ፥ ትሩፋት ፥ ናት ።

ዘከመ ፥ ሃይማኖት ።

ይህችውም ፥ እንደ ፥ ሃይማኖት ፥ ያለች ፥ ናት ።

ወተስፋ ።

ተስፋ ፥ መንግሥተ ፥ ሰማያት ፥ ነው ።

ወአፍቅሮ ፥ እግዚአብሔር ፥ ወሰብእ ።

ሰውን ፥ እግዚአብሔርን ፥ መውደድ ፥ ነው ።

ለሳም ።

ፍቅር ፥ አንድነት ፥ ነው ።

ወምሕረት ።

ይቅርታ ፥ ነው ።

ወአንኖ ፥ መንፈስ ።

ልበ ፥ ሰፊ ፥ ነገር ፥ አላፊ ፥ መሆን ፥ ነው ።

ወንጽሕ ።

ንጽሕና ፥ ነው ።

ወጒሩት ።

በጎነት ፥ ነው ።

ትሕትና ፥ ወአእምሮ ።

ትሕትና ፥ ነው ፤ ፈሊጥ ፥ ነው ።

ወጸሎት ፥ መንፈሳዊት ።

መንፈሳዊ ፥ ጸሎትም ፥ ነው ።

ወዛት ፥ ጥሪታት ፥ ታሠጥም ፥ ባሕረ ፥ ፍትወታት ፥ ዓለማውያት ።

አሁን ፥ የተናገርናቸውን ፥ ትሩፋት ፥ ባሕረ ፥ ፍትወታት ፥ ታሠጥማቸዋለች ።

ወተሐንት ፥ ሕሊናቲሃ ።

ክፉ ፥ ሕሊናም ፥ ያስቀራቸዋል ።

ወአስተሐምኖታ ፥ ለዓለም ።

ይህን ፥ ዓለም ፥ ማሰብም ፥ ያስቀራቸዋል ። አንድም ፥ ለላይኛው ፥ አጫፋሪ ፥ ትሩፋትን ፥ በጎ ፥ ሕሊናን ፥ በጎ ፥ ተዘክሮን ፥ ባሕረ ፥ ፍትወት ፥ ታሰጥማቸዋለች ።

ወይሠርቆን ፥ ስብሐት ፥ ብሙል

ውዳሴ ፥ ከንቱ ፥ ያስቀራቸዋል ። አንድም ፥ ዛቲ ፥ ጥሪታት ፤ ይች ፥ ትሩፋት ፥ ባሕረ ፥ ፍትወታትን ፥ ክፉ ፥ ሕሊናን ፥ ክፉ ፥ አሳብን ፥ ውዳሴ ፥ ከንቱን ፥ ታስቀራለች ። አንድም ፥ ለላይኛው ፥ ዋጋ ፤ ትሩፋት ፥ በጎ ፥ ሕሊና ፥ በጎ ፥ ተዘክሮ ፥ ባሕረ ፥ ፍትወትን ፥ ታስቀራለች ። ወትሠርቅ ፥ ስብሐተ ፥ ብሙለ ፤ ውዳሴ ፥ ከንቱን ፥ ታስቀራለች ።

ወሶበ ፥ ርእየ ፥ ብፁዓዊ ፥ በጎይን ፥ ልቡ ፥ ክመ ፥ ብዙኃን ፥ እምሳሕቱያን ፥ ኃጥኡ ፥ ዛተ ፥ ጥፉተ ፥ መንፈሳዊተ ።

ንዕድና ፥ ያለው ፥ አባ ፥ ይስረን ፥ በግይነ ፥ ልቡናው ፥ ከ ባሕታውያን ፥ ወገን ፥ ብዙዎቹ ፥ ይችን ፥ ትሩፋት ፥ እንዳጡ ፥ ባየ ፥ ጊዜ ።

ፀክመ ፥ ሕግ ፥ እፍቅሮተ ፥ አኃው ።

እኃውን ፥ መውደድ ፥ ሥርዓት ፥ እንደመሆኑ ።

ረዕየ ፥ ይብኪ ፥ ወያስቆቁ ፥ በእንቲኣሆሙ ።

ስለነሱ ፥ አዘነ ፥ አለቀሰ ።

ክመ ፥ ዘይበኪ ፥ በእንተ ፥ ነፍሱ ።

ለራሱ ፥ እንደሚያለቅስ ፥ ሰው ።

ወክመ ፥ ውእቱ ፥ ምስኪን ፥ ዘተወተመ ፥ ጥፉቱ ፥ ወተመርቀ ፥ ንዋየ ፥ እምቤቱ ።

ገንዘቡ ፥ በባሕር ፥ እንደ ፥ ተሰጠመበት ፤ ከቤቱ ፥ እንደ ፥ ተሠረቀበት ፥ ድኃ ፥ ሁኖ ፥ አዘነ ፥ አለቀሰ ። አንድም ፥ እንደ ፥ ተሠጠመበት ፤ ታሠጥም ፤ እንደ ፥ ተሠረቀበት ፤ ይሠርቆን ።

ወኮነ ፥ ይበእሎ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ክመ ፥ ይረስዮ ፥ ድልወ ፥ ለብፅዕ ፥ ፍቅሩ ፥ ወጥፉቱ ፥ ኀሬቲው ።

ለክቡር ፥ ፍቅሩ ። አንድም ፥ በፍቅሩ ፥ ለሚሰጣት ፤ በቸርነቱ ፤ ለሚያወርሳት ፥ ለመንግሥተ ፥ ሰማያት ፥ የበቃ ፥ ያደርገው ፥ ዘንድ ፥ ጌታን ፥ ለመነው ።

ተስእሎ ። ፳፮ ።

ይቤሉ ፥ አኃው ፤ ምንትኑ ፥ እግንቱ ፥ ትሩፋተ ፥ ተሰጎቱ ፥ እንክ ፥ ለዝ ፥ ብእሲ ።

ላንድ ፥ ሰው ፥ ዘጠኝ ፥ ትሩፋት ፥ አሉት ፥ ያለው ፥ ምንድር ፥ ነው ፥ ብለው ፥ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፥ መተርጕም ፤ እትሐዘብ ፥ ክመ ፥ እሱ ፥ ውእቶሙ ፤ እሐዱ ፥ አ ውጎደተ ፥ ጥፉት ።

አንዱ ፥ መንኖ ፥ ጥሪት ፥ ይመስለኛል ።

ወክልኤቱ ፤ ተእኅዞተ ፥ ጸም ፥ እስከነ ፥ ምሉት ፥ ለዓለም ።

ሁለተኛው ፤ ሁለገዜ ፥ እስከ ፥ ሠርክ ፥ መጸም ፥ ነው ።

ወሠለስቱ ፤ ትጋህ ።

ሶስተኛው ፤ ትጋህ ፥ ሌሊት ፥ ነው ።

ወአርባዕቱ ፤ ጸሎታት ፥ ዘሰብዓቱ ፥ ዕዓታት ፥ መዓልተ ፥ ወሌሊተ ።

አራተኛው ፤ የመዓልትና ፥ የሌሊት ፥ የሚሆን ፥ በሰባቱ ፥ ጊዜያት ፥ የታዘዘዉን ፥ ጸሎት ፥ ማድረስ ፥ ነው ።

ሐምስቱ ፤ አንብቦ ፥ መጻሕፍት ፥ ቅዱሳት ፥ ማዕከለ ፥ ጸሎታት ፥ ዕዓታት ።

አምስተኛው ፥ ጊዜ ፥ አድርሶ ፥ በዚያ ፥ መካከል ፥ መጽሐፍ ፥ መመልከት ፥ ነው ።

ወሰድስቱ ፤ የውሀት ።

ስድስተኛው ፥ የዋሃት ፥ ነው ።

ወሰብእቱ ፤ ትሕትና ።

ሰባተኛው ፥ ትሕትና ፥ ነው ።

ወሰመንቱ ፤ አፍቅሮ ፥ ቢጽ ።

ስምንተኛው ፥ አፍቅሮ ፥ ቢጽ ፥ ነው ።

ወተስዓቱ ፤ አርምሞ ።

ዘጠነኛው ፥ አርምሞ ፥ ነው ።

ዛተ ፥ ትሩፋተ ፥ ዘአጥረየ ።

ያ ፥ ሰው ፥ አሊህን ፥ ትሩፋት ፥ ገንዘብ ፥ ያደረገ ።

በጸግ ፥ ብዙኃ ፥ ወፀብዕ ፥ ኀቢይ ።

በብዙ ፥ ያርነት ፥ በብዙ ፥ ድካም ፥ ነው ።

ባሕቱ ፥ ሞአ ፥ ሁሎ ፥ ሕግግተ ።

ነገር ፥ ግን ፥ ኃጣውእን ፥ ሁሉ ፥ ድል ፥ ነሣ ። አንድም ፥ በብዙ ፥ ያር ፥ በብዙ ፥ ድካም ፥ ዘጠኙን ፥ ትሩፋት ፥ ገንዘብ ፥ ያደረገ ፥ ሰው ፥ ኃጣውእን ፥ ሁሉ ፥ እንጂ ፥ ድል ፥ ነሣ ።

ወበአውጎደተ ፥ አጥርኮ ፥ ሞአ ፥ እፍቅሮ ፥ ብፋሮ ።

በመንኖ ፥ ጥሪት ፥ ፍቅረ ፥ ንዋይን ።

ወበእኂዝ ፥ ሞአ ፥ ክርሥና ።

በከፊለ ፥ ጎብስት ፥ ሀዳምነትን ።

ወበጸም ፥ ሞአ ፥ ስስዕተ ።

በጸም ፥ ስስትን ።

ወበትጋህ ፥ ሞአ ፥ ንዋመ ።

www.ethiopianorthodox.org

በትጋህ ፡ እንቅልፍን ።
ወበጸሎታት ፡ ሞአ ፡ ሕሊናተ ።
ነገራተ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በጸሎት ፡ ጨዋታን ።
ወበእንብዐተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዳሳት ፡ ሞአ ፡ ነገራተ ፡ እኩያተ ።
ሕሊናተ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡ ከ
ፉ ፡ ሕሊናን ።
ወበብሕተ ፡ ብሑለ ።
ውዳሴ ፡ ከንቱን ።
ወበተየውሦ ፡ ሞአ ፡ ትቍጥዕተ ፡ ወመንተ ።
በየውሃት ፡ ቍጣን ፡ ብስጭትን ።
ወበትሕትና ፡ ሞአ ፡ ስብሐተ ፡ ብሑለ ፡ ወትዝኅርተ ።
በተሕትና ፡ ትዕቢትን ፡ ትዝኅርትን ።
ወበአፍቅሮ ፡ ሰብእ ፡ ሞአ ፡ ጾልእ ፡ ወትንአተ ፡ ወተጻብሮተ ፡ ወብዙ
ኃተ ፡ እክያተ ።
በፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ መጸላትን ፡ ምቀኝነትን ፡ ድል ፡ ነሣ ።
ወበዘአርምሞ ፡ ሞአ ፡ ነገረ ፡ ዘርቅ ፡ የሚል ፡ ይገኛል ።
ወአሥፈሰበ ፡ ትርፍት ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ የኃጥኣ ፡ በዓለ ፡ ዛቲ ፡ ተስ
ዓቱ ።
አሥረኛይቱ ፡ ግን ፡ ዘጠኙን ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ የማያገ
ኛት ፡ ፍጽምት ፡ ናት ።
ይእቲኬ ፡ ፍልሐት ፡ ዘበዓለም ፡ ውስተ ፡ አፍቅሮ ፡ እግዚአብሔር ።
ይኸውም ፡ ሁለ ፡ ጊዜ ፡ በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲ
ናደዱ ፡ መኖር ፡ ነው ።
ወይእቲሰ ፡ ዘትጠረይ ፡ እምጸሎት ፡ ጎበዕት ፡ ዘውስተ ፡ ሕሊና ፡ እን
ተ ፡ እንበለ ፡ ጽርኅት ፡ ወኢፍልሰት ።
ዬችም ፡ ሁለጊዜ ፡ ያለመባከን ፡ በሚሆን ፡ ጸሎተ ፡
ልብ ፡ ትገኛለች ።
ወእምአዝልፎ ፡ ሰዲደ ፡ ሕሊናት ፡ ወሙለተ ፡ ሕማማት ፡ ወበፍጠተ ፡
ሰይጣናት ።
ኃጣውእ ፡ ድል ፡ የሚነሡበት ፡ ክፉ ፡ ሕሊናን ፡ የሰ
ይጣናትን ፡ ሽንገላ ፡ ሁለጊዜ ፡ በማራቅ ፡ ትገኛለች።
ወዘእምቀዳሚ ፡ ተክውሶቱን ፡ ውስተ ፡ ልብ ።
መጀመሪያ ፡ በልቡና ፡ እንደ ፡ ታሰበች ፡ በማራቅ ፡ ት
ገኛለች ።
ወበእንተ ፡ ዘክመ ፡ ዛቲ ፡ ፍድፋዲ ፡ ፍጽምት ፡ እምሆሉ ፡ ትፋፋት ።
እንደ ፡ ፍቅር ፡ ያለች ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ፡ ከትፋፋት ፡ ሁሉ ፡
የምትበልጥ ፡ ስለሆነች ። አንድም ፤ እንደ ፡ ንጽሐ ፡
ልብ ፡ ስላለች ፡ ስለ ፡ ጸሎተ ፡ ልብ ።
ሰይጣናት ፡ ኃያላን ፡ ወእኩያን ፡ ይትጋደልዎሙ ፡ ለባሕታውያን ፡ በብ
ዙኅ ።
ኃያላን ፡ እኩያን ፡ የሚሆኑ ፡ አጋንንት ፡ ባሕታውያ
ንን ፡ በብዙ ፡ መገን ፡ ይዋጓቸዋል ።
ክመ ፡ ኢይብጽሑ ፡ ኀቤሃ ፡
ከጸሎተ ፡ ልብ ፡ እንዳይደርሱ ።
ወኢይጽንዑ ፡ ውስቴታ ።
በርሷ ፡ እንዳይጸኑ ።
ወበእንተዝ ፡ ኮነት ፡ ምግባር ፡ ዘመብጽሑት ፡ ኀቤሃ ፡ መድኅኖተ ፡ እ
ምግባራተ ፡ ትሩፋት ።
የሚዋጓቸው ፡ ስለሆነ ፡ ከጸሎተ ፡ ልብ ፡ የምታደርስ ፡
ጸሎተ ፡ አፍአ ፡ ከሌላው ፡ ትሩፋት ፡ ይልቅ ፡ ወጣን
ያንን ፡ አጋንንትን ፡ የምታደክማቸው ፡ ናት ።
ወዘተኅፅብኒ ፡ እምኔሆን ።
ፈጽማ ፡ የምታስጨንቃቸው ፡ ናት ። አንድም ፡ እን
ደ ፡ ጸሎተ ፡ ልብ ፡ ስለ ፡ አለች ፡ ፍቅር ፤ ያችን ፡ ከ
ሁሉ ፡ የምትበልጥ ፡ አላት ። እኩያን ፡ ኃያላን ፡ የሚ
ሆኑ ፡ አጋንንት ፡ ባሕታውያንን ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ይ
ዋጓቸዋል ፤ ከፍቅር ፡ እንዳይደርሱ ፡ በርሷ ፡ እንዳይ
ጸኑ ፤ እንዲህ ፡ ስለሆነ ፡ ከፍቅር ፡ የምታደርስ ፡ ተዘ
ክሮ ፡ ወጣንያንን ፡ የምታደክም ፡ የምታስጨንቅ ፡ ና
ት ። አንድም ፡ እንደ ፡ ፍቅር ፡ ስለ ፡ አለች ፡ ተዘከ
ሮ ፤ የቀረው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ስለሆነ ፡ ከተ
ዘክሮ ፡ የምታደርስ ፡ ሰቂለ ፡ አዕይንት ፡ ሰፊሐ ፡ አእ
ዳው ፡ ወጣንያንን ፡ አጋንንትን ፡ ፈጽማ ፡ የምታደክ
ም ፡ ሆነች ፤ የምታስጨንቅም ፡ ሆነች ። ከተዘክሮ ፡ ጀ
ምሮም ፡ ወደላይ ፡ ያስተረጉማል ፤ ከመን ፡ ትቶ ፡ ደ
ግሞ ፡ ስለ ፡ ጸሎተ ፡ ልብ ፤ ስለ ፡ ፍቅር ፤ ስለ ፡ ተዘ
ክሮ ፡ ብሎ ፡ ወደላይም ፡ ወደታችም ፡ ያስተረጉ
ማል ።
ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓዊ ፡ ማርቆስ ።
ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ማርቆስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
እስመ ፡ ዘበእንተ ፡ ተየርሮተ ፡ ሰይጣናት ፡ ለዝንቱ ፡ ግብር ።
ይህን ፡ ጸሎተ ፡ ልብ ፡ ፍቅር ፡ ተዘክሮ ፡ ያለውን ፡
ትሩፋት ፡ ለማስቀረት ፡ ሰይጣናት ፡ የሚዋጉት ፡ ስለ ፡
ሆነ ።
አልበ ፡ ክሂል ፡ ክመ ፡ ፍጡን ፡ ይትፈጸም ፡ ውስተ ፡ አፍቅሮ ፡ ክርስቶ
ስ ።
ሰው ፡ በፍቅረ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡
አይቻለውም ፡ አለ ።
እምተኀብሮ ፡ ሕሊናት ፡ ወፍልሐት ፡ እንተ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ክፉ ፡ ሕሊና ፡ በጎ ፡ ሕሊና ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ ከመቃሰ
ቡ ፡ የተነሣ ። አንድም ፤ ተኀብሮ ፤ ክፉ ፡ ሕሊና ፡ በ
ጎ ፡ ሕሊና ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ ከመቃሰቡ ፡ የተነሣ ፤ በ

ፍቅረ ፡ ክርስቶስ ፡ ወፍልሐት ፡ እንተ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ። በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ መሆን ፡
አይቻለውም ፡ አለ ።
ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ወቅሪስ ።
ወቅሪስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
ለእመ ፡ ሞእከ ፡ ፍልሰተ ፡ ሕሊናት ።
የሕሊና ፡ መባከንን ፡ ድል ፡ የነሣህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።
ወጸናዕክ ፡ ውስተ ፡ ተዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ።
በተዘከሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ የጸናህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።
ድልው ፡ እንከሰ ፡ አንተ ፡ ለፍጹም ፡ ዘውስተ ፡ አፍቅሮ ፡ ክርስቶስ ፡
ወሰብእ ።
በፍቅረ ፡ ክርስቶስና ፡ በፍቅረ ፡ ሰብእ ፡ ለፍጹምነት ፡
የበቃህ ፡ ትሆናለህ ።
ዘበቱ ፡ ትትመዋእ ፡ ሆሎ ፡ ሕማማት ፡ ዘሕሊናት ።
ለፍቅር ፡ ሲቀጽል ፡ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ሕሊና ፡ ድል ፡ የም
ትነሣበት ፡ አለ ።
እንተ ፡ ትሰቀል ፡ ቅድመ ፡ በእፍቅሮተ ፡ ክርስቶስ ።
በአፍቅሮተ ፡ ነፍስ ፡ ይላል ፤ ነፍስን ፡ ክርስቶስን ፡ በ
መውደድ ፡ የምትርቅ ፡ ብሎ ፡ ለክፉ ፡ ሕሊና ፤ የም
ትፈጸም ፡ ብሎ ፡ ለበጎ ፡ ሕሊና ። አንድም ፡ በአፍቅ
ሮተ ፡ ክርሥ ፤ በአፍቅሮተ ፡ ርእስ ፡ ይላል ። ራስን ፡
በመውደድ ፤ ሆድን ፡ በመውደድ ፡ የምትቀር ፡ ብሎ ፡
ለበጎ ፡ ሕሊና ፤ የምትፈጸም ፡ ብሎ ፡ ለክፉ ፡ ሕሊ ።
ወዘይመልክ ፡ ዘንተ ፡ ፍጹመ ።
ይህን ፡ ክፉ ፡ ሕሊና ፡ ፈጽሞ ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ ሰው ።
ውእቱኬ ፡ ይፈቱ ፡ ክመ ፡ ይትመሠጥ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወይትፈስ
ጥ ፡ እምዝ ፡ ሥጋ ።
በሞት ፡ ከሥጋ ፡ በምናኔ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሊለይ ፡
ይወዳል ።
ወየሀሉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘበእፍቅሮ ።
በፍቅር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ተውሕዶ ፡ ይኖር ፡
ዘንድ ።
ወይነ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ ማኅደረ ፡ ጻድቃን ፡ ወደወል ፡ ፍጹማን ።
ፍጹማን ፡ ጻድቃን ፡ በሚከብሩበት ፡ በንጽሐ ፡ ነፍስ ፡
በንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ይከብር ፡ ዘንድ ፤ በምናኔ ፡ ከዚ
ህ ፡ ዓለም ፡ ዛሬ ፡ ጻድቃን ፡ ባሉበት ፡ በገነት ፤ ኃላ ፡
ፍጹማን ፡ ባሉበት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይኖር ፡
ዘንድ ፤ በሞት ፡ ከሥጋው ፡ ሊለይ ፡ ይወዳል ።
ዘውስቱ ፡ ልዑል ፡ እምሕማማት ፡ ወሰይጣናት ።
ይኸውም ፡ ገነት ፡ ኃጣውኣ ፡ ሰይጣናት ፡ የሌሉበት ።
ወአጽባዕ ፡ ወድቀታት ።
ያር ፡ መከራ ፡ የሌለበት ።
መክነ ፡ ዕረፍት ፡ እምጻማት ፡ ትሩፋ ።
ከድካም ፡ የሚያርፉበት ፡ ቦታ ፡ ነው ።
እሰክ ፡ እስተርእዮተ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘይትፈሣሕ ፡ በሰብ
ሐቲው ፡ ትፍሥሕተ ፡ ዘኢየኃልቅ ።
ሰው ፡ በጌትነቱ ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ የሚያደርግበት ፡
ክርስቶስ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ከዚያ ፡ ሊኖር ፡ ይወ
ዳል ።

ተስእሎ ፡ ፸፯ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፡ ተርጉም ፡ ለን ፡ ምግባረ ፡ ገዙ ፡ አረጋይ ፡ በዓለ ፡ አበ
ፈፈዳት ፡ ወሮም ፡ ደቃቅ ።
የዚያን ፡ የበዐለ ፡ አሸዋዉን ፡ ነገር ፡ ተርጕምልን ፡ አ
ሉት ። እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡
እንቅብ ፡ ሰፍቶ ፡ አንዱን ፡ በቀኝ ፤ አንዱን ፡ በግ
ራ ፡ አኑሮ ፡ አሸዋ ፡ ከፊቱ ፡ አለ ፤ ያን ፡ እያነሣ ፡ በ
ጎ ፡ ሕሊና ፡ ሲታሰበው ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፤ ክፉ ፡ ሕሊና ፡
ሲታሰበው ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ይጥላል ። ኃላ ፡ ቢያዩት ፡
የቀኙ ፡ መልቶ ፡ የግራው ፡ ጕድሎ ፡ ተገኝቷል ። አ
ንድም ፡ ጠጠሩንስ ፡ የሚጥለው ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡
ነው ፡ ብሎ ፤ አንዱን ፡ እንቅብ ፡ አሸዋ ፡ መልቶ ፡ በ
ቀኝ ፤ አንዱን ፡ እንቅብ ፡ ባዶውን ፡ በግራ ፡ አኑሮ ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ሲታሰበው ፡ ከቀኙ ፡ እያነሣ ፡ ወደ ፡ ግ
ራው ፡ ይጥል ፡ ነበር ። ኃላ ፡ ቢታይ ፡ የቀኙ ፡ ሳይጕ
ድል ፡ እንደመላ ፤ የግራው ፡ እንደ ፡ ጕደለ ፡ ሳይመ
ላ ፡ ተገኝቷል ። ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ አዳም ፡ ቀድሞ ፡
በንጽሐ ፡ ጠባይዕ ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ ያጠይቃል ።
እንዲህ ፡ የሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ አለውን ፡ ሁለጊ
ዜ ፡ ነው ፤ ትሩፋቱስ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነውን ፤ ሌላም ፡
አለ ፤ የልቡና ፡ ሥራስ ፡ ባይኖረው ፡ ነውን ፤ ብለው ፡
ይጠይቃሉ ።
ይቤ ፡ መተርጉም ፤ ሥርዓተ ፡ ልቡና ፡ ውእቱ ፡ ዘያበጽሖ ፡ ለብሕት ፡
ኀበ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ።
አንዱን ፡ አመጣው ፤ መነኰሴውን ፡ ከንጽሐ ፡ ልብ ፡
የሚያደርሰው ፡ የልቡና ፡ ሥራ ፡ ነው ።
ወምግባሩስኬ ፡ ውእቱ ።
ይሠራው ፡ የነበረ ፡ ሥራም ፡ ይህ ፡ ነው ።
አንበረ ፡ አስፈሬዳተ ፡ በየማኑ ፡ ወአስፈሬዳተ ፡ በጸጋሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

አንዱን ፡ እንቅብ ፡ በቀኝ ፤ አንዱን ፡ እንቅብ ፡ በግራ ፡ አኑሮ ።

ወሶሎ ፡ ሕሊናተ ፡ ሠናያተ ፡ ዘትመጽእ ፡ ኀቤሁ ፡ ይወዲ ፡ ኀጣው ፡ ውስተ ፡ አስፈሬዳ ፡ እንተ ፡ በየማኑ ።

በጎ ፡ ሕሊና ፡ በታሰበው ፡ ጊዜ ፡ እየታሰበው ፡ ጠጠሩን ፡ ወደ ፡ ቀኙ ፡ ይጨምር ፡ ነበር ።

ወሶሎ ፡ ሕሊናተ ፡ እኪተ ፡ ዘትመጽእ ፡ ላዕሌሁ ፡ ይወዲ ፡ ኀጣ ፡ ውስተ ፡ አስፈሬዳ ፡ እንተ ፡ በጸጋሙ ።

ክፉ ፡ ሕሊና ፡ በታሰበው ፡ ጊዜ ፡ እየታሰበው ፡ ጠጠሩን ፡ ወደ ፡ ግራው ፡ ይጨምር ፡ ነበር ።

ወገንቱ ፡ ሶሎ ፡ ምስለ ፡ ተጸምይቱ ፡ ውስተ ፡ ቅኔሁ ፡ ወጸሶቱ ፡ ወኅብሩ ።

ትሩፋቱ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ላሉት ፡ አመጣ ፡ ይህንም ፡ ማድረጉ ፡ በሰጊድ ፡ በቁመት ፡ በጸም ፡ በጸሎት ፡ በትሩፋት ፡ ዕሙድ ፡ ከመሆን ፡ ጋራ ፡ ነው ።

ወበእንተኒ ፡ አዝልፎቱ ፡ ለገ ፡ ግብር ፡ ትፍሳ ።

በዚህ ፡ በፍጹምነት ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ኮኑ ፡ ይቀንው ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰይጣናት ።

ሰይጣናት ፡ ቀኒበት ።

ወያክውሱ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ብዙኀ ፡ እክያተ ።

በልቡናው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አሳሰበት ።

ወየሐምም ፡ በነፍሱ ፡ ወሥጋሁ ።

በሥጋውም ፡ በነፍሱም ፡ ያገን ፡ ይደክም ፡ ነበር ።

ወአኮ ፡ ነፍስ ፡ ባሕቲታ ፡ ዘተሐምም ፡ በእንተ ፡ ጸማተ ፡ ሥጋ ፡ በበይነ ፡ ክዊናታ ፡ አሐደ ፡ ምስሌሁ ።

ሥጋ ፡ በሚቀበለው ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተዋሐደችው ፡ የምታገን ፡ የምትደክም ፡ አይደለም ።

አላ ፡ ልያሳናትኒ ፡ እለ ፡ ይትታተልዋ ፡ ይጸምዉ ፡ ዘይበገን ።

የሚቀጣት ፡ አጋንንትም ፡ ከሷ ፡ ይልቅ ፡ ይደክማሉ ፡ እንጂ ።

ይጹ ፡ ግር ፡ ወቅሪስኒ ።

ግንሸ ፡ ይኸን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ይቤ ፡ መጽሐፈ ፡ ገነት ። አንድም ፡ ጸሐፌ ፡ ገነት ፡ ጳላድዮስ ፡ ተናገረ ፡ ማር ፡ ወቅሪስም ።

ዕበ ፡ ተዋጠወ ፡ ምስሌሁ ፡ ሰይጣን ፡ ገሙት ።

ሰይጣን ፡ ገሙት ፡ በተዋጋው ፡ ጊዜ ።

ተወርቀ ፡ አልባሲሁ ።

ልብሱን ፡ ጣለ ።

ወቆመ ፡ ዕራቆ ፡ ታሕተ ፡ ክዋኔይ ፡ ኮነ ፡ ሌሊት ፡ በመዋዕለ ፡ ክረምት ።

በክረምት ፡ ወራት ፡ ከደጅ ፡ ዕራቁቱን ፡ አደረ ፡ እንደ ፡ ዳስ ፡ ያለ ፡ የለበትምና ፡ ታሕተ ፡ ሰማይ ፡ አለ ።

ወአድኅሞ ፡ ለሰይጣን ፡ ገሙት ፤ እስክን ፡ ጉየ ፡ እምኔሁ ፡ ውእቱ ፡ ርጉም ።

ከእሱ ፡ ተለይቶ ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ ሰይጣን ፡ ገሙትን ፡ ድል ፡ ነሣው ።

ጸማሃሙኪ ፡ ለቅዱሳን ፡ ዘለዓለም ፡ ያደክሞሙ ፡ ውእቱ ፡ ለሰይጣናት ።

ባሕታውያን ፡ በትሩፋት ፡ የሚደክሙት ፡ ድካማቸው ፡ ሰይጣናትን ፡ ያደክማቸዋል ።

እስመ ፡ ይሣቅይምሙ ፡ መላእክት ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ።

መላእክት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዘው ፡ ሥዕይ ፡ ያጸኑባቸዋልና ።

እስመ ፡ ዕበ ፡ ፈቀደ ፡ ሰይጣን ፡ ክሙ ፡ ይንፍቅ ፡ ማእክለ ፡ ክልኤቱ ፡ አኃው ፡ ዘዘሥጋ ።

ይህንም ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፤ ሰይጣን ፡ ሁለቱን ፡ ወንድማማች ፡ ሊለያይ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ።

ወዕበ ፡ አኅተወ ፡ ማኅቶተ ፡ እኁ ፡ ዘይንዕስ ፡ አጥፍወ ።

ታናሹ ፡ መብራት ፡ አብርቶ ፡ ይዘ ፡ ሲመጣ ፡ አጠፋበት ።

ወአውደቆ ፡ ሰይጣን ፡ ሶቱኒ ።

እሱንም ፡ ሰርጅቶ ፡ ጣለው ።

ወማኅቶተኒ ።

መብራቱንም ፡ አጠፋው ።

ወዘበጠ ፡ እንክ ፡ እኁሁ ፡ ላዕለ ፡ መልታሕቱ ።

ታላቁ ፡ ይህ ፡ ሊል ፡ ዘሊል ፡ ብሎ ፡ ፈቱን ፡ ጸፋው ።

ወገብረ ፡ ሶቱ ፡ ስግደተ ፡ ወይቤ ፡ እኁየ ፡ እኁኒ ፡ መኑፈስክ ፡ ላዕሌየ ፡ ወእኁስ ፡ እኁትም ።

ወንድሜ ፡ ማረኝ ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ሁነህ ፡ ታገሠኝ ፤ ፈትም ፡ ያበረሁት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አሁንም ፡ መልሼ ፡ አበራዋለሁ ። እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ታላቅና ፡ ታናሽ ፡ ናቸው ። ታላቁ ፡ መጽሐፍ ፡ እመለከትበት ፡ መብራት ፡ አምጣልኝ ፡ አለው ፡ አብርቶ ፡ ሲመጣ ፡ ሰይጣን ፡ ሰርጅቶ ፡ ጣለው ። እሱ ፡ ሲወድቅ ፡ መብራቱ ፡ ጠፋ ፤ ይህ ፡ ሊል ፡ ብሎ ፡ በጥፊ ፡ መታው ። ሰይጣን ፡ እንዲህ ፡ ማድረጉ ፡ ብወደቅ ፡ ማዘን ፡ ይመስል ፡ ይመታኛልን ፡ ብሎ ፡ መልሶ ፡ ይመታዋል ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይለያያሉ ፡ ብሎ ፡ ነው ። እሱ ፡ ጣን ፡ ማረኝ ፡ እኔ ፡ መልሼ ፡ አበራዋለሁ ፡ አለ ።

ወዕበ ፡ ርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዕግሥቶ ፡ ለደቂቅ ፡ ወትሕትናሁ ።

ጌታም ፡ የታናሹን ፡ ትእግሥት ፡ እንደማዘን ፡ ሁሉ ፡ መታኝ ፡ ሳይል ፡ መታገሡን ፤ ወትሕትናሁ ፤ አንሰ ፡ አኃትዎ ፡ ማለቱን ፡ ብየ ፡ ጊዜ ።

አዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመልአክ ፡ ውእቱ ፡ ደቂቅ ።

መልአክ ፡ ዑቃቢውን ፡ እሠርና ፡ ግረፈው ፡ አለው ።

ወአሠሮ ፡ እንክ ፡ ለገዝኩ ፡ ሰይጣን ፡ በውስተ ፡ በኅት ።

ያን ፡ ሰይጣን ፡ ከዚያው ፡ ከበዓቱ ፡ ሳይወጣ ፡ አሥሮ ።

ወግፋዖ ፡ እስክ ፡ ሳኒታሁ ።

ሲገርፈው ፡ አደረ ።

ወሀየንተ ፡ አሐቲ ፡ ገብጠት ፡ ዘተዓገሠ ፡ ገዝኩ ፡ እጉ ፡ እምን ፡ እጉ ፡ በጥብረ ፡ ሰይጣን ፡ አሠሮ ፡ መልአክ ፡ ለገዝኩ ፡ ሰይጣን ።

ሰይጣን ፡ ባደረገው ፡ ነገር ፡ ታናሹ ፡ ከታላቁ ፡ ስለተቀበላት ፡ አንድ ፡ ጥፊ ፡ መልአኩ ፡ ሰይጣንን ፡ አሥሮ ።

ወቀመር ፡ ኑን ፡ ሌሊት ፡

ሲገርፈው ፡ አደረ ፤ አይነኩ ፡ ቢነኩ ፡ ያድሯል ፡ ሲታወኩ ፡ እያለ ፡ ሲለፈልፍ ፡ አድሯል ።

ተስእሎ ፡ ፭፰ ።

ይዜሉ ፡ አኃው ፡ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ ይፈርሀ ፡ ሰይጣናት ፡ እምግብረ ፡ ባሕታውያን ።

ሰይጣናት ፡ ባሕታውያን ፡ ከሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ የሚፈሩት ፡ ማናቸውን ፡ ነው ።

ክሙ ፡ ታስ ፡ አበውኑ ።

አበው ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ።

ለእመ ፡ ፈቀድክ ፡ ይፍርሁ ፡ ሰይጣናት ፡ እምኔክ ።

ሰይጣናት ፡ ሊፈሩህ ፡ ብትወድ ።

መንኑክ ፡ እንክ ፡ ፍትወታተ ።

ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ናቅ ፡ እንዳሉ ፡ ቢንቁ ፡ ነውን ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፡ በእንተ ፡ ሠለስቱ ፡ ግብራት ።

ስለ ፡ ሶስት ፡ ነገር ፡ ነው ።

ቀዳሚሁስ ፡ እስመ ፡ እግዚእን ፡ ዕበ ፡ መነኑ ፡ ሠለስተ ፡ ሕማማተ ፡ እንተ ፡ ታስተጋብዕ ፡ ግብራተ ፡ ሕማማት ።

አንዱ ፡ ጌታ ፡ ኃጣውኦን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስባ ፡ የምታሠራ ፡ ሶስቱን ፡ አርእስተ ፡ ኃጣውኦ ፡ ድል ፡ በነሣ ፡ ጊዜ ።

ወይእቲ ፡ ፍትወት ።

ይህችም ፡ ስስት ።

ወአፍቅሮ ፡ ንዋይ ።

ፍቅረ ፡ ንዋይ ።

ወስብሐት ፡ ብሑል ።

ትዕቢት ፡ ናት ።

ዘየሙ ፡ ተጻብኦ ፡ ሰይጣን ፡ በጥቡዕ ።

ሰይጣን ፡ ጌታን ፡ ጸንቶ ፡ የተዋጋበት ። በኅብዕ ፤ ቢል ፡ ተሠውሮ ።

በውስተ ፡ ገዳም ።

በገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ።

በጎድኣት ፡ ወበጸም ፡ ወበጸሎት ፡ ሞዖ ፡ ለሰይጣን ፡ እንክ ።

ጎድዓት ፡ ያለው ፡ ትዕግሥት ፤ ጸም ፡ ያለው ፤ ጸሊዓ ፡ ንዋይ ፤ ጸሎት ፡ ያለው ፡ ትሕትና ፡ ነው ። በስስት ፡ ቢመጣበት ፡ በትእግሥት ፤ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ቢመጣበት ፡ በጸሊዓ ፡ ንዋይ ፤ በትዕቢት ፡ ቢመጣበት ፡ በትሕትና ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ነሥቶታልና ። አንድም ፡ ሰይጣን ፡ የተባለ ፡ ያ ፡ ነው ። ስስትን ፡ በትእግሥት ፤ ፍቅረ ፡ ንዋይን ፡ በጸሊዓ ፡ ንዋይ ፡ ትዕቢትን ፡ በትሕትና ፡ ድል ፡ ነሥቷልና ።

አሰኒ ፡ የሐውሩ ፡ አሠሮ ።

ጌታ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ባሕታውያንም ።

ያፈርሱ ፡ ሕሊናተ ፡ ኃጢአት ፡ ክመ ፡ ይስደዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰይጣናት ።

ሰይጣናት ፡ ከሰቸው ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ ሐልዮ ፡ ኃጢአትን ፡ ድል ፡ ይነሣሉ ።

ወዘክመ ፡ ይፈርሁ ፡ ሰይጣናት ።

መስቀልን ፡ እንዲፈሩ ።

አኮ ፡ እመስቀል ፡ ባሕቲቱ ።

መስቀልን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ትች ።

አላ ፡ እምትእምርትኒ ፡ ዘክማሁ ፡ አምሳሊሁ ።

መስቀልን ፡ የመሰለም ፡ በሕሊና ፡ ቢያማትቡቸው ፡ ይፈራሉ ፡ እንጂ ፤ አንድም ፡ በሕሊና ፡ ቢያማትቡቸው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ወዘክማሁ ፤ በሕሊና ፡ ማማተብን ፡ የመሰለ ፡ በእጅ ፡ ቢያማትቡባቸው ፡ ይፈራሉ ፡ እንጂ ፤ አንድም ፡ በእጅ ፡ ቢያማትቡባቸው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ወዘክማሁ ፤ በእጅ ፡ ማማተብን ፡ የመሰለ ፡ እንደ ፡ መስቀል ፡ ያለ ፡ የተመሰቀለ ፡ እንጨት ፡ የተመሰቀለ ፡ ጎዳና ፡ ቢያዩ ፡ ይፈራሉ ፡ እንጂ ፤ እንዲህ ፡ እንደሆነ ።

ወኢክነሂ ፡ ዘይትመውዑ ፡ ወይትይዩ ፡ እምን ፡ ምግባራት ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕቲቱ ።

ድል ፡ ተነሥተው ፡ የሚሄዱም ፡ ክርስቶስ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

አላ ፡ እምግባሬተ ፡ ተላውያኒሁ ፡ በምግባሬት ።
እሱን ፡ የመሰሉ ፡ ሐዋርያት ፡ ባሕታውያን ፡ በሠሩት ፡ ሥራም ፡ ድል ፡ ይነሣሉና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ክልእኒ ።
ሁለተኛውም ።

በክመ ፡ ባሕታውያን ፡ ዖበ ፡ ተወክፉ ፡ ስፍጠተ ፡ ሰይጣናት ፡ በሕሊናተ ፡ ኃጢአት ።
ባሕታውያን ፡ የሰይጣናትን ፡ ሽንገላ ፡ በሕሊናቸው ፡ ቢስማሙ ።

ወተፈግው ፡ ቦቶን ።
በዚያው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ቢያደርጉ ።

ትጸለምት ፡ ነፍሳቲሆሙ ።
ሰውነታቸው ፡ ትለወጣለች ።

በእንተ ፡ ርኁቅ ፡ እምእግዚአብሔር ።
ከጌታ ፡ ስለተለዩ ።

የነፍሩ ፡ ወየነሥሩ ።
ያፍራሉ ፡ ይዋረዳሉ ።

ወይትነወሩ ።
ይነቀፋሉ ።

ለእመሰ ፡ ኢተወክፉ ፡ ስፍጠታቲሆሙ ።
ሽንገላቸውን ፡ ባይቀበሉ ፡ ግን ።

ወአርሐቁ ፡ ሕሊናተ ፡ እምቀዳሚሁ ፡ ለእንስሐስሖቆሙ ።
ክፉ ፡ ክፉ ፡ ሕሊናትን ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ታሰቡ ፡ ቢያርቋቸው ።

ወይፈስዩ ፡ እግዚአሙ ፡ ለረድኤቆሙ ።
ጌታቸውን ፡ እርዳን ፡ ብለው ፡ ቢለምኑ ።

ይሰዐሩ ፡ እንክ ፡ ሰይጣናት ።
ድል ፡ ሁነው ።

ወየነሥሩ ፡ ወይትመየጡ ፡ ፍጡነ ።
አፍረው ፡ ይመለሳሉና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

በክመ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓዊ ፡ ማርቆስ ።
ማርቆስ ፡ እንደተናገረ ፡ ምናለ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ።

ክመ ፡ ዘይፈርህ ፡ ወይጉይይ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይዘመ ፡ ምስለ ፡ መጻምር ተ ፡ ክልኤ ።
ከሰው ፡ ሚስት ፡ የይረሰ ፡ ሰው ።

ዖበ ፡ ስምዐ ፡ ድምዐ ፡ ምታ ።
የባሏን ፡ ድምጽ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፊርቶ ፡ እንዲሸሽ ።

ከማሁ ፡ ይደነግፅ ፡ ሰይጣንኒ ፡ ወይጉይይ ፡ ዖበ ፡ ስምዐን ፡ እንዘ ፡ ንጹዕ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ሰይጣንም ፡ የጌታን ፡ ስም ፡ ስንጠራ ፡ ጌታን ፡ ስናነሣ ፡ የሰማ ፡ እንደሆነ ፡ ሸሽቶ ፡ ይሄዳል ፡ አለ ።

ማልስሂ ።
ሥስተኛም ።

በእንተ ፡ ኦሆ ፡ ብሂሎቆሙ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ለጌታ ፡ እሺ ፡ በጎ ፡ ስላሉ ።

ወበእንተ ፡ አፍቅሮቆሙ ፡ ኪያሁ ።
ጌታን ፡ ስለ ፡ ወደዱ ።

ይጠረይ ፡ ሎሙ ፡ ቀሪብ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።
ከጌታ ፡ ባለሟልነት ፡ ይሰጣቸዋል ።

ወይርኅቁ ፡ እንክ ፡ ሰይጣናት ፡ እምኔሆሙ ።
አጋንንትም ፡ ይርቁላቸዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ወነዋ ፡ ይቤ ፡ እግዚእንኒ ፡ ለፍቁራኒሁ ።
ጌታም ፡ ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ባለሟሎቹን ፡ ሐዋርያትን ።

ናሁ ፡ ወሀብኩክሙ ፡ ሥልጣን ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ኃይላተ ፡ጸላኢ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይጎክየክሙ ።
እንዲህ ፡ አላቸው ።

ተስእሎ ፡ ፶፱ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፡ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ ጊዜ ፡ ይትመየጡ ፡ ሰይጣናት ፡ በስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ወትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወጊዜ ፡ ኢይትመየጡ ።
ሰይጣናት ፡ የጌታን ፡ ስም ፡ ስንጠራባቸው ፡ መስቀል ፡ ስናማትብባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ተነሥተው ፡ የሚመለሱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ተነሥተው ፡ የማይመለሱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፡ አሉት ።

ይኸም ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ክሰው ፡ ተለይተው ፡ ከበዓት ፡ ተከተው ፡ ብቻቸውን ፡ ይኖራሉ ፡ ሰይጣን ፡ አረጋዊ ፡ መስሎ ፡ መጥቶ ፡ እናንተ ፡ አረጋዊ ፡ አትጠይቁ ፡ ምነው ፡ አላቸው ፡ ባናውቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሉት ፡ ለእንግዲህ ፡ እንድትጠይቁኝ ፡ እንሂድና ፡ በዓቴን ፡ ላሳያችሁ ፡ ብሎ ፡ ይዝዋቸው ፡ ሄደ ፡ ከገደል ፡ አፋፍ ፡ ደረሱ ። ከገደሉ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሕር ፡ ነው ፤ በዓቴ ፡ ይህን ፡ አልፎ ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እስክንዘር ፡ ይመሽብናል ፡ በዚህ ፡ ተጭነን ፡ እንሂድ ፡ ብሎ ፡ በምትሐቱ ፡ ደመና ፡ ጠቅሶ ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ አንዱ ፡ ባሕታዊም ፡ ወጥቶ ፡ አብሮ ፡ ተቀመጠ ። አንደኛው ፡ ማማተብ ፡ ለምዶ ፡ ነበርና ፡ ሊወጣ ፡ ቢያማትብ ፡ ያን ፡ አብሮ ፡ የተሰፋነውን ፡ ጥሎት ፡ ሸሸ ፡ ተንቴሌቅሎጮ ፡ ወርዶ ፡ ከባ

ሕሩ ፡ ዳር ፡ ወደቀ ። በመዘሪያ ፡ ሂዶ ፡ አማትቦ ፡ ወንድሙን ፡ አንሥቶ ፡ ዕድሚያቸውን ፡ ሁሉ ፡ እያማተቡ ፡ የሚኖሩ ፡ ሁነዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ተመይጠቆሙስኬ ፡ በክመ ፡ ቀደመ ፡ ቃል ።
አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ተነሥተው ፡ መመለሳቸው ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ የጌታን ፡ ስም ፡ ቢጠሩባቸው ፤ መስቀል ፡ ቢያማትቡባቸው ፡ ነው ።

ወክዕኖቶሙሰ ፡ ዘኢይትመየጡ ፡ ጊዜያተ ፡ ወኢይፈርሁ ፡ እምስም ፡ ወኢ ፡ እምትእምርት ፡ ወኢ ፡ እምጸሎት ፡ አላ ፡ ይጸንሁ ።
አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የጌታን ፡ ስም ፡ ቢጠሩባቸው ፡ መስቀልም ፡ ቢያማትቡባቸው ፡ ጸሎትም ፡ ቢጸልዩባቸው ፡ ጸንተው ፡ ይዋጋሉ ፡ እንጂ ፡ የማይፈሩ ፤ ድል ፡ ተነሥተውም ፡ የማይመለሱ ፡ መሆናቸው ።

ወናሁ ፡ አኮ ፡ ኢይፈርሁሰ ፡ ባሕቲቱ ።
አለመፍራት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

አላ ፡ ይዘብጥዎሙኒ ፡ ለባሕታውያን ።
ባሕታውያንን ፡ ደፍረው ፡ ይመትዋቸዋል ፡ እንጂ ።

ወበእንተ ፡ ዝሰኩ ፡ እስመ ፡ ይከውን ።
እንዲህ ፡ መሆኑ ።

ዖበ ፡ ነሥኡ ፡ እምእግዚእነ ፡ ሥልጣነ ፡ በእንተ ፡ ረባሒሙ ።
ባሕታውያን ፡ ሊጠቀሙ ፡ ከጌታ ፡ ቢሰናበቱ ፡ ቢታዘዙ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ናሁ ፡ ኮነ ፡ ቅዱስ ፡ ጳኩሚስ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡ ምስለ ፡ አባ ፡ ታድራስ ፡ ሌሊተ ።
ይኸን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ጳኩሚስ ፡ ከታድራስ ፡ ጋራ ፡ ሁኖ ፡ ሌት ፡ ሲሄድ ።

ወተርእዩ ፡ ሎሙ ፡ ሰይጣናት ፡ ዘበመትህ ፡ መንክር ።
ሰይጣናት ፡ መሬቱን ፡ እንደ ፡ ሰፈድ ፡ ቅርቅብ ፡ ቅርቅብ ፡ እያደረጉ ፡ እያንቀረቀቡ ፡ በድንቅ ፡ ምትሐት ፤ አንድም ፡ በምትሐት ፡ ተአምራት ፡ ታዩዋቸው ።

ወኮኑ ፡ ይጺልዩ
ሁሉም ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ጸለዩ ።

ውእቱሰ ፡ ያስተርኢ ፡ ሎሙ ፡ ዘበድፍረት ።
ሰይጣን ፡ ግን ፡ ደፍሮ ፡ ታያቸው ፤ ተናገራቸው ።

ወይቤሎሙ ፡ ኢትጸምዉ ፡ ክንዳ ፡ ወኢትጸልዩ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ነሣእነ ፡ ሥልጣነ ፡ በእንተ ፡ አመክርትክሙ ።
በመከራ ፡ ልንፈትናችሁ ፡ ታዘን ፡ ተሰናብተን ፡ መጥተናልና ፤ በከንቱ ፡ አትድከሙ ፡ አትጸልዩ ፡ አላቸው ።

ወይደሉ ፡ ለነ ፡ ክመ ፡ ኢናብጥል ፡ ንሕነሰ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወኢ ፡ ሰምዮተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወጸሎት ።
ምንም ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ ቢል ፤ ሰይጣን ፡ ይህን ፡ አለ ፡ ብለን ፡ መስቀል ፡ ማማተባችንን ፤ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ መጥራታችንን ፤ ጸሎታችንን ፡ እንዳንተው ፡ መሆን ፡ ይገባናል ።

ዖበ ፡ ተርእዩ ፡ ለነ ፡ ሰይጣናት ።
ሰይጣናት ፡ በታዩበት ፡ ጊዜ ።

እመኒ ፡ ተመይጡ ፡ ዘበእንተ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚእነ ፡ ለነ ።
እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ረዳን ፡ ድል ፡ ተነሥተው ፡ ቢመለሱም ።

አው ፡ ተጉናደዩ ፡ በተፈንዎ ፡ እምእግዚእነ ፡ ስረባሕነ ።
እኛ ፡ ልንጠቀም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተሰናብተው ፡ ድል ፡ ሁነውም ፡ ባይመለሱ ፤ እንዳንተው ፡ መሆን ፡ ይደሉ ። አንድም ፡ ድል ፡ ተነሥተውም ፡ ቢመለሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ረዳን ፡ ነው ፤ መላልሰውም ፡ ቢዋጉን ፡ እኛ ፡ ልንጠቀም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ታዘዙ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፷ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ መለስቱ ፡ ሰይጣናት ፡ ዖኡ ፡ ኀበ ፡ ማር ፡ ወቅሪስ ፡ በአምላስ ፡ መለስቱ ፡ ቀዳውስት ።
ሰይጣናት ፡ ማኒን ፤ ንስጥሮስን ፤ አርዮስን ፡ መስለው ፡ ወደ ፡ ማር ፡ ወቅሪስ ፡ መጡ ። ከተማረው ፡ የተማረ ፤ ካልተማረው ፡ ያልተማረ ፡ ጨዋ ፡ መስለው ፡ ይሔዳሉና ።

ወተዋቀሱ ፡ ምስሌሁ ።
ማኒ ፡ ምትሐት ፡ ነው ፤ ንስጥሮስ ፡ ጎድረት ፡ ነው ፤ አርዮስ ፡ ፍጡር ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ተከራከሩት ።

መላእክትኒ ፡ ሖሩ ፡ በአምላስ ፡ ዓለማውያን ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ በዓታት ፡ በእንተ ፡ በዐለ ፡ አስፈፈዳት ፡ ወኖኅ ።
መላእክትም ፡ ዓለማውያን ፡ መስለው ፡ ስለ ፡ ባለ ፡ እንቅበ ፡ ስለ ፡ ባለ ፡ አሸዋው ፡ ከአበ ፡ ምኔቱ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ።

ወኮኑ ፡ ይሰግዱ ፡ ለመስቀል ፡ ወይኤምጎዖ ፡ ወይጺልዩ ።
እጅ ፡ ነሡ ፤ ጸለዩ ።

ቦኑ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ጥይቀ ፡ አው ፡ አልቦ ።
ይህ ፡ እንዲህ ፡ መሆኑ ፡ እውነት ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ አሉት ። እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ በዚያ ፡ በባለ ፡ አሸዋው ፡ ከገዳም ፡ ቅልሞሽ ፡ ሲጫወት ፡ የሚውል ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ለአበ ፡ ምኔቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ንኅሩበት ። ይህን ፡ በምቶ ፡ ሥርዓተ ፡ ማኅበር ፡ የም
ሠራ ፡ ነኝና ፡ ተሰብሰቡ ፡ ብሎ ፡ መነኰሳቱን ፡ ሁሉ ፡
ሰበሰባቸው ። ሥራት ፡ የሚሠሩ ፡ ፊት ፡ አስታዝተ
ው ፡ ነውና ፡ ለማስታኰት ፡ ሲነሡ ፡ መላእክትም ፡ ዓ
ለማውያንን ፡ መስለው ፡ ነጭ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሰ
ው ፡ ጉበተው ፡ ቆሙ ። ሲሰግዱ ፡ እየሰገዱ ፡ እጅ ፡
ሲነሡ ፡ እየነሡ ፡ አብረው ፡ አስታኰቱ ። ሲጨርሱ ፡
አበ ፡ ምኔቱ ፡ ሥራት ፡ ልንሠራ ፡ ነውና ፡ እንግዲህ ፡
እላንት ፡ ዓለማውያን ፡ ውጡልን ፤ የመነኰሳት ፡ ሥ
ራት ፡ በዓለማውያን ፡ ፊት ፡ አይሠራም ፡ አሳቸው ።
ከምንሆንስና ፡ ሥራ ፡ ማናቸው ፡ ይበልጣል ፡ አሉት ፤
የልቡና ፡ ሥራ ፡ ነዋ ፡ አላቸው ። እንግዲያስ ፡ በዚ
ህ ፡ ሰው ፡ አትፍረዱበት ፡ ብለዉት ፡ ተሠውረዋል
ና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ወመላእክትሰ ፡ ኮኑ ፡ ይሰግዱ ፡ ወይኤምኑ ፡ ወይ
ጸልዩ ፡ በርእሶሙ ።

መላእክትስ ፡ በውነት ፡ ይሰግዳሉ ፤ እጅ ፡ ይነሣሉ ፤
ይጸልያሉ ።

በከመ ፡ ይሰግዳ ፡ ወይኤምኃ ፡ ወይጸልዩ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ኅፍጹግን ፡
ምስለ ፡ ሥጋቲሆሙ ።

የፍጹግን ፡ ነፍሳት ፡ ከሥጋቸው ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ እ
ንዲሰግዱ ፡ እንዲጸልዩ ፡ መጠን ።

ሰይጣናሰ ፡ ኮኑ ፡ ይገብሩ ፡ ውእተ ፡ ዘበምትሓታቲሆሙ ፡ ሕሰውት ።

ሰይጣናት ፡ ግን ፡ ይህን ፡ መታየቱን ፡ በሐሰተኛ ፡ ም
ትሐት ፡ ያደርጉታል ።

እስመ ፡ አልቦሙ ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ አምሳለ ፡ ዘበአግን ፡
ዘእምጠባይዕ ፡ ዘከመ ፡ ይገብሩ ፡ መላእክት ።

ከነፋስ ፡ ግዘፍ ፡ ነሥተው ፡ እውነተኛ ፡ ምትሐት ፡ ያ
ደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ከሂል ፡ የላቸውምና ፤ አንድም ፡ መላ
እክት ፡ ከነፋስ ፡ ግዘፍ ፡ ነሥተው ፡ እውነተኛ ፡ ምት
ሐት ፡ እንዲያደርጉ ፤ እውነተኛ ፡ ምትሐት ፡ ማድረ
ግ ፡ አይቻላቸውምና ።

«ቅኔ ፤ ይቤሎ ፡ እጉ ፡ ለአረጋዊ ፤ አንሰ ፡ እጸ
ልየሙ ፡ ለእለ ፡ ያፈቅርዎ ፡ ለስብሐት ፡ ዕሩቅ ። ይ
ቤ ፡ አረጋዊ ፤ አንሰ ፡ አፈቅሮሙ ፤ እስመ ፡ ዝንቱ ፡
ያበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ፈጽሞ ፡ ሥምረተ ፡ እግዚአብሔር» ።

(ፎ) ይቤ ፡ አረጋዊ ፤ እስመ ፡ ይገብሩ ፡ ደቂቅኒ ፡ ቀዳሙ ፡ በእን
ተ ፡ ስብሐተ ፡ ስብእ ።

ወጣንያን ፡ ከተባሕትዎ ፡ አስቀድመው ፡ በማኅበር ፡
ሳሉ ፡ ሰው ፡ ያመስግኑን ፡ ብለው ፡ ትሩፋት ፡ ይሠራ
ሉ ።

ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ተሐዕሮ ፡ ጸጋ ፡ በክብረ ፡ ስብሐተ ፡ እምላ
ክ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጣን ፡ ጸጋ ፡ ክቡር ፡ ጌትነቱን ፡ ለማገ
ልገል ፡ ብለው ። አንድም ፡ ጌታን ፡ ለማክበር ፤ ለማ
መስገን ፡ ብለው ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ታደርጋቸዋለ
ች ።

ከመ ፡ ይድኀኑ ፡ በእሠ ፡ ብሂሎቶሙ ፡ ወበአፍቅሮቶሙ ፡ ባሕቲቱ ።

ለእሱ ፡ እሺ ፡ በጎ ፡ በማለት ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ በመው
ደድ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ።

ወይቤ ፡ ወቅፅበኒ ።

ወቅረበም ፡ ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፤ ም
ን ፡ አለ ፡ ብትል ።

ለእመ ፡ ተሞአ ፡ ረድእከ ፡ ሰርዮ ።

ረድእህ ፡ ድል ፡ ቢነግ ፡ ጸልይለት ።

ወለእመ ፡ ሞአ ፡ ሰብሖ ።

ድልም ፡ ቢነግ ፡ አመስግነው ።

እስመ ፡ ስብሖ ፡ ይዌስክ ፡ ለጽኑዕ ፡ ኃይለ ።

ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ለኃይለኛው ፡ ወጣኒ ፡ ኃይል ፡ ይጨ
ምርለታልና ፡ አለ ።

ተፈጸመ ፡ ዘበአሕጽሮ ፡ ኪያው ፡ ዘውስተ ፡ ክፍል ፡ ካዕብ ።

በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ አሳጥረው ፡ ያጠየቁት ፡ ነገር ፡
ደረሰ ፤ ተፈጸመ ።

ክፍል ፡ ሣልስ ።

ሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፴፩ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ይብል ፡ ተፋቅሮ ፡ ኢ
ወድቅ ፡ ግሙራ ።

ጳውሎስ ፡ ፍቅር ፡ አያዋርድም ፡ አለ ፤ ትች ።

ወናሁ ፡ ስብእ ፡ ተለዐሉ ፡ እስክነ ፡ ልዕልና ፡ አፍቅሮ ፡ እግዚአብሔር ፡
ካዕበ ፡ ወድቁ ።

እነሆ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከልዑል ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ደርሰው ፡ ዳግመኛ ፡ ወረዱ ፤ ትች ። እሱ ፡ አ

ይወርድም ፡ ሲል ፡ እኒያ ፡ የወረዱት ፡ እንደ ፡ ምን ፡
ነው ፤ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ አሉት ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ትዕቢቶሙ ፡ ኮነት ምክንያተ ፡ ድቀቶሙ ።

የመውረዳቸው ፡ ምክንያት ፡ የሆነባቸው ፡ ትዕቢታቸ
ው ፡ ነው ፡ አለ ፤ ቢታበዩ ነው ።

ይቤሉ ፤ ምንትኑ ፡ ይእቲ ፡ ትዕቢት ።

ትዕቢት ፡ ምንድር ፡ ናት ፡ አሉት ። እንዲህስ ፡ አይሉ
ም ፡ ብሎ ፤ ትዕቢት ፡ ያልኸው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡
ነው ፡ አሉት ።

ይቤ ፤ ለእመ ፡ የሐስብ ፡ ሰብእ ፡ ነፍሶ ፡ ኀጢአ ።

ሰው ፡ ራሱን ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ቢል ፡ ነው ፡ አለ ።

ወለእመ ፡ ውእቱ ፡ ኀለየ ፡ ከመ ፡ ትሩፍ ፡ እምኀጥኣን ።

ከኀጥኣን ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ ፍጹም ፡ ነኝ ፡ ቢል ፡ ነው ፡
አለ ።

ይቤሉ ፤ እፎኑ ፡ ይትከሀሎ ፡ ለጸድቅ ፡ ትሩፍ ፡ ከመ ፡ የሐስብ ፡ ርእሶ ፡
ኀጥአ ፡ ወሕጹጸ ፡ እምሕጹጻን ።

ፍጹሙ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ከኀጥኣን ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ ኀጥ
እ ፡ ነኝ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይቻለዋል ፡ አ
ሉት ።

ይቤ ፤ በብዙኀ ፡ ኅብፈት ።

ይኸስ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ወእምኔሃ ።

ከብዙውም ፡ አንዱ ።

ከመ ፡ ያእምር ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይክል ፡ ከመ ፡ ያፍቅር ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ በከመ ፡ አፍቀር ።

እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ወደደው ፡ ሰውም ፡
እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ አስተካክሎ ፡ ይወደ
ው ፡ ዘንድ ፡ እንዳይቻለው ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
አንድም ፡ ይወቅ ።

ወኢ ፡ ከመ ፡ ይተሐት ፡ በእንቲኣሁ ፡ በከመ ፡ ተትሕተ ፡ ውእቱ ፡ በእ
ንተ ፡ መድኃኒተ ፡ ስብእ ።

እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ለማዳን ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተ
ዋረደ ፤ ሰውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ከ
ሱ ፡ ተካክሎ ፡ ይዋረድ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይቻለው ፡ ያ
ውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድም ፡ ይወቅ ።

ወኢ ፡ ከመ ፡ ይተሐት ፡ ሎቱ ።

እንደ ፡ እሱ ፡ ሁኖ ፡ የትሕትና ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ዘን
ድ ።

ወያፍቅር ፡ ከመ ፡ ነቢያቲሁ ፡ ወቅዱሳኒሁ ።

ስንኳን ፡ እንደ ፡ እሱ ፤ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡
ወደዱት ፡ አድርጎ ፤ ከነዚያ ፡ አስተካክሎ ፡ ይወደው ፡

ዘንድ ፡ እንዳይቻለው ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድ
ም ፡ ይወቅ ።

ወኢ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ኦሆ ፡ ብሂሎቶ ፡ ወሥምረቶ ።

እሺ ፡ በጎ ፡ ብሎ ፡ ፈቃዱን ፡ መፈጸም ፡ እንዳይቻለ
ው ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድም ፡ ይወቅ ።

ጽሑፍ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ አፍቀሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ። (ዮሐ
ፎ ፡ ፲፯) ።

እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ወደደው ፡ ተ
ጽፍል ።

እስክ ፡ መጠወ ፡ ወልደ ፡ ፍቁረ ፡ ለሞት ፡ በእንተ ፡ መድኃኒቶሙ ።

ልጁን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ ሰጠለት ፡ ተነግሯ
ል ። አንድም ፡ ወዶታልና ፤ ከመ ፡ አፍቀሮ ። ሰጥቶ
ለታልና ፤ ከመ ፡ ይተሐት ።

ወልድኒ ፡ ዋሕድ ፡ ሐመ ፡ ወመጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ለተሰቅሎ ፡ ወለሞት ፡
በእንቲኣሆሙ ።

ወልድም ፡ ለሰው ፡ ብሎ ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፤
ራሱን ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡
ተነግሯል ። አንድም ፡ መከራ ፡ ተቀብሏልና ፡ ከመ ፡
ተትሕተ ።

ወመንፈስ ፡ ቅዱስኒ ፡ ይጼልል ፡ ዲቤሆሙ ፡ ከመ ፡ ያፍ ፡ ላዕለ ፡ አፍ
ርኅቲሃ ፡ ወከመ ፡ ወላዲት ፡ ላዕለ ፡ ደቂቃ ። (ዘፍጽ ፡ ፪) ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያፍ ፡ ጫጩቶቿን ፤ እናት ፡ ልጆ
ቿን ፡ እንድትጠብቅ ፤ ምእመናንን ፡ እንዲጠብቃቸ
ው ፡ ተጽፏል ። አንድም ፡ ይጠብቃቸዋልና ፤ ከመ ፡
ተትሕተ ።

ወተጽሕፈ ፡ ካዕበ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ተመሀሩ ፡ እምኔየ ፡ እስ
መ ፡ አነ ፡ የዋህ ፡ ወትሑት ፡ ልብየ ። (ማቴ፲፩ ፡ ፳፱) ።

ዳግመኛም ፡ ጌታ ፡ እንዲህ ፡ እንዳለ ፡ ተጽፏል ።

ወእምኔሃ ።

ከነዚህም ፡ አንዱ ።

ከመ ፡ የሐሊ ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ ወከመ ፡ ይነ ኑ ፡ እልክቱ ፡ እለ ፡ ይትሐ
ዘብ ፡ ኄከመ ፡ ጎዮአን ፡ እሙንቱ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ንጹሓን ፡ እምኔ
ሁ ፡ በእንተ ፡ ትሕትናሁ ።

ጎጥኣን ፡ የሚላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ትሕትና ፡ ከሱ ፡
ይልቅ ፡ ንጹሓን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ያስብ ፡ ዘንድ ፡ እን
ዲገበው ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድም ፡ ይወቅ ።

ወዘሰኪ ፡ ይሬኢ ፡ ነፍሶ ፡ ከመ ፡ ፍጹም ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘበበይነ ፡ መ
ንፈቀ ፡ ትሩፋት ።

ጥቂት ፡ ትሩፋት ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ከነዚያ ፡ አበልጣለሁ ፡
ፍጹም ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ግን ፤ መንፈቅ ፡ አለ ፤
እንደ ፡ በዓለ ፡ መክሊት ፤ እሱሌታው ፡ የጌታ ፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ና ። አንድም ፡ የርድና ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ። አንድም ፡ ትሩፋት ፡ ሥጋ ፡ ሠርቶ ፡ ትሩፋት ፡ ነፍስ ፡ አልሠራምና ።

ውእቱሰ ፡ ኢየአምር ፡ ክመ ፡ ውእቱ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ዘጸውዖ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኀበ ፡ ምሳሕ ።

ይህ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ጌታን ፡ ወደ ፡ ምሳ ፡ እንደ ፡ ጸራው ።

ወይቤ ፡ በነፍሱ ፡ ለእመ ፡ ነቢይ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ እምኢያእመራ ፡ ክመ ፡ ኀጥእት ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ፡ ብእስት ። (ሉቃ፯ ፡ ፴፱) ።

በልቡናው ፡ ነቢይማ ፡ ከሆነ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ እግሩን ፡ ስታጽበው ፡ ሰውነቱን ፡ ስትዳስሰው ፡ ስትስመው ፡ ዘማ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ባላወቀም ፡ ነበርን ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተጠራጠረ ፡ እንደ ፡ ፈሪሳዊ ፡ እንደ ፡ ስምዖን ፡ ዘለምጽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላወቀም ።

ወእግዚእነሰ ፡ ግእምረ ፡ ሀሎ ።

ሁሉን ፡ የሚያውቅ ፡ ጌታ ፡ ግን ።

በዘሉ ፡ ጊዜያት ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ አውቆ ፡ መተው ፡ አለና ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚያውቅ ፡ አለ ።

ርእያ ፡ ክመ ፡ ንጽሕት ፡ ይእቲ ።

ንጽሕት ፡ እኁደ ፡ ሆነች ፡ አወቀና ።

ወይቤላ ፡ ጎጣውኢሃ ፡ ብዙኃት ፡ ጎድጓት ፡ ላቲ ።

ተጎድግ ፡ ለኪ ፡ ኀጢአትኪ ፡ አላት ።

እስመ ፡ ይእቲ ፡ እፍቀሪተኒ ፡ ብዙኃ ።

አንተ ፡ እጅ ፡ እንኳ ፡ አልነሣኸኝ ፤ እሷ ፡ ከገባሁ ፡ ጀምራ ፡ እግሬን ፡ ለመሳም ፡ አላቋረጠችም ። አንተ ፡ ዘይት ፡ እንኳ ፡ አልቀባኸኝ ፤ እሷ ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ የተገዛ ፡ ሽቱ ፡ ቀባችኝ ፤ ካንተ ፡ ይልቅ ፡ ወዳኛለችና ፡ ብሎ ፡ ተጎድገ ፡ ለኪ ፡ አላት ።

ወክሣሁ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ካልእኒ ፡ ጸላዪ ፡ ዘሐሳበ ፡ ነፍሱ ፡ ክመ ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ እምካልእ ፡ ጸላዪ ፡ ዘውእቱ ፡ መጸብሓዊ ።

ከመጸብሓዊ ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ለማለት ፡ ዘኢረሰይኪኒ ፡ ክመ ፡ ዝንቱ ፡ መጸብሐዊ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ሌላውም ፡ ፈሪሳዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላወቀም ።

ወይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ክመ ፡ ንጹሕ ፡ እምኔሁ ፡ መጸብሓዊ ። (ሉቃ፲፰ ፡ ፲-፲፬) ።

ጌታ ፡ ሳን ፤ አተወ ፡ ዝንቱ ፡ እንዘ ፡ ይጼደቅ ፡ እምዝ ፡ ክቱ ፡ ብሎ ፡ መጸብሓዊ ፡ እንዲበልጠው ፡ ተናገረ ።

ወእመኒሃመ ፡ ይደሉ ፡ ክመ ፡ የሐሊ ፡ ዘይትሐዘብ ፡ ክመ ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ወትፋፍ ፡ ክመ ፡ ይፈልስ ፡ ግብሩ ፡ ኀበ ፡ ካልኣ ፡ እምዘንበረ ፡ ውስቴቱ ።

ከዚህም ፡ ፍጹም ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ሰው ። አንድም ፡ ፍጹም ፡ ነው ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡ ካለበት ፡ ከበጎው ፡ ወደክፉ ፡ እንዲለወጥ ፤ ይፍልስ ፡ ቢል ፤ ይለወጥ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ያስብ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ቦ ፡ ነው ፤ ቦ ፡ ይወቅ ። አንድም ፡ ከመ ፡ ንጹሓን ፡ ወትሩፋን ፡ ይላል ፤ ፍጹማን ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ። አንድም ፡ ፍጹማን ፡ ናቸው ፡ የሚላቸው ፡ ሰዎች ፡ ይፍልስ ፡ ግብሮ ፤ ሥራቸው ፡ ካለበት ፡ ከበጎው ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ይለወጥ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፤ ይፈልስ ፡ ቢል ፤ እንዲለወጥ ፡ ያስብ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። አንድም ፡ ነው ። አንድም ፡ ይወቅ ።

ክመ ፡ ግብረ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፤ ወግብረ ፡ ፈያታዊ ፡ ዘየማን ።

የይሁዳ ፡ ግብር ፡ ወደ ፡ ክፉ ፤ የፈያታይ ፡ ዘየማን ፡ ግብር ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ እንደ ፡ ተለወጠ ።

እመሰ ፡ ኮንክ ፡ ንጹሐ ።

ንጹሕም ፡ ብትሆን ።

ወመፍቀሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጠቢባ ።

ጌታን ፡ የምትወድ ፡ ብልሕ ፡ አዋቂ ፡ ብትሆን ።

ወፍቁረ ፡ እምኔሁ

ጌታ ፡ የሚወድህ ፡ ብትሆን ።

ተዘክር ፡ እንክ ፡ ለገዝኩ ፡ እጉ ፡ ሰሊማን ።

ያን ፡ ሰው ፡ ሰሊማንን ፡ አስበው ።

ዘነበረ ፡ ክመገ ፡ በደቂቁ ።

በወጣኒነቱ ፡ አዋቂ ፡ የነበረ ።

ወኮነ ፡ በልህቅናሁ ፡ አብደ ፡ ወመፍቅሬ ፡ ፍትወት ።

ኋላ ፡ ግን ፡ አላዋቂ ፡ የሆነ ፡ አለ ፤ ሰሊማን ፡ ያልታወቀ ፡ መነኩሴ ። አንድም ፡ ሰሎሞን ፡ ነው ፤ ሰሎሞንን ፡ አስበው ፤ በሕፃንነቱ ፡ አዋቂ ፡ እንደነበረ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ አላዋቂ ፡ ዘማዊ ፡ እንደሆነ ። ወሰሎሞንኒ ፡ ክነ ፡ መፍቀሬ ፡ አንስት ፤ ዕበድከ ፡ አደንገፀኒ ፡ ይላል ። (፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ። ሲራ፵፯) ።

ወለእመ ፡ ኮንክ ፡ ነቢየ ።

ነቢይም ፡ ብትሆን ።

ተዘክር ፡ እፎ ፡ ድኅፀ ፡ ገዝኩ ፡ ነቢይ ።

ያ ፡ ነቢይ ፡ እንደምንም ፡ እንደተዋረደ ።

ወኅለወ ፡ አመ ፡ አስሐቆ ፡ ወአብልዖ ፡ ኀብስተ ፡ ገዝኩ ፡ ሐሳዊ ፡ ነቢይ ። (ጸነገ ፡ ፲፫ ፡ ፩-፳፪) ።

ያ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ አታሎ ፡ ኅብስት ፡ ባበላው ፡ ጊዜ ፡ የጌታውን ፡ ሕግ ፡ እንዳፈረሰ ፡ አስበው ።

ወለበሮ ፡ ጽጋበ ።

ጽጋው ፡ ሰበረው ፡ አለ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ መና ገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰበረውስ ፡ አንበሳ ፡ ነው ። አንድም ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መሰልቸት ፡ አጠፋው ። እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ነቢዩ ፡ ኢዮሄል ፡ ይባላል ፤ ሰማርያ ፡ ሂደህ ፡ ደግ ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሣል ፡ ጣዖቱን ፡ ይሰብራል ፤ ነቢያተ ፡ ሐሰትንም ፡ ያሉትን ፡ ያጠፋል ፤ የሞቱትንም ፡ አጽማቸውን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላል ። ለዚህ ፡ ምልክት ፡ ይነቅዕ ፡ ምሥዋዑ ፡ ወይትከሥው ፡ ስብሐ ፤ ምሥዋዓ ፡ ብርቱ ፡ ይገመሳል ፡ ስቡ ፡ ይፈሳል ፡ ብለህ ፡ ይህን ፡ ነግረህ ፡ ተመለስ ፤ እህል ፡ ወህ ፡ አትቅመስ ፡ አለው ፤ አህያውን ፡ ጭኖ ፡ ሄዶ ፤ አሥራኤል ፡ ተሰብስበው ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ መሥዋዕት ፡ ሲሠዉ ፡ አገኛቸው ። እንደ ፡ ተላከ ፡ አድርጎ ፡ ነገራቸው ፤ ለዚህ ፡ ምልክት ፡ ይንቃዕ ፡ ምሥዋዓ ፡ ብርቱ ፡ ይቀደድ ፡ ስቡ ፡ ይፍሰስ ፡ አለ ፤ ስቡ ፡ ፈሰሰ ፤ ንጉሡ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ነው ፡ አጎዝሃ ፡ አለ ፤ ስቡን ፡ እንዳይፈስ ። አንድም ፡ ነቢዩን ፡ ያዙት ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ ቢዘረጋ ፡ እጁ ፡ እንደጓጨት ፡ ደረቀ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ጸልዮ ፡ አድኖታል ። ነቢዩም ፡ ንጉሡን ፡ ምሮ ፡ ትንቢቱን ፡ ተናግሮ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደይሁዳ ፡ ተመለሰ ። አንድ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ በርግና ፡ ምክንያት ፡ ልጆቹን ፡ ሰዶ ፡ ከበዓል ፡ ሳይሄድ ፡ ውሎ ፡ ነበር ። ልጆቹ ፡ የዛሬ ፡ በዓል ፡ እንደምን ፡ ዋለ ፡ አላቸው ፤ በዓሉስ ፡ ደግ ፡ በዓል ፡ ውሎ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ የይሁዳ ፡ ነቢይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ አሉት ። ምነዋ ፡ ይዛችሁት ፡ በመጣችሁ ፡ አላቸው ፤ አሁን ፡ በዚህ ፡ አለፈልህ ፡ አሉት ። አህያውን ፡ ጭኖ ፡ ቢሄድ ፡ እሱም ፡ ደክሞት ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ አርፎ ፡ አገኘው ፤ ተነሣ ፡ ና ፡ እህል ፡ ቀምሰህ ፡ ትሄዳለህ ፡ አለው ፤ አልታዘዝሁም ፡ አለ ፤ ምነው ፡ ነቢዩ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህን ፡ እኔንም ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ እህል ፡ አቅምሰው ፡ ብሎኝ ፡ ነው ፡ የመጣሁ ፡ አለው ፤ እውነት ፡ መስሎት ፡ ተታሎ ፡ ሄደ ። ምግብ ፡ አቅርቦለት ፡ ሲበላ ፡ ለነቢየ ፡ ሐሰቱም ፡ ቢሉ ፡ ለሱም ፡ ቢሉ ፡ ሞቱ ፡ ተገለጸለት ፤ ወዲያው ፡ የማይቀር ፡ ነውና ፡ ተነሥቶ ፡ ሲሄድ ፡ አንበሳ ፡ ሰብሮት ፡ ሞተ ፤ ያን ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ አንበሳ ፡ ሰበረው ፡ በለው ፡ ነገሩት ፤ ቢሄድ ፡ አንበሳው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አህያው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ቁሞ ፡ እሱ ፡ ከመከከል ፡ ወድቆ ፡ አገኘው ፤ ወስዶ ፡ ከበታው ፡ ቀበረው ። ልጆቹን ፡ እኔንም ፡ ስሞት ፡ ከዚህ ፡ ቀበሩኝ ፡ አላቸው ፤ ቀበሩት ። ከሮጀ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ኢዮስያስ ፡ ነግሦ ፡ ጣዖቱን ፡ እየሰበረ ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰትንም ፡ ያሉትን ፡ እያጠፋ ፡ የሞቱትንም ፡ ዓጽማቸውን ፡ እያቃጠለ ፡ ከዚያ ፡ ደረሰ ፤ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አለ ፡ የነቢየ ፡ ሐሰት ፡ መቃብር ፡ ነው ፡ አሉት ፡ አውጥታችሁ ፡ አቃጥሉ ፡ አለ ፤ ነቢየ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ተደርበበታል ፡ አሉት ፡ እንኪያስ ፡ ተዉት ፡ ብሏቸው ፡ ትተውታል ። አጽመ ፡ ነቢየ ፡ ቤቴል ፡ ድኅነት ፡ ምስለ ፡ አጽመ ፡ ባዕድ ፤ እንዘ ፡ ነፍሱ ፡ ትውኒ ፡ በነድ ፤ እንዳለ ፡ ባለ ቅኔ ።

ለእመ ፡ ኮንክ ፡ ሐዋርያኒ ።

ሐዋርያም ፡ ብትሆን ።

ወታወዕእ ፡ ሰይጣናተ ።

ጋኔን ፡ ብታወጣ ።

ወትገብር ፡ ተአምራተ ።

ታምራት ፡ ብታደርግ ።

ተዘክር ፡ እፎ ፡ ወድቀ ፡ ይሁዳ ፡ ውስተ ፡ እፍቅር ፡ ብሩር ፡ እምድኅረ ፡ ውእቱ ።

ይሁዳ ፡ ሐዋርያ ፡ ከተባለ ፡ ጋኔን ፡ ካወጣ ፡ በኋላ ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ እንደተሰነካከለ ፡ አስብ ። አንድም ፡ ወደታች ።

እስክ ፡ ተሰምየ ፡ ሰይጣን ፡ ወወልደ ፡ ኃጕል ።

ሐዋርያ ፡ ከተባለ ፡ በኋላ ፡ ሰይጣን ፡ ወልደ ፡ ኃጕል ፡ እስክ ፡ መባል ፡ ደርሶ ፡ እንደተሰነካከለ ፡ አስብ ።

ወለእመ ፡ ርኢክ ፡ ፈያቂ ፡ አው ፡ ቀታሌ ።

ወንበደ ፡ ብታይ ፤ ነፍስ ፡ ገዳይም ፡ ብታይ ።

በል ፡ በአይቱ ፡ አአምር ፡ ለእመ ፡ ኮን ፡ ይበድረኒ ፡ በዊአ ፡ ኀበ ፡ ገኔት ፡ ክመ ፡ ፈያታዊ ፡ ዘየማን ።

አዳምን ፡ ቀድሞት ፡ እንደገባ ፡ ቀድሞኝ ፡ ገኔት ፡ ይባ ፡ እንደሆነ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ ፡ በል ፡ ዛሬ ። አንድም ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ንስሐ ፡ ገብቶ ።

ወለእመ ፡ ርኢክ ፡ ዘማዌ ፡ ወኃጥአ ።

ዘማዊ ፡ ብታይ ፤ ኃጥአም ፡ ብታይ ።

በል ፡ በአይቱ ፡ አአምር ፡ ለእመ ፡ ኮን ፡ ለዝንቱ ፡ ሀለዎ ፡ ያፍቅሮ ፡ ለክርስቶስ ።

ክርስቶስን ፡ ይወደው ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ።

ወይብኪ ፡ በእንተ ፡ ኃጣውኢሁ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ።

ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ያዝን ፡ ያለቅስ ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ ፡ በል ፡ ዛሬ ። አንድም ፡ ኋላ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ንስሐ ፣ ገብቶ ።
ወዘይኄሊኬ ፣ ከመዝ ፣ ለዓለም ፣ ኢይወድት ፣ እምፍቅረ ፣ እግዚእነ ።
ሁለጊዜ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ አሳብ ፣ የሚያስብ ፣ ሰው ፣ ከፍቅረ ፣ እግዚአብሔር ፣ ተለይቶ ፣ አይወርድም ።
እመሰ ፣ ጸን ፣ ኀበ ፣ ትዝኅርት ፣ ይወድት ፣ እመልዕልት ።
ወደ ፣ ትዕቢት ፣ ቢሳብ ፣ ግን ፣ ከማዕርጉ ፣ ይወርዳል ።
ወይቤ ፣ አረጋዊ ።
አረጋዊም ፣ እንዲህ ፣ አለ ።
ወማዕዜ ፣ ያመፅ ፣ ብሑት ፣ ትሕትና ፣ ፍጹመ ።
ባሕታዊ ፣ ፍጹም ፣ ትሕትናን ፣ የሚያገኝ ፣ መቼ ፣ ነው ፣ ቢሉ ።
ወውእቱ ፣ ያነዲ ፣ ነፍሶ ፣ በኵሉ ፣ ጊዜ ።
ትሩፋት ፣ የለኝም ፣ ኃጥእ ፣ ነኝ ፣ ባለ ፣ ጊዜ ፣ ነው ።
አንድም ፣ ፍጹም ፣ ትሕትናን ፣ የሚያገኝ ፣ ባሕታዊ ፣ እንደምን ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ቢሉ ፤ ትሩፋት ፣ የለኝም ፣ ኃጥእ ፣ ነኝ ፣ የሚል ፣ ነው ።
ወውስተኒ ፣ ኵሉ ፣ ገብር ፣ ይቤዋል ፣ እምኔሁ ፣ ተቃትሎ ።
እንዲህ ፣ የሚል ፣ ሰው ፣ በሥራው ፣ ሁሉ ፣ ጦር ፣ ይጠፋለታል ።
ወለእመኒ ፣ ኮነ ፣ በቀዳሚው ፣ ለጸብእ ፣ አው ፣ በውስተ ፣ ማዕከሉ ፤ አው ፣ በውስተ ፣ ተፍጻሜቱ ።
ጦር ፣ በመጀመሪያውም ፣ ቢሆን ፤ በመካከሉም ፣ በመጨረሻውም ፣ ቢሆን ።
በከመ ፣ ይቤ ፣ ማርቆስ ፣ ዘየዓቢ ።
ማርቆስ ፣ ዘየዓቢ ፣ እንደ ፣ ተናገረ ፤ ዘይንዕስ ፣ አለና ፣ ዘየዓቢ ፣ አለ ።
ወናሁ ፣ ይቤ ፣ አባ ፣ ሲሶይኢ ።
አባ ፣ ሲሶይም ፣ እንዲህ ፣ አለ ።
ለእመ ፣ መጽአ ፣ ብሑት ፣ ኀበ ፣ ትሕትና ፣ በጽሐ ፣ ኀበ ፣ ፍጹም ።
መነኮሴ ፣ ፈጽሞ ፣ ትሑት ፣ ቢሆን ፣ ከፍጹምነት ፣ ደረሰ ፣ በለው ።
ወይቤ ፣ ሥርዓተ ፣ ባሕታውያን ።
መጽሐፈ ፣ ገነትም ፣ እንዲህ ፣ አለ ። አንድም ፤ ወይቤ ፣ መተርጕም ፣ ሥርዓተ ፣ ባሕታውያን ። የባሕታውያን ፣ ሥራት ፣ እንዲህ ፣ ነው ።
ይደክሙ ፣ እሙንቱ ፣ በቀዳሚው ፣ በምግባራት ፣ ሥጋውያት ፣ በእንተ ፣ ጸብእ ፣ ሕሊናት ፣ ወበእንተ ፣ መዊአቶን ፣ ለሕሊናት ።
ባሕታውያን ፣ አስቀድመው ፣ የሕሊናን ፣ ጾር ፣ ለማጥፋት ፣ በትሩፋት ፣ ሥጋ ፣ ይደክማሉ ።
ወእምድኅረ ፣ ውእቱ ፣ ያጠርዩ ፣ ንጽሐ ፣ ልብ ።
ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ንጽሐ ፣ ልቡና ፣ ይሰጣቸዋል ።
ወእምድኅረ ፣ ውእቱኒ ፣ ይፌእዩ ፣ ብርሃን ፣ ልቡናሆሙ ።
ከንጽሐ ፣ ልቡና ፣ ደርሰው ፣ የልቡናቸውን ፣ ጽርየት ፣ ያያሉ ።
ወእምድኅረዝሙ ፣ ይፌእዩ ፣ በብርሃና ፣ ብርሃና ፣ ለክርስቶስ ፣ በፌእዩ ፣ መንፈስ ።
በጽርየተ ፣ ልቡና ፣ ሁነው ፣ ጌታ ፣ የሚሰጣቸውን ፣ የጸጋ ፣ ብርሃን ፣ በዓይነ ፣ ነፍስ ፣ ያያሉ ። አንድም ፣ ማሸጋሸግ ፣ ነው ፤ ከዚያ ፣ በኋላ ፣ የልቡና ፣ ጽርየት ፣ ይሰጣቸዋል ፤ በጽርየት ፣ የጸጋውን ፣ ብርሃን ፣ ያያሉ ፤ በጸጋው ፣ ብርሃን ፣ የጌታን ፣ ያካሉን ፣ ብርሃንነት ፣ በልቡናቸው ፣ ተገልጸ ፣ ያዩታል ።
ወናሁ ፣ ያስተርኢ ፣ ዝንቱ ፣ ብርሃናዌ ፣ ለሰብእ ፣ እምቅድመ ፣ ይፃእ ፣ እምዝንቱ ፣ ዓለም ።
የጸጋው ፣ ብርሃን ፣ ለብዙ ፣ ሰዎች ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ ሳይወጡ ፣ ይገለጽላቸዋል ።
ወይክውን ፣ ሎሙ ፣ መርሐ ፣ ለወጺእ ፣ እምዓለም ፣ ኀበ ፣ ምኔት ።
ከዓለም ፣ ወጥቶ ፣ ወደገዳም ፣ ለመሄድ ።
ወእምኔት ፣ ለተባሕትዎ ።
ከገዳም ፣ ወጥቶ ፣ ተባሕትዎ ፣ ለመያዝ ፣ መሪ ፣ ይሆናቸዋል ፤ እንደነ ፣ አብርሃም ፣ ላሉት ።
ቅድመሰ ፣ በእንተ ፣ ሕሊናት ።
አስቀድሞ ፣ ከዓለም ፣ ወደ ፣ ገዳም ፣ መሄድ ፣ የሕሊናን ፣ ያር ፣ ለመዋጋት ፣ ነው ።
ወእምድኅረኒ ፣ መዊኦቶን ፣ ለሕሊናት ፣ እኩያት ።
የሕሊናን ፣ ያር ፣ ድል ፣ ከነሡ ፣ በኋላ ፣ ከማኅበር ፣ ወጥቶ ፣ ተባሕትዎ ፣ መያዝ ።
በእንተ ፣ ሬእይ ፣ ዘያስተርኢ ፣ ዘበፍርሃት ፣ ካዕበኒ ፣ በዘቢጥ ።
አጋንንት ፣ እያስፈራሩ ፣ እየተማቱ ፣ ተያይተው ፣ የሚዋጉትን ፣ ያር ፣ ለማጥፋት ፣ ነው ።
ወናሁ ፣ ይትቃተልዎሙ ፣ ሰይጣናት ፣ ለመንፈቀ ፣ ባሕታውያን ፣ ቀዳሚ ፣ በአፍርሆ ፣ ወካዕበ ፣ በዘቢጥ ።
እኵሴቶቹን ፣ ባሕታውያን ፣ አስቀድመው ፣ በማስፈራት ፣ በመማታት ፣ ይዋጓቸዋል ።
ዝንቱሰ ፣ ይክውን ፣ ለዘንበረ ፣ እንዘ ፣ ያንዕሱ ፣ ውስተ ፣ ዓለም ፣ ውስተ ፣ እክያት ፣ ብዙኃት ።
ይኸም ፣ የሚደረገው ፣ በዓለም ፣ ሳለ ፣ ክፉ ፣ ሥራ ፣ ሲሠራ ፣ ለነበረ ፣ ነው ።
ከመ ፣ አባ ፣ ሙሴ ፣ ጸሊም ፣ ወደፈሩ ፣ ላዕሌሁ ፣ ሰይጣናት ፣ ወተቃተልዎ ፣ ገሃደ ፣ ዘበአፍርሆ ፣ ወዘቢጥ ።
ሰይጣናት ፣ ተገልጸው ፣ እያስፈራሩ ፣ እየተማቱ ፣ እንደ ፣ ተዋጉት ፣ እንደ ፣ ሙሴ ፣ ጸሊም ። አንድም ፣ የተዋጉት ።
በእንተ ፣ ክልኤ ፣ ግብር ።
ስለ ፣ ሁለት ፣ ነገር ፣ ነው ።
አሐዱ ፣ እምኔሆሙ ፣ እስመ ፣ ውእቱ ፣ ኦነ ፣ ዘኢየአምር ፣ ጸብአ ፣ ሕሊናት ፣ በቀዳሚሁ ።
አንዱ ፣ በመጀመሪያው ፣ የሕሊና ፣ ያር ፣ የማያውቅ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ነው ።
ወክልኤ ፣ በእንተ ፣ ሰበሰ ፣ እግዚአብሔር ፣ እምኔሁ ።
ሁለተኛው ፣ ረድኤተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ስለ ፣ ተለየው ፣ ነው ።
ወዘቲሰ ፣ ታስተርኢ ፣ አምጣነ ፣ ኃይሉ ፣ ወትዕግሥቱ ፣ ወተጋድሎቱ ።
እንዲህ ፣ ያለ ፣ ያር ፣ መምጣቱ ፤ የሥራው ፤ የትዕግሥቱ ፤ የትሩፋቱ ፣ መጠን ፣ ይታወቅ ፣ ዘንድ ፣ ነው ።
አንድም ፣ እንዲህ ፣ አድርጎ ፣ መዋጋቱ ፤ ያርኢ ፤ የሥራውን ፤ የትዕግሥቱን ፤ የትሩፋቱን ፣ ደግነት ፣ ያስረዳል ።

ተስእሎ ፣ ፴፱ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ ምንትኑ ፣ ትርጓሜሁ ፣ ለቃለ ፣ አባ ፣ እብሎ ።
አባ ፣ ዕብሎ ፣ የተናገረው ፣ ነገር ፣ ትርጓሜው ፣ እንደምን ፣ ነው ።
እምከመ ፣ ተቀጥቀጠ ፣ ርእሱ ፣ ለክይሲ ፣ ኮኑ ፣ ሥጋሁ ፣ ይክውን ፣ ምውተ ።
እባብ ፣ ራሱን ፣ ከተመታ ፣ መላ ፣ አካሉ ፣ ይሞታል ፣ ያለው ፣ ትርጓሜው ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ነው ።
ይቤ ፣ መተርጕም ፤ ይኤምር ፣ ርእሶ ፣ ለክይሲ ፣ ሕሊና ፣ ቀዳሚት ፣ እንተ ፣ ያክውስዋ ፣ ሰይጣናት ፣ ውስተ ፣ ልበ ፣ ብሑት ፣ በእንተ ፣ አይኑ ፣ ዘኮነት ፣ ጎጢአት ።
ርእስ ፣ ያላት ፣ ስለ ፣ ማናቸውም ፣ ጎጢአት ፣ የምትታሰብ ፣ አጋንንት ፣ በመነኮሴው ፣ ልቡና ፣ የሚያሳስቢት ፣ ነቅዐ ፣ ሐልዮ ፣ ናት ።
ወይፈክር ፣ ሥጋሁኒ ፣ ሕሊናት ፣ ብዙኃት ፣ እንተ ፣ መነኰስ ፣ ብሑት ።
ሥጋ ፣ ያለውም ፣ ከዚያ ፣ በኋላ ፣ መነኰሴ ፣ የሚያስበው ፣ ክፉ ፣ ክፉ ፣ ሕሊና ፣ ነው ።
ዘሰ ፣ ይቀትላ ፣ ለይእቲ ፣ ስእለት ፣ ቀዳሚት ፣ እንተ ፣ ተህውክት ፣ ላዕሌሁ ፣ ምግባረ ፣ ጎጢአት ።
ክገቢረ ፣ ጎጢአት ፣ ለማድረስ ፣ መጀመሪያ ፣ የታሰበችውን ፣ ነቅዐ ፣ ሐልዮ ፣ ድል ፣ የነሣ ።

ይመውት ፣ እምኔሁ ፣ ዘይትወለድ ፣ እምድኅረሃኒ ።
ከሷ ፣ በኋላ ፣ የሚመጣው ፣ ያር ፣ ይጠፋለታል ።

ተስእሎ ፣ ፵፫ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ በእንተ ፣ ምንትኑ ፣ ጎሠሠ ፣ ዝኩ ፣ እኁኑ ፣ እምአባ ፣ ጵላ ፣ ከመ ፣ ይጸሊ ፣ በእንቲኣሁ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ከመ ፣ የሀቦ ፣ ጸጋ ።
ያ ፣ መነኰሴ ፣ አባ ፣ ጵላን ፣ ጸልየህ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ጸጋ ፣ አሰጠኝ ፣ ብሎ ፣ የለመነው ።
ወሶበ ፣ ጸለየ ፣ በእንቲኣሁ ፣ ተውህቦ ፣ ሀብተ ፣ ትሕትና ፣ ወንድየት ፣ ወአፍቅሮት ።
ቢጸልይለት ፣ ያልለመነው ፣ የፍቅር ፣ የትሕትና ፣ ትሩፋት ፣ የለኝም ፣ የማለት ፣ ሀብት ፣ የተሰጠው ፣ ምን ድር ፣ ነው ።
ይቤ ፣ መተርጕም ፤ እስመ ፣ ውእቱ ፣ እኁ ፣ አቅደመ ፣ ገድላተ ፣ ብዙኃተ ፣ በእንተ ፣ ትሩፋት ።
ያ ፣ ሰው ፣ አስቀድሞ ፣ ትሩፋት ፣ ለመሥራት ፣ ብሎ ፣ ብዙ ፣ መከራ ፣ ተቀብሎ ፣ ነበርና ።
ወኢፈቀደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ከመ ፣ የሀሣሃ ፣ ሱቱ ፣ እንበለ ፣ ይኅሥሥ ፣ እምእግዚአብሔር ፣ ውሂቦተ ፣ ትሕትና ፣ እንከ ።
ጌታም ፣ ትሕትናን ፣ ስጠኝ ፣ ሳይለው ።
ወይእኤል ፣ በእንቲኣሃ ።
ትሕትናን ፣ ሳይለምነው ፣ ሌላ ፣ ጸጋ ፣ ሊሰጠው ፣ አልወደደምና ።
ወበእንተ ፣ ውእቱኬ ።
ትሕትና ፣ የሚገባ ፣ ስለ ፣ ሆነ ።
ፈቀደ ፣ እግዚእነ ፣ ከመ ፣ ይዕርጉ ፣ አኃው ፣ ኀበ ፣ ፍጹመኢሆሙ ፣ ምስለ ፣ ዐፀቀ ፣ ምክረ ፣ አኃው ፣ ወጸሎታቲሆሙ ፣ በእንቲኣሆሙ ።
አኃው ፣ የአኃውን ፣ ምክራቸውን ፣ ጸሎታቸውን ፣ አስታራቂ ፣ ከማድረግ ፣ ጋራ ፣ ወደ ፣ ፍጹምነት ፣ ይደርሱ ፣ ዘንድ ፣ አዘዘ ።

ተስእሎ ፣ ፵፬ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ በእንተ ፣ ምንትኑ ፣ ተረክበ ፣ ሰይጣን ፣ ትዝኅርት ፣ ጴጥ ፣ መቃብሮቲሁ ፣ ለአባ ፣ ጵላ ፣ እምድኅረ ፣ ዳግቲሁ ፣ ወፍጹሙ ።
ከፍጹምነት ፣ ከደረሰ ፣ በኋላ ።
ወኅሩየተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ሶቱ ።
ጌታ ፣ ከመረጠው ፣ በኋላ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወፈንዎቱ ፡ ለመድኃኒ ፡ ብዙኃን ።
ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ መክረህ ፡ አስተምረህ ፡ አድንልኝ ፡ ካለው ፡ በኋላ ፤ ሰይጣን ፡ ትዕቢት ፡ ከሚንቃው ፡ ላይ ፡ የተገኘበት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፡ አሉት ። እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ። ሂደህ ፡ ሪፍ ፡ አጠገብ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ አስተምርልኝ ፡ አለው ። ጌታዬ ፡ የኔን ፡ መማር ፤ የነዚያን ፡ አለመማር ፤ የኔን ፡ መብቃት ፤ የነዚያን ፡ አለ ፡ መብቃት ፡ አይቸ ፡ ብታበይ ፡ አጕዳ ፡ የለምን ። ሂድስ ፡ ካልሽኝ ፡ ሰይጣን ፡ ትዕቢትን ፡ አርቅልኝ ፡ ብሎ ፡ አመለከተ ። እሹሀን ፡ ከሚንቃህ ፡ ላይ ፡ አውጣው ፡ አለው ፤ ያምጣው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ይቤሉ ፡ አበው ።
አበው ፡ ተናግረዋል ።

እምድኅረ ፡ ሙስተ ፡ ሠሎሙ ፡ ሰይጣናት ፡ ወሕግግት ፡ ይሄሉ ፡ ምስለ ፡ ፍጹግን ፡ እስክን ፡ መሞት ፡ ወተቃትሉ ።
ሰይጣናትን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ከነሡ ፡ በኋላ ፡ የትዕቢት ፡ ያር ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ አይጠፋላቸውም ።

ትዝኅርትስ ፡ ወስብሐት ፡ ዕፍት ፡ ታርሕቆሙ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ክመ ፡ ኢያጥብው ፡ ውስተ ፡ ተጋድሎቶሙ ፡ ወፍጹሞሙ ።
በትሕትናቸው ፡ በፍጹምነታቸው ፡ ጸንተው ፡ እንዳይ ኖሩ ፡ የትዕቢት ፡ የውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ያር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትለያቸዋለች ፡ አሉ ።

ወዶበ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሑር ፡ ገዳመ ፡ ዘቅርብት ፡ እምሪፍ።
አባ ፡ ጽላንም ፡ ጌታ ፤ ኀበ ፡ ሪፍ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሪፍ ፡ አጠገብ ፡ ካለች ፡ ገዳም ፡ ሂደህ ።

ወጽምድ ፡ ሊተ ፡ ሕገበ ፡ ዘይሴብሐኒ ፡ ወዘይሜኒ ፡ ለምግባሬተ ፡ ሠናያት ።
የሚያገለግለኝን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ የሚገባውን ፡ ሕዝቤን ፡ ምከርልኝ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ።

ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ጽላ ፡ ኦእግዚኦ ፡ አዕትትኪ ፡ እምላዕሌየ ፡ ትዝኅርተ ፡ ክመ ፡ ኢይዘንር ፡ ላዕለ ፡ አኃው ፡ ወክመ ፡ ኢይኅጕል ፡ ሠሎ ፡ ሠናያተ ።
አቤቱ ፡ ሂድስ ፡ ካልሽኝ ፡ የኔን ፡ መማር ፡ የነዚያን ፡ አለመማር ፡ አይቸ ፡ እንዳልታበይ ፤ ጸጋ ፡ ክብር ፡ አጥቼ ፡ እንዳልጐዳ ፡ ትዕቢትን ፡ አርቅልኝ ፡ አለው ።

ወአዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክመ ፡ ያንሳ ፡ እይሁ ፡ ዲበ ፡ ክግዱ ፡ ወያንብር ፡ ዘይረክቦ ፡ ዲበ ፡ መትክፍቱ ።
ጌታም ፡ እጅህን ፡ ካንገትህ ፡ በላይ ፡ አውጥተህ ፡ ከሚንቃህ ፡ ላይ ፡ አኑረው ። አንድም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ከሚንቃህ ፡ ላይ ፡ ያገኘኸውን ።

ወይደፍኖ ፡ ዲበ ፡ ኖኅ ።
ካሸዋ ፡ ቀብረህ ፡ አኑረው ፡ አለው ።

ወረክበ ፡ ኢትዮጵያዌ ፡ ንዑስ ።
እጁን ፡ ከሚንቃው ፡ ላይ ፡ ቢያወጣ ፡ ደበል ፡ ባሪያ ፡ ያህል ፡ አገኘ ።

ወቀብሮ ፡ ውስተ ፡ ኖኅ ።
ካሸዋ ፡ ቀብረው ።

ወውእቱ ፡ ይኬልሕ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አነ ፡ ሰይጣን ፡ ትዝኅርት ።
ወይ ፡ እኔ ፡ ሰይጣን ፡ ትዕቢት ፡ በለልሁ ፡ ጠፋሁ ፡ እያለ ፡ ሲጮህ ፡ ይኖራል ።

አበውኒ ፡ ይቤሉ ፤ እስመ ፡ ለሕግም ፡ ዘይመልኮ ፡ ብእሲ ፡ ይነብር ፡ ሰይጣን ፡ ዲበ ፡ አባሉ ፡ ዘበቱ ፡ ይፈጽም ፡ ገቢረ ።
አበውም ፡ ኃጢአት ፡ መሥራት ፡ የሚወደውን ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ በሚፈጽምበት ፡ አካሉ ፡ ተጠግቶ ፡ ቀርቦ ፡ ሰይጣን ፡ ይዋጋዋል ፡ አሉ ።

ለዘይመልኮ ፡ ሕማመ ፡ ዝሙት ፡ ርእዩ ፡ አበው ፡ ሰይጣን ፡ ዝሙት ፡ ነቢሮ ፡ ውስተ ፡ እስኪቱ ።
የዝሙት ፡ ያር ፡ የሚዋጋውን ፡ ሰይጣን ፡ ዝሙት ፡ ከአባለ ፡ ዘሩ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ አድርግ ፡ አድርግ ፡ ሲለው ።

ወለዘይመልኮ ፡ ትቀጕፅ ፡ ይነብር ፡ ሰይጣን ፡ ቀጥዓ ፡ ውስተ ፡ ልቡ።
ቀጣ ፡ የሚዋጋውን ፡ ሰይጣን ፡ ቀጥዓ ፡ ከልቡ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ተቈጣ ፡ ተቈጣ ፡ ሲለው ።

ወለዘያንኮረጕር ፡ ወይትናገር ፡ ነገረ ፡ እኩየ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ ልሳኑ ።
የሚበጸበጸውን ፡ ጠማማ ፡ ነገር ፡ የሚናገረውን ፡ ካንደበቱ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ተናገር ፡ ተናገር ፡ ሲለው ።

ወለዘይንውም ፡ በውስተ ፡ ጸሎት ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ አዕይንቲሁ ።
በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ የሚያንቀላፋውን ፡ ካይኑ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ተኛ ፡ ተኛ ፡ ሲለው ።

ወለሰራቂኒ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ የግኑ ።
ሌባውንም ፡ ከእጁ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ አንጣ ፡ አንጣ ፡ ሲለው ፡ አዩ ።

ተስእሎ ፡ ፴፭ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ ዘኮነ ፡ ያነውር ፡ አረጋዊ ፡ ለብሑታን ፡ አሰ ፡ ይሰብሱ ፡ ሐጊን ፡ ወያነውጹ ፡ ሥእርተ ።
አረጋዊ ፡ ጽሩር ፡ የሚለብሱትን ። አንድም ፡ ሰንሰለት ፡ የሚያስሩትን ፡ ጸጉራቸውን ፡ የሚያሳድጉትን ፡ በሕታውያንን ፡ ይነቅፍ ፡ የነበረ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።

ወብዙኃንኒ ፡ አርትዑ ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ።
ይህን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አድርገውታል ፤ አመስግነውታል ፤ ትች ። የሚነቅፍ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘያነውር ፡ ፍጹግነስ ።
እሱስ ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ፍጹግንን ፡ ነቅፎ ፡ አይደለም ።

አላ ፡ ጎሙኣን ፡ ትሩፋት ፡ ሥውርተ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ዝክተ ፡ በእንተ ፡ ስብሐት ፡ ዕሩት ።
የልቡና ፡ ሥራ ፡ የሌላቸውን ፡ ለውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ብለው ፡ እንዲህ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ነቅፎ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ተስእሎ ፡ ፴፮ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ ዘኮኑ ፡ በቀዳሚ ፡ ስብክት ፡ ክር ስቶሳዊት ፡ ብዙኃንን ፡ ባሕታውያን ።
ቀድሞ ፡ ወንጌል ፡ በተነገረችበት ፡ ወራት ፡ ባሕታውያን ፡ የበዙ ።

ወፈድፋደስ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ።
ይልቁንም ፡ በግብጽ ፡ የበዙ ።

ወይእዜስ ፡ ጎዳጣን ፡ እሙንቱ ።
ዛሬ ፡ ግን ፡ ያነሱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ፈነዎሙ ፡ እግዚእነ ፡ ለሐዋርያቲሁ ።
ጌታ ፡ ሐዋርያትን ፡ ሑሩ ፡ ወመህሩ ፡ ብሎ ፡ አዟቸው ፡ ነበርና ።

ወእዘዞሙ ፡ ክመ ፡ ይጽምዱ ፡ ስብእ ፡ በሃይማኖት ። (ማቴጽ፳ ፡ ፳፱)።
ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያሳምኑ ፡ ዘንድ ፡ አሳምኑ ፡ ብሎ ፡ ሰደዟቸው ፡ ነበርና ።

ወይግበሩ ፡ ሥርዓተ ፡ ፍጹመ ።
ፍጹም ፡ ሥራን ። አንድም ፡ ሥርዓተ ፡ ፍጹም ፡ ይላል ፤ የፍጹም ፡ ሥራን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ትሩፋት ፡ አስተምሯቸው ፡ ነበርና ።

ወጸንዖሙ ፡ ተአምራተ ፡ ዐበይተ ፡ ለፍጻሜ ፡ ውእቱ ። (ግርጋኔ ፡ ፭)።
ትምርትን ፡ ለማስረዳት ፤ ሃሃይማኖትን ፡ ፍጹም ፡ ለማድረግ ፤ ድውይ ፡ ፈውሱ ፤ ጋኔን ፡ አውጡ ፤ ሙት ፡ አንሡ ፡ ብሎ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበርና ።

ወአስተርአየት ፡ አመረ ፡ ክሂሎቱ ፡ በላዕለ ፡ ብዙኃን ፡ እስ ፡ እምኑ ፡ ወእስ ፡ ንብሩ ።
አምነው ፡ ተጠምቀው ፡ ሥራ ፡ በውሩ ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የከሃሊነቱ ፡ ምልክት ፡ ተአምራት ፡ ተገል

ጸ ፡ ነበርና ፤ ስለዚህ ፡ ነው ።

ወበክመ ፡ እስ ፡ የአምኑ ፡ ኢኮኑ ፡ ሽሓታተ ፡ ወኢ ፡ እእላፋተ ፤ አላ ፡ አህጉር ፡ ወበሐውርት ።
ያመኑት ፡ ሰዎች ፡ አገሩ ፡ መንደሩ ፡ ይቆጠራል ፡ እንጂ ፤ ሽሕ ፡ ብቻ ፡ እልፍ ፡ ብቻ ፡ እንዳይደሉ ።

ክ ንውኬ ፡ እስ ፡ ገብሩኒ ።
ትሩፋት ፡ የሠሩ ፡ መነኰሳትም ፡ እንዲህ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፤ አይቆጠሩም ።

በክመ ፡ ተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ ገድለ ፡ መነኰሳት ።
በመጽሐፈ ፡ ገነት ፡ እንደ ፡ ተነገረ ።

እስመ ፡ አባ ፡ ሖር ፡ ነበረ ፡ ርእሰ ፡ ኅዕለ ፡ አሠርቱ ፡ ምዕት ፡ እምን ፡ ባሕታውያን ።
አባ ፡ ሖር ፡ ከባሕታውያን ፡ ወገን ። አንድም ፡ ልዩ ፡ በሚሆኑ ፡ በሽሕ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ተሾሞ ፡ ነበር ።

ወኤስድሮስኒ ፡ ዲበ ፡ አሠርቱ ፡ ምዕት ።
አባ ፡ ኤስድሮስም ፡ በሽሕ ፡ ማኅበር ፡ ተሾሞ ፡ ነበር ።

ወለአባ ፡ አሞንኒ ፡ ኮነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ዲበ ፡ ሠላሳ ፡ ምዕት ፡ እምን ፡ ባሕታውያን ።
አባ ፡ አሞንም ፡ ሹመቱ ፡ ከባሕታውያን ፡ ወገን ፡ አንድም ፡ ልዩ ፡ በሚሆኑ ፡ በሦስት ፡ ሽሕ ፡ ማኅበር ፡ ነበር ።

ወአባ ፡ ጳኵሚስኒ ፡ ዲበ ፡ ስባ ፡ ምዕት ።
አባ ፡ ጳኵሚስም ፡ በስድስት ፡ ሽሕ ፡ ማኅበር ፡ ተሾሞ ፡ ነበር ።

ወአባ ፡ ስራጵዩን ፡ ኮኑ ፡ ታሕተ ፡ እዲሁ ፡ እልፍ ። «ዓሠርቱ፡ምዕት»
አባ ፡ ስራጵዩን ፡ የተሾመበት ፡ እልፍ ፡ ማኅበር ፡ ነበሩ ።

ወይቤ ።
መጽሐፈ ፡ ገነት ። አንድም ፡ ጸሐፈ ፡ ገነት ፡ ጳላድዮስ ።

ኤጲስቆጶስ ፡ ዘህገረ ፡ ብህንሳኒ ፡ ዘየዐቢ ፡ ክመ ፡ ውስተ ፡ ሚመቱ ፡ ታሕተ ፡ ሥልጣኑ ፡ እልፍ ፡ ባሕታውያን ፡ ወክልኤቱ ፡ እልፍ ፡ መነኰሳ ይያት ።
ዘይንዕስ ፡ አለና ፡ ዘየዐቢ ፡ አለ ፤ የብህንሳ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ የተሾመበት ፡ ማኅበር ፡ እልፍ ፡ መነኰሳት ፤ ሁለት ፡ እልፍ ፡ መነኰሳይያት ። አንድም ፡ እልፍ ፡ ባለው ፡ ዓሠርቱ ፡ ምዕት ፤ ወክል ኤቱ ፡ እልፍ ፡ ባለው ፡ እሥራ ፡ ምዕት ፡ ይላል ። ሽሕ ፡ መነኰሳት ፤ ሁለት ፡ ሽሕ ፡ መነኰሳይያት ፡ ነበሩ ። በዓረብና ፡ በዕብራይስጥ ፡ በሴም ፡ ቋንቋ ፡ ሁሉ ፡ እልፍ ፡ ማለት ፤ ሽሕ ፡ ወይም ፡ ዓሥር ፡ መቶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ግለት ፣ ነው ፣ እንጂ ፤ እንደ ፣ ግእዝ ፣ እልፍ ፣ መቶ ፣ ጊዜ ፣ መቶ ፤ ወይም ፣ ወሥር ፣ ጊዜ ፣ ሽሕ ፣ አይደለም ።

ወክዕበ ፣ በቀዳሚ ፣ ስብክት ፣ ተመሰልዎሙ ፣ ሰብእ ፣ ለሰባክያን ።

ዳግመኛም ፣ ቀድሞ ፣ ወንጌል ፣ በተነገረችበት ፣ ወራት ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ሐዋርያትን ፣ በግብር ፣ መሰሏቸው ።

እስመ ፣ ክርስቶስ ፣ ኮነ ፣ ብሑተ ።

ክርስቶስ ፣ ባሕታዊ ፣ ነበርና ፣ የቦታ ፣ አይደለም ፣ የግብር ፣ ነው ።

ወይቤ ፣ ተመሐሩ ፣ እምኔየ ፣ ወዘኢይፀውር ፣ መስቀልየ ፣ ወኢይተል ወኒ ፣ ኢይደሉ ፣ ሊተ ፤ ወለእመ ፣ ፈቀድክ ፣ ክመ ፣ ትኩን ፣ ፍጹመ ፣ ሀብ ፣ ሁሎ ፣ ንዋየክ ፣ ለምስኪናን ፣ ወትልወኒ ።

እንዲህ ፣ ብሏቸው ፣ ነበርና ።

ጳውሎስኒ ፣ ኮነ ፣ ይብል ፣ ተመሰሉ ፣ ኪያየ ፣ በክመ ፣ ተመሰልክዎ ፣ አነኒ ፣ ለክርስቶስ ፤ ወእፈቅድ ፣ ለሎሱ ፣ ሰብእ ፣ ይኩን ፣ ክግየ ፣ ውስተ ፣ ንጽሕ ፤ ወይኄይሶ ፣ ለብእሲ ፣ ክመ ፣ ኢይቅረብ ፣ ብእሲተ ፤ እስመ ፣ ዘቦቱ ፣ ብእሲት ፣ ይሄሲ ፣ ውእቱ ፣ ዘክመ ፣ እፎ ፣ ያሙሥ ፤ ወዘሰ ፣ አልቦቱ ፣ ብእሲት ፣ ይሄሲ ፣ ውእቱ ፣ ዘክመ ፣ እፎ ፣ ያሙሥ ፣ ለእግዚአብሔር ።

ጳውሎስም ፣ ተመሰሉ ፣ ኪያየ ፣ ብሏቸው ፣ ነበርና ። (፩ቆሮ ፣ ፯፩ ፣ ፩) ።

እለሰ ፣ ኢይትሜሰሉ ፣ በዘያርእይዎሙ ፣ ትሩፋት ።

ትሩፋት ፣ ሠርተው ፣ አብነት ፣ የሚሆኑዋቸውን ፣ ሰዎች ፣ አብነት ፣ የማያደርጉስ ።

እሙንቱኬ ፣ ውስተ ፣ እክይ ፣ ዘዘልፍ ።

ሁለጊዜ ፣ በክፉ ፣ ሥራ ፣ ጸንተው ፣ ይኖራሉ ።

ወበዘሶሙ ፣ እምጸጋ ፣ እሙንቱሂ ፣ ውስተ ፣ አሠረ ፣ ትዝኅርት ፣ ፈድፋደ ፣ እምእለ ፣ ኢይትሜሰሉ ፣ በሰሚዐ ፣ ዜናት ፣ እምድኅረ ፣ አዝማን ፣ ነዋኃት ።

ከብዙ ፣ ዘመን ፣ በኋላ ፣ ዜናቸውን ፣ ሰምተው ፣ መጻፋቸውን ፣ ተመልክተው ፣ አብነት ፣ ከማያደርጓቸው ፣ ይልቅ ፤ ከዘመናቸው ፣ ደርሰው ፣ ቃላቸውን ፣ ሰምተው ፣ መልካቸውን ፣ አይተው ፣ ትሩፋት ፣ ሠርተው ፣ አብነት ፣ የሚሆኑዋቸውን ፣ ከጸጋ ፣ ወገን ፣ በተሰጣቸው ፣ ጸጋ ፣ ትሕትና ፣ ሠርተው ፣ አብነት ፣ የማያደርጉ ፣ በትዕቢት ፣ ተይዘው ፣ በክፉ ፣ ሥራ ፣ ጸንተው ፣ ይኖራሉ ።

ተስእሎ ፣ ፴፯ ።

ይቤሉ ፣ እጋው ፤ በእንተ ፣ ምንትኑ ፣ ዘኮኑ ። መንፈቀ ፣ ቅዱሳን ፣ የኃሥሡ ፣ እምእግዚአብሔር ፣ በዘይትሜሰሉ ።

እሉሌዶቹ ፣ ቅዱሳን ፣ ከነቢያት ፣ ክሐዋርያት ፣ ወገን ፣ በመማርዓ ፣ የሚመስላቸውን የሚመስሉትን ፣ ሳለጽልን ፣ ብለው ፣ ጌታን ፣ የሚለምኑ ።

ወኮነ ፣ ይፈንዎሙ ፣ ኀበ ፣ ሰብእ ፣ ኀለግዎያን ፣ ዘሕወኅን ፣ እምኔሆሙ ።

ከሳቸው ፣ ወደሚያንሱ ፣ ወደዓለማውያን ፣ የሚሰዳቸው ፣ ስለምን ፣ ነው ።

በክመ ፣ ፈነዎ ፣ ለቅዱስ ፣ እንጦንዮስ ፣ ኀበ ፣ አስካፍ ፤ ወለመቃርዮስ ፣ ኀበ ፣ ክልኤ ፣ አንበት ።

እንጦንዮስን ፣ ወደ ፣ አስካፍ ፤ መቃርዮስን ፣ ወደ ፣ ክልኤቲ ፣ አንስት ፣ እንደ ፣ ሰደደው ፣ ይላሉ ። እንጦንስና ፣ መቃርስ ፣ በትዕቢት ፣ ምክንያት ፣ ማዕርጋችን ፣ ከነቢያት ፣ ነውን ፣ ከሐዋርያት ፣ ሳለጽልን ፣ ብለው ፣ ለመኑ ። እንጦንስን ፣ ክአስካፍ ፣ ሂድ ፣ አለው ። ይህ ፣ አስካፍ ፣ የንጉሥ ፣ ባለሟል ፣ ነበረ ፤ ራስ ፣ ቢትወደድ ፣ ነው ፤ ውሥጡን ፣ ግን ፣ ሠቅ ፣ ታጥቆ ፣ በተባሕትዎ ፣ ይኖራል ። ከዚያ ፣ ቢሄድ ፣ ከንጉሥ ፣ ቤት ፣ ውሎ ፣ ሲወጣ ፣ ደረሰ ፣ ሠራዊቱ ፣ ሲጋፉ ፣ ሠቁን ፣ ቢነኩት ፣ ወገቡን ፣ ቄርጦት ፣ ወደቀ ፤ አፍሰው ፣ ወስደው ፣ ከቤቱ ፣ አገቡት ፤ ተከትሎ ፣ ሂዶ ፣ ንገሩልኝ ፣ አለ ፤ ነገሩለት ፣ ገባ ፤ አናወርህ ፣ እንደምን ፣ ነው ፣ ግብርህን ፣ ሳለጽልኝ ፣ አለው ፤ የኔ ፣ ግብር ፣ ምን ፣ ይጠየቃል ፣ እንደምታየኝ ፣ የቤተ ፣ መንግሥት ፣ ሰው ፣ ነኝ ፣ አለ ። አይደለም ፣ ታዝዝር ፣ መጥቻለሁና ፣ ሳለጽልኝ ፣ አለው ፤ እንኪያስ ፣ ከዓለሙ ፣ ፈቃድ ፣ የለኝም ፣ ፈቃዴ ፣ ጥሎ ፣ መሄድ ፣ ነበረ ፣ አናወራም ፣ እንዲህ ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ሠቁን ፣ ፈትቶ ፣ ወገቡን ፣ የቄረጠውን ፣ አሳየው ፤ ይህ ፣ እንኳ ፣ ዓለማዊ ፣ ሲባል ፣ እንዲህ ፣ የሆነ ፣ እኔማ ፣ ምን ፣ ሥራ ፣ ሠርቻለሁ ፣ ብሎ ፣ ትሕትና ፣ ተምርዋል ። መቃርስን ፣ ከክልኤቲ ፣ አንስት ፣ ሂድ ፣ አለው ። እሊህም ፣ ወንድማማቾቼን ፣ አባብተው ፣ በፍቅር ፣ አንድነት ፣ የሚኖሩ ፣ ናቸው ። ልጅም ፣ የወለዱ ፣ እንደሆነ ፣ ያንዲቱን ፣ ልጅ ፣ አንዲቱ ፤ ያንዲቱን ፣ ልጅ ፣ አንዲቱ ፣ አጥብተው ፣ የሚያሳድጉ ፣ ናቸው ። እንግዳም ፣ የመጣ ፣ እንደሆነ ፣ ተቀብለው ፣ አንድ ፣ እግሩን ፣ አንዳቸው ፤ አንድ ፣ እግሩን ፣ አንዳቸው ፣ ያጥቡታል ። ደዓሞ ፣ አንድ ፣ አሮጌ ፣ ውሻ ፣ ነበረ ፤ አንዲቱ ፣ ምሳውን ፣ አንዲቱ ፣ እራቱን ፣ እየሰጡ ፣ ይረዱታል ፤ ከዚያ ፣ ቢሄድ ፣ ተቀብለው ፣ አንድ ፣ እግሩን ፣ አንዳቸው ፤ አንድ ፣ እግሩን ፣ አንዳቸው ፣ አጠቡት ። ልጆቹ ፣ ኑሯችሁ ፣ እንደምን ፣ ነው ፣ አላቸው ፤ የኛ ፣ ኑሮ ፣ ምኑ ፣ ይጠየቃል ፣ ዓለማውያን ፣ ነን ፤ ባል ፣ አግብተን ፣ ወልደን ፣ ከብደን ፣ ቤት ፣ ንብረት ፣ ገዝተን ፣ እንኖራለን ፣ አሉት ። አይደለም ፣ ታዝዝር ፣ መጥቻለሁና ፣ ግድ ፣ ግለጹልኝ ፣ አላቸው ። እንኪያስ ፣ ባሎቻችን ፣ የማይሰዱን ፣ ቢሆኑ ፣ ልጆቻችንንም ፣ እናሳድግ ፣ ብለን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ ለመኖር ፣ ፈቃድ ፣ የለንም ፤ ፈቃዳችን ፣ ጥሎ ፣ መሄድ ፣ ነው ። ግብራችንም ፣ እንደምታየን ፣ እንግዳ ፣ ተቀብለን ፤ ይህን ፣ አሮጌ ፣ ውሻ ፣ ረድተን ፣ ልጅም ፣ ብንወልድ ፣ ያንዳችንን ፣ ልጅ ፣ አንዳችን ፤ ያንዳችንን ፣ ልጅ ፣ አንዳችን ፣ አጥብተን ፣ አሳድገን ፣ ነው ፣ አሉት ። እሊህ ፣ ስንኳ ፣ ዓለማውያት ፣ ሲሆኑ ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ ሥራ ፣ የሠሩ ፣ እኔማ ፣ ምን ፣ ሥራ ፣ ሠራሁ ፣ እላለሁ ፣ ብሎ ፣ ትሕትና ፣ ተምሯል ። እሱም ፣ ሲሄድ ፣ ይልቁንም ፣ ከዚህ ፣ ሁሉ ፣ የተቀበለላችሁ ፣ የዚህን ፣ የውሻውን ፣ ነው ፤ አትተዉ ፣ ብሏቸው ፣ ሂዷል ።

ወለበብኑዳሂ ፣ ኀበ ፣ አሐዱ ፣ ፈያታዊ ፣ መፀንዝር ።

በብኑዳንም ፣ በገና ፣ ከሚደረድር ፣ ከፈያታይ ፣ እንደ ፣ ሰደደው ፣ አለ ። እንደ ፣ ምን ፣ ነው ፣ ቢሉ ፤ ይህ ፣ በብኑዳ ፣ ፍቅረ ፣ ንዋይ ፣ ይዋጋው ፣ ነበር ። ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ መንገድ ፣ ሲሄድ ፣ ይህ ፣ ፈያታይ ፣ መአንገር ፣ አየው ። ከባልንጀሮቹ ፣ ጋራ ፣ የወይን ፣ ጠጅ ፣ አቅርቦ ፣ ሲጠጣ ፣ ነበር ። ሂዶ ፣ ከጫማው ፣ ላይ ፣ ወድቆ ፣ እባክህ ፣ ጠጣልኝ ፣ ብሎ ፣ ወስዶ ፣ አጠጣው ፤ ይህ ፣ ስንኳ ፣ ወንበዴው ፣ እንዲህ ፣ አድርጎ ፣ ገንዘብ ፣ ሲንቅ ፣ እኔ ፣ ገንዘብ ፣ መውደድ ፣ ብሎ ፣ ፍቅረ ፣ ንዋይ ፣ ጠፍቶለታል ።

ወለአዩጸንሂ ፣ ኀበ ፣ ኖላዊ ፣ ትሩፍ ።

አዩጸንንም ፣ ከኖላዊ ፣ ትሩፍ ፣ እንደ ፣ ሰደደው ፣ አለ ። እንደምን ፣ ነው ፣ ቢሉ ፤ አዩጸን ፣ ቍጣ ፣ ይዋጋው ፣ ነበር ። ኖላዊ ፣ ትሩፍ ፣ ያለው ፣ አወ ፣ ክርስቶስ ፣ ነው ። ባለ ፣ ሕሳ ፣ ነበር ፤ በግብር ፣ ግን ፣ አያውቃትም ። በጎች ፣ አርብቶ ፣ ጸጉራቸውን ፣ እየ ፣ ሸለተ ፣ እየ ፣ ሸጠ ፣ ራሱንም ፣ ነዳያንንም ፣ ረድቶ ፣ እንግዳ ፣ ተቀብሎ ፣ ይኖራል ። ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ አሸከሩ ፣ ያስያዘውን ፣ ዕቃ ፣ ጥሎ ፣ ሲያለቅስ ፣ ከመንገድ ፣ ላይ ፣ አዩጸን ፣ አገኘው ። ምነው ፣ ታለቅሳለህ ፣ ቢለው ፣ ጌታዬ ፣ ያስያዘኝ ፣ ዕቃ ፣ ጠፍቶብኝ ፣ አለ ። ና ፣ አስታርቅኻለሁ ፣ ብሎ ፣ ይዞት ፣ ሄደ ። ምን ፣ ስታደርግ ፣ ጣልኸው ፣ ቢለው ፣ ተኝቼ ፣ አለ ። እንኳን ፣ ተኝተህ ፣ እንዲያውስ ፣ ቢጠፋ ፣ ገንዘብ ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ነውን ፣ ብሎ ፣ ሲታገሥ ፣ አየው ፤ ይህ ፣ እንኳ ፣ እንዲህ ፣ ሲያደርግ ፣ ብሎ ፣ ትዕግሥት ፣ ተምሯል ።

ይቤ ፣ መተርጉም ፤ ጎሚሶቶሙስ ፣ እምእግዚአብሔር ፣ ዘበበይን ፣ ግጻዌሆሙ ፣ በእንተአሁ ።

የሚመስሏቸውን ፣ ሳለጽልን ፣ ብለው ፣ ከእግዚአብሔር ፣ መለመናቸው ፣ ባለ ፣ ሚል ፣ ስለ ፣ ሆኑ ፣ ነው ። አንድም ፣ ለመረዳት ፣ ነው ።

በክመ ፣ ደሰዎ ፣ ግጻዌ ፣ ለዮሐንስ ፣ በእንተ ፣ እግዚእነ ።

ለዮሐንስ ፣ ባለ ፣ ሚልነት ፣ እንደ ፣ ተሰጠው ። አንድም ፣ መረዳት ፣ እንደ ፣ ተገባው ።

እስመ ፣ ውእቱ ፣ ረፈቀ ፣ ዲበ ፣ እንግድኅው ።

ባለ ፣ ሚሉ ፣ ተብሏልና ፤ ባለ ፣ ሚል ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ነው ።

ወተስእሎ ፣ በእንተ ፣ መኑ ፣ ውእቱ ፣ ዘያገብኦ ። (ዮሐ፲፫ ፣ ፳፭) ።

ጠይቆታልና ፣ መረዳት ፣ እንደ ፣ ተገባው ።

ወፈቀዱ ፣ በእንተገ ፣ ተስእሎተ ።

እነሱም ፣ ስለዚህ ፣ መጠየቅን ፣ ወደዱ ።

ወውእቱ ፣ እንከ ፣ ለዘይመስሎሙ ፣ እምቅዳሳን ፣ ለአሰስሎተ ፣ ፍርሀቶሙ ።

ከነቢያት ፣ ከሐዋርያት ፣ ወገን ፣ የሚመስሏቸውን ፣ መጠየቃቸውም ፣ ፍርሀተ ፣ ገሃነምን ። አንድም ፣ ጥር ጥራቸውን ፣ ለማራቅ ፣ ነው ።

ወለኃይል ፣ ትውክልቶሙ ፣ ወተስፋሆሙ ።

ለሃይማኖታቸው ፣ ለተስፋቸው ፣ አጋዥ ፣ ሊሆናቸው ።

ወተውሳክ ፣ ፍልሐቶሙ ፣ በእንተ ፣ አፍቅሮ ፣ እግዚአብሔር ።

በጌታ ፣ ፍቅር ፣ ለመናደዳቸው ፣ አጋዥ ፣ ሊሆናቸው ፣ ነው ።

ወፈንዎቱ ፣ ኪያሆሙ ፣ ኀበ ፣ ኀለግውያን ፣ እለ ፣ እሙንቱ ፣ ዘሕጸጻን ፣ እምኔሆሙ ፣ ለፍጻሜ ።

ጌታም ፣ እነ ፣ እንጦንስን ፣ በፍጹምነት ፣ ከሳቸው ፣ ወደሚያንሱ ፣ ወደ ፣ እለ ፣ አስካፍ ፣ መስደዱ ።

ክመ ፣ ያጽንዕዎሙ ፣ ውስተ ፣ ትሕትና ።

እለ ፣ አስካፍ ፣ እለ ፣ እንጦንስን ፣ በትሕትና ፣ ያጸኑዋቸው ፣ ዘንድ ፣ ነው ።

ወክመ ፣ ይርብሕዎሙ ፣ ለእልክቱኒ ፣ ኀለግውያን ፣ በጉዘዜ ፣ ባሕታውያን ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ጸሐፈ ፡ በአዝማን ፡ ቴዎደስዮስ ፡ ዘየዓቢ ።
ይሩማኔስ ፡ በቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ ጽፍዋልና ፡ አሐዱ ፡ ዘይሩማኔስ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መነኮሳት ፡ አልበዙም ።
ወጸላድዮስሰ ፡ ጸሐፈ ፡ በዘመን ፡ አርቃድዮስ ፡ ወልዱ ።
ጸላድዮስ ፡ በልጁ ፡ በአርቃድዮስ ፡ ዘመን ፡ ጽፍዋልና ፡ ክልኤቱ ፡ ክፍል ፡ ዘጸላድዮስ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በዝ ተዋል ።
ወለእግዚአብሔር ፡ አኰቴት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ወትረ ።
ለጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

ክፍል ፡ ራብዕ ።

አራተኛው ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ወውእቱ ፡ ደኀረ ፡ ዘእምዜናሆሙ ፡ ለባሕታውያን ፡ እንተ ፡ ተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ገነት ፡ እምክፍል ፡ ደኀሪ ።
በመጽሐፈ ፡ ገነት ፡ ከተጻፈ ፡ ከአበው ፡ ዜና ፡ የመጣ ፤ ክፍል ፡ ደኀሪ ፡ እምክፍል ፡ ደኀሪ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።
ዘጸሐፍ ፡ ጸላድዮስ ፡ ተስእሎታተ ፡ አኃው ።
ጸላድዮስ ፡ አኃውን ፡ እየጠየቀ ፡ የጻፈው ፡ የሁለተኛው ፡ ተከታይ ፡ የሚሆን ፤ የሶስተኛው ፡ ተከታይ ፡ አራተኛው ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፴፱ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ንዌጥን ፡ በረድኤተ ፡ እግዚእን ፡ ንሰእል ፡ ሥርዓተ ።
ሥርዓትን ፡ እንረዳ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ጥያቄ ፡ እንጀምራለን ።
በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ እምቅድመ ፡ ሁሉ ፡ መሠሩን ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ።
አበው ፡ ቅዱሳን ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመው ፡ ይኸን ፡ ያስተማሩን ፡ ስለምን ፡ ነው ።
እፎ ፡ ወኒኦ ፡ እምዓለም ፡ ወነቢር ፡ ውስተ ፡ ምኔት ።
ከዓለም ፡ ወጥቶ ፡ ወደገዳም ፡ መግባት ።
ወከዕበ ፡ ወኒኦ ፡ እግዓነር ፡ ወተባሕትዎ ፡ ውስተ ፡ በዓት ።
ኀላ ፡ ደጓሞ ፡ ከገዳም ፡ ወጥቶ ፡ ከማኅበር ፡ ተለይቶ ፡ ተባሕትዎ ፡ መያዝ ፡ እንዲገባ ፡ ያስተማሩን ፡ ስለምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ መሠረት ፡ ዘይትሐነጽ ፡ ዲቤሁ ፡ ወየኅርግ ፡ እምኔሁ ፡ ኀበ ፡ ማኅፈድ ፡ ላዕላይ ፡ ዘጽድቅ ።
ወደ ፡ ንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ሰገነት ፡ የሚወጡበት ፡ ማኅፈድ ፡ ትሩፋቶች ፡ የሚሠራባቸው ፡ መሠረት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።
እስመ ፡ ውእቶሙ ፡ ይጸንዑ ፡ በውስተ ፡ ማኅበር ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮተ ፡ ሰብእ ።
ወጣንያን ፡ በማኅበር ፡ ሳሉ ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡ ለመፈጸም ፡ ጸንተው ፡ ይረዳሉ ።
ወበውስተ ፡ ተባሕትዎን ፡ ይትፈጸሙ ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮ ፡ እግዚአብሔር ።
በተባሕትዎም ፡ ጊዜ ፡ በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹማን ፡ ይሆናሉ ።
እስመ ፡ አፍቅሮ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሕግ ፡ ውእቱ ።
ፍቅር ፡ ፍጹም ፡ ሕግ ፡ ነውና ።
በክመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእን ። (ማቴ፳፪ ፡ ፴፯—፵) ።
ጌታ ፡ ወበእላ ፡ ክልኤቲ ፡ ትእዛዝት ፡ ተሰቅሉ ፡ አሪት ፡ ወነቢያት ፡ እንዳለ ።
ወሐዋርያኒ ።
ጳውሎስም ፡ ተፋቅሮ ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡ እንዳለ ። (ሮሜ፲፫ ፡ ፲) ።
በቀዳሚው ፡ ይፃእ ፡ እንክ ፡ ብእሲ ፡ እምኅበም ።
እንኪያስ ፡ ወጣኒ ፡ በመጀመሪያ ፡ ከዓለም ፡ ወጥቶ ።
ወይትመተር ፡ እምራእዩ ፡ ወአፍቅሮቱ ።
ይህን ፡ ዓለም ፡ ከማየት ፡ ከማሰብ ፡ ተለይቶ ፡ ከፍቅሩም ፡ ተለይቶ ፡ ይኑር ።
እስመ ፡ አፍቅሮ ፡ ዓለም ፡ ይእቲ ፡ ዐራ ፡ ለአፍቅሮ ፡ እግዚአብሔር ።
ፍቅረ ፡ ዓለም ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታራርሳለችና ።
በክመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውእቱ ።
እስመ ፡ ሕሊናሁ ፡ ለነፍስትነ ፡ ፀሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ። (ሮሜ፰ ፡ ፯ ።)
ወዘኢያጸልእ ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፤ ብእሲቶ ፡ ወውዱያ ።
አባት ፡ እናቱን ፤ ሚስቱን ፡ ልጆቹን ።
ወንፍሶ ።
ራሱን ፡ ያልጸላ ።
ዘውእቱ ፡ ዘመደ ።
የላይኛውን ፡ ፈታ ፤ ይኸውም ፡ ዘመዱን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዘመዶቹን ፡ ጥሎ ፡ ያልሄደ ።
ወልግጻቲሁ ፤ ወፍትወታቲሁ ።

እነ ፡ እንጠንስም ፡ በምክር ፡ በጸሎት ፡ ዓለማውያን ፡ እለ ፡ አስካፍን ፡ ይጠቅሻቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድም ፤ ያጽንዖሙ ፤ ጌታ ፡ እነ ፡ እንጠንስን ፡ በትሕትና ፡ ያጸናቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ወከመ ፡ ይርብሑሙ ፡ በኩዘዜ ፡ በሕታውያን ። እለ ፡ አስካፍንም ፡ በነእንጠንዮስ ፡ ምክር ፡ ጸሎት ፡ ይጠቅማቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
በእንተ ፡ ጻማ ፡ ጽድቆሙ ።
በትሩፋት ፡ ስለ ፡ ደከሙ ።
ወይጽናዕ ፡ ተስፋሆሙ ።
ተስፋቸውም ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
ወከመ ፡ ይርብሕዎሙ ፡ ለካልኣኒሆሙ ፡ በተመስሎ ፡ ኪያሆሙ ፡ እም ክመ ፡ አእመሩ ፡ ክመ ፡ እሙንቱ ፡ ይትጓረምሙ ፡ ለባሕታውያን ፡ ጻድቃን ፡ ለእመ ፡ ተጋደሉ ፡ በእንተ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ።
በትሩፋት ፡ ቢጋደሉ ፡ ዓለማውያን ፡ ባሕታውያንን ፡ እንዲተካከሏቸው ፡ ቢያውቁ ፤ እነሱን ፡ መስለው ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ እለ ፡ እንጠንስ ፡ እለ ፡ አስካፍን ፡ ይጠቅሻቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድም ፡ በትሩፋት ፡ ቢጋደሉ ፡ እለ ፡ አስካፍ ፡ እለ ፡ እንጠንስን ፡ እንዲተካከሏቸው ፡ ቢያውቁ ፤ እነሱን ፡ መስለው ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ እለ ፡ አስካፍ ፡ አብነት ፡ ሁነው ፡ ሌሎች ፡ ዓለማውያንን ፡ ይጠቅሻቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፴፰ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ማር ፡ ወቅሪስ ፡ ይኤዝዞሙ ፡ ለአኃው ፡ ክመ ፡ ኢይጽገቡ ፡ እማይ ።
ማር ፡ ወቅሪስ ፡ አኃውን ፡ ውሀ ፡ እስኪጠግቡ ፡ እንዳይጠጡ ፡ ያዛቸው ፡ ነበር ፤ ቡችላ ፡ እንኳ ፡ በውሀ ፡ ፈትፍቶ ፡ ቢሰጡት ፡ አይበላውም ፤ ምን ፡ ይጕዳቸው ፡ ብሎ ፡ ነው ።
ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእን ፤ እስመ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ እምክመ ፡ ወጽአ ፡ እምሰብእ ፡ የጎሥሥ ፡ መክን ፡ ዘእልፎ ፡ ውስቴታ ፡ ማይ ፡ እንዘ ፡ የጎሥሥ ፡ ዕረፍተ ፡ ወኢይረክብ ፤ ወይገብእ ፡ እንክ ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ። (ማቴ፲፪ ፡ ፵፫—፵፭) ።
ጌታ ፡ እንዲህ ፡ ስላለ ፡ ነው ።
አበውኒ ፡ ይቤሉ ፤ ዘኢያሐጽጽ ፡ እመብልዑ ፡ ወመብዝኀቶሰ ፡ እምሰትየ ፡ ማይ ፡ ኢይመውኡ ፡ ለመንፈሰ ፡ ገሙት ፡ ወኢይፈጽም ፡ ጽድቀ ።
አበውም ፡ ከምግቡ ፡ የማያከፍል ፡ ይልቁንም ፡ ብዙ ፡ ውሀ ፡ ከመጠጣት ፡ የማያከለከል ፡ ሰው ፤ ሰይጣን ፡ ገሙትን ፡ ድል ፡ አያነሣውም ፤ ትሩፋትንም ፡ አይፈጽምም ፡ አሉ ።
ወአልቦ ፡ ዘየዓብስ ፡ ዓባስ ፡ ወይክልኦ ፡ እምሕልም ፡ ወነቅዐ ፡ ፈሰስ ፡ ወያጎድዕ ፡ ሕሊተ ፡ ደነስ ፡ በመዓልት ።
አካል ፡ የሚያደርቅ ፤ ከሕልመ ፡ ሌሊት ፡ ከዘር ፡ መፍሰስ ፡ የሚከለክል ፤ በመዓልት ፡ ኃልዮ ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያጠፋ ።
ከመ ፡ ጽምእ ።
እንደ ፡ ውሀ ፡ ጥም ፡ የለም ።
እስመ ፡ ለእመኒ ፡ ጸመ ፡ ወአሕጸጸ ፡ ሲሳየ ፡ ኢይረብሕ ፡ ምስለ ፡ መብዝኀት ፡ ሰትየ ፡ ማይ ።
ምንም ፡ ቢጸም ፡ ምንም ፡ ምግብ ፡ ቢከፍል ፡ አብዝቶ ፡ ውሀ ፡ ከጠጣ ፡ አይጠቀምምና ።
ትሜልኣ ፡ ከርሡ ።
ጦነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ሆዱ ፡ ቂብ ፡ ትላለች ።
ወትትዋስክ ፡ አባሉ ፡ ርጥበተ ።
ሰውነቱ ፡ ትለመልማለች ፤ ጠሩም ፡ ይፈኤመርበታል ።
ወይረክብ ፡ እንክ ፡ ሰይጣን ፡ ምክንያተ ፡ ለእስሕቶ ፡ በሕሊናተ ፡ መዓልት ፡ ወአሕላመ ፡ ሌሊት ።
ሰይጣን ፡ ቀንም ፡ ሌሊትም ፡ ገሙትን ፡ በማሳሰብ ፡ የሚያስትበት ፡ ምክንያት ፡ ያገኛል ።
ይቤ ፡ ማር ፡ ወቅሪስኒ ፡ ለእመ ፡ ፈቀድክ ፡ ንጽሐ ፡ አሕጽጽ ፡ እምሲሲት ።
ማር ፡ ወቅሪስም ፡ ንጽሕና ፡ ሊጠበቅልህ ፡ ከወደድህ ፡ ምግብ ፡ ክፈል ።
ወአጽብብ ፡ ላዕሌክ ፡ እምስትየ ፡ ማይ ።
ውሀ ፡ ከመጠጣትም ፡ በሰውነትህ ፡ ጭንቅ ፡ ሥራ ፡ ሥራበት ፤ ውሀ ፡ ነስተህ ፡ አስፈጌንቀው ።
ዖቤሃኬ ፡ ትበርህ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ።
ንጽሐ ፡ ልብ ፡ ይሰጥሃል ።
ወይበርህ ፡ ልቡናከ ፡ ክመ ፡ ኮኮብ ፡ ትፌንዮ ፡ በውስተ ፡ ጸሎትክ ።
ልቡናህ ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኮከብ ፡ ሲበራ ፡ ታየዋለህ ፡ አለ ።
መልእ ፡ ክፍል ፡ ግልጽ ፡ በአሕጽሮ ።
አሳጥረው ፡ የጠየቁት ፡ ዖስተኛው ፡ ክፍል ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።
አሐዱ ፡ ዮይፋንኔስ ፡ ዘአንበረ ፡ ተስእሎታተ ።
አንዱ ፡ ክፍል ፡ አኃውን ፡ እየጠየቀ ፡ የጻፈው ፡ የሩሚኔስ ፡ ነው ።
ወክልኤ ፡ ክፍላት ፡ ዘጸላድዮስ ።
ሁለቱ ፡ ክፍል ፡ የጸላድዮስ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሕጉን ፣ ትእዛዙን ፣ ማሰብ ፣ ነው ።
ወርእይ ፣ ለዓለም ፣ ጎቤሁ ።
ሁለጊዜ ፣ እሱን ፣ መዘከር ፣ ነው ።
ወተናግሮ ፣ ምስሌሁ ።
ከሱ ፣ ጋራ ፣ መጨዋወት ፣ ነው ።
ወእንታክቲ ፣ ጸሎት ፣ ዘእንበለ ጽርኅት ፣ ወኢፍልሰተ ፣ ሕሊናት ።
ተናግሮም ፣ ያልሁት ፣ ሁለጊዜ ፣ የሚሆን ፤ ያለመባከን ፣ የሚሆን ፣ ጸሎተ ፣ ሕሊና ፣ ነው ።
ወጸሊኢ ፣ ሕግማት ።
ኃጣውኢን ፣ መጽሳት ፣ መተው ፣ ነው ።
ወመቂረ ፣ ሕሊናት ፣ እኪት ፣ እምቀዳሚሁ ፣ ለተሐውሶታ ፣ ውስተ ፣ ልብ ።
ክፉ ፣ ሕሊናን ፣ መጀመሪያ ፣ በልብ ፣ እንደ ፣ ታሰበች ፣ ማራቅ ፣ ነው ።
ወበዝንቱኪ ፣ ምግባር ፣ ያጠፊ ፣ ብሑት ፣ ንጽሐ ፣ ልብ ።
በዚህ ፣ ሥራ ፣ ቢጸና ፣ መነሱሴ ፣ ከንጽሐ ፣ ልብ ፣ ማዕርግ ፣ ይደርሰል ።
እስክ ፣ የኃድር ፣ ውስቴቱ ፣ ክርስቶስ ፣ ዘይቤ ፣ እን ፣ ወእቡየ ፣ ኀመጽእ ፣ ወኀንብር ፣ ውስቴቱ ፣ ማኅደረ ። (ዮሐ፲፬ ፣ ፳፫) ።
ክርስቶስ ፣ እስኪያድርበት ፣ ድረስ ፣ ደርሶ ።
ወሶቤሃ ፣ ይፌኢ ፣ ለሊሁ ፣ ብርሃን ፣ ዘልቡናሁ ።
የልቡናውን ፣ ጽርየት ፣ ያያል ።
ወይደልዎ ፣ ክመ ፣ ይርአይ ፣ ብርሃና ፣ ለዘይሰግዱ ፣ ሎቱ ፣ እግዚአ ፣ ስብሐት ።
በጽርየት ፣ የጸጋውን ፣ ብርሃን ፣ ያያል ። አንድም ፣ ጽርየተ ፣ ልቡናን ፣ ያገኛል ። አንድም ፣ በጸጋው ፣ ብርሃን ፣ የጌታን ፣ የአካሉን ፣ ብርሃንነት ፣ ያያል ።

ተስእሎ ፣ ፵ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ እስፍንተ ፣ ይደልዎ ፣ ለእጉ ፣ ክመ ፣ ይንበር ፣ ውስተ ፣ ማኅበር ፤ ወይባእ ፣ በዓተ ፣ ብሕትውና ።
መነኩሴ ፣ በማኅበር ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ዘመን ፣ ኑሮ ፣ ተባሕትዎ ፣ ሊይዝ ፣ ይገባል ።
ይቤ ፣ መተርጉም ፤ በክመ ፣ ይደሉ ፣ ለእርኣያሁ ።
ለመልኩ ፤ አንድም ፣ ላብነትነቱ ፣ እንዲገባ ፣ መጠን ፣ ነው ። መልኩ ፣ መከራ ፣ የሚችል ፣ የማይችል ፣ አለ ና ፤ አብነትነቱ ፣ የተማረ ፣ ያልተማረ ፣ አለና ።
ወመኅርጊሁ ።
ለዕውቀቱ ፣ ለመኅርጉ ፣ እንደሚስማማ ፣ መጠን ፣ ነው ፤ አስቀድሞ ፣ ሥራ ፣ የሠራ ፣ ያልሠራ ፣ አለና ።
ወትምህርተ ፣ ቁመቱ ።
በሥራ ፣ ጸንቶ ፣ መኖርን ፣ እንደ ፣ መማሩ ፣ መጠን ፣ ነው ።
ወጽንዐ ፣ ምግባሩ ።
በሥራ ፣ ጸንቶ ፣ እንደ ፣ መኖሩ ፣ መጠን ፣ ነው ።
ወዝንቱ ፣ ታሕተ ፣ ሥልጣን ፣ ወአእምሮ ፣ አበው ፣ አዕራግ ፣ ማኅምራን ፣ ምኩራን ።
ይኸም ፣ መዝጋቱ ፣ ሹማምቱ ፣ በዕውቀት ፣ የተፈተኑ ፣ አበው ፣ ፈቅደወለት ፣ ይሁን ።
ወናሁ ፣ ርእዩ ፣ ማኅበረ ፣ ቅዱሳን ፣ እስመ ፣ ለአኃው ፣ እለ ፣ ይክውኑ ፣ ውስተ ፣ ቁመት ፣ ፍጽምት ።
በበጎ ፣ ሥራ ፣ ጸንተው ፣ ለሚኖሩ ።
ወምሁራን ፣ ለአእምሮ ፣ ወጽንዕ ፣ ውስተ ፣ ምግባሩት ።
ጠሩን ፣ ለማወቅ ፣ በትሩፋት ፣ ለመጽናት ፣ ሥርዓቱን ፣ ለተማሩ ።
ወይፈልሑ ፣ ውስተ ፣ ፍቅር ።
በፍቅር ፣ ለሚናደዱ ።
ወሥሩዓን ፣ ውስተ ፣ ትሕትና ።
በትሕትና ፣ ለተወሰኑ ።
ወይክውኑ ፣ ውስተ ፣ ዛቲ ፣ ሁላ ፣ ዘያፈቅሩ ፣ ጽሙና ፣ ውስተ ፣ በዓት ።
ይኸን ፣ ሁሉ ፣ ይዘው ፣ በተባሕትዎ ፣ መኖርን ፣ ለሚወዱ ፣ አኃው ።
የአክሰሙ ፣ ሠለስቱ ፣ ዓመት ፣ ተምህሮ ፣ ምግባራት ፣ ንጹሓት ፣ እንተ ፣ ባቲ ፣ ይቂውም ፣ አፍቅሮ ፣ ቢጽ ።
ፍቅረ ፣ ቢጽ ፣ የሚፈጸምበትን ፣ በጎ ፣ ሥራ ፣ መማር ፣ ምስት ፣ ዓመት ፣ ይበቃቸዋል ፣ ብለው ፣ ፈርደዋል ።
ወእምድኅሬሃ ፣ ይደልዎሙ ፣ ክመ ፣ ይባኡ ፣ ኀበ ፣ ጽሙና ።
ሥስት ፣ ዓመት ፣ ረድተው ፣ ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ተባሕትዎ ፣ ሊይዙ ፣ ይገባቸዋል ።
ዘውእቱ ፣ ብሒር ።
ከኖሩበት ፣ ብሎ ፣ ተባሕትዎን ፣ ብሒር ፣ አለው ። አንድም ፤ ዘውስተ ፣ ብሒር ፤ በረዱበት ፣ ቦታ ፣ አጠገብ ፣ ተባሕትዎ ፣ ሊይዙ ፣ ይገባቸዋል ።
ዘበውስቴታ ፣ ያደምዑ ፣ ምግባራተ ፣ ኀበእተ ፣ ዘባቲ ፣ ይትፈጸም ፣ ፍቅር ፣ ፍጹም ፣ ዘበእንተ ፣ አምላክ ።
የጌታ ፣ ፍቅር ፣ የሚፈጸምባትን ፣ የልቡና ፣ ሥራ ፣ የሚሠሩበት ፣ አለው ።
እስሰ ፣ ይመጽኡ ፣ ኀበ ፣ ምኔት ፣ ወውእቶሙ ፣ ዘበሕገ ፣ ደቂቅ ።
ለ ፣ የቀረው ፣ ነው ፤ ገና ፣ በወጣኂነት ፣ ግብር ፣ ሳሉ ፣ ከዓለም ፣ ወደ ፣ ገዳም ፣ ለሚመጡ ።

ነፍሶ ፣ ያለውን ፤ ክፉ ፣ ልማዱን ፤ ክፉ ፣ ፈቃዱን ፣ ያልተወ ።
ኢይክል ፣ ይፈጽም ፣ አፍቅሮ ፣ እግዚአብሔር ።
ፍቅረ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ይፈጽም ፣ ዘንድ ።
ወይኩን ፣ ረድኦ ፣ ለክርስቶስ ፣ ዘበአማን ።
ክርስቶስን ፣ ያገለግለው ፣ ዘንድ ፣ አይቻለውም ።
ወኢይፈጽም ፣ በውስተ ፣ ዓለም ።
በዓለም ፣ ሁኖ ፣ ፍጹምነት ፣ አያገኝም ። አንድም ፣ ሥራውን ፣ አይፈጽምም ።
በእንተ ፣ ዘይትቃወም ፣ እምአፍቅሮ ፣ ፍጥረታዊት ።
ከባሕርይ ፣ ፍቅር ፣ ወገን ፣ የሚያፈርስ ፣ ነገር ፣ ስላለበት ።
ዘውእቱ ፣ አፍቅሮ ፣ ዘመድ ።
ይኸውም ፣ የዘመድ ፣ ፍቅር ፣ ነው ።
ወአፍቅሮ ፣ ዘንሁራት ።
በቆጥ ፣ የተሰቀለውን ፣ በማገር ፣ የተንጠለጠለውን ፣ መውደድ ፣ ነው ።
ወአፍቅሮ ፣ ትፍግዕታት ።
ተድላ ፣ ደስታውን ፣ መውደድ ፣ ነው ።
ወእምድኅረ ፣ ዐእቱ ፣ እምኅሊም ፣ ምስለ ፣ ልቡ ።
ልብ ፣ ሳይቀረው ፣ ፈጽሞ ።
ወኮስንታሁ ።
ጨልጠ ፣ ገርኝቶ ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ ከተለየ ፣ በኋላ ።
ይባእ ፣ ኀበ ፣ ምኔት ፣ ማኅበረ ፣ ድርገተ ፣ አኃው ።
አኃው ፣ አንድ ፣ ሁነው ፣ ወዳሉበት ፣ ማኅበር ፣ ይግቡ ።
ክመ ፣ ይግበር ፣ ምስሌሆሙ ፣ ትእዛዘ ፣ ክርስቶስ ፣ ጸመ ፣ ወጸሎተ ፣ ወትጋህ ፣ ወአንብቦ ።
ከሳቸው ፣ ጋራ ፣ ሁኖ ፣ ክርስቶስ ፣ ያዘዘውን ፣ ጾምን ፣ ጸሎትን ፣ ትጋህ ፣ ሌሊትን ፣ መጽሐፍ ፣ መመልከትን ።
ወኮሎ ፣ ግብረ ፣ ዘበቱ ፣ ይትፈጸም ፣ አፍቅሮተ ፣ አኃው ።
የአኃው ፣ ፍቅር ፣ የሚፈጸምበትን ፣ ሥራ ፣ ሁሉ ፣ ይሠራ ፣ ዘንድ ።
ዘክመ ፣ መልእክተ ፣ ድውያን ፣ ወቅዱሳን ።
ይህም ፣ ድውያንን ፣ ነዳያንን ፣ እንደ ፣ መርዳት ፣ ያለ ፣ ነው ።
ወተቀብሎ ፣ ንግድ ።
እንግዳ ፣ መቀበል ፣ ነው ።
ወተአዝዞ ፣ አዕሩግ ፣ ወሊቃናት ።
ለሽማግሌች ፣ ለሹማምቱ ፣ መታዘዝ ፣ ነው ።
ወክዕበ ፣ እስመ ፣ ኢይክል ፣ ውእቱ ፣ በቀዳሚ ፣ ፀአቱ ፣ እምዓለም ፣ ይትቃተል ፣ ምስለ ፣ ብዙኃት ፣ ሕሊናተ ፣ ዕይጣናት ።
ዳግመኛም ፣ ወጣኒ ፣ መጀመሪያ ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ በወጣ ፣ ጊዜ ፣ ሰይጣናት ፣ የሚያመጡትን ፣ የሐሊና ፣ ያር ፣ መዋጋት ፣ አይቻለውምና ።
ይትመሀር ፣ እንክ ፣ ብእሲ ፣ አእምሮ ፣ ሥርዓት ፣ በማእክለ ፣ ማኅበረ ፣ አኃው ።
ስለዚህ ፣ በአኃው ፣ መካከል ፣ ሁኖ ፣ ከነዚያ ፣ ጋራ ፣ እየኖረ ፣ የጠሩን ፣ ስልት ፣ የሚያውቅበትን ፣ ጣብር ፣ ይማር ።
ወውጥንተ ፣ አዕባኑ ፣ ግህድ ።
ተገልጦ ፣ የሚመጣውን ፣ የጠሩን ፣ አጀማመር ።
ወሀኬተ ፣ ክፍጣዊ ።
ፈንታነት ፣ ያለውን ፣ የሐኬቱን ፣ አጀማመር ፣ ይወቅ ። ክፍጣዊ ፣ አለ ፣ እንደ ፣ መብል ፣ እንደ ፣ መጠጥ ፣ ይወዱታልና ። እንደ ፣ አባ ፣ አርሳንዮስ ፣ ፀሐይ ፣ ጫንቃውን ፣ ስትመታው ፣ የቆመ ፣ ዙራ ፣ ተመልሳ ፣ ግንባሩን ፣ እስክትመታው ፣ ድረስ ፣ ቁሞ ፣ አድሮ ፤ ንግእ ፣ መከፈልተከ ፣ አ ፣ ሀካይ ፣ ብሎ ፣ ከድካሙ ፣ ያርፍ ፣ እንደነበረ ።
ወእምድኅረ ፣ ዝንቱ ፣ ትምህርት ።
ይህን ፣ ከተማረ ፣ በኋላ ።
ታኦድሮ ፣ ጸጋ ፣ በውስተ ፣ ብሕትውና ፣ በውስተ ፣ በዓት ።
ጸጋ ፣ እግዚአብሔር ፣ ከሰው ፣ ተለይቶ ፣ ከበዓት ፣ ተከቶ ፣ በተባሕትዎ ፣ እንዲኖር ፣ ታደርገዋለች ።
ከመ ፣ ይኩን ፣ ሎቱ ፣ ዕርቃን ፣ ለገቢረ ፣ ሱሱ ፣ ትእዛዛት ፣ ልዑላት ፣ እንተ ፣ ይመጽእ ፣ ባቲ ፣ ፍቅር ፣ ፍጽምት ፣ ዘለእግዚአብሔር ።
ፍቅረ ፣ እግዚአብሔር ፣ የሚፈጸምበትን ፣ ትሩፋት ፣ ለመሥራት ፣ ከሌላው ፣ ግብር ፣ መለየት ፤ አንድም ፣ ከፍቅረ ፣ ዓለም ፣ መለየት ፣ ይሰጠው ፣ ዘንድ ።
ወዝንቱኬ ፣ ውእቱ ፣ ዐቅም ፣ ለዝኩሩ ፣ ዘለጽድቅ ፣ ወልዕልና ፣ ማኅፈደ ፣ ትሩፋት ።
ትሩፋት ፣ ለመሥራት ፤ ወደትሩፋት ፣ ሰገነት ፣ ለመውጣት ፣ የተወሰነ ፣ ሥርዓት ፣ ይህ ፣ ነው ።
ወዝንቱ ፣ ምግባር ፣ ዝኩር ፣ ውእቱ ፣ ተዘክሮ ፣ እግዚአብሔር ።
ይህም ፣ የታወቀው ፣ የተነገረው ፣ ሥራ ፣ እግዚአብሔርን ፣ መዘከር ፣ ነው ።
ወተዘክሮ ፣ ፍርሃታቲሁ ።
የፍርዱን ፣ አስፈሪነት ።
ወትእዛዛቲሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ወጕደላውያን ፡ እምውስተ ፡ ትምህርት ፡ ዘበእንተ ፡ አእምሮ ፡ ወጽንዕ ፡
ጠሩን ፡ ለማወቅ ፡ በትሩፋት ፡ ለመጽናት ፡ ትምርት ፡
ወመሰቀተ ፡ ፍቅር ፡
በፍቅር ፡ መናፍድ ፡ ለሌላቸው ፡ አኃው ፡ ግን ፡
ሠናይ ፡ ሎሙ ፡ ክመ ፡ ይትዐደዉ ፡ ሰመንተ ፡ ወተስዓተ ፡ ወዓሠርተ ፡ ዓመታት ፡ በውስተ ፡ ማኅበር ፡ ወአሜሃ ፡ ይደልዎሙ ፡ ጽሙና ፡ በውስተ ፡ በዓት ፡
ስምንት ፡ ዓመት ፤ ወይም ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፤ ወይም ፡ ዓሥር ፡ ዓመት ፡ ረድተው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ተባሕትዎ ። አንድም ፡ ስምንቱን ፡ አልፈው ፡ በዘጠነኛው ፤ ዘጠኙን ፡ አልፈው ፡ ባሥረኛው ፤ ዓሥሩን ፡ አልፈው ፡ ባሥራንደኛው ፡ ዓመት ፡ ተባሕትዎ ፡ ሊ ይዙ ፡ ይገባል ።
ወናሁ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓዊ ፡ ማርቆስ ፡ በአርእስተ ፡ ዜናው ።
ማርቆስም ፡ ዜና ፡ አበውን ፡ በተናገረበት ፡ መጽሐፍ ፡ በአርእስቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
ከመዝ ፡ ይዜምር ፡ ሕግሂ ፡ ምስለ ፡ ቃሉ ፡ በሰዱስ ፡ መዋዕል ፡ ይደሉ ፡ ገቢር ፤ ወበዕስት ፡ ሳብዕ ፡ ያዕርፍ ፡ በእንተ ፡ ዘክመ ፡ ይደሉ ፡ ውእቱ ፡ ክመ ፡ ይኩን ፡ ገቢር ፡ ውስተ ፡ ማኅበር ፡ ስድስተ ፡ ዓመተ ፤ ወበሳብዕት ፡ ይኩን ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ ወዕረፍት ፡ እምግብር ፡ ግሁድ ። (ዘዘፀጅ ፡ ፱-፲፭) ።
ሕገ ፡ አሪት ፡ ነገሩን ፡ ክቶ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ረድቶ ፡ በሰባተኛው ፡ ተባሕትዎ ፡ እንዲገባ ፡ ሲያስረዳ ፤ ሰዱሰ ፡ መዋዕል ፡ ተገበር ፡ ግብረከ ፤ ሳብዕትሰ ፡ ዕለት ፡ ዕረፍተ ፡ ትኩንከ ፡ ብሏል ። ብሎ ፡ ተናገረ ። አንድም ፤ ሕገሂ ፡ ምስለ ፡ ቃሉ ፡ ይሏል ። ሰዱሰ ፡ መዋዕል ፡ ተገበር ፡ ግብረከ ፤ ሳብዕትሰ ፡ ዕለት ፡ ዕረፍተ ፡ ትኩንከ ፡ ያለውን ፡ ሕገ ፡ አሪትን ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ረድቶ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ተባሕትዎ ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ከተናገረው ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ አሰማምቶ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ ።

ተስእሎ ፡ ፸፩ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ምንትኑ ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ትጸውያመሙ ፡ ጸጋ ፡ ለአኃው ፡ ኀበ ፡ ምንሰኮና ።
ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኃውን ፡ ወደ ፡ ምንሰኮና ፡ የምትጠራበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አሉት ።
ይቤ ፡ መተርጉም ፤ ግብሬት ፡ ብዙኃት ።
ይህስ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ነው ።

ወእምኔሃ ፡ አንትሉ ፡ ልብ ።
ከብዙውም ፡ አንዱ ፡ ልቡና ፡ ማኒቃቃት ፡ ነው ።
በክመ ፡ አንቅሐት ፡ ልቦ ፡ ለሙሴ ፡ ጽልሙት ።
የሙሴ ፡ ጸሊምን ፡ ልቡን ፡ ወደንስሓ ፡ እንደነቃቃችው ።
ወንስሐ ።
ንስሓ ፡ እንደ ፡ ገባ ።
ወእምኔሃ ፡ አንብቦ ።
ከዚህም ፡ አንዱ ፡ መጽሐፍ ፡ መመልከት ፡ ነው ።
ክመ ፡ እንጦንዮስ ፡ ወስምዖን ፡ ዐምዳዊ ፡ አለ ፡ እምሰሚዐ ፡ አንብቦ ፡ ወንጌል ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወዕኡ ፡ እምዓለም ።
እንጦንዮስ ፤ ስምዖን ፡ ዘዓምድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወንጌል ፡ ሲነበብ ፡ ሰምተው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ወጡ ። ስምዖን ፡ ዘዓምድ ፡ ምንት ፡ ይበቍዖ ፡ ለሰብእ ፡ ያለውን ፡ እንጦንዮስ ፡ እመሰ ፡ ትፈቅድ ፡ ፍጹመ ፡ ትኩን ፡ ሚጥ ፡ ሑሰ ፡ ዘብከ ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ ፡ ያለውን ፡ ሰምተው ፡ ሂደዋልና ።
ወእምኔሃ ፡ ሰሚዐ ፡ ነገረ ፡ ምዕዳን ።
ከዚህም ፡ አንዱ ፡ ምክር ፡ መስማት ፡ ነው ።
ክመ ፡ ሜጡ ፡ ሰራጵዮን ፡ ወባዕዳን ፡ በትምህርታቲሆሙ ፡ ብዙኃን ፡ እምፈያት ፡ ወዘማውያን ።
ሰራጵዮን ፤ ሴሎችም ፡ እነ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዊር ፡ መከረው ፡ አስተምረው ፡ ከወንበዶች ፡ ከዘማውያን ፡ ወገን ፡ ብዙዎችን ፡ እንደ ፡ መለሱ ። ዘማውያን ፤ እንደ ፡ አትናስያ ፡ ተርክ ።
ወእምኔሃ ፡ ፍርሃታት ፡ ወምንዳቤያት ፡ ዘበእደ ፡ መላእክት ፡ ክመ ፡ አባ ፡ ወቅሪስ ።
ከዚህም ፡ አንዱ ፡ ፍርሀት ፡ ዘበእደ ፡ መላእክት ፤ ምንዳቤ ፡ ዘበእደ ፡ መላእክት ፡ ብለህ ፡ ግጠም ። በመላእክት ፡ ቃል ፡ የሚሆን ፡ ፍርሀት ፡ ነው ። እንደ ፡ አባ ፡ ወቅሪስ ፤ ይህ ፡ ወቅሪስ ፡ መልክ ፡ መልክም ፡ መልኩ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ የመሰለ ፡ ጌጸኛ ፡ ደብተራ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ ያንዱን ፡ መኰንን ፡ ሚስት ፡ ተነጋገራት ፤ ነገ ፡ እንደሆን ፡ እንጂ ፤ ዛሬስ ፡ አይሆንም ፡ አለችው ። በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ራእይ ፡ ያያል ፤ እንደ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፤ ንጉሥ ፡ ከዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ባለሟሎቹ ፡ በወዲያና ፡ በወዲህ ፡ ከበው ፤ አምስት ፡ ያልተጋዙ ፡ በቀኝ ፤ አምስት ፡ የተጋዙ ፡ በግራ ፡ ቁመው ፤ እሱ ፡ ከወደ ፡ ተጋዙት ፡ ሁኖ ፤ ንጉሥ ፡ በዓይነ ፡ መዓት ፡ ሲመለከተው ፤ ከባለ ፡ ሟሎቹ ፡ አንዱ ፡ መጥቶ ፡ አንተ ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ በዓይነ ፡ መዓት ፡ ያይሃል ፡ ምን ፡ አድርገሃል ፤ እንግዴህ ፡ አልደ

ግምም ፡ በልና ፡ ላስታርቅህ ፡ ሲለው ፡ አየ ። ሂላኔ ፡ የምትባል ፡ ከነጽሮ ፡ የደረሰች ፡ ሴት ፡ ነበረች ፤ ሂዶ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሕልም ፡ አየሁ ፡ አላት ። ምን ፡ አስበህ ፡ ኑሯል ፡ ብትለው ፡ ነገራት ። እንኪያስ ፡ ንጉሡ ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ ባለ ፡ ሟሎቹም ፡ መላእክት ፡ ናቸው ። አምስት ፡ ያልተጋዙ ፡ በቀኝ ፤ ሐምስ ፡ ጠባባት ። አምስት ፡ የተጋዙ ፡ በግራ ፤ ሐምስ ፡ አብዳት ፡ ናቸው ። አንተ ፡ ወደ ፡ ተጋዙት ፡ መሆንህ ፤ ሐምስ ፡ አብዳት ፡ ከተባሉት ፡ ልትቆጠር ፡ ኑሯል ፤ ያም ፡ አልደግምም ፡ በልና ፡ ላስታርቅህ ፡ ያለህ ፡ መልአክ ፡ ዑቅቢህ ፡ ነው ፡ አለችው ። እንዴት ፡ ልሁና ፡ አላት ፤ ጥለኸው ፡ ሂድ ፡ አለችው ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያውቀኛልሳ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ ልሂድ ፡ አላት ። ተራ ፡ ልብስ ፡ ለብሰህ ፤ አልባሌ ፡ መስለህ ፡ ሂድ ፡ ሰው ፡ እንዳያውቅህ ፡ አለችው ። እንዳለችው ፡ ሁኖ ፡ እስክንድርያ ፡ ደረሰ ። ከእስክንድርያ ፡ ደግሞ ፡ አስቄጥስ ፡ ገብቶ ፡ መንሶሰ ፡ ከፍጹምነት ፡ ደርሶ ፡ አርፏልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ምንዳቤ ፡ ዘበእደ ፡ መላእክት ፤ በመላእክት ፡ እጅ ፡ የሚሆን ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ እንጣዎስ ፡ አሞራዊ ፤ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ታውቋል ። ይህ ፡ እንጣዎስ ፡ ቀሳውስትን ፡ ዲያቆናትን ፡ የሚበድል ፤ እነሱ ፡ ቅዳሴ ፡ ሲገቡ ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ እየ ፡ ገባ ፤ መሥዋዕት ፡ እየ ፡ ሰረቀ ፡ እየ ፡ ቀማ ፡ የሚወስድ ፡ ሴባ ፡ ወንበዴ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ እንደ ፡ ለመደ ፡ ሊሰርቅ ፡ ሊቀማ ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ቢገባ ፡ መላእክት ፡ ሐጸ ፡ እሳት ፡ ኩናተ ፡ እሳት ፡ ይዘው ፡ ታዩት ፤ ደነገጠ ። እንዴት ፡ ልሁን ፡ አላቸው ፤ ሂደህ ፡ ተጠመቅ ፡ አሉት ፤ አምኖ ፡ ተጠምቆ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሙቷልና ።
ወእምኔሃ ፡ ጽዋዔ ፡ ዘእምእግዚአብሔር ፡ ክመ ፡ ጽዋዔ ፡ አርሳንዮስ ።
ከዚህም ፡ አንዱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጸራት ፡ ነው ፤ አርሳንዮስ ፡ እንደ ፡ ተጸራ ።

ተስእሎ ፡ ፸፪ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ ጸሐፈ ፡ ኀንት ፡ ጸሐፈ ፡ ግብረ ፡ አርሳንዮስ ፡ በውስተ ፡ ቀዳሚሁ ፡ ለመጽሐፍ ፡ እምቅድመ ፡ ትምህርቱ ፡ አዕሩግ ።

ጳላድዮስ ፡ የአርሳንዮስን ፡ ነገር ፡ ከመጽሐፈ ፡ ገኝት ፡ በመጀመሪያው ፡ የጻፈው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።
ዘበእንተ ፡ ዐኣት ፡ እምዓለም ፡ ኀበ ፡ ምኔት ።
ፈት ፡ ከዓለም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ማኅበር ፡ መግባት ።
ወዐኣተ ፡ መነኰስ ፡ እምኔት ፡ ኀበ ፡ ጽሙና ፡ በውስተ ፡ በዓት ።
ኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከማኅበር ፡ ወጥቶ ፡ ተባሕትዎ ፡ መያዝ ፡ እንዲገባ ፡ አበው ፡ ከስተማሩት ፡ ትምርት ፡ አስቀድሞ ፡ የአርሳንዮስን ፡ ነገር ፡ የጻፈው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።
ይቤ ፡ መተርጉም ፤ በእንተ ፡ ዘተጸውዐ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ምኔት ።
በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አስቀድሞ ፡ ከዓለም ፡ ወደ ፡ ገዳም ።
ወእምኔት ፡ ኀበ ፡ በዓት ።
ኋላ ፡ ከማኅበር ፡ ወደ ፡ ተባሕትዎ ፡ ስለ ፡ ተጸራ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማክበር ፡ ነው ።
በእንተ ፡ ገዝኤ ፡ አቅደመ ፡ ገድስ ፡ ዚኣሁ ።
ነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክቡር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ጳላድዮስ ፡ ያርሳንዮስን ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ ጻፈው ።
ወሠርዐ ፡ በአምሳሊሃ ፡ ትምህርቶሙ ።
አበውም ፡ ትምርታቸውን ፡ በአርሳንዮስ ፡ ግብር ፡ አምሳል ፡ አስተማሩ ። አንድም ፤ በአምሳሊሁ ፤ ሥራቸውን ፡ በአርሳንዮስ ፡ አምሳል ፡ ሠሩ ።
ወዜናሁስ ፡ ክመዝ ፡ ጽሑፍ ።
ነገሩም ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ ተጽሕፏል ።
ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ይትመነደብ ፡ በውስተ ፡ ዓለም ፡ እምዓፅራት ፡ ብዙኃት ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳለ ፡ ከብዙ ፡ ፃር ፡ ጋር ፡ የተነሣ ፡ ይጨነቅ ፡ ነበር ።
ወክልሐ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምሕማመ ፡ ልብ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፤ ኦ ፡ እግዚኦ ፡ ሥርዐኒ ፡ ዘክመ ፡ እፎ ፡ አሐደ ።
ኋላ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ እንድኖር ፡ እዘዘኝ ፡ ብሎ ፡ በልቡናው ፡ አዝኖ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመለከተ ።
ወሰምዐ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤሎ ፡ ኦ ፡ አርሳኒ ፡ ጕየይ ፡ እም ስብእ ፤ ወእንተ ፡ ትሐይ ።
ጌታም ፡ ዓለሙን ፡ ጥለኸው ፡ ሂድ ፤ ትድናለህ ፡ አለው ።
ወሶበ ፡ ኮነ ፡ በውስተ ፡ ማኅበር ፡ ኮነ ፡ ጥዉቀ ፡ እምሕዋሳቱ ።
ከማኅበር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ሕዋሳቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ማኅበርን ፡ አልችልለት ፡ አሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወፍልሰተ ሕሊናቲሁ ።
ሕሊናው ፣ በክነ ፤ ዓይን ፣ ካየ ፤ ጆሮ ፣ ከሰማ ፤ ልቡና ፣ ይባክናልና ። እስመ ፣ እምርእይ ፣ ወሰሚዐ ፣ ነገር ፣ ት ከውን ፣ እንጉጋዌ ፣ ሕሊና ፣ ብሎ ፣ ያመጣዋል ።

ይቤሎ ፣ እግዚአብሔር ፣ ጕየይ ።
ጌታ ፣ ከሰው ፣ ተለይ ።

ወአርምም ።
ተባሕትዎን ፣ ያዝ ።

ወጎዳዕ ።
በዓት ፣ አጽንተህ ፣ ኑር ፣ አለው ። ክነ ፣ ጥውቀ ፣ ያለ ው ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ነው ፣ ቢሉ ። መንኖ ፣ ገዳም ፣ ገባ ፤ የማኅበሩ ፣ ምግባቸው ፣ እንዲህ ፣ እንደ ፣ ንብረ ፣ ያ ለ ፣ ነው ። ክነ ፣ ገለፈቱ ፣ ይመገቡታል ። እሱ ፣ ያን ፣ እየ ፣ ፈለፈለ ፣ እየ ፣ ጠረጠረ ፣ ሲመገብ ፣ አይቶ ፣ አ በ ፣ ምኔቱ ፣ ዛሬ ፣ ገና ፣ የማልችለው ፣ ሰው ፣ መጣብ ኝ ፣ ብሎ ፣ አዘነ ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ሥርዓተ ፣ ማኅበር ፣ እሠራለሁ ፣ ብሎ ፣ ከጠገቡ ፣ የሚቀመጠውን ፣ ሰው ፣ ባንተ ፣ ሥ ራት ፣ የምሠራብህ ፣ ነኝና ፣ እንደሱ ፣ እየጠረጠርህ ፣ ብላ ፣ አለው ። ካርሳንዮስ ፣ ባጠገብ ፣ ሁኖ ፣ እንደሱ ፣ እየጠረጠረ ፣ ሲበላ ፣ ይህ ፣ ሊል ፣ ብሎ ፣ በጥፊ ፣ መ ታው ። አወቀበት ፣ ዝ ፣ ጽፍአት ፣ ዘአርሰኒ ። ይህ ፣ የኔ ፣ ተጣሣጽ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እሱ ፣ ምን ፣ አድርጎ ፣ ብሎ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ አመለከተ ፤ ተባሕትዎ ፣ ያዝ ፣ አለው ፤ ከማኅበሩ ፣ ወጥቶ ፣ እልፍ ፣ ብሎ ፣ ብ ቻውን ፣ ተቀመጠ ፣ ረዱ ፣ እንዲህ ፣ እንደ ፣ ጕልቋስ ፣ ያለ ፣ ቅጠል ፣ አለ ፣ ምግቡን ፣ በዘያ ፣ እያለሰለ ሰ ፣ እንደ ፣ ገመንም ፣ እየቀቀለ ፣ ወጥ ፣ እየሠራ ፣ ሲ ሰጠው ፣ ሰነበተ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ አበ ፣ ምኔቱ ፣ ረ ዱን ፣ አስጠርቶ ፣ ከኛ ፣ ከተለያችሁ ፣ ምን ፣ ጨመራ ችሁ ፣ ምንስ ፣ ከፈላችሁ ፣ ብሎ ፣ ጠየቀው ፣ እኛስ ፣ የጨመርነው ፣ ነገር ፣ የለ ፤ የከፈልነውም ፣ የለ ፤ እን ደ ፣ ጕልቋስ ፣ ያለ ፣ ቅጠል ፣ አለ ፣ ያን ፣ እየቀቀልሁ ፣ በዚያ ፣ እሰጠዋለሁ ፣ አለ ፤ ይኸማ ፣ እንግዲያ ፣ በገ ዳም ፣ ወጥ ፣ ከመብላት ፣ ሌላ ፣ ምን ፣ ይያደርግ ፣ ኑሩ ዋል ፣ ብሎ ፣ ዝም ፣ አለ ። እንዲህ ፣ ሁኖ ፣ ሰለ ፣ ያሳ ይ ፣ የሚባል ፣ ሌላ ፣ ሰው ፣ ከበረሀ ፣ ሂዶ ፣ ሰሌን ፣ ቁርጠ ፣ ሲመለስ ፣ ደረቂያ ፣ ሰጡት ፣ በወሀ ፣ ነክሮ ፣ ሲበላ ፣ ከማኅበሩ ፣ አንዱ ፣ አይቶ ፣ ርእዩ ፣ ያሳይሃ ፣ በገዳም ፣ ይበልዕ ፣ ጸብኔ ፣ ብሎ ፣ ለአበ ፣ ምኔቱ ፣ ነገረበት ። ይህን ፣ ሰምቶ ፣ ሥርዓት ፣ እሠራለሁና ፣ ማኅበሩን ፣ ተሰብሰቡ ፣ አለ ፤ አርሳንዮስንም ፣ እንዳ ትቀር ፣ ና ፣ ይገባልና ፣ አለው ፤ ሄደ ፤ ክዚያ ፣ በኋላ ፣ በሉ ፣ እስኪ ፣ ፍረዱኝ ፣ በገዳም ፣ ወጥ ፣ መብላት ፣ ይገባልን ፤ አርሳንዮስ ፣ እስኪ ፣ ፍረዱኝ ፣ አለው ፤ አ ወቀበት ፤ አጸበኒ ፣ ምግባረ ፣ ዝንቱ ፣ ገቢር ፣ ግብጻዊ ፣ አለ ። ፍልስፍና ፣ አውቃለሁ ፤ ሥርዓተ ፣ ቤተ ፣ ክር ስቲያን ፣ አውቃለሁ ፤ የዚህ ፣ የገበሬ ፣ ነገር ፣ የማይ መረመረኝ ፣ ሆነ ፣ ብሎ ፣ አመለከተ ፤ ርቀህ ፣ ሂድ ፣ አለው ፤ ከዚያ ፣ ደግሞ ፣ ተነሥቶ ፣ ዓሥር ፣ ምዕራ ፍ ፣ ያህል ፣ ርቆ ፣ ሄዶአልና ፣ እንዲህ ፣ አለ ።

ወሶበ ፣ ጸልአ ፣ እኪተ ፤ ወአብደረ ፣ ጒሩተ ፣ ወናይተ ።
ክፋ ፣ ሥራን ፣ ቢጸላ ፤ በጎ ፣ ሥራን ፣ ቢወድ ።

ኮነ ፣ ሎቱ ፣ እግዚአብሔር ፣ መምህረ ።
ጌታ ፣ መምር ፣ ሆነው ።

ቅድመ ፣ በእንተ ፣ ምንኵስና ፤ ወድጎረኒ ፣ በእንተ ፣ ብሕትውና ።
አስቀድሞ ፣ ከዓለም ፣ ወደ ፣ ገዳም ፣ የመሄድን ፤ ኋ ላ ፣ ደግሞ ፣ ከማኅበር ፣ ወጥቶ ፣ ተባሕትዎ ፣ የመያ ዝን ፣ ነገር ፣ አስተማረው ።

ተስእሎ ፣ ፵፫ ።

ይቤሎ ፣ ኦኅው ፤ ተርጕም ፣ ለን ፣ ትርጓሜሆሙ ፣ ለእሉ ፣ ፪፥ ፣ ጽዋኤ ።
የሁለቱን ፣ አጸራር ፣ ነገር ፣ ተርጕመህ ፣ ንገረን ።

ይቤ ፣ መተርጕም ፣ ጽዋኤ ፣ ቀዳሚት ።
መጀመሪያዪቱ ፣ አጸራር ።

ወይእቲ ፣ ብሂሎቱ ፣ ጕየይ ፣ ወተሐደ ።
ጕየይ ፣ ማለቱ ።

ትርጓሜሁ ።
ቢተረጕሙት ።

ለእመ ፣ ፈቀድክ ፣ ከመ ፣ ትድኀን ፣ እሞት ፣ ዘዕልወተ ፣ ትእዛዝ ።
ሕግ ፣ በማፍረስ ፣ ከመጣ ፣ ሞት ፣ ልትድን ፣ ከወደ ህ ።

ጎድግ ፣ ጥሪተክ ፣ ወሰብእክ ፣ ወቤተክ ።
ገንዘብህን ፣ ቤተ ፣ ሰብኽን ፣ ጥለህ ፣ ሂድ ።

ወኩን ፣ ፈላሴ ፣ ውስተ ፣ ገዳም ፣ ኀበ ፣ እሰ ፣ ይገብሩ ፣ ትእዛዘትየ ።
እኔ ፣ ያዘዝኩትን ፣ ሥራ ፣ ከሚሠሩ ፣ ጋራ ። አንድ ም ፣ በሚሠሩበት ፣ ገዳም ፣ ፈላሲ ፣ ሁነህ ፣ ኑር ።

ወአኀተ ፣ ተሐደ ።
ሕያው ፣ ትሆናለህ ፣ ማለት ፣ ነው ።

በክመ ፣ ተጽሕፈ ፣ አንሰ ፣ አፍቀርኩ ፣ ትእዛዛቲከ ፣ ወአሕይወኒ ፣ በጸ ጋከ ።
እንዲህ ፣ ተብሎ ፣ እንደተነገረ ።

ወባህሱኒ ፣ በእንተ ፣ ጽዋኤ ፣ ክዕቢት ።
የሁለተኛዪቱም ፣ አጸራር ፣ ነገር ።

ጕየይ ።
ጕየይ ፣ ማለቱ ።

ዘውእቱ ፣ እማኅበር ።
ከማኅበር ፣ ውጣ ፣ ነው ።

ወባህሱ ፣ አርምም ፣ ወጎዳዕ ።
ያለውም ፣ ይህ ፣ ነው ።

ዘውእቱ ፣ ኢትጎድግ ፣ ይባኡ ፣ ብዙኃንኒ ፣ ኀቡከ ፣ ወይትናገሩ ፣ ምስሌ ከ ፣ ወይሁኩከ ።
ኢትጎድግ ፣ ብዙኃንኒ ፤ ይባኡ ፣ ብዙኃን ፣ ብሎ ፣ ይ ገጥሻል ፤ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ወዳንተ ፣ እየገቡ ፣ እያናገሩ ፣ ያናውጡህ ፣ ዘንድ ፣ አታሰናብት ፣ ማለት ፣ ነው ።

እስመ ፣ እምርእይ ፣ ወሰሚዐ ፣ ነገር ፣ ብዙኅ ፣ ትከውን ፣ እንጉግወ ፣ ሕሊናት ።
ከማየት ፣ ከመስማት ፣ የተነሣ ፣ ሕሊናህ ፣ ትባክናለች ና ፤ አንድም ፣ እንጉጋዌ ፣ ሕሊና ፤ የሕሊና ፣ መበከን ፣ ይመጣልና ፣ ኢትጎድግ ።

ወፈቀድሰ ፣ አርምሞተ ፣ ልሳን ።
አርምም ፣ ማለቱ ።

እምነገር ፣ ምስለ ፣ ሰብእ ።
ከሰው ፣ ጋራ ፣ ከመነጋገር ፣ ነው ።

በህሳዊሆሙ ።
ሳሉ ።

ወጽግዌ ፣ ልብኒ ።
ሳዳሰ ፣ ማለቱም ።

እምተናግሮ ፣ ምስሌሆሙ ።
ከነዚያ ፣ ጋራ ፣ ከመነጋገር ፣ ነው ።

እንዘ ፣ ኢህለዉኢ ።
ሳይኖሩ ።

እስመ ፣ ነዋ ፣ ይኄሊ ፣ ውእቱ ፣ ውስተ ፣ ስን ፣ ወላሕይ ፣ ዘእምእንስት ፣ ወተባዕት ፣ በፍትወተ ፣ ዝሙት ።
ዝሙትን ፣ በመሸት ፣ መልከዓ ፣ አንስት ፤ መልከዓ ፣ ዕ ደው ፣ ማየትን ፣ ያስባልና ፣ ሳይኖሩ ፣ መነጋገር ፣ ነው ።

ወይሰሐብ ፣ እንከ ፣ በልቡ ፣
በልቡ ፣ ወደ ፣ ፈቲው ፣ ይሳባልና ።

ወዳግመኒ ፣ ናሁ ፣ ይኄሊ ፣ ውስተ ፣ ግብራት ፣ ክልኣን ።
ዳግመኛም ፣ ሌላ ፣ ነገር ፣ ያስባልና ።

ወይትቄጣዕ ፣ በልቡ ፣ ዲበ ፣ መንፈቀ ፣ ሰብእ ፣ ወያነውሮሙ ።
በልቡናው ፣ እሡሌቶቹን ፣ ሰዎች ፣ ይጸላል ፣ ይነቅፋ ል ።

ወየኃሥሥ ፣ እመንፈቀ ፣ ሰብእ ፣ አክበሮ ፣ ወስባሔ ።
እሡሌቶቹን ፣ ያከብራል ፣ ያመሰግናል ፤ አንድም ፣ ቀ ድሞ ፣ እንዲያ ፣ ያለ ፣ ክፉ ፣ ሥራ ፣ ስሠራ ፣ አነገሌ ፣ ቢያዩኝ ፣ እንደምን ፣ ባሙኝ ፣ በነቀፉኝ ፣ ኑሯል ፤ ዛ ሬስ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ በጎ ፣ ሥራ ፣ ስሠራ ፣ ቢያዩ ፣ እን ደምን ፣ ባከበሩኝ ፣ ባመሰገኑኝ ፣ ኑሯል ፣ ይላል ።

በነገረ ፣ ሕሊናቲሁ ።
በሕሊናው ፣ እየተነጋገረ ።

ወጊዜ ፣ ይሔሊ ፣ ውስተ ፣ ሥርዓተ ፣ ንዋይ ።
አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ ገንዘብ ፣ ማኖር ፣ ያስባል ፣ አለ ፤ በገዳም ፣ ገንዘብ ፣ ቢያኖሩ ፣ ምን ፣ ይጎዳል ፣ መርዳት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ይላል ።

ወሥርዓተ ፣ ሚመት ።
መሾም ፣ ያስባል ፣ አለ ፣ በገዳም ፣ መሾም ፣ ምን ፣ ይ ጐዳል ፣ ረድኤ ፣ መሆን ፣ ነው ፣ እንጂ ።

ወበእንተዝ ፣ ዖበ ፣ ተስእልዎ ፣ ለትዱስ ፣ መቃርዮስ ።
ይህ ፣ እንደምን ፣ ነው ፣ ብለው ፣ መቃርዮስን ፣ ቢጠ ይቁት ።

እፎ ፣ ይደሉ ፣ ለወጣኒ ፣ ነመ ፣ ይኩን ፣ ውስተ ፣ ጽሙና ፣ ፀዓቱ ።
ወጣኒ ፣ ከሰው ፣ ተለይቶ ፤ ከበዓት ፣ ተከቶ ፣ ይኖር ፣ ዘንድ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ይገባል ፣ ቢሉት ።

ይቤ ፣ ኢይክውን ፣ ሎቱ ፣ ተናግሮ ፣ ምስለ ፣ ሰብእ ፣ ፍጹመ ።
ከሰው ፣ ጋራ ፣ መነጋገር ፣ የሰው ፣ ነገር ፣ ማሰብ ፣ ፈ ጽሞ ፣ አይኑረው ፣ አለ ።

እስመ ፣ ኢይረብሕ ፣ ምንተኒ ፣ ለእመ ፣ ኢእንዘ ፣ ሕዋሳቲሁ ፣ እምተናግሮ ፣ ምስለ ፣ ሰብእ ።
የውሥጥ ፣ የአፍኣ ፣ ሕዋሳቱን ፣ ከሰው ፣ ጋራ ፣ ከመ ነጋገር ፤ የሰው ፣ ነገር ፣ ከማሰብ ፣ ወስኖ ፣ ገቶ ፣ ክልያ ዘ ።

ወኢያስተጋብኦ ፣ ሕሊናሁ ፣ ውስተ ፣ ጽሙና ።
ሕሊናውን ፣ በ ኮባሕትዎ ፣ ክልወሰነ ፣ ምንም ፣ ምን ፣ አይጠቀምምና ።

www.ethiopianorthodox.org

ተስእሎ ፡ ፸፬ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ጽሑፍ ፡ ክመ ፡ እጉ ፡ ይቤሎ ፡ ለአርሳንዮስ ።

አንድ ፡ መነኰሰ ፡ አርሳንዮስን ፡ እንደ ፡ ጠየቀው ፡ ተነግሯል ።

ኦአበየ ፡ እስመ ፡ ሕሊናየ ፡ ተሀውክኒ ።

አባቴ ፡ ሕሊናዬ ፡ ታውክኛለች ።

ወትብለኒ ፡ ኢትክል ፡ ትጹም ፡ ወትግበር ።

ጸም ፡ ትጸም ፡ ዘንድ ፤ ትሩፋት ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ አይቻልህምና ።

ወፃእ ፡ እንከ ፡ ወተለእከ ፡ ለይኩግን ።

ወጥተህ ፡ ድኩማንን ፡ እርዳ ።

ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትእዛዝ ፡ በላይ ።

ከሁሉም ፡ ይህ ፡ ይበልጣል ፡ ትለኛለች ፡ አለ ።

ወይቤሎ ፡ አርሳንዮስ ፡ ብላዕ ፡ ወስተይ ፡ ወኑም ።

አርሳንዮስ ፡ ሲመክረው ፡ ብላ ፤ ጠጣ ፤ ተኛ ።

ወኢትግበር ።

ሥራም ፡ አትሥራ ።

እምበኅትከ ፡ ባሕቱ ፡ ኢትፃዕ ።

በዓትህን ፡ ግን ፡ ለቀህ ፡ አትውጣ ።

ወዖበ ፡ ነበረ ፡ ሠላሰ ፡ መዋዕለ ፡ ጸሩዐ ።

ሦስት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ፈቶ ፡ በዋለ ፡ ጊዜ ።

ነሥአ ፡ እንከ ፡ ጎዳጎ ፡ ደጓዕሌ ።

እንዳይህስ ፡ ጥቂት ፡ ልሥራ ፡ ብሎ ፡ ሰሌን ፤ አንድም ፡ ጣራምጣ ፡ አቀረበ ።

ወሠጠቆ ።

ሰሌን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ሰለሰለው ። ግራምጣ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ሠነጠቀው ።

ወበዕለት ፡ ካልዕት ፡ አርሐቦ ።

በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ከወሀ ፡ ነከረው ።

ወወጠነ ፡ ክመ ፡ ይጽፍሮ ።

ሰሌን ፡ ቢሉ ፡ ይታታ ፤ ግራምጣ ፡ ቢሉ ፡ ይሰፋ ፡ ጀመር ።

ወዖበ ፡ ፈጸመ ፡ ይቤ ፡ አንብብ ፡ ንስቲተ ።

ያን ፡ ሰፊጽም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሳድርስ ፡ መጽሐፍ ፡ ልመልከት ፡ አለ ።

ወዖበ ፡ ርኅበ ፡ ይቤ ፡ እፈጽም ፡ ወእበልዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ሣዕር ።

ቢረበውም ፡ ሥራዬን ፡ ፈጠርሽ ፡ አለብኝ ፡ አለብኝ ፡ ሳልል ፡ እመገባለሁ ፡ አለ ።

ወክመዝ ፡ ቀርበ ፡ በዘ ፡ ንስቲተ ፡ ንስቲተ ፡ በረድኡተ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እያለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ጓብሩ ፡ ቀረበ ።

እስክን ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ መኃርኒው ፡ ዘቀዳሚ ።

ከቀድሞ ፡ መጓርጉ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ቀረበ ።

ወንሥእ ፡ ሥልጣን ፡ ዳዕ ፡ ሕሊናቲው ።

በክፉ ፡ ሕሊዎት ፡ ሠለጠነባቸው ።

ወገብኔ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ክፍል ፡ ደኃሪ ፡ ውስተ ፡ ትምህርተ ፡ አዕሩግ ፡ በእንተ ፡ ጽሙና ፡ ውስተ ፡ በዓት ።

ይህም ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ካበዓት ፡ ተክቶ ፡ መኖር ፡ እንዲገባ ፡ አበው ፡ ባስተማሩት ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ተጽፏል ።

ወጽሑፍ ፡ ካዕበ ፡ ውስተ ፡ ትምህርተ ፡ አዕሩግ ፡ ፍቅር ፡ ወምሕረት ።

ዳግመኛም ፡ እርድና ፡ እንዲገባ ፡ አበው ፡ ባስተማሩት ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ፍቅር ፡ ወምሕረት ፡ የሚል ፡ ተጽፏል ።

ተስእሎ ፡ እጉ ፡ ለአረጋዊ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሀለዉ ፡ ክልኤቱ ፡ አኃው ።

ጽሑፍ ፡ ካዕበ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሁለት ፡ አኃው ፡ ነበሩ ፡ ብሎ ፡ እጉ ፡ አረጋዊን ፡ ጠየቀው ፡ አንዱ ፡ ራሱን ፡ አርቆ ፡ አንዱ ፡ በቁመ ፡ ሌላ ፡ ነው ።

አሐዱ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ በዓቱ ።

ይተርክል ፡ አንዱ ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፤ በበዓት ፡ ተክቶ ፡ የሚኖር ፡ ነው ።

ወይጸውም ፡ ዕዳስ ፡ መዋዕለ ፡ ወዕዳስ ፡ ለያልየ ።

ስድስት ፡ ቀን ፡ የሚጸም ፡ ነው ።

ወያጸሙ ፡ ነሩዶ ፡ ብዙኃ ።

ብዙ ፡ ትሩፋት ፡ እየሠራ ፡ ሰውነቱን ፡ የሚያደክም ፡ ነው ።

ወኢሐዱ ፡ ይትለእክ ፡ ለድውያን ።

አንዱ ፡ ድውያንን ፡ የሚረዳ ፡ ነው ።

አይኮ ፡ እምኔሆሙ ፡ ጸግው ፡ ውኩፍ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈድፋደ ፡ እምን ፡ ቢጹ ።

ከሊህ ፡ ከሁለቱ ፡ ጊታ ፡ ድካሙን ፡ ካንዱ ፡ ይልቅ ፡ የሚቀበልለት ፡ ማናቸው ፡ ነው ፡ አለ ።

ወእውሥእ ፡ አረጋዊ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ለእመኒ ፡ ይሰቀል ፡ ገዝቱ ፡ ጸዋሚ ፡ በተራንብተ ፡ አዕድንቲው ።

አረጋዊም ፡ ያ ፡ ጸዋሚው ፡ ተሐራሚው ፡ በግንባሩ ፡ ቢተክል ፡ በሸፍሸፍቱ ፡ ቢሰቀል ። አንድም ፡ ሥጋው ፡ ሁሉ ፡ አልቆ ፡ ባንዲት ፡ ጠጕሩ ፡ ብቻ ፡ ቢንጠለጠል ።

ኢይትኄረይ ፡ ምስለ ፡ ዘይትለእክ ፡ በቅድመ ፡ እ ፡ አብሐር ።

ረዱን ፡ አይተካከለውም ፡ አለ ።

ቦኑኬ ፡ መስተጻርራን ፡ ቃላተ ፡ አበው ።

የአበው ፡ ቃላቸው ፡ ይለያያልን ፤ ትች ።

ወእመ ፡ አኮ ፡ ምንት ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለውእቱ ።

ካልተለያየስ ፡ ይህ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ያ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የዚህ ፡ ትርጓሜው ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ አሉት ።

ይቤ ፡ መላ ርጉም ፤ ኢኮኑ ፡ ቃላተ ፡ አበውሰ ፡ መስተሣርራት ።

የአበውስ ፡ ነገራቸው ፡ አይለያይም ።

አላ ፡ ውእቶሙ ፡ ይሜህሩ ፡ ለነሶሱ ፡ አሐዱ ፡ እሐዱ ፡ ዘይገብርዋ ፡ በ ጎድኣት ፡ ዘኪያሁ ፡ ይኄይዶ ፡ ወይበንሥዖ ፡ ሎቱ ።

ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ላንዱም ፡ ላንዱ ፡ የሚሻለውን ፡ የሚበልጠውን ፤ ለሱ ፡ የሚስማማውን ፡ የሚረባ ፡ የሚጠቅመውን ፡ በተባቅቦ ፡ ሁኖ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ያስተምሩታል ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ ናሁ ፡ ኀብሩ ፡ በዕሪና ፡ ዘይክውን ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ ስን ፡ ወ ክማሁ ፡ ድውይኒ ፡ ዘየአሹት ፡ ወዘይትለእክ ፡ ካዕበ ፡ በጥቡዕ ፡ ልብ ፡ ወበትፍሥሕት ።

ባሕታዊ ፡ ዘበዓድአት ፤ ድውይ ፡ ዘበአኩቴት ፤ ረድ ፡ ዘበጥብዓት ፡ አንድ ፡ ሁነዋልና ።

ወእመ ፡ አኮ ፡ ለድውያን ፡ አው ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ ወምኔት ።

እርድናው ፡ ለድውያንም ፡ ለባሕታውያንም ፡ ቢሆን ፡ ሲል ፡ ነው ።

ወዖበ ፡ አእመረ ፡ ሰይጣን ፡ ዘንተ ፡ ቀንኣ ፡ ኅዕሌሆሙ ።

ሰይጣን ፡ ይህን ፡ መተካከላቸውን ፡ ቢያውቅ ፡ ቀናባቸው ።

ወተዜነወ ፡ በእንተ ፡ ዘክመ ፡ ያኃጥኦሙ ፡ ለዮሱ ፡ ጸዲ ፡ እምሠላስ ፡ ትፍፋት ፡ በእስተሐውዞ ፡ ያፍቅር ፡ ጸዲ ፡ ትፍፋተ ፡ ካልኢ ።

ከሶስቱ ፡ ትሩፋት ፡ አንዱንም ፡ አንዱን ፡ ያሰጣቸው ፡ ዘንድ ፤ ላንዱ ፡ ያንዱን ፤ ላንዱ ፡ ያንዱን ፡ ሥራ ፡ የሚበልጥ ፡ አስመስሎ ፡ በማሳየት ፡ ተተንኰላቸው ፤ አንዱ ፡ ያንዱን ፤ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ትሩፋት ፡ ይወድ ፡ ዘንድ ።

ወያኅጕል ፡ እንከ ፡ ጽሙና ።

ተባሕትዎን ፡ ያፈርስ ፡ ዘንድ ።

ወያዓፅብ ፡ መልእክተ ፡ ለእለ ፡ ይትሰእኩ ፡ ለብሔታን ፡ ዘውስተ ፡ ጽሙና ።

በተባሕትዎ ፡ ያሉ ፡ ባሕታውያንን ፡ ለሚረዱ ፡ እርድናን ፡ ጭንቅ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል ።

ወያበስሐውዝ ፡ ጽሙና ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ አልዐሙ ፡ ክሂል ፡ በእንተ ፡ ጎድኣት ።

ለተባሕትዎ ፡ ክሂል ፡ የሌላቸውን ፡ ተባሕትዎ ፡ የሚበልጥ ፡ አስመስሎ ፡ ያሳያቸዋል ።

ክመ ፡ ያኅጕሎሙ ፡ ክልኤተ ፡ ትፍፋተ ፤ ወያኅጕል ፡ ጎድኣተ ፡ ወመልእክተ ።

እርድናውንም ፡ ተባሕትዎውንም ፡ ያሰጣቸው ፡ ዘንድ ።

ወያጎይስ ፡ መልእክተ ፡ ጎቤሆሙ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ እንዘ ፡ ኦልዖሙ ፡ ክሂል ፡ ለተለእኩ ።

በተባሕትዎ ፡ ላሉትም ፡ ለመርዳት ፡ ክሂል ፡ ሳይኖራቸው ፡ እርድናን ፡ የሚበልጥ ፡ አስመስሎ ፡ ያሳያቸዋል ።

ክመ ፡ ያኅጥኦሙ ፡ ረባሒ ፡ እምክልኤ ፡ ግብር ።

ከሁለቱ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ረብሕ ፡ ጥቅም ፡ ያሰጣቸው ፡ ዘንድ ፤ አልጸም ፡ አልጸልይ ፡ አልረዳ ፡ ከዚህ ፡ ተወ ትፌ ፡ እንዲሉ ፡ ያደርጋቸዋል ።

ወክመዝ ፡ ያርኢ ፡ ለድውይኒ ፡ ኃጕለ ፡ በኃጢአ ፡ ጸም ፡ ወጸሎት ፡ ወመልእክት ።

ድውይንም ፡ አልጸም ፡ አልጸልይ ፡ አልረዳ ፤ በዚህ ፡ በደዌ ፡ ብቻ ፡ ምን ፡ እጠቀማለሁ ፡ እንዲል ፡ ያደርገዋል ።

ክመ ፡ ይሠግር ፡ እምትዕግሥት ፡ ወእኩቱት ።

ደዌውን ፡ ከመታገሥ ፤ ጊታን ፡ ከማመኣገን ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ።

ወይኅጣእ ፡ ረባሒ ፡ ደዌ ፡ ወኢይክል ፡ እንከ ፡ ስገቢረ ፡ ጽድቅ ።

የደዌውን ፡ ዋጋ ፡ ያጣ ፡ ዘንድ ፤ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ግማኝነት ፡ የማይቻለው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

ወይፈስዮ ፡ ለጽዱ ፡ እምን ፡ ይቱ ፡ ያውትር ፡ ፍልሰተ ፡ ለጎበ ፡ ምግባር ፡ ካልእ ።

ከሶስቱ ፡ አንዱንም ፡ አንዱን ፤ አንዱን ፡ ያንዱን ፡ ሥራ ፡ እንዲወድ ፡ ያደርገዋል ።

አኮ ፡ በእንተ ፡ ትፍፋ ።

ለሱ ፡ ይበልጽለት ፡ ብሎ ፡ አይደለም ።

ባሕቱ ፡ በእንተ ፡ ዕረፍት ፡ እምድካማተ ፡ ግብሩ ።

መነኰሰውን ፡ በሥራ ፡ ከሚደክመው ፡ ድካም ፡ አወጣው ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ። አንድም ፡ እሱ ፡ በመነኰሴው ፡ ሥራ ፡ ከሚደክመው ፡ ድካም ፡ አርፍ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ወገፍትየት ፡ እምውስተ ፡ ትጋድሎቱ ።

መነኰሴውን ፡ ትሩፋት ፡ ከመሥራት ፡ አወጣው ። አንድም ፡ ተገፍትየት ፡ ይላል ፤ እሱ ፡ በመነኰሴው ፡ ትሩፋት ፡ ድል ፡ ከመነሣት ፡ እድን ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ወበእንተ ፡ አእምሮተ ፡ አበው ፡ ስግብራተ ፡ ደዌያት ፡ በዘሎሙ ፡ ጸጋ ፡ መርሐ ፡ ጸጋ ፡ ወትምህርተ ፡ መክራ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጸጋ ፡ ከጸጋ ፡ ያደርሳልና ፤ መርሐ ፡ ጸጋ ፡ አለ ። አበውም ፡ ከጸጋ ፡ ወገን ፡ በተሰጣቸው ፡ ጸጋ ፤ የጦሩን ፡ ስልት ፤ የመከረውን ፡ ትምርት ፡ ስላወቁ ።

ይንገሩ ፡ ለሎሱ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ዘይኄርዎ ፡ እምሥራት ።

ላንዱም ፡ ላንዱ ፡ ከጦሩ ፡ መድኃኒት ፡ ከትሩፋት ፡ ወገን ፡ የሚሰማማውን ፡ ሥራ ፡ ያስተምሩታል ፡ እንጂ ፤ ቃላቸው ፡ የሚለያይ ፡ አይደለም ።

አባ ፡ አርሳንዮስ ፡ አእሚር ፡ ክመ ፡ ውእቱ ፡ ጽዮዕ ፡ ለቅኔ ፡ ጽሙና ።

አባ ፡ አርሳንዮስም ፡ ለተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ የጸና ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቆ ።

ወክመ ፡ ተጋደሎ ፡ ሰይጣን ፡ በሀኬት ።

ሰይጣን ፡ በሀኬት ፡ እንደ ፡ ተዋጋው ፡ አውቆ ።

ወአቍረረ ፡ መቀቶ ፡ ክመ ፡ ይነእ ፡ እምበዓቱ ።

በዓቱን ፡ ጥሎ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ መናደዱን ፡ እንዳበረደው ፡ አውቆ ።

ወክመ ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡ ጸንዐ ፡ ውስተ ፡ በዓቱ ፡ አዝማን ፡ ሕቀ ፡ ይትዐደው ፡ እምኔሁ ፡ ተቃትሎ ፡ ወይገብእ ፡ ኀቤሁ ፡ ፍልሐተ ፡ ጥብዓቱ ።

ጥቂት ፡ ቀን ፡ በበዓቱ ፡ ቢጸና ፡ ጦሩ ፡ እንዲጠፋለት ፤ ለትሩፋት ፡ መናደዱ ፡ እንዲመለስለት ፡ አውቆ ።

ወለእመ ፡ ወፅአ ፡ እምበዓቱ ፡ ይጠፍዕ ፡ ሥርዓተ ፡ ጽማዌሁ ።

በዓቱን ፡ ግን ፡ ለቆ ፡ ቢወጣ ፡ የደከመበት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ እንዲቀር ፡ አውቆ ።

ወኢይክል ፡ ይጽናእ ፡ ውስተ ፡ መልእክተ ፡ ድውያንኒ ።

ድውይ ፡ በመርዳት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዳይቻለው ፡ አውቆ ።

ወየኀጕል ፡ እንከ ፡ ክልኤተ ፡ ትሩፋተ ።

ሁለቱን ፡ ትሩፋት ፤ ርድናውንም ፡ ተባሕትዎውንም ፡ እንዲያጣ ፡ አውቆ ።

አምክሮ ፡ እንከ ፡ በክመ ፡ ቀደመ ፡ ቃል ።

ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፤ ብላዕ ፡ ወስተይ ፤ ኑም ፡ ወኢትግበር ። ባሕቱ ፡ ኢትፃዕ ፡ እምበዓትከ ፡ ብሎ ፡ መከረው ።

እጕኒ ፡ ዘተሰእሎ ፡ ለአረጋዊ ፡ በእንተ ፡ ክልኤቱ ፡ አኃው ።

የእኃውን ፡ ነገር ፡ ካረጋዊ ፡ የጠየቀው ፡ ሰሙም ።

ኮነኩ ፡ ዘተውህቦ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ሀብተ ፡ መልእክተ ፡ ድውያን ፡ ወአእሩግ ፡ ድኩማን ።

ድውያን ፤ ድኩማን ፤ አእሩጓን ፡ የመርዳት ፡ ሀብት ፡ የተሰጠው ፡ ነበርና ።

ወፈቀደ ፡ እንከ ፡ ሰይጣን ፡ ክመ ፡ ያኅጥኦ ፡ አክሊሎ ።

ሰይጣን ፡ ክብሩን ፡ ሊያሰጣው ፡ ወዶ ።

ወአስተሐወከ ፡ እንከ ፡ ሶቱ ፡ ጽሙና ፡ ክመ ፡ ይኅጣእ ፡ ዘውስተ ፡ እዩ ።

የተያዘውን ፡ የተሰጠውን ፡ የርድና ፡ ሀብት ፡ ይተው ፡ ዘንድ ።

ወይኅሥሥ ፡ ዘኢይጽሕ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢይክል ፡ ላዕለ ፡ ገቢኦኒ ፡ ኀበ ፡ ዘኮነ ፡ ሶቱ ።

ሊሠራው ፡ የማይቻለውን ፡ ተባሕትዎ ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፤ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ግብሩ ፡ መመለስ ፡ የማይቻለው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

አምክሮ ፡ እንከ ፡ አረጋይ ፡ ዘይሰንአዎ ፡ ሶቱ ።

ተባሕትዎ ፡ የሚበልጥ ፡ አስመስሎ ፡ አሳይቶት ፡ ነበርና ፤ ለእመ ፡ ይሰቀል ፡ ዝንቱ ፡ ጸዋሚ ፡ በቀራንብኡ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ኢይትዔረይ ፡ ለዘይትልአክ ፡ ብሎ ፡ የሚሰማማውን ፡ ምክር ፡ መከረው ።

«ቅኔ ፤ ሶበ ፡ ይቤሎ ፡ እጕ ፡ ለአረጋይ ፤ ምንት ኑ ፡ ሐዊረ ፡ ገዳም ፡ እምዓለም ፤ ኢይትረከብኑ ፡ ጽድቅ ፡ ወትሩፋት ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ዓለም» ።

(፬) ይቤ ፡ አረጋዊ ፤ እስመ ፡ ዘውስተ ፡ ዓሸም ፡ ኢይክል ፡ ይነጽር ፡ ሎሳ ፡ ኀጣውኢሁ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ የራሱን ፡ ኀጢአት ፡ ይመረምር ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውም ።

እስመ ፡ ልቡ ፡ ይበርሕ ፡ በእስተሐምሞ ፡ ዓለም ፡ ወሕሊናቲሁ ።

ልቡናው ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በማሰብ ፤ በማውጣት ፤ በማውረድ ፤ በማንከራከር ፡ ይደክማልና ።

ወለእመኒ ፡ ውስተ ፡ ምሕረተ ፡ መፍቅዳውያን ፡ ወገብረ ፡ ሰላመ ፡ ማእክለ ፡ ምውዓን ፡ ምስለ ፡ ዘወሀበ ፡ እግዚእ ፡ ለእሱ ፡ ካዕበ ፡ ብዕዓን ፤ በብሂሎቱ ፡ ብዙኀን ፡ መሓርያን ፡ ወገባርያን ፡ ሰላም ፡ (ማቴ፭ ፡ ፱ናይ)። ብዕዓን ፡ የሰጠ ፡ ጌታ ፤ ብዙዓን ፡ መሓርያን ፡ ስላለ ፡ ምንም ፡ ለሚሹት ፡ ሰዎች ፡ ቢመጸውት ። ብዙዓን ፡ ገባርያነ ፡ ሰላም ፡ ስላለ ፡ ምንም ፡ የተጣላ ፡ ቢያስታርቅ ። አንድም ፡ ጌታ ፡ ብዙዓን ፡ መሓርያን ፤ ብዙዓን ፡ ገባርያነ ፡ ሰላም ፡ ብሎ ፡ ከሰጠው ፡ ብዕዓን ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ ቢመጸውት ፤ ቢያስታርቅ ። አንድም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ብዕዓን ፡ ከሰጠ ፡ ጌታ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ለመሆን ፡ ምንም ፡ ቢመጸውት ፤ ቢያስታርቅ ። አንድም ፡ ብዙዓን ፡ ነዳያን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፤ ብዙዓን ፡ መሓርያን ። ብዙዓን ፡ መሓርያን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፤ ብዙዓን ፡ ገባርያነ ፡ ሰላም ፡ ስላለ ፡ ምንም ፡ ቢመጸውት ፡ ቢያስታርቅ ፤ ኢይክል ።

ዘሰ ፡ ይወፅእ ፡ እምዓለም ።

ከዓለም ፡ የሚወጣ ።

ወይበውእ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ በዓት ፡ እምድኅረ ፡ ተምሂሮቱ ፡ በውስተ ፡ ምኔት ።

ጦሩን ፡ በማሳበር ፡ ከተማረ ፡ በኋላ ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፤ ከበዓት ፡ ተከቶ ፡ የሚኖር ፡ ግን ።

ወኢያጸርዕ ፡ ተጋድሎ ።

ትሩፋቱን ፡ ባይተው ።

እስመ ፡ ይኄሊ ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ኀጣውኢሁ ።

የራሱን ፡ ኀጢአት ፡ ያስባል ፤ ይመረምራል ።

ወይኔጽር ፡ ውስተ ፡ ትሕጻጹሁ ።

ሕጸጽነቱን ፡ ያውቃል ።

ወየአምር ፡ ሕማማቲሁ ።

ጦሩን ፡ ያውቃል ።

ወሶበ ፡ ጸልአ ፡ ኪያሃ ።

ክፉ ፡ ሥራን ፡ ቢጸላ ።

ወአዝለፈ ፡ ጸሎተ ፡ ኀብእተ ።

ጸሎተ ፡ ልቡናን ፡ ቢወድ ።

ይሬኢ ፡ እንከ ፡ ብርሃነ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘይቤ ፡ ብዑኣን ፡ ንጹሓነ ፡ ልብ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይሬእይዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የጌታን ፡ ብርሃን ፡ ያያል ።

ተስእሎ ፡ ፸፭ ።

ይቤሎ ፡ አኃው ፤ ምንትኑ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለቃለ ፡ አባ ፡ ሲሶይ ፡ ለአባ ፡ አሞን ፡ የእክለኒ ፡ ግዕዛነ ፡ ሕሊናየ ።

አባ ፡ ሲሶይ ፡ ለአባ ፡ አሞን ፡ የነገረው ፡ ነገር ፡ ትርጓሜው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ። የእክለኒ ፡ ግዕዛነ ፡ ሕሊናየ ፡ ያለው ፡ ምንድር ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ አባ ፡ ሲሶይ ፡ ኮነ ፡ ይነብር ፡ ሎሱ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ርኅቅት ።

አባ ፡ ሲሶይ ፡ ዘመኑን ፡ ሁሉ ፡ ከሰው ፡ ርቆ ፡ በገዳም ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

ወእምድኅረ ፡ ርሥኣኑ ፡ ወድክመቱ ፡ አብጽሕዎ ፡ አበው ፡ ኀበ ፡ ምኔት ፡ አኃው ።

ካረጀ ፡ ከደከመ ፡ በኋላ ፡ አኃው ፡ ወዳሉበት ፡ ማኅበር ፡ አቀረቡት ።

ወኮኑ ፡ ይበውኡ ፡ ዕደው ፡ ኀቤሁ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ በቍጌት ፡ ወረድኤት ፡ ጸሎት ።

ከኃአው ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ወደሱ ፡ እየገቡ ፡ እዘንልን ፡ ጸልይልን ፤ ምከረን ፡ አስተምረን ፡ ይሉት ፡ ነበር ።

ወኢኮን ፡ ልሙደ ፡ ለነገር ።

ነገር ፡ አልለመደም ፡ ነበርና ።

ወወጠነት ፡ ክመ ፡ ትፍልስ ፡ ሕሊናሁ ፡ ውስተ ፡ ተዘክሮ ፡ ነገረ ፡ አኃው ፡ ወሐልዮ ፡ ግብሮ ።

ለአኃው ፡ የሚመልሰውን ፡ ነገር ፡ በማሰብ ፡ ያንኑ ፡ በማውጣት ፡ በማውረድ ፡ ሕሊናው ፡ ትባክን ፡ ነበር ።

ወርእዮ ፡ አባ ፡ አሞን ፡ ሕዙን ፡ በእንተ ፡ ምጽአቱ ፡ እምገዳም ።

አባ ፡ አሞን ፡ ከገዳም ፡ በመምጣቱ ፡ አዝኖ ፡ አየው ።

ወይቤሎ ፡ እስመ ፡ ኢኮን ፡ ድልወ ፡ ትሕዝን ፡ በእንተ ፡ ንብረትከ ፡ ማእክለ ፡ አኃው ።

ከአኃው ፡ ጋራ ፡ በመኖርህ ፡ ልታዝን ፡ አይገባህም ፡ አለው ።

እስመ ፡ ናሁ ፡ ደክመ ፡ ሥጋከ ።

ትሩፋት ፡ እሠራለሁ ፡ እንዳትል ፡ ሰውነትህ ፡ ደክሟልና ።

ወኢትክል ፡ ትጸመ ፡ በክመ ፡ ነበርከ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ።

ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበርኸው ፡ በትሩፋት ፡ መድከም ፡ አይቻልህምና ። አንድም ፡ ተገብሮ ፡ ይገር ፡ እኖራለሁ ፡ እንዳትል ፡ ሰውነትህ ፡ ደክሟልና ። ትጹም ፡ ይላል ፤ እንዳትጸምም ፡ ትጸም ፡ ዘንድ ፡ አይቻልህምና ፤ ልታዝን ፡ አይገባህም ፡ አለው ።

ወተሥጥዎ ፡ በፍርሀት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ግዕዛነ ፡ ሕሊናየ ፡ በውስተ ፡ ገዳም ፡ እምኮንኑ ፡ ተእክለኒ ።

እሱም ፡ ዘገዳምስ ፡ ብሆን ፡ ንጽሐ ፡ ልቡናዬ ፡ ትበቃኝ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ በትሕትና ፡ ሁኖ ፡ መለሰለት ።

ወዘቲ ፡ ኢትትክላዕ ፡ እምርሥእ ፡ ወድክም ።

ንጽሐ ፡ ልቡናን ፡ ዕርግና ፡ ድካም ፡ አያስቀራትም ።

ወትፌኢ ፡ ኀቤክ ፡ ቅልልተ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ።

አንተ ፡ አቅለህ ፡ ታያታለህ ፤ ይዘሃታልና ፤ የረከበው ፡ ቀሊል ፡ እንዲሉ ። አንድም ፤ ትትርአይ ፤ ንጽሐ ፡ ልብ ፡ በንተ ፡ ዘንድ ፡ ቀሊል ፡ ሁኖ ፡ ትታያለች ፤ አልደረስህባትምና ።

ዘትጠረይ ፡ እምጽሙና ።

ከተባሕትዎ ።

ወተደምሮ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ጸሎት ፡ እንተ ፡ እንበለ ፡ ጽርዐት ፡ ወኢ ፡ ፍልሰት ።

ማቋረጥ ፤ መባከን ፡ በሌለባት ፡ ጸሎት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ከመሆን ።

www.ethiopianorthodox.org

ወቀዘክሮቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወርእይ ፡ ኀቤሁ ።
ክርስቶስን ፡ ከማሰብ ፤ ከመዘከር ፡ የምትገኝ ።
ወፍሥሓሃ ፡ ለንፍስ ።
ዘትጠረይ ፡ ወፍሥሓሃ ፡ ብለህ ፡ ሳጠም ። የንፍስ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የምትሆን ።
በእፍቅሮቱ ።
ጌታን ፡ በመውደድ ።
ወእፍቅሮተ ፡ ትእዛዛቲሁ ።
ሕጉን ፡ በመፈጸም ።
ወፍትው ፡ ኄራቲሁ ፡ ወውብሐቲሁ ።
በቸርነቱ ፤ በጌትነቱ ፡ የሚያወርሰት ፡ መንግሥቱ ፡ ሰማያትን ፡ በመዘክር ።
ወተናግሮ ፡ ዕበያቲሁ ።
ጌትነቱን ፡ በመዘከር ።
ወእንዝር ፡ እምትሕትናሁ ።
ትሕትናውን ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ በማንከር ፡ የምትገኝ ፡ ኀጽሐ ፡ ልብ ፡ ትትረአይ ።
ዛተ ፡ ግብራተ ፡ መዘእምሳሰሊሃ ፡ ኢይክልእ ፡ ርሥኦን ፡ ወይክህም ።
ይኸን ፡ ሥራ ፡ የመሰለውን ፡ ሁሉ ፡ ዕርግና ፡ ድካም ፡ አያስቀረውም ።
እስመ ፡ ትጠፍእ ፡ ይእቲ ፡ እምተደምሮ ፡ ዘለፈ ፡ ምስለ ፡ ዕብእ ።
ከሰው ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ በመኖር ።
ወእስተሐምሞት ፡ ለካልኦ ።
የሌላውን ፡ ነገር ፡ በማሰብ ፡ ይነግል ፡ እንጂ ።

ተስእለ ፡ ፵፯ ።

ይቤሉ ፡ እኃው ፡ ገዝ ፡ ብእሲ ፡ ነኅዊ ፡ አዶሊት ፡ ዘንጸር ፡ አባ ፡ ሲሶይ ፡ ዘክን ፡ የ ነድር ፡ ውስተ ፡ በኀቱ ፡ ለእንጦንዮስ ።
በእንጦንዮስ ፡ በዓት ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ ሲሶይ ፡ ያየው ።
ወይቤሎ ፡ ሊተ ፡ ኅሥርቱ ፡ ወእሐዱ ፡ አውራኅ ፡ ባሕቲትየ ።
ብዖዱን ፡ ከዚህ ፡ ስኖር ፡ ዓሥራንድ ፡ ወር ፡ ሆነኝ ።
ኢርኢኩ ፡ አሐደኒ ፡ ብእሲ ፡ ዘእንበሌክ ፡ ዮም ።
ዛሬ ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ አላየሁም ፡ ያለው ፡ ያ ፡ አዳኝ ።
ዕብእኩ ፡ እንጋ ፡ እው ፡ መልአኩ ።
ሰው ፡ ነውን ፡ መልአክ ። ምንድር ፡ ነው ፦ቢሉ ፤አባ ፡ ሲሶይን ፡ በመንፈቅ ፡ ፬መንፈቅ ፡ የሚጠይቀው ፡ ዓለማዊ ፡ ረድኡ ፡ ነበር ። ሳይጠይቀው ፡ ንሥር ፡ ወር ፡ ኖረ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እንደኔ ፡ ያለ ፡ መነሡሴ ፡ ረዲ ፡ ስንኳ ፡ ከጠየቀኝ ፡ ዓሥር ፡ ወር ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ትምክህት ፡ አሰበ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታ ፡ መልአከ ፡ ውቃቢውን ፡ ሰው ፡ መስለህ ፡ ታየው ፡ ብሎታል ፡ ያም ጣው ።
ይቤ ፡ መተርጉም ፡ እንሰ ፡ እትሐዘብ ፡ ክመ ፡ መልአክ ፡ ውእቱ ።
እኔስ ፡ መልአክ ፡ ይመስለኛል ።
እስመ ፡ አሐዱሰ ፡ ሰብእ ፡ ኢይነው ፡ አፈጥተ ።
አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ በዚህ ፡ ወጣ ፡ በዚህ ፡ ወረደ ፡ የሚለው ፡ ሳይኖር ፡ አውሬ ፡ አያደንምና ።
ዓለማዊኒ ፡ ኢይንብር ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ውሣጢት ፡ ኅሥርተ ፡ ወአሐደ ፡ አውራኅ ።
ዓለማዊሰ ፡ ኰንጎ ፡ ከሚሰቱ ፡ ተለይቶ ፡ ዓሥራንድ ፡ ወር ፡ መ[illegible] ፡ በአስክንድርያና ፡ በአስቁጥስ ፡ አንድም ፡ በዳርና ፡ በዳር ፡ መካከል ። አንድም ፡ በጽኑ ፡ በረሃ ፡ አይኖርምና ።
እስመ ፡ ረድኡ ፡ ለአባ ፡ ሲሶይ ፡ ጕንደየ ፡ እምኔሁ ፡ ኅሥርተ ፡ አሐራን ።
በ፴ት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በመንፈቅ ፡ በመንፈቅ ፡ ይጠይቀው ፡ የነበረ ፡ ረዱ ፡ ከጠየቀው ፡ ዓሥር ፡ ወር ፡ ሁኖት ፡ ነበር ።
ወኢርእየ ፡ ሰብእ ።
፲ወር ፡ ምሉ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ አልተገናኘም ፡ ነበርና ።
ወተቃተሉ ፡ እንከ ፡ ሰይጣን ፡ ዘበትምክህት ።
ሰይጣን ፡ በኀ ምክህት ፡ ጸር ፡ ተዋጋው ፡ ቢዋጋው ።
ወእዘዞ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ቅዱስ ፡ ለአሐዱ ፡ እመላእክት ፡ ያስተርኢ ፡ ሎቱ ፡ በአምላስ ፡ ዕብእ ።
ጌታም ፡ መልአኩን ፡ እንዳይመካ ፡ ሰው ፡ መስለህ ፡ ተገለጽለት ፡ አለው ።
ወዘለፈ ፡ ሕሊናው ።
ጌታ ፡ አንድም ፡ መልአኩ ፤ አንድም ፡ ሲሶይ ፡ ሕሊናውን ፡ ዘለፈ ።
ወክልዖ ፡ እምተመክሖ ።
መልአኩ ፡ ሲሶይን ። አንድም ፡ ሲሶይ ፡ ሕሊናውን ፡ አንዳይመካ ፡ አደረገው ።
ወበአ ፡ እንከ ፡ ኀበ ፡ በዓቱ ፤ ወጸፍአ ፡ ገጸ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፤ ወኢ ፡ ከመ ፡ ዝንቱኒ ፡ ዓለማዊ ፡ ኢገብርኩ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኤ ፡ እንደዚህ ፡ ዓለማዊ ፡ ስንኳ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ያልሠራሁ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ እየ ፡ ገሠጸ ፡ ፈቱን ፡ እየጸፋ ፡ ተመልሶ ፡ ከበዓቱ ፡ ገባ ።

ተስእለ ፡ ፵፯ ።

ይቤሉ ፡ እኃው ፡ እስመ ፡ እጉሥ ፡ ሥረ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ሰርማማ ።
አንድ ፡ ሰው ፡ ከአባ ፡ ሰርማማ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ።
ወይቤሎ ፡ ሚ ፡ እግበር ፡ አአቡየ ።
አባቴ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ልሥራ ፡ አለው ።
እስመ ፡ ሕዩይ ፡ አነ ፡ እበልዕ ፡ ወእሰቲ ፡ ወእነውም ።
ቸልተኛ ፡ እዩይ ፤ ባሕና ፡ ነኝ ። እበላለሁ ፤ እጠጣለሁ ፤ እተኛለሁ ።
ወአነ ፡ ውስተ ፡ ሕሊና ፡ ህክክት ።
በምጉበጻበጽ ፡ ሕሊና ።
ወውስተ ፡ ውልዋሌ ።
በማውጣት ፡ በማውረድ ።
ወውክተ ፡ ነፍስ ።
በሁከተ ፡ ነፍስ ፡ እኖራለሁ ፡ አለ ።
ወይቤሎ ፡ አረጋይ ፤ተዐገሥ ፡ ውስተ ፡ በዓትክ ።
አረጋዊ ፡ አባ ፡ ሰርማማም ፡ ሲመክረው ፡ ከበዓትህ ፡ ጽና ።
ወዘክህልክ ፡ ግበር ፡ ዘእንበለ ፡ ውክት ።
ሳትበጻበጽ ፡ የተቻለህን ፡ ያህል ፡ ሥራ ።
ወዝንቱ ፡ ግብር ፡ ጎጻጥ ፡ ዘትገብር ፡ ውእቱኬ ፡ ክመ ፡ ግብር ፡ ብዙኃ ፡ ዘይገብሮ ፡ እንጦንዮስ ፡ በውስተ ፡ ደብሩ ።
በበዓትህ ፡ ጸንተህ ፡ የምትሠራው ፡ ይኸ ፡ ጥቂቱ ፡ ሥራ ፡ እንጦንስ ፡ በበዓቱ ፡ ሁኖ ፡ እንደሚሠራው ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ይሆንልሃል ፡ አለው ።
ወእተፈ ፡ አነ ፡ ክመ ፡ ለእመ ፡ አንተ ፡ ነበርከ ፡ ውስተ ፡ በዓትክ ፡ በእንተ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትትረኩብ ፡ አንተ ፡ በውስተ ፡ መክን ፡ እንጦንስ ፡ ዕሚያኖት ።
እኔም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ በበዓትህ ፡ ጸንተህ ፡ ብትኖር ፡ በእንጦንስ ፡ መዓርግ ፡ እንድትገኝ ፡ አምና ለሁ ፡ አለ ።
ወእመ ፡ ይእኅዝኒ ፡ ክመ ፡ ይክኅ ፡ እኃኑ ፡ ወጣኒ ፡ ተሐያዪ ፡ እነዝ ፡ ይበልዕ ፡ ወይሰቲ ፡ ወይነውም ፡ ወይትፈጋዕ ፡ በሕሊናቲሁ ፡ ይትኤረዮ ፡ ለዓቢይ ፡ እንጦንዮስ ፡ ውስተ ፡ ገቢር ፡ ነዊኅ ፡ ወውስተ ፡ ዕሜቱ ፡ ሠናይ ።
ቸልተኛው ፡ ወጣኒው ፡ እየዘኅ ፤ እየጠጣ ፤ እየተኛ ፤ በኃልዮ ፡ ኃጢአት ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እያደረገ ፤ እሮ ፡ ይትኤረዮ ፡ ዓቢይ ፡ እንጦንዮስን ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ዋጋ ፡ በማግኘት ፤ ፅሚት ፡ ሠናይ ፡ ሲል ፡ ነው ። አንድም ፡ ዓቢይ ፡ ሠናይ ፤ እንጦንዮስን ፡ በሥራ ፤ በዋጋ ፡ እንደምን ፡ ይተካከሰዋል ፡ አለ ።
ይቤ ፡ መተርጉም ፡ እስመ ፡ እግዝ[illegible]ኤር ፡ ገብረ ፡ ትእዛዛተ ፡ ዘሥጋ ፡ በመዋዕል ፡ ሙሴ ፡ ለሕዝበ ፡ እና ኦድ ።
ጌታ ፡ በሙሴ ፡ ዘመ[illegible] ፡ ለእይሁድ ፡ ሥጋዊት ፡ ሕግ ፡ አሪትን ፡ ሠራ ፤ ሠርቶ ፡ ነበር ።
ዘእምርት ፡ እምንገር ፡ ወ እምግባራት ።
ከነቢብ ፡ ከገቢር ፡ የምትከለከል ።
እኮሰ ፡ እምሕሊና ፡ ወፈቃድ ።
ከሐልዮ ፡ ከፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ አይደለም ።
ክመ ፡ ትእዛዝ ፡ መንፈሳዊት ፡ እንተ ፡ እንበራ ፡ ለመሲሓውያን ፡ በእደ ፡ ወልዳ ፡ ብሉኅ ።
እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ በልጁ ፡ ቃል ፡ ለምእመናን ፡ እንደሠራት ፡ እንደ ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ።

(ዘክመ ፡ ወሀበ ፡ እ[illegible]ር ፡ ሕገ ፡ ለሙሴ)

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ እግዚእን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይቤ ፡ ለመሃይምናን ፡ ዕግዕ ክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ለቀደምት ፡

ክርስቶስ ፡ ምዕመናንን ፡ ለቀደምት ፡ ብሏልና ፡

ዘውእቱ ፡ ለአይሁድ ፡ ኢትቅትል ፡

ይኸውም ፡ ለአይሁድ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለአይሁድ ፡ ኢ ትቅቸል ፡ የተባለውን ፡

ዘውእቱ ፡ በገቢር ፡

ይኸውም ፡ መትተህ ፡ ወግተህ ፡ አትግደል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ።

ወኢትዘሙ ፡

አታመንገዝር ፡ የተባለውን ፡

ዘውእቱ ፡ በሥጋ ፡

ይኸውም ፡ በገቢር ፡ አትሰስን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ፡ ብሏልና ። ዘእምርት ፡ እምነገር ፡ ወእምግባራት ፡ ላለው ፡

ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኢትትመሓዕ ፡ ዘውእቱ ፡ ኢትቅትል ፡ በሕሊናክ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ኢትትመሓዕ ፡ እላለሁ ፤ ይኸውም ፡ እገላለሁ ፡ ብለህ ፡ አታስብ ፡ ማለት ፡ ነው ። ።

ኢትዘሙ ፡ ዘውእቱ ፡ በርእዮትክ ፡ ወበልብክ ።

ይኸውም ፡ አይተህ ፡ በሕሊና ፡ አትሰስን ፡ ማለት ፡ ነው ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ አየሂ ፡ ዘተምዐ ፡ ኅዕለ ፡ እጕሁ ፡ በክንቱ ፡ ደለወት ፡ ላዕሌሁ ፡ ደይን ። (ማቴጽ ፡ ፭፳፪ ፡ ፳፪)

በማናቸውም ፡ ነገር ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ የተቆጣ ፡ ደለወት ፡ ላዕሌሁ ፡ ደይን ፡ ብሏልና ።

ዘውእቱ ፡ ደይን ፡ ቀትል ።

ይኸውም ፡ የቀቲል ፡ ፍርድ ፡ ይፈረድበታል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወእመቦ ፡ ዘርእየ ፡ ኀበ ፡ ብእሲት ፡ እጕሁ ፡ ወፈተዋ ፡ ወድዐ ፡ ዘመ ወ ፡ ባቲ ፡ በልቡ ። (ማቴጽ ፡ ፭፯)

እንዲህ ፡ ብልዋልና ። ወአከሰ ፡ እምሕሊና ፡ ወፈቃድ ፡ ላለው ።

ወበቀዳሚሰ ፡ አንበረ ፡ ተግሣጸ ፡ ሥጋዊ ።

በቀደመው ፡ ዘመን ፡ ሥጋዊ ፡ ሕግ ፡ አሪትን ፡ ሠራ ። በእንተ ፡ ግብር ፡ ሥጋዊ ።

ኃጢአቱ ፡ በሥጋ ፡ የሚሠራ ፡ ስለሆነ ።

ወበደኃሪሰ ፡ ነገረን ፡ ፍዳ ፡ መንፈሳዊተ ።

በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ አስተማረ ።

በእንተ ፡ መንፈሳዊ ፡ ምግባር ።

ኃጢአቱ ፡ በነፍስ ፡ የሚሠራ ፡ ስለሆነ ።

ዘይክውን ፡ በሕሊና ፡ ወፈቃድ ።

ያን ፡ በሕሊና ፡ በፈቃድ ፡ የሚፈጸም ፡ አለ ። አንድም ፡ በአሪት ፤ ሥጋዊ ፡ ፍርድ ፡ አዘዘ ፡ ሕጉ ፡ ሥጋዊ ፡ ስለሆነ ። በወንጌል ፡ ግን ፡ መንፈሳዊ ፡ ፍርድ ፡ አስተማረ ፡ ሕጉ ፡ መንፈሳዊ ፡ ስለሆነ ፤ ዘሕሊና ፡ በፈቃድ ፡ የሚፈርድ ።

ወምግባር ፡ ሥጋዊ ፡ ኃላፊ ፡ ውእቱ ።

የቀደመው ፡ ሕግ ፤ ፍርድ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ወምግባርሰ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዘኢኃላፊ ፡ ውእቱ ።

የኋለኛው ፡ ሕግ ፤ የኋለኛው ፡ ፍርድ ፡ ግን ፡ የማያልፍ ፡ ነው ።

ወናሁ ፡ ኮነ ፡ ድቀታት ፡ በብሊት ።

በነፈረት ፡ በኃጢአት ፡ መሰነካከል ፡ ነበረ ።

በእንተ ፡ ምግባር ፡ ሥጋዊ ።

ሕጉ ፡ ሥጋዊ ፡ ስለሆነ ።

ወበመንፈሳዊሰ ፡ አልቦ ።

በወንጌል ፡ ግን ፡ መሰነካከል ፡ የለም ።

እስመ ፡ ቀዳሚት ፡ ኢትክል ፡ ትክላዕ ፡ ሕሊና ፡ ወፈቃደ ።

የቀደመችዪቱ ፡ ሕገ ፡ አሪት ፡ ከሐልዮ ፡ ኃጢአት ፤ ከፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ ትከለክል ፡ ዘንድ ፡ አይቻላትምና ፡ ከነት ፡ በብሊት ፡ ድቀት ።

ወበእንተዝ ፡ ይቤሉ ፡ መንፈቀ ፡ አበው ።

ስለዚህ ፡ መተካከሉ ፡ ሳይናር ፡ አሪትና ፡ ወንጌል ፡ ሕግ ፡ ሕግ ፡ በመበል ፡ እንደተካከሉ ፤ መተካከሉ ፡ ሳይናር ፡ ይተካከለዋል ፡ አሉ ። አንድም ፡ የልቡና ፡ ሥራ ፡ ክቡር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይተካከለዋል ፡ አሉ ።

እስመ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይግበር ፡ ዘኮነ ፡ ወኢይክል ፡ ይትኄረዮ ፡ ለዘይክል ፡ ወይገብር ።

የታዘዘውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሊሠራ ፡ የሚወድ ፡ አልቻለው ፡ ብሎ ፡ የሚቀርበት ፡ ተችሎት ፡ የሚሠራውን ፡ ይተካከለዋልና ።

ጽድቅሰኒ ፡ ኢኮነ ፡ በአምጣነ ፡ ምግባረ ፡ ሥጋ ።

እንኪያስ ፡ ፡ ጽድቅ ፡ በሥራ ፡ አይደለም ።

ወውእቱኒ ፡ ይትቤየን ፡ እምግባረ ፡ ማርታ ፡ ወማርያም ፡ እኅታ ።

ይኸውም ፡ ከማርያና ፡ ከማርታ ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ ይታወቃል ።

እስመ ፡ እግዚእን ፡ ወደሶ ፡ ለምግባረ ፡ ማርያም ፡ ፈድፋደ ፡ እምግባረ ፡ ማርታ ። (ሉቃ፲ ፡ ፴፰—፵፪ ።

ጌታ ፡ ከማርታ ፡ ይልቅ ፡ የማርያምን ፡ ሥራ ፡ ማርያምሰ ፡ ኅርየት ፡ ብሎ ፡ አመስግኖታልና ።

እስመ ፡ ማርታ ፡ ተልእክት ፡ በሥጋሃ ፡ ለሥጋት ።

ማርታ ፡ በሥጋዊ ፡ ግብር ፡ ለሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተገዛች ።

ዘውእቱ ፡ ምሳሓት ።

ይኸውም ፡ ምግብ ፡ ማሰናዳት ፡ ነው ።

ወማርያምሰ ፡ ተልእክት ፡ በመንፈሳ ፡ ለመንፈሳውያት ።

ማርያ ፡ ግን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ግብር ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተገዛች ።

ዘውእቱ ፡ ለሰሚዐ ፡ ቃለ ፡ እግዚእ ።

ይኸውም ፡ የጌታን ፡ ትምርት ፡ መስማት ፡ ነው ።

ጽድቅሰ ፡ ኢኮነ ፡ በቀዲመ ፡ ዓመታት ፡ ወመልእክት ።

እንኪያስ ፡ ክብር ፡ ማግኘት ፡ በቀዲመ ፡ ዓመታት ፡ በሥራ ፡ አይደለም ።

ወያዜጕ ፡ በእንቲኣሁ ፡ ክዊነ ፡ አፍቅሮ ፡ ክርስቶስ ፡ ለዮሐንስ ፡ ፈድፋደ ፡ እምጴጥሮስ ።

ይህንንም ፡ ጌታ ፡ ከጴጥሮስ ፡ ይልቅ ፡ ዮሐንስን ፡ መውደዱ ፡ ያስረዳል ።

ለብዕዕትኒ ፡ ማርያም ፡ ኢክልዓ ፡ ደቂቅናሃ ፡ ክመ ፡ ትኩን ፡ ቡርክተ ፡ እምአንስት ።

እመቤታችንንም ፡ ሕፃንነቷ ፡ ቡርክት ፡ አንቲ ፡ እም አንስት ፡ መባልን ።

ወምልዕተ ፡ ጸጋ ፡ ፈድፋደ ፡ እምአረጊት ፡ ኤልሳቤጥ ።

ከኤልሳቤጥ ፡ ይልቅ ፡ ምልዕተ ፡ ጸጋ ፡ መባልን ፡ አላስቀረባትም ።

ወአምሐና ፡ ነቢዪት ፡ እንተ ፡ ተጸምደት ፡ ጸመ ፡ ወጸሎተ ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሰማንያ ፡ ወአርባዕተ ፡ ዓመተ ። (ሉቃ፪ ፡ ፴፯-፴፰) ።

ለጸም ፡ ለጸሎት ፡ ጽምድት ፡ ሁና ፡ ሰማንያ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ከኖረች ፡ ከሐና ፡ ይልቅ ፡ ምልዕተ ፡ ጸጋ ፡ መባልን ፡ አላስቀረባትም ።

ጽድቅሰኒ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ በብዝኀ ፡ አቅርቦ ።

እንኪያስ ፡ ጽድቅ ፡ አብዝቶ ፡ በመሥራት ፡ አይደለም ። ኂ ፤ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀዲመ ፡ ዓመታት ፡ አይደለም ፤ አብዝቶ ፡ በመሥራትም ፡ አይደለም ።

እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእን ፡ በእንተ ፡ በዐልተ ፡ ክልኤ ፡ ጸሪቅ ፡ ክመ ፡ ይኅቲ ፡ አብአት ፡ ፈድፋደ ፡ እምአበዕልት ። (ሉቃ፳፩ ፡ ፪-፬) ።

ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ከባለ ፡ ጸጎች ፡ ይልቅ ፡ ድኃዪቱ ፡ አብዝታ ፡ አቀረበች ፡ ብሏልና ።

መጸብሓዊሰ ፡ በእንተ ፡ ትሕትናሁ ፡ ጸድቀ ፡ ፈድፋደ ፡ እምፈሪሳዊ ፡ ዘበዝኀ ፡ ጸመ ፡ ወምጽዋቱ ፡ ወጸሎቱ ። (ሉቃ፲፰ ፡ ፲-፲፬) ።

መጸብሓዊም ፡ ትሑት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ጸመ ፡ ጸሎቱ ፡ ምጽዋቱ ፡ ብዙ ፡ ከሆነ ፡ ከፈሪሳዊ ፡ ይልቅ ፡ ከበረ ።

አተወ ፡ ዝንቱ ፡ እንዘ ፡ ይጼደቅ ፡ እምዝኩቱ ፡ ተባለ ።

ወንጥእትሂ ፡ አርአየት ፡ ብዝኀ ፡ አፍቅሮታ ፡ በእንብዓ ፡ በጊዜ ፡ ሀሎ ፡ በቤት ፡ ስምዖን ፡ ፈሪሳዊ ። (ሉቃ፯ ፡ ፶፪-፶፰) ።

ኀጥኣት ፡ ማርያምም ፡ ጌታ ፡ ከስምዖን ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሳለ ፡ በማልቀሷ ፡ የፍቅሯን ፡ ብዛት ፡ ገለጠች ።

ወወደሳ ፡ እግዚእን ፡ ወአፍቀራ ፡ ፈድፋደ ።

ከስምዖን ፡ ይልቅ ፡ አመሰገናት ፡ ወደዳት ።

ወሰረየ ፡ ላቲ ፡ ብዙኃ ፡ ኀጣውኢሃ ።

ተኀድግ ፡ ለኪ ፡ ኀጠአትኪ ፡ አላት ።

ወፈያታዊኒ ፡ ዘየማን ፡ ዘሰፈ ፡ ርእሶ ፡ በጊዜ ፡ ሞቱ ። (ሉቃ፳፫ ፡ ፵—፵፫) ።

ፈያታዊ ፡ ዘየማንም ፡ በጊዜ ፡ ሞቱ ፤ ንሕነሰ ፡ በከመ ፡ ምግባሪን ፡ ተፈደይነ ፤ ውእቱሰ ፡ አልቦ ፡ ዘገብረ ፡ እኩየ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ዘለፈ ።

ወአስተብቍዖ ፡ ኀበ ፡ እግዚእ ፡ ክመ ፡ ይዘክሮ ፡ አመ ፡ ይመጽእ ፡ በመንግሥቱ ።

ተዘከረኒ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትክ ፡ አለ ።

ወደለዎ ፡ ገነት ።

ዮም ፡ ትሄሉ ፡ ምስሌየ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ አለው ።

እሉኬ ፡ እሙንቱ ፡ ዘዓሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ሰዓት ።

ገባዕተ ፡ ሠርክ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

እለ ፡ ይበውዑ ፡ በተፍጻሜተ ፡ ሰዓታት ፡ ኀበ ፡ ተገብሮ ፡ ዐዐደ ፡ ወይን ።

በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ሥራ ፡ የተመለሱ ።

ወይሁቦሙ ፡ እግዚእ ፡ አስቦሙ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ተመንደቡ ፡ በክበደ ፡ መዓልት ፡ ወሐሩር ።

ከገባዕተ ፡ ነግህ ፡ ጋራ ፡ አስተካክሎ ፡ ዋጋቸውን ፡ የሚሰጣቸው ።

ዘውእቱ ፡ እምኀለሙ ፡ እስከ ፡ ርስኣኖሙ ።

ይኸውም ፡ ከሕፃንነት ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ ዕርጓና ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ላዕለ ፡ ዛቲኬ ፡ ግብር ፡ ገብሩ ፡ አበውኒ ፡ ዘበእንተ ፡ ሥርዓቶሙ ፡ ለአኃው ።

አበውም ፡ ለአኃው ፡ ትምርታቸውን ፡ ሥራታቸውን ፡ በእንጦንዮስ ፡ አምሳል ፡ አደረጉ ። እንድም ፡ የአኃውን ፡ ሥራት ፡ አሁን ፡ በተነገሩ ፡ በገባዕተ ፡ ሠርክ ፡ አምሳል ፡ ሠሩ ።

ወኮኑ ፡ ይናዝዝዎሙ ፡ በአገማን ፡ መክራሆሙ ፡ በተስፋ ፡ ሠናይ ።

አኃውንም ፡ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ በጎ ፡ ተስፋ ፡ ነግ

www.ethiopianorthodox.org

ረው ፡ ያጸናኑዋቸው ፡ ነበር ።

ክመ ፡ ያጥርዩ ፡ ሀየንተ ፡ ሐዘን ፡ ወሀኬተ ፤ ወመቲረ ፡ ተስፋ ።

ስለ ፡ ሐዘን ፡ ፈንታ ፡ ደስታን ፤ ስለ ፡ ሀኬት ፡ ፈንታ ፡ ትጋሀን ፤ ስለ ፡ ተስፋ ፡ መቊረጥ ፡ ፈንታ ፡ ተስፋን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ። እንዲያውም ፡ ገልጸ ፡ ሀየንተ ፡ ሐዘን ፡ ትፍሥሕተ ፤ ወሀየንተ ፡ ሀኬት ፡ ትጋሀ ፡ ይላል ።

ወእያቀ ፡ ክመ ፡ ለብሑታን ፡ ይጸራዕ ፡ ጥብዐቶሙ ፡ በእንተ ፡ ምግባራ ት ፡ ሥጋ ፡ ጊዜያተ ፡ እምሀኬት ፡ ወልሀላሄ ፡ አባል ፤ ወበእንተ ፡ ምግ ባራተ ፡ ሕሊናት ፤ ወጊዜያተ ፡ እምጸብአ ፡ ሕሊና ፡ ወምትረተ ፡ ተስፋ ። የበሕታውያን ፡ ሥራቸው ፡ ትሩፋታቸው ፡ ከሀኬት ፡ ከድካም ፡ ወገን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሚሠሩት ፡ በሥ ጋዊ ፡ ሥራ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ከሕሊና ፡ ጸር ፡ ወ ገን ፡ በሚሆን ፡ በክፉ ፡ ሕሊና ፡ እንዲፈርስ ፡ አስረ ዳ ። አንድም ፡ ጥብዐቶሙ ፡ ለምግባራት ፤ በሥጋ ፡ ለሚሠሩ ፡ ለትሩፋት ፡ ሥጋ ፡ መትጋታቸው ፤ ከሀኬ ት ፡ ከድካም ፡ የተነሣ ፤ በልቡና ፡ ለሚሠራ ፡ ለትሩ ፋት ፡ ነፍስ ፡ መትጋታቸው ፡ ከሕሊና ፡ ጸር ፡ የተነሣ ፡ እንዲቀር ፡ አስረዳ ።

በእንተዝኩ ፡ ናዘዞ ፡ በጊዜ ፡ መክራው ።

እንዲህ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በመከራው ፡ ጊዜ ፤ ወዝንቱ ፡ ግ ብር ፡ ጎዳጥ ፡ ዘትገብሮ ፡ ውእቱኬ ፡ ከመ ፡ ግብረ ፡ እንጠንዮስ ፡ ብሎ ፡ አጸናው ።

ወይቤሎ ፡ ለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ምግባራቲክ ፡ ሕዕዐተ ፡ ይእዜ ፡ እምጸብአ ፡ ለይጣናት ፡ አሳ ፡ ሕሊናክሰ ፡ ርትዕት ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ በውስተ ፡ በዓ ትክ ፡ ዘበእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢጉደለት ።

ከአጋንንት ፡ ያር ፡ የተነሣ ፡ ሥራህ ፡ ምንም ፡ ጥቂት ፡ ብትሆን ፡ ሕሊናህ ፡ የቀና ፡ ከሆነ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ብለህ ፤ በዓት ፡ አጽንተህ ፡ ጥቂቲቱ ፡ ሥራ ፡ ካልጐ ደለችብህ ።

ባቲኬ ፡ ትትሜሰሎ ፡ ለእንጠንዮስ ።

በዚያችው ፡ እንጠንዮስን ፡ ትተካከለዋለህ ፡ አለው ።

በከመ ፡ ተመሰሎ ፡ ሕሊናክ ፡ ለሕሊናሁ ፡ ከማሁ ፡ ትትሜስሎ ፡ ፍጻክ ኒ ፡ ለፍጻሁ ።

ሕሊናህ ፡ ሕሊናውን ፡ እንደመሰለው ፤ ዋጋህም ፡ ዋ ጋውን ፡ ይመስለዋል ፡ ብሎ ፡ ደስ ፡ አሰኘው ።

ወምግባርክ ፡ ጎደጥ ፡ ዘውስተ ፡ ፍና ፡ መክራክ ፡ ምስለ ፡ ጽንዓትክ ፡ ው ስተ ፡ በዓትክ ፡

በዓት ፡ ከማጽናት ፡ ጋራ ።

ወሕፀፀ ፡ አእምሮትክ ።

አእምሮዬ ፡ ሕውዕ ፡ ነው ።

ወድካመ ፡ ኃይልክ ።

ኃይሌ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ጋራ ።

ወውጎደተ ፡ ኩንዮትክ ፡ ለካልእክ ።

በሌላው ፡ መፍረድን ፡ ከመተው ፡ ጋራ ፡ የምትሠራ ው ። አንድም ፡ በበዓትህ ፡ ጸንተህ ፡ መከራ ፡ እየተ ቀበልህ ፡ የምትሠራው ፡ ጥቂቱ ፡ ሥራ ፡ ሕፁፅ ፡ ነኝ ፡ ደካማ ፡ ነኝ ፡ ማለትህ ።

በተጸምዶ ።

ለትሕትና ፡ ጽሙድ ፡ ሁነህ ፡ በሌላ ፡ መፍረድን ፡ መ ተውህ ።

በእንተ ፡ አእምሮቱ ፡ ፍጹም ፡ ለእንጠንዮስ ፡ ወኃይሉ ፡ ወትጎርም ቱ ፡ ትትጌረዮ ፡ በጎበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእንጠንዮስ ፡ በውስተ ፡ ም ግባሩ ፡ ብዙኅ ።

ትትጌረዮ ፡ ውስተ ፡ ምግባሩ ፡ ብዙኅ ። በእንተ ፡ አ እምሮቱ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ አእምሮው ፡ ፍጹም ፡ ስ ለሆነ ፤ ኃያል ፡ ስለሆነ ፤ ተኃራሚ ፡ ስለሆነ ፡ እንጠን ዮስ ፡ ከሚሠራው ፡ ከብዙ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ትትሜረይ ።

አንድም ፡ በጥቂቱ ፡ ሥራ ፡ እንጠንዮስን ፤ ፍጹም ፡ ኃያል ፡ ስለሆነ ፡ በሚሠራው ፡ በብዙ ፡ ሥራ ፡ በእግ ዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ትተካከለዋለህ ።

ወበእንተዝኩ ፡ ይትጌረይ ፡ እንከ ፡ ፍጻክሙ ።

ሥራችሁ ፡ ስለተካከለ ፡ ዋጋችሁም ፡ ይተካከላል ፡ አ ለው ።

ወብሂሎቱ ፡ ኢትትሀወክ ።

ኢትትሀወክ ፡ ማለቱም ።

ዘውእቱ ፡ ኦሆ ፡ ኢትበል ፡ ለሕሊናክ ።

ለክፉ ፡ ሕሊና ፡ እሺ ፡ በጎ ፡ ብለህ ፡ አትታዘዝ ፡ ማለ ት ፡ ነው ።

ወኢትትሀወክ ፡ ልብክ ፡ በሐዘን ፡ ወመቲረ ፡ ተስፋ ።

ልቡናህም ፡ በሐዘን ፡ በቀቢፀ ፡ ተስፋ ፡ አትበየበጽ ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

ካዕበ ፡ ናዘዞ ፡ በብሂሎቱ ፡ አንስ ፡ እትአመን ፡ ክመ ፡ ለእመ ፡ ጸናዕክ ፡ አንተ ፡ ውስተ ፡ በዓትክ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ እስክኑ ፡ ትትሳደው ፡ መ ክራክ ።

እተፈ ፡ ያለውን ፡ እትአመን ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፤ ዳ ግመኛም ፡ ለክርስቶስ ፡ ብለህ ፡ ያሩ ፡ መከራው ፡ እስ ኪያልፍልህ ፡ በበዓትህ ፡ ብትጸና ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ታደምዕ ፡ ፍልሐተ ፡ አፍቅሮ ።

በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ መናደድን ።

ወኃይለ ፡ ምግባራት ።

ትሩፋት ፡ ለመሥራት ፡ ክሂልን ፡ እንድታገኝ ፡ አምና ለሁ ፡ ብሎ ፡ ደስ ፡ አሰኘው ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ጽሑፍ ፡ እስመ ፡ አሐዱ ፡ እምአኃው ፡ መጽአ ፡ ኀበ ፡ አርሳንዮስ ፡ ከመ ፡ ይርአዮ ።

ከአኃው ፡ አንዱ ፡ አርሳንዮስን ፡ ሊገናኘው ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ተጽፏል ።

ወዖበ ፡ ጉድጉደ ፡ ኖኅተ ፡ አርጎወ ፡ ሎቱ ።

ደጅ ፡ በመታ ፡ እጅ ፡ በጸፋ ፡ ጊዜ ፡ ከፈተለት ።

ወርእዮ ፡ አርሳንዮስ ።

አርሳንዮስም ፡ አየው ፤ አይቶ ።

አውድቀ ፡ ነፍሶ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በገጹ ።

ወድቆ ፡ እጅ ፡ ነሣው ።

ወሰአሎ ፡ እንክ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተንሥእ ፡ ኦአቡየ ፡ ከመ ፡ አአምኅ ክ ፡ ወአሐር ።

አባቴ ፡ ተነሣና ፡ እጅ ፡ ነሥቼህ ፡ ልሂድ ፡ ብሎ ፡ ማ ለደው ።

ወይቤሎ ፡ ኢይትነሣእ ፡ እስክ ፡ ተሐውር ።

አንተ ፡ ካልሄድህ ፡ አልነሣም ፡ አለው ።

ወአንበሮ ፡ ብዙኃ ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ማለደው ።

ወኢተንሥአ ።

አልተነሣለትም ።

ወኀደገ ፡ እንክ ፡ ወሖረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደጉን ፡ ሰው ፡ አባብ ፡ ይመስል ፡ በግ ንባሩ ፡ ተክዬው ፡ እውላለሁን ፡ ብሎ ፡ ትቶ ፡ ሄደ ፤ አገናኝዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ቢመጣ ፡ እንዲህ ፡ ማድረጉ ፡ ስለምን ፡ ነው ፡ አሉት ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ አስመ ፡ እስ ፡ ያፈቅሩ ፡ ጽሙና ፡ ወያወትሩ ፡ ብ ሕትውና ፡ ዘበገዙሉሩ ፡ በውስተ ፡ በዓት ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ርኅቅት ።

ተባሕትዎ ፡ የሚወዱ ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ በበዓት ፡ ተከተው ፡ ሊኖሩ ፡ የሚወዱ ።

ኢይፈንዩ ፡ አሐደኒ ፡ ዘእንበለ ፡ አርድእቲሆሙ ፡ ባሕቲቶሙ ።

አርድእቶቻቸውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከአርድእቶቻቸው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይገናኙምና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ወእምድኅረ ፡ ርስዓን ፡ ወድካም ፡ ነገሩ ፡ አዕሩግ ።

ከርግና ፡ ከድካም ፡ በኋላም ፡ እንዳይገናኙ ፡ ነገሩ ፡ ይ ፈል ። አንድም ፡ አርድዕቶቻቸው ፡ ሳይቀር ፡ አያዩ ም ፤ ባሕቲቱ ፤ ከርግና ፡ ከድካም ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እንዳ ያዩ ።

በእንተ ፡ አባ ፡ መቃሪ ፡ ዘየኅሊ ፡ ግብጻዊ ።

አበው ፡ የአባ ፡ መቃራን ፡ ነገር ፡ ተናገሩ ።

ወይቤልዎ ፡ ለእመ ፡ ኮንክ ፡ ዘኢትክል ፡ ትኩን ፡ ክግን ፡ እንደኛ ፡ ፈላሲ ፡ መሆን ፡ ባይቻልህ ።

ንበር ፡ ውስተ ፡ በዓትክ ።

በበዓትህ ፡ ጸንተህ ፡ ኑር ።

ወብኪ ፡ በእንተ ፡ ኃጣውኢክ ። (ተስእ ፡ ፸፩) ።

ኃጢአትህን ፡ አስበሕ ፡ አልቅስ ፡ አሉት ።

ወአባ ፡ አርሳንዮስኒ ፡ አፍቀረ ፡ ጽግፍ ፡ ፍጹመ ።

አርሳንዮስም ፡ ተባሕትዎ ፡ ስለ ፡ ወደደ ።

ወኮን ፡ ይበኪ ፡ እስክን ፡ ተመልሑ ፡ ሥዕርተ ፡ አዕይንቲሁ ።

ያይኑ ፡ ሽፋሽፍት ፡ ተነቃቅለው ፡ ተመዛዘው ፡ እስኪ ወድቁ ፡ ድረስ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ። «ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ አርድእቶቹ ፡ አጐዛ ፡ ድሪቶ ፡ አቅርበው ፡ የሚፈሰው ን ፡ እንቡን ፡ እየ ፡ ተቀበሉ ፡ በዚያ ፡ እያራሱ ፡ ግራ ምጣ ፡ ይሰፋበት ፤ ሰሌን ፡ ይታቱበት ፡ ነበር» ።

ወኮንኅ ፡ በዓቱ ፡ ርሕቅተ ፡ ውስተ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ኅሙርተ ፡ ምዕራፈ ።

በዓቱም ፡ ከአስቄጥስ ፡ ዓሥር ፡ ምዕራፍ ፡ ርቆ ፡ ነበ ር ።

ወዖበ ፡ ይቤሎ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ እስክንድርያዊ ፤ በእንተ ፡ አይ ፡ ፍ ና ፡ ነበርክ ፡ ርሑቀ ፡ እምኔነ ።

አባ ፡ መቃርስ ፡ ከኛ ፡ ርቀህ ፡ የምትኖር ፡ ስለ ፡ ም ን ፡ ነው ፤ እኛንም ፡ እንደ ፡ ዓለማውያን ፡ አየኸንን ፡ ባለው ፡ ጊዜ ።

ይቤሎ ፡ አርሳንዮስ ፡ ኢይክል ፡ እኩን ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰ ብእ ፡ ኅቡረ ።

ከሰውና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ መ ኖር ፡ አይቻለኝም ፡ አለ ።

እስመ ፡ አሐቲ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አንዲት ፡ ናት ።

ወፈቃደ ፡ ሰብእስ ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሁ ።

የሰው ፡ ፈቃድ ፡ ሣን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነውና ።

በእንተ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡ ምግቱ ፡ ወጽንት ።

መሸበር ፡ ጽንት ።

ወውጎደተ ፡ አእምሮ ።

የአእምሮ ፡ ሕጸጽ ።

ወድካመ ፡ ጠባይዕ ።

የባሕርይ ፡ ድክም ።

ወብዙኃን ፡ ሕግግት ።

ብዙ ፡ ጸር ፡ ስላለባቸው ።

ወኢይክል ፡ እንክ ፡ ይግዐዝ ፡ እምኔሃ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ ፣ ሁሉ ፣ ጸር ፣ ድኖ ።
ወይማእ ።
ይሀን ፣ ሁሉ ፣ ድል ፣ ነሥቶ ።
ወያሥምር ፣ ፈቃደ ፣ እግዚአብሔር ።
የጌታን ፣ ፈቃድ ፣ ይፈጽም ፣ ዘንድ ፣ አይቻለውምና ።
ዘእንበለ ፣ በውስተ ፣ ጽማዌ ፣ ወብሕትውና ።
ከሰው ፣ ተለይቶ ፤ በበዓት ፣ ተከቶ ፣ ቢሆን ፣ ነው ፣ እንጂ ።
ወርሒቅ ፣ እምርእይ ፣ ጎበ ፣ ሰብእ ።
ሰውን ፣ ከማየት ፣ ከመስማት ።
ወተናግሮ ፣ ምስሌሆሙ ።
ከሰው ፣ ጋራ ፣ ከመነጋገር ፤ ከመጫወት ፣ ርቆ ፣ ቢኖር ፣ ነው ፣ እንጂ ።
ወኢይክሉ ፣ መላእክትኒ ፣ እሙንቱ ፣ አእላፈ ፣ አእላፍ ፣ ወትእልፊተ ፣ አእላፋት ፣ ክመ ፣ ይኩኑ ፣ ምስለ ፣ እግዚአብሔር ።
መላእክት ፣ ስንኳ ፣ ብዙ ፣ የብዙ ፣ ብዙ ፣ ሲሆኑ ፣ ከጌታ ፣ ጋራ ፣ አንድ ፣ መሆን ፣ ባልተቻላቸውም ፣ ነበር ።
ወእሙንቱ ፣ እንዘ ፣ ጉቡኣን ፣ ዘእንበለ ፣ በእንተ ፣ ክሢነ ፣ ጸቋዔ ፣ ፈቃዳቲሆሙ ፣ ውስተ ፣ አፍቅሮ ፣ እግዚአብሔር ።
ብዙ ፣ ሲሆኑ ፣ ፈቃዳቸው ፣ ጌታን ፣ በመውደድ ።
ወስብሑቱ ።
ጌታን ፣ በማገልገል ፣ አንድ ፣ ቢሆኑ ፣ ነው ፣ እንጂ ።
ወኀጢአት ፣ ክልኣታት ፣ ወመቲሮታት ፣ እምውስቴ ።
እሱን ፣ ከመውደድ ፣ ከማገልገል ፣ የሚያርቃቸው ፤ የሚከለክላቸው ፣ ባይኖር ፣ ነው ፣ እንጂ ።
ወበእንተ ፣ አፍቅሮቱኪ ፣ ጽሙና ፣ ኦነ ፣ ያስተሐምም ፣ ለመቲረ ፣ ግብራት ፣ እንተ ፣ ታጸርዕ ።
አርሳንዮስም ፣ ተባሕትዎን ፣ ስለ ፣ ወደደ ፣ ትሩፋቱን ፣ የምታስቀርበት ፣ ሥራን ፣ ለማራቅ ፣ ያስብ ፣ ነበር ።
እስመ ፣ እምዘመደ ፣ ነገሥት ፣ ውእቱ ።
ከነገሥታት ፣ ወገን ፣ የአኖሬዎስ ፣ የአርቃድዮስ ፣ አጎት ፣ ነበርና ።
ወብዙኀ ፣ እንብዶቱ ፣ ውስተ ፣ መጻሕፍት ፣ ቅዱሳት ።
ብሉይ ፣ ሐዲስ ፣ ተምሮ ፣ ነበርና ።
ወትምህርተ ፣ መጽሓፍ ።
ፍልስፍናም ፣ ያውቅ ፣ ነበርና
ወኮነ ፣ ያንሶሱ ፣ ውስተ ፣ ሥርዓት ፣ ትርፍት ፣ ፈደዬደ ፣ እምብዙኃን።
ከሌሎቹ ፣ ይልቅ ፣ እሱ ፣ በመመጽወት ፤ በማስተማር ፣ ይኖር ፣ ነበርና ።
ወተሰምዐ ፣ ዜናሁ ።
ዜናው ፣ በሁሉ ፣ ተነግሮ ፣ ነበርና ።
ወኮኑ ፣ ዐበይት ፣ ወጌራን ፣ ወትሩፋን ፣ ሰብእ ፣ እምርሑቅ ፣ ይመጽኡ ፣ ኀቤሁ ።
ወይዛዝሩ ፤ ደጋጎቹ ፤ ፍጹማኑ ፣ እሱን ፣ ለመገናኘት ፣ ይመጡ ፣ ነበር ። ዐበይት ፤ ጎራን ፤ ትሩፋን ፣ ያላቸው ፣ አርእስት ፣ ናቸው ፤ ለሁሉም ፣ ሳዳግ ፣ ያመጣላቸዋል ።
እስክ ፣ ይእቲ ፣ ብእሲት ፣ ዐባይ ፣ መጽአት ፣ ኀቤሁ ፣ እምሮምያ ፣ ክመ ፣ ትርአየ ።
ስሟን ፣ እልአርታ ፣ ይላታል ፤ ያች ፣ ሴት ፣ ወይዘሮ ፣ ልትገናኘው ፣ ከሮም ፣ ተነሥታ ፣ እስክትመጣ ፣ ድረስ ። አንድም ፣ መጥታ ፣ ነበርና ፤ ዐበይት ፣ ላለው ።
ወኪዐበ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳትኒ ፣ ዐቢይ ፣ ጢሞቴዎስ ፣ ዘእለእስክንድርያ ፣ ሐረ ፣ ኀቤሁ ፣ በእንተ ፣ ተናግሮ ፣ ምስሌሁ ።
የእስክንድርያ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳስ ፣ አባ ፣ ጢሞቴዎስ ፣ ልገናኘው ፣ ብሎ ፣ ሂዶ ፣ ነበርና ፤ ጎራን ፣ ላለው ።
ወምስሌሁ ፣ ኤጲስቆጶሳት ።
ብዙ ፣ ኤጲስቆጶሳትም ፣ ተከትለዉት ፣ ነበርና ፤ ትሩፋን ፣ ላለው ።
ወገብኡ ፣ እምኀቤሁ ፣ እንዘ ፣ ሕዙናን ፣ እሙንቱ ።
ሁሉም ፣ እያዘኑ ፣ ተመለሱ ።
በእንተ ፣ ክሢናቱ ፣ ዘኢንበረ ፣ ምስሌሆሙ ፣ ለተናግሮ ፣ በኦኀ ፣ መንፈስ ።
ተቀምጠ ፣ ስላላጫወታቸው ፤ ልበ ፣ ሰፊ ፣ ሆኖ ፣ ስላላንጋገራቸው ።
ወምዕረ ፣ ካልእኒ ፣ ሖረ ፣ ኀቤሁ ፣ ቴዎፍሎስኒ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ ወምስሌሁ ፣ ኤጲስቆጶሳት ።
ቴዎፍሎስም ፣ አንድ ፣ ጌዜ ፤ ሁለት ፣ ጊዜ ፣ ኤጲስቆጶሳት ፣ ተከትለዉት ፣ ሂዶ ፣ ነበር ።
ወሶበ ፣ ለአልዎ ፣ ክመ ፣ ይንግሮሙ ፣ ነገረ ፣ በቍጹት ።
ምክረን ፣ ባሉት ፣ ጊዜ ።
ይቤሎሙ ፣ እመ ፣ እቤለክሙ ፣ ነገረ ፣ በቍጹት ፣ ተዐቅብዎኑ ።
ብመክራችሁ ፣ ትሠሩታላችሁን ፣ አላቸው ።
ወይቤልዎ ፣ እወ ።
ከመከርኽንስ ፣ እንሠራዋለን ፣ አሉት ።
ወይቤሎሙ ፣ መክነ ፣ አርሳንዮስ ፣ ኢትሑሩ ፣ እንክ ፣ ኀቤሁ ።
እንኪያስ ፣ ሌላም ፣ ምክር ፣ የለኝ ፤ ከአርሳንዮስ ፣ ቦታ ፣ አትሂዱበት ። አንድም ፣ እንደኔ ፣ ጻድቅ ፣ መባልን ፣ አትውደዱ ፣ አላቸው ።

ሞ ፣ በውስተ ፣ ጽሙና ።
እንዲህም ፣ ማለቱ ፣ አዋጅ ፣ ተነግሮበት ፣ ነው ፤ ጌታ ፣ ሳዳአ ፣ ወአርምም ፣ ብሎታልና ።
ወበበይነ ፣ ዝንቱ ፣ ኢያርአየ ፣ ገጸ ፣ ለውእቱ ፣ አብ ፣ ዘበአስሎ ፣ ይትነግእ ፣ ክመ ፣ የአምኖ ።
ተነግ ፣ እጅ ፣ ነሥቼሀ ፣ ልሂድ ፣ ያለውን ፣ አረጋዊ ፣ ሳይገናኘው ፣ የቀረ ፣ ስለዚህ ፣ ነው ።

ተስእሎ ፣ ፸፱ ።

ይቤሎ ፣ አኃው ፤ ለምንትኑ ፣ አሕዘና ፣ ለይእቲ ፣ ብእሲት ፣ መሃይምንት ።
ያችን ፣ ሴት ፣ ለምን ፣ አሳዘናት ።
ዘመጽአት ፣ በሥርዓተ ፣ እግዚአብሔር ፣ እምሮምያ ፣ ጎበ ፣ ግብጽ ።
እየ ፣ ሰጠች ፣ እየ ፣ መጸወተች ፣ ነው ፣ እንጂ ፤ እየ ፣ ዘረፈች ፣ እየ ፣ በዘበዘች ፣ አልመጣችምና ፤ በሥርዓተ ፣ እግዚአብሔር ፣ አለ ። አንድም ፣ ዘያከብሮሙ ፣ ለፈራሀያነ ፣ እግዚአብሔር ፣ ያለውን ፣ ይዛ ፣ ከሮም ፣ ወደ ፣ ግብጽ ፣ የመጣች ።
እስክን ፣ ርእየቶ ፣ ወጎሠአት ፣ ጸሎቶ ።
እስክትገናኘው ፣ ድረስ ፤ ጸልይልኝ ፣ እስክትለው ፣ ድረስ ።
ክመ ፣ አሐዱ ፣ እምነቢያት ፣ ወሐዋርያት ።
ከነቢያት ፣ ከሐዋርያት ፣ እንዳንዱ ፣ አድርጋው ።
በክመ ፣ ትቤሎ ፣ ዐቴዎፍሎስ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ ኢትርሥዐኒ ።
ቴዎፍሎስን ፣ ምን ፣ አመጣሽ ፣ ቢላት ፣ አርሳንዮስን ፣ አትርሰኝ ፣ ልል ፣ መጥቻለሁ ፣ እንዳለችው ፤ ጎሠሠት ፣ ጸሎቶ ። አንድም ፣ ለምን ፣ መጣሽ ፣ አላት ፤ አርሳንዮስን ፣ ልገናኝ ፣ መጥቻለሁና ፣ ያገናኛት ፣ ብለህ ፣ አትርሰኝ ፣ እንዳለችው ፤ እስከ ፣ ርእየቶ ። አንድም ፣ ለምን ፣ መጣሽ ፣ ቢላት ፣ አር ንዮስን ፣ ልገናኝ ፣ አለችው ። እሱማ ፣ እንጂ ፣ ከሰው ፣ እንዳይገናኝ ፣ አዋጅ ፣ ተነግሮበታል ፣ አላት ። እንኪያ ፣ በሊቀ ፣ ካህናቱ ፣ ሥፍራ ፣ ያለህ ፣ አንተ ፣ ተገናኛት ፣ ብለህ ፣ አሽከር ፣ ላክልኝ ፤ አትርሰኝ ፣ እንዳለችው ፣ ርእየቶ ። ወጎሠሠት ፣ ጸሎቶ ፣ ላለውም ፣ ይሆናል ።
ወይቤላ ፤ አንሰ ፣ አንሥሥ ፣ እምእግዚአብሔር ፣ ክመ ፣ ይክላእ ፣ ዝክረ ፣ ዚአኪ ፣ እምልብየ ።
ለምንት ፣ አሕዘና ፣ ወለምንት ፣ ይቤላ ፣ ብለህ ፣ ግጠም ። እኔስ ፣ አሳብሽን ፤ ምትሐትኑሽን ፤ ደግ ፣ ሰው ፣ ማለትሽን ፣ ከልቡናዬ ፣ ያርቅልኝ ፣ ዘንድ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ እለምናለሁ ፣ ለምን ፣ አላት ።
ወኀዘነት ፣ እንክ ፣ በእንቲኣሁ ፣ ወደመየት ።
ይሀን ፣ ስለ ፣ ተናገራት ፣ አዘነች ፤ ደዌ ፣ ወደቀባት ። እንደ ፣ ምን ፣ ነው ፣ ቢሉ ፤ ብዙ ፣ ሠራዊት ፣ ተከትሏት ፣ እገናኛለሁ ፣ ብላ ፣ መጣች ። አርሳንዮስ ፣ ከበዓቱ ፣ ወጥቶ ፣ ፀሐይ ፣ ሲሞቅ ፣ ነበር ። አይቶ ፣ ዛሬስ ፣ ይህ ፣ ቦታ ፣ የሴት ፣ መራመጫ ፣ ሆነን ፣ ብሎ ፣ እገባለሁ ፣ ሲል ፣ ከበሩ ፣ ላይ ፣ ቆመች ። እግዚአብሔር ፣ ያሰስል ፣ ሊተ ፣ ዝክረኪ ፣ እምውስተ ፣ ልብየ ፣ ብሎ ፣ ገፍቷት ፣ ገባ ። ደንግጣ ፣ ወደቀች ፤ ደዌ ፣ አደረባት ። አፋፍሰው ፣ እስክንድርያ ፣ ከቴዎፍሎስ ፣ ዘንድ ፣ ወሰዷት ። እንደ ፣ ምን ፣ ሁነሽ ፣ መጣሽ ፣ አላት ። መክፈልት ፣ ሲሹ ፣ መቅሠፍት ፣ እንዲሉ ፤ እገናኛለሁ ፣ ብዬ ፣ ደዌ ፣ አትርፌ ፣ መጣሁ ፣ እንጂ ፤ እሱስ ፣ እንድም ፣ አልተናገረኝ ፣ አለችው ። አይዞሽ ፤ ቅዱሳን ፣ ቀን ፣ ያዩ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ሌሊት ፣ ይዋጋቸዋልና ፣ ያን ፣ ፈርቶ ፣ ነው ፣ እንጂ ፤ አሁን ፣ ያዝንልሻል ፣ አላት ። ይህን ፣ ሲላት ፣ ወዲያው ፣ ድናለች ።
ይቤ ፣ መተርጕም ፤ እስመ ፣ ዕራቁ ፣ ስብሐት ፣ የሐሥሞሙ ፣ ለትሩፋን ፣ ፈድፋደ ፣ እምዘተርፉ ፣ ሕግማት ።
ከቀሩት ፣ ጎጣውእ ፣ ይልቅ ፣ ውዳሴ ፣ ከንቱ ፣ ፍጹማንን ፣ ይጐዳቸዋልና ።
ወውእቱ ፣ ይወልድ ፣ ሎሙ ፣ ትዝጎርተ ።
ትዕቢትን ፣ ያመጣባቸዋልና ፣ ስለዚህ ፣ ነው ።
ወአባ ፣ ወቅሪስኒ ፣ ይሰምዮ ፣ እልቅርጥበ ።
አባ ፣ ወቅሪስም ፣ ውዳሴ ፣ ከንቱን ፣ ዳሞትራ ፣ አለው ።
እስመ ፣ ይንስክ ፣ እምኵሉ ፣ ገቦ ።
በብዙ ፣ ወገን ፣ ይነድፋልና ። ዳሞትራ ፣ ካንድ ፣ ላይ ፣ የነደፈ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ በሰውነት ፣ ሁሉ ፣ ተሰራጭቶ ፣ ይገድላል ። የዚህም ፣ መድኃኒቱ ፣ ፍየል ፣ አርዶ ፣ አወራርዶ ፣ የዚያን ፣ አንጀት ፣ ጫፉን ፣ ይዞ ፣ ያገቡት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ መርዙ ፣ በዚያ ፣ ሁሉ ፣ ይገኛል ። አንድም ፣ እልቅርጥብ ፣ የተባለ ፣ አሜከላ ፣ ክሽሽላ ፣ ነው ፤ ሁለንተናው ፣ እሾህ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ በብዙ ፣ ወገን ፣ ይዋጋልና ።
ወይሬሲ ፣ ድኩመ ፣ ንጹለ ።
ውዳሴ ፣ ከንቱ ፣ ደክማውን ፣ ኃይለኛ ፣ ያደርጋል ።
እገሌ ፣ እንጂ ፣ ብርቱ ፣ ነው ፣ ያሉት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣

www.ethiopianorthodox.org

አፈፍ ፡ አፈፍ ፤ በድረግ ፡ በድረግ ፡ ይላል ።

ወለኃያል ፡ ድኩመ ።

ኃይለኛውን ፡ ደከማ ፡ ያደርጋል ፡ አለ ፤ እገሌማ ፡ ምን ፡ ዓቅም ፡ አግኝቶ ፡ ዓቅም ፡ የለው ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈጽሞ ፡ ይደክማል ።

ወለአረጋዊ ፡ ደቂቶ ።

አረጋዊን ፡ ሕፃን ፡ ያደርጋል ፡ አለ ፤ እገሌ ፡ እንጂ ፡ ላዩ ፡ ሽበት ፡ ውሥጡ ፡ ብረት ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይጸናናል ።

ወለደቂቅ ፡ አረጋዊ ።

ሕፃንን ፡ አረጋዊ ፡ ያደርጋል ፡ አለ ፤ እገሌ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይለዝባል ።

ወያስተሬሲ ፡ ምስኪን ፡ ዘይለብስ ፡ ሠቀ ፡ ምስለ ፡ ዘይለብስ ፡ ሐሪር ።

ሚነ ፡ ቢል ፤ በተንኮል ። ምስኪነ ፡ ቢል ፤ ማቅ ፡ ምንጸፍ ፡ የለበሰ ፡ ድኃውን ፡ ወርቀ ፡ ዘበ ፡ ግምጃ ፡ ከለበሰ ፡ ጋራ ፡ ያስተካክለዋል ፡ አለ ፤ የኔ ፡ እንጂ ፡ ዳባ ፡ ከፓ ፡ ላንቃ ፡ ናት ፡ ይላል ።

ወበእንቲኣሁ ፡ ይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘደረጊ ፡ ክመ ፡ ኢይትገፈታዕ ፡ እምኔሁ ፡ አሐዱኒ ።

ደረጊ ፡ አገሩ ፤ አንድም ፡ ማዕርጋዊ ፡ ሲል ፡ ነው ። ዓረባዊ ፡ ሲል ፡ ዓረቢ ፡ እንዲል ፤ ደረጋዊ ፡ ሲል ፡ ደረጊ ፡ አለ ። ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ እንዲህ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ካሥረኛው ፡ ማዕርግ ፡ ደርሶ ፡ የነበረ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ የሚያመልጥ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የለም ፡ አለ ።

ወለእመ ፡ ረክበ ፡ ውስተ ፡ ሰብእ ፡ ማኅደረ ፡ ርሑቅኬ ፡ ክመ ፡ ይሑር ፡ እምኔሁ ።

በሰውም ፡ ያደረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መለየቱ ፡ ጭንቅ ፡ ነው ፤ ያስቸግራል ። አንድም ፡ ርሑቅኬ ፡ ይላል ፤ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ በበዓት ፡ ተከቶ ፡ ወደሚኖር ፡ ባሕታዊ ፡ መሄድ ፡ ያሻል ።

ወዝንቱ ፡ እሱር ፡ ያንሳጉ ፡ ኅሊናሁ ፡ ድኅረ ፡ ትፍግዕቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርኅት ።

በውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ያር ፡ የተያዘ ፡ ሰው ፡ ሁለጊዜ ፡ የሚያሻውን ፡ ተድላ ፡ ደስታውን ፡ ተከትሎ ፡ ሀሊናውን ፡ ያባክናል ።

ወይትክፈል ፡ ዘእንበለ ፡ ኅቡም ።

ከአባዚአብሔር ፡ ፈጽሞ ፡ ይለያል ።

ወኢያኃድግ ፡ በጊዜ ፡ ሕቅ ፡ ማእሰሪሁ ፡ ዕፁብ ፡ ፍትሐት ፡ እምኔሁ ።

ሊፈቱት ፡ ጭንቅ ፡ የሚሆን ፡ ግሥሪያንቱ ፡ ከሕሊና ፡ ፈጥኖ ፡ አይሰይም ።

ብውኅኒኒ ፡ ግርቆስ ፡ ይብል ፡ ክመ ፡ ብዙኃ ፡ ምሕረት ፡ ወተግሣጽ ፡ ፈድፋደ ፡ ይክል ፡ ያግርሮ ፡ ለዝ ፡ ሕግም ።

ማርቆስም ፡ ብዙኅ ፡ ምሕረት ፤ ብዙኅ ፡ ተግሣጽ ፡ ጌታ ፡ ይህን ፡ የውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ያር ፡ ያጠፋልን ፡ ዘንድ ።

ወያዕትት ፡ አዕጹቂሁ ፡ እንተ ፡ ትበቍል ፡ ወትትወለድ ፡ እምኔሁ ።

ከውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ የምትነቃ ፡ የምትገኝ ።

ወተጎድር ፡ ምስሌሁ ።

ከሱ ፡ ጋራ ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ ግብሩንም ፡ ያርቅልን ፡ ዘንድ ፡ እንዲቻለው ፡ ተናገረ ።

ዘክመ ፡ ውኅደተ ፡ ሃይማኖት ።

ይህም ፡ እንደ ፡ ሕፀፀ ፡ ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይትወለድ ፡ እምኔሁ ።

የሃይማኖት ፡ ሕፀፅ ፡ ከውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ይገኛልና ።

በክመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በውስተ ፡ ወንጌል ።

ጌታ ፡ በወንጌል ።

እፎ ፡ ትክሉ ፡ ክመ ፡ ትእመኑ ፡ እንዘ ፡ ተኃሥሡ ፡ እንትሙ ፡ ስብሐተ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ወኢተኃሥሡ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋሕድ ። (ዮሐ ፭ ፣ ፵፬) ።

እንዲህ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ።

ወይትወለድመ ፡ እምኔሁ ፡ ቅንዓት ።

ዳግመኛም ፡ ከውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ምቀኝነት ።

ወተቃሕዖ ፡

ፍክክር ።

ወሚን ።

ተንኮል ።

ወአፍቅሮተ ፡ መዊዕ ።

እኔ ፡ ያልሁት ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ በነገር ፡ ማሸነፍን ፡ መውደድ ።

ወጽልዕ ።

መጸላት ።

ወአድልዎ ።

ማድላት ።

ወንጕርጓር ።

ቂም ፡ በቀል ።

ወሕብል ።

ሐሰት ፤ አንድም ፡ አጥብቆ ፡ ድፍረት ።

ወሕግማት ፡ ኅቡኣት ።

ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ያር ፡ ይመጣል ።

ወሰይጣን ፡ ስብሐት ፡ ብሁል ፡ ብዙኅ ፡ ሚን ፡ ወእክይ ።

ተንኮሉ ፡ የበዛ ፡ ሰይጣን ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱም ፡ ይመጣል ። አንድም ፡ ማንሽ ፤ ይህ ፡ ሰይጣን ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ተንኮሉ ፡ ክፋቱ ፡ የበዛ ፡ ነው ።

ወእስሰኬ ፡ በጽሑ ፡ ኀበ ፡ ተቃትሎ ፡ ዝ ፡ ሕግም ።

ይህን ፡ ያር ፡ መዋጋት ፡ የሚቻላቸው ፡ ሰዎች ።

እምድኅረ ፡ ሙኅት ፡ ኮሎ ፡ ሕግማት ።

ያሩን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ከነሡ ፡ በኋላ ።

ለእመ ፡ ሞዕዎ ።

ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ ድል ፡ ቢነሱ ።

ይበጽሑ ፡ ኀበ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ፡ ወፍጹም ።

ወደ ፡ ፍጹምነት ፡ መዓርግ ፤ ወደ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ፡ ይደርሳሉ ።

ክመ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘኮነ ፡ ተሐያዬ ፡ ስብሐተ ፡ ወኀሳረ ፡ ዕዕለተ ፡ ወውዳሴ ፡ እስክኑ ፡ ይቤ ፡ ምውት ፡ አነ ፡ በኀበ ፡ ኅለም ፤ ወኀለምኒ ፡ ምውት ፡ በኀቤየ ። (ገላ፮ ፣ ፲፬) ።

እንዲህ ፡ እስከማለት ፡ ደርሶ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ ስብሐት ፡ ብጡልን ፤ ስድቡን ፡ ተዋርዶውን ፡ ቸል ፡ ይል ፡ እንደነበረ ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ይበጽሑ ።

እስሰ ፡ ውእቶሙኒ ፡ ክመዝ ፡ ያስተሓቅፉ ፡ ክብራቲሁ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ።

እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ሹመት ፡ ሽልማት ፡ ይንቃሉ ።

ወይፌስይዖ ፡ ሀኮሰ ።

ይጐዳናል ፡ ይላሉ ፤ አንድም ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ሥጋዊ ፡ ክብርን ፡ የሚንቁ ፡ ይሬስይዖ ፡ ሀኮሰ ፡ እንዲጐዳ ፡ ያውቁታል ።

እስክነ ፡ ውእቶሙ ፡ የንዝኑ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘያክብሮሙ ።

የሚያከብራቸው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እስከማዘን ፡ ደርሰው ።

በክመ ፡ ገብረ ፡ አርሳንዮስ ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ፡ ሮማዊት ።

አርሳንዮስ ፡ ከሮም ፡ በመጣች ፡ ሴት ፡ እንዳደረገው ።

ወታድራስ ፡ ዘመጽአ ፡ ጸጹ ፡ እምሊቃናት ፡ ክመ ፡ ይርአዮ ።

አባ ፡ ታድራስም ፡ ከአለቆች ፡ ወገን ፡ ሊገናኘው ፡ በመጣ ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እንዳደረገው ።

ወተናገረ ፡ እንክ ፡ ምስሌሁ ፡ በተሐይዮ ።

ይተርክል ፤ በተሐይዮ ፡ ሁኖ ፡ ተነጋገረው ።

ወቆብው ፡ ውሩት ፡ ዲበ ፡ መትክፍቱ ።

ቆቡ ፡ ከጫንቃው ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ነበር ።

ወእንግድዓው ፡ ዕፍቅ ።

ደረቱም ፡ ተገልጦ ፡ ነበር ።

እስመ ፡ ኮነ ፡ ትዕርዝቱ ፡ ሕልትተ ።

ጥብቆው ፡ አልቆበት ፡ ነበርና ።

ወዖበ ፡ ሖረ ፡ ሲቅ ፡ ይቤሎ ፡ አረጋይ ፤ ለምንት ፡ ገበርክ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ ክመዝ ፡ ዘመጽአ ፡ ክመ ፡ ይትባረክ ፡ ወይብቍዕ ፡ እምኔክ ።

አለቃው ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ አረጋዊ ፡ መጥቶ ፡ እመረቃለሁ ፡ እጠቀማለሁ ፡ ብሎ ፡ የመጣውን ፡ ሰው ፡ ምነው ፡ እንዲህ ፡ አደረግኸው ።

ወአናፈቆ ፡ እንክ ።

ለምን ፡ አጠራጠርከው ።

ወአንጕልክሁ ።

አንተን ፡ ነቅፎ ፡ አምቶ ፡ እንዲጎዳ ፡ ለምን ፡ አደረግኸው ፡ አለው ።

እውሥአ ፡ እንዘ ፡ ይብል ።

እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፤ ምን ፡ አለ ።

ኢኮነ ፡ ኀስነስ ፡ ዘነኃሥሥ ፡ ሥምረተ ፡ ብእሲ ፡ አላ ፡ ሥምረተ ፡ እግዚአብሔር ።

እኛስ ፡ የጌታን ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰውን ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸም ፡ የምንወድ ፡ አይደለንም ።

ዘፈቀደ ፡ ለይብቍዕ ፡ ወዘፈቀደ ፡ ለይናፍቅ ።

እጠቀማለሁ ፡ ያለ ፡ ይጠቀም ፤ እጠራጠራለሁ ፡ ያለም ፡ ይጠራጠር ፡ አለ ። እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ የጌታውን ፡ ዕቃ ፡ ጥሎ ፡ አስታርቀኝ ፡ ብሎ ፡ መጣበት ፤ ሂድ ፡ ይታረቅሃል ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ፡ ታረቀ ፤ ለጌታው ፡ ደግሞ ፡ ጌታ ፡ አለው ፤ ያ ፡ ተጣልቶት ፡ አዝኖ ፡ አየው ፤ ምነው ፡ አዝነሃል ፡ ቢለው ፡ ጌታዬ ፡ ተጣልቶኝ ፡ አለ ፤ እኔ ፡ ስታረቅ ፡ የነገረኝ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ እስኪ ፡ ከሱ ፡ እንሂድ ፡ ብሎ ፡ ይዞት ፡ ሄደ ።

አባ ፡ ታድራም ፡ እንደ ፡ መጡበት ፡ አውቆ ፡ በዓቱን ፡ ለቆ ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፤ ቆቡን ፡ ከትከሻው ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ዕራቁቱን ፡ ሁኖ ፡ ቸ ፡ ቸ ፡ ሲል ፡ ቆያቸው ። እነዚያም ፡ ከበዓቱ ፡ አይተው ፡ ቢያጡት ፡ ካለበት ፡ ሄደው ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ አባ ፡ ታድራን ፡ አታውቅምን ፡ አሉት ። አባ ፡ ታድራን ፡ አላቸው ፤ አዎን ፡ ቢሉት ፤ እልፍ ፡ ብለው ፡ ምስር ፡ የሚነቅሉ ፡ አሉ ፤ እሊያ ፡ ሰዎች ፡ ይንገሯችሁ ፡ አላቸው ። ሲያልፉ ፡ ምላሱን ፡ አውጥቶ ፡ አለመጠባቸው ። ሂደው ፡ አባ ፡ ታድራን ፡ አታውቁምን ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁ ፡ እሱን ማ ፡ ከዚያ ፡ አልፋችሁት ፡ መጥታችሁ ፡ አሏቸው ። ይኸ ፡ ዕብዱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተመልሰው ፡ ሂደዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ኋላ ፡ የሚያውቀው ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ እንጠቀማለን ፡ ብለው ፡ የመጡትን ፡ ለምን ፡ አጠራጠርሃቸው ፡ ቢለው ፤ አባ ፡ ታድራ ፡ እንዲህ ፡ ማድረጉ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ፈርቶ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ይበል ፤ የሚያማኝም ፡ ይማኝ ፡ ብሎታል ።

ተስእሎ ፡ ፶ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምንትኩ ፡ ሙሴ ፡ ጽልሙት ፡ ኮነ ፡ ይትቄበል ፡ ነገደ ፡ ምስለ ፡ አፍቅሮቱ ፡ ጽሙና ።

ሙሴ ፡ ጸሊም ፡ ተባሕትዎን ፡ ሲወድ ፡ እንግዳ ፡ ይቀበል ፡ የነበረ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ያርኢ ፡ ለሰብእ ፡ ግብረ ፡ ምንዮስናሁ ።

የምንዮስናን ፡ ሥራ ፡ ለሰው ፡ ይገልጥ ፡ ዘንድ ።

ወአፍቀረ ፡ እንክ ፡ ያዕርፎሙ ፡ ለሰብእ ፡ በጻግሁ ፡ በጊዜ ፡ ንስሓው ።

በመነኰሰ ፡ ጊዜ ፡ ጽሮ ፡ ጳሮ ፡ ባገኘው ፡ ገንዘብ ፡ አኃውን ፡ ያሰርፍ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ወደደ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፶፩ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ዝኩ ፡ አረጋዊ ፡ ርእየ ፡ መላእክት ፡ ምስለ ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ በውስተ ፡ ሠረገላ ፡ በአምሳለ ፡ ሰብእ ።

ያ ፡ አረጋዊ ፡ መላእክትን ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ከአባ ፡ ሙሴ ፡ ጋራ ፡ በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ አየ ፤ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ።

ወእፎ ፡ ተርእየ ፡ መንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ አርሳንዮስ ፡ በውስተ ፡ መረገላ ፡ ክልእ ። (ተስእ ፡ መተ) ።

መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በንድ ፡ መርከብ ፡ አርሳንዮስን ፡ እሳት ፡ ሁኖ ፡ ተውሕዶት ። አንድም ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ተቀምጠበት ፡ ታየ ።

ወእፎሙ ፡ ርእየ ፡ አረጋዊ ፡ ክልእኒ ፡ በሳዕለ ፡ ጥምቀት ፡ ወእስኬማ ፡ ምንዮስና ።

ሌላውም ፡ አረጋዊ ፡ በጥምቀት ፡ ጊዜ ፤ ምንዮስና ፡ በመቀበል ፡ ጊዜ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ አየው ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አምሳል ፡ መታየቱ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ዮሐንስኒ ፡ መጥምቅ ፡ ርእየ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ። (ማቴ፫ ፡ ፲፮) ።

ልማድ ፡ ነው ፤ ዮሐንስም ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ሲወርድ ፡ አይቶታል ።

ወግብረ ፡ ሐዋርያትኒ ፡ ትሰምዕ ፡ ክመ ፡ ወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕለ ፡ አርድእት ። (ግብ፪ ፡ ፩—፱) ።

ግብረ ፡ ሐዋርያትም ፡ የእሳት ፡ ላንቃ ፡ መስሎ ፡ ለሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ተሰጣቸው ፡ ትመሰክራለች ።

ወዜናትኒ ፡ ይሰምዓ ፡ ክመ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አስተርአየት ፡ ዲበ ፡ ርእሰ ፡ አሐዱ ፡ እምቅዱሳን ፡ በአምሳለ ፡ ብርሃን ፡ ኮከብ ።

በዜና ፡ አበውም ፡ ከቅዱሳን ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ብሩህ ፡ ከከብ ፡ መስሎ ፡ እንደ ፡ ታየ ፡ ተነግሯል ።

ወለካልእኒ ፡ በአምሳለ ፡ ደቂቅት ፡ ድንግልት ፡ ናዝዘቶ ፡ ወአኅየለቶ ፡ በውስተ ፡ መክራው ።

ለሌላውም ፡ በልጃገረድ ፡ አምሳል ፡ ታይታ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመከራው ፡ ጊዜ ፡ አጸናችው ።

እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ አንድ ፡ መነኰሴ ፡ ጸር ፡ ተነሥቶበት ፡ ዓለሙን ፡ መስዬ ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲመጣ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተኳለች ፡ የተቀባች ፡ ሕፃን ፡ መስሎ ፡ ታየው ። እቴ ፡ ወዴት ፡ ትሄጃለሽ ፡ አላት ፤ ይኸ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ያልፋል ፤ እንዳበባ ፡ ይረግፋል ፡ ሲሉ ፡ ሰምቼ ፡ ለምናኔ ፡ መውጣቴ ፡ ነው ፡ አለችው ። ኤ ፡ ይሆት ፡ እንኳ ፡ ስትመንን ፡ እኔ ፡ ምንዮስናዬን ፡ ላፈርስ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ተመልሶ ፡ ሂዷል ።

ወይእቲ ፡ ታስተርኢ ፡ ለረኣይያን ፡ በአምሳላት ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሁ ።

ልማድ ፡ ነው ፤ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምሥጢር ፡ ለሚያዩ ፡ ለበቁ ፡ ሰዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አምሳል ፡ ትታያለች ።

ተስእሎ ፡ ፶፪ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ጽሑፍ ፡ እስመ ፡ አባ ፡ ሲሶይ ፡ ኮነ ፡ ሶበ ፡ የአቱ ፡ እግብር ፡ ወእምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይጕይይ ፡ ኀበ ፡ በዓቱ ፡ ፍጡነ ።

አባ ፡ ሲሶይ ፡ ከማኅበር ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ በዓቱ ፡ ሸሽቶ ፡ ይገባ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ተጽኗል ።

ወኮኑ ፡ መንፈቀ ፡ አኃው ፡ ይብሉ ፤ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ሰይጣን ።

እኩሉቶቹ ፡ አኃው ፡ ከዚያ ፡ ከበረሃ ፡ ብቻውን ፡ ሰለ ፡ ሰው ፡ የማያስወድድ ፡ ሰይጣን ፡ እንኚ ፡ አድሮበት ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ውእቱሰ ፡ ኮነ ፡ ይገብር ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ።

እሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ማድረጉ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነው ።

ምንትኑ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለቃሉ ፡ ወምግባሩ ።

ቃሉ ፡ ያለውን ፡ ጕየዩ ፡ ብሎ ፡ ያመጣዋል ፤ ምግባሩ ፡ መሸሹ ። አንድም ፡ ቃሉሙ ፤ ቦቱ ፡ ሰይጣን ፡ ማለታቸው ፤ ወምግባሮሙ ፤ መንቀፋቸው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስ ፡ ኮኑ ፡ ልሕሱሓን ።

ቦቱ ፡ ሰይጣን ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ደካሞች ፡ ነበሩና ።

ወበማእከል ፡ ዘክማሆሙ ፡ ይትቃተልዎሙ ፡ ሰይጣናት ፡ ለተገላደያን ።

ሰይጣናት ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ድኩማን ፡ አኃውን ፡ ጋሻ ፤ መከታ ፤ ሠረገላ ፡ አድርገው ፡ ትሩፋት ፡ የሚሠሩ ፡ ፍጹማንን ፡ ይዋጓቸዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ጊዜ ፡ በዘርዝዮ ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመንቀፍ ።

ክመ ፡ ዝንቱ ።

አሁን ፡ ቦቱ ፡ ሰይጣን ፡ እንዳሉት ።

ወጊዜ ፡ በካልኣታ ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሌላ ፡ ጸር ።

ወምግባረ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ዘኮነ ፡ ይገብሮ ።

ሲሶይ ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ይሠራው ፡ የነበረ ፡ ሥራ ።

ውእቱኬ ፡ ጕዩዮቱ ፡ ኀበ ፡ በዓቱ ።

ይኸውም ፡ ወደ ፡ በዓቱ ፡ መሸሽ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ መሸሹ ።

እምዜና ፡ ወነገር ።

ወሬ ፡ ከመስማት ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ከመነጋገር ፡ ነው ።

ክመ ፡ ትእዛዘ ፡ አባ ፡ ኢሳይያስ ፡ ዘይብል ።

አባ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንደተናገረ ።

ሶበ ፡ ሠርሕዎሙ ፡ ለማኅበር ፡ አው ፡ ተንሥኡ ፡ እማዕድ ።

ማኅበር ፡ ከተሰነባበቱ ፤ ከማዕድ ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ።

ኢትንበር ፡ እንክ ፡ ትትናገር ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ኢ ፡ ነገረ ፡ ዓለም ፡ ወኢ ፡ ነገረ ፡ በቍዔት ።

ሥጋዊም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፤ መንፈሳዊም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ትነጋገር ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጠህ ፡ አትቅር ።

አላ ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ በዓትከ ፡ ወብኪ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትከ ።

ወደ ፡ በዓትህ ፡ ተመልሰህ ፡ ኃጢአትህን ፡ አስበህ ፡ አልቅስ ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ።

አባ ፡ መቃርስኒ ፡ ይቤ ፡ ሶበ ፡ ሠርሖት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኦኦኃውየ፡ ጕየዩ ፡ እንክ ።

አባ ፡ መቃርስም ፡ አኃውን ፡ ምዕመናን ፡ በተሰናበቱ ፡ ጊዜ ፡ እናንተም ፡ ሽሹ ፡ አላቸው ።

ወይቤልዎ ፡ አይቴ ፡ ንጕይይ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዝ ፡ ገዳም ።

ከዓለም ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ሸሽተን ፡ መጥተናል ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ገዳም ፡ ሸሽተን ፡ ወዴት ፡ እንደርሳለን ፡ አሉት ።

ወአልዓለ ፡ እደው ፡ ዲበ ፡ አፉው ።

እጁን ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ ቃጣ ።

ወይቤ ፡ እምዝንቱ ፡ ጕየዩ ።

ሽሹ ፡ ያልኋችሁ ፡ ከዚህ ፡ ከነገሩ ፡ ነው ፤ መናገሩን ፡ ተዉ ፡ አላቸው ።

ወከመዝ ፡ ኮኑ ፡ ይጕይዩ ፡ ኮኑ ፡ ፭፭ ፡ እምኔሆሙ ።

ይህን ፡ ይዘው ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ እየሸሹ ፡ ወደ ፡ በዓታቸው ፡ ይገቡ ፡ ነበር ።

ወውእቱኬ ፡ አርምሞ ።

ይኸውም ፡ አርምሞ ፡ ነው ። አንድም ፡ አርምሞን ፡ ለመያዝ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፶፫ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምንትኑ ፡ ዘኮኑ ፡ አበው ፡ ቀደምት ፡ ይትአምኑ ፡ በበይናቲሆሙ ፤ ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ይጼልዩ ፡ ወካዕበ ፡ ይትአምኑ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ በፍጻሜ ።

ቀደምት ፡ አበው ፡ አስቀድመው ፡ እጅ ፡ ይነሣሉ ፤ ኋላ ፡ ያስታዝቱ ፤ ሲጨርሱ ፡ ደግሞ ፡ እጅ ፡ ተነሣሥተው ፡ ይቀመጡ ፡ የነበረ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ጀሉት ፡ የቀደመ ፡ ተአምኖ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የሆነ ፡ ስለምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ብሑታን ፡ ኮኑ ፡ በቀዳሚ ፡ ዖበ ፡ ያርኅዉ ፡ ጥኅት ፡ ወይፌእይዎ ፡ ለእግ ፤ እው ፡ ለእጉሉ ፡ ይወድቁ ፡ ሶቱ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በገጻቲሆሙ ።

ባሕታውያን ፡ ቀድሞ ፡ በር ፡ ከፍተው ፡ አረጋዊን ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ ወድቀው ፤ ወጣኒዉንም ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ እጅ ፡ ይነሡት ፡ ነበር ።

ወካዕበ ፡ ይትአምኑዎ ፡ ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ይበውኡ ፡ ወይጼልዩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገብተው ፡ ያስታዝታሉ ።

ወይገብኡ ፡ ይትአምኑ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወይነብሩ ።

ሲጨርሱ ፡ ደግሞ ፡ እንደፊተኛው ፡ እጅ ፡ ተነሣሥተው ፡ ተመልሰው ፡ ይቀመጣሉ ።

ወክመዝ ፡ ገብረ ፡ አባ ፡ አርሳንዮስ ፡ ምስለ ፡ ዝኩ ፡ አብ ፡ ዖበ ፡ ርእዮ ፡ ሰገደ ፡ ሶቱ ።

አርሳንዮስም ፡ በዚህ ፡ ልማድ ፡ ሊገናኘው ፡ የመጣውን ፡ አረጋዊ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ወድቆ ፡ እጅ ፡ ነሣው ።

www.ethiopianorthodox.org

ወበእንተሰ ፡ እፍቅሮቱ ፡ ጽሙና ፡ ኢተንሥአ ፡ ክመ ፡ ይትአምኖ ፡ ወይባእ ፡ ምስሌሁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ተባሕትዎን ፡ ስለ ፡ ወደደ ፡ ተግናኝቶት ፡ አብሮት ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ።

ወይቤሎ ፡ አረጋዊ ፡ ኦአብ ፡ ተንሥእ ፡ ክመ ፡ አአምኅክ ፡ ወኢተንሥአ ።

አባቴ ፡ ተነሣና ፡ እጅ ፡ ነሥፎህ ፡ ልሂድ ፡ ብሎ ፡ ለ መነው ፡ አልተነሣለትም ።

ወሶበ ፡ ኮኑ ፡ ሰይጣናት ፡ የሐውሩ ፡ ኀበ ፡ ባሕታውያን ፡ ተመሲሎመ ፡ አኃው ፡ ክመ ፡ ያስሕትዎሙ ፡ ወያብጥልዎሙ ፡ አምግባሮሙ ፡ መንፈሳዊ ።

ዛሬ ፡ ግን ፡ ሰይጣናት ፡ አኃውን ፡ መስለው ፡ ሊያስታቸው ፤ ከበጎ ፡ ሥራቸው ፡ ሊያሰነካክሏቸው ፤ ወደ ፡ ባሕታውያን ፡ የሚሄዱ ፡ ቢሆን ።

ኮኑ ፡ እንከ ፡ አኃው ፡ ያቀድሙ ፡ ጸሎተ ።

ጸሎትን ፡ አስቀደሙ ።

እስክ ፡ ዖበ ፡ የአምርዎ ።

ለይተው ፡ እስኪያውቁት ፡ ድረስ ።

ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሰይጣን ፡ ይቤጥል ፡ በኃይለ ፡ ጸሎት ።

ሰይጣን ፡ ቢሆን ፡ በጸሎት ፡ ድል ፡ ተነሥቶ ፡ ይሄዳል ።

ወአሐዱ ፡ እምብዑኣውያን ፡ ኮነ ፡ በውስተ ፡ ጸሎቱ ፡ ጊዜ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ።

ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ ከቅዱሳን ፡ አንዱ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ሲጸልይ ።

መጽአ ፡ እንከ ፡ ጎቤሁ ፡ ሰይጣን ።።

ሰይጣን ፡ ወደሱ ፡ መጣ

ወጸርሐ ፡ ሎቱ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አነ ፡ እገሌ ፡ ኀርክከ ።

እኔ ፡ ወዳጅህ ፡ እገሌ ፡ ነኝ ፡ ከፈትልኝ ፤ ከፈትልኝ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ወአርኃወ ፡ እንከ ፡ ኖኅተ ።

በሩን ፡ ከፈተለት ።

ወዖበ ፡ አርኃወ ።

በከፈተለት ፡ ጊዜ ።

ተአምኅ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ።

ሰይጣን ፡ ከመነኩሴው ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ።

ሰይጣንሰ ፡ ኮነ ፡ ክልበ ፡ ነዊኅ ።

ሰይጣን ፡ ሶለግ ፡ ውሽ ፡ ሆነ ።

ወሰፍሐ ፡ ቆሞ ፡ እምድር ፡ እስከ ፡ ርእሰ ፡ ዝኩ ፡ እጉሉ ።

ቁመቱን ፡ አስተካከለ ፤ አንድም ፡ ቆሙ ፡ ይላል ፤ ቁመቱ ፡ ከእግር ፡ እስከራሱ ፡ ተካክሎ ፡ ቆመ ።

ወሐቀፎ ፡ በእደሁ ።

በወርቹ ፡ አቀፈው ።

ወነፍሐ ፡ ውስተ ፡ ገጹ ።

አፈነፈነው ።

ወጎሠሦ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ።

የሚነክሰው ፡ መሰለ ።

ወኢደንገፀ ፡ እጉሉ ፡ እምኔሁ ።

ያ ፡ መነኩሴ ፡ ጭን ፡ ምሑረ ፡ ዐብዕ ፡ ነውና ፡ አልደ ነገጸለትም ።

አላ ፡ ይቤሎ ፡ እንትሰኬ ፡ ሰይጣንሰ ፡ ውእቱ ።

ከነገሩስ ፡ ሰይጣን ፡ ነህን ፤ ለካ ፡ ሰይጣን ፡ ነህ ።

ሰላምከኒ ፡ ይመስል ፡ ሰላመ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፡ ረድእከ ።

ሰላምታህም ፡ የደቀ ፡ መዝሙርህ ፡ የይሁዳን ፡ ሰላምታ ፡ ይመስላል ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ ኢደንገፀ ።

ተስእሎ ፡ ፶፩ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ በከመ ፡ ዓሣ ፡ ዖበ ፡ ወጽአ ፡ እማይ ፡ ይመውት ።

አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ አሣ ፡ ከባሕር ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሞት ፤ ውሀ ፡ ቢደርቅ ፡ ዓሣ ፡ ያልቅ ፡ እንዲሉ ።

ከማሁ ፡ መነኮስኒ ፡ እምከመ ፡ ጕንደየ ፡ እምኔቱ ፡ ወበዓቱ ፡ ጎበ ፡ ካልእ ፡ ይጠፍዕ ።

መነኰሴም ፡ ከገዳሙ ፡ ከበዓቱ ፡ ወጥቶ ፡ ከሌላ ፡ ቢውል ፡ ቢያድር ፡ ይጠፋል ፡ አለ ፤ መጥፋቱ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ዘውእቱ ፡ ይመውት ፡ በመንፈሱ ።

ይጠፍዕ ፡ ያለው ፡ በነፍሱ ፡ ይሞታል ፡ ሲል ፡ ነው ።

እስመ ፡ ሕይወታ ፡ ለነፍስ ፡ ይእቲ ፡ ቀራብ ፡ ጎበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ።

የነፍስ ፡ ሕይወቷ ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ መቅረብ ፡ ነውና ።

ወከመዝ ፡ ይከውን ፡ በተዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ።

ይኸም ፡ ቀራብ ፡ ያለው ፡ ሁለጊዜ ፡ ጌታን ፡ በመዘከር ፡ ይገኛል ።

ወለእመሰ ፡ ጕንደየ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ይትመተር ፡ ተዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምኔሁ ።

በዓለም ፡ ቢውል ፡ ቢያድር ፡ ጭን ፡ ተዘክሮ ፡ ከልቡናው ፡ ይለያል ።

በእንተ ፡ ርእየቱ ።

የሚያይ ፡ የሚሰማ ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ወተናግሮቱ ፡ ምስለ ፡ ዕብእ ።

ከሰው ፡ ጋራ ፡ የሚጫወት ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ወይረሥዕ ፡ ጻማቲሁ ፡ ትሩፋተ ።

ደክሞ ፡ የሚሠራውን ፡ ትሩፋቱን ፡ ይዘነጋል ።

ወያፈቅር ፡ ዕረፍተ ።

ዕረፍተ ፡ ሥጋ ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡ ይወዳል ።

ወይትህወክ ፡ ልቡ ፡ በፍትወት ።

ልቡናው ፡ በፈቲው ፡ ጸር ፡ ይነሣሣል ፤ ይሰነካከላል ።

ወይወድቅ ፡ ልቡ ፡ ውስተ ፡ ሕማማት ።

ልቡ ፡ በሐልዮ ፡ ኃጢአት ፡ ይያዛል ።

እንተ ፡ ባቲ ፡ ይከውን ፡ ሞቱ ።

ያን ፡ ሞቱ ፡ የሚደረግበት ፡ አለ ።

ዘውእቱ ፡ ርሑቅ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ሕያው ።

ይኸውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መለየት ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፶፪ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ አኃው ፡ ተጋብኡ ፡ በበኀለ ፡ ትንግዴሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ።

አኃው ፡ የትንግዴ ፡ ለት ፡ ተሰብስበው ፡ በአስቄጥስ ፡ ጉባኤ ፡ አደረጉ ።

ገዳማውያን ።

እንደ ፡ ሲሶይ ፡ ያሉ ።

መፈላስያን ።

ከሰንያ ፡ ከአስክንድርያ ፡ ተወፃዕተው ፡ የሄዱ ።

ወዝጉሓውያን ።

እንደ ፡ አጋቶን ፡ የዘጉ ።

ወባሕታውያን ፡ ቅሩበ ፡ ምኔት ።

እንደ ፡ ጠሞቴዎስ ፡ ከገዳሙ ፡ አጠገብ ፡ ተባሕትዎ ፡ የያዙ ። አንድም ፤ ተጋብኡ ፡ ቅሩበ ፡ ምኔታት ፤ ከገዳሙ ፡ አጠገብ ፡ ተሰብስበው ።

ወጎብሩ ፡ በእንተ ፡ ጎዳጎ ፡ በኀቱ ፡ ለመነኰስ ፡ ክሙ ፡ ዕፀብ ፡ ቀትላት ።

መነኰሰ ፡ ከበዓቱ ፡ ቢወጣ ፡ ጸር ፡ እንዲጸናበት ።

እስመ ፡ እስሰ ፡ ተርፋ ፡ ቀትላት ፡ ይቤጥል ፡ ፍጡን ።

ከበዓቱ ፡ ባይወጣ ፡ ጭን ፡ ጸር ፡ እንዲቀልለት ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ተናግሩ ። የትንግኤ ፡ ለት ፡ ተሰብስቦ ፡ እንደ ፡ መብላት ፤ እንደ መጠጣት ፡ ይህን ፡ ሥርዓት ፡ ሠርተው ፡ ተለያይተዋል ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ለአዝልፎ ፡ ጽሙና ፡ ይከውን ፡ ምስሌሃ ፡ ተስፋ ፡ ሠናይ ።

በበዓት ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ በጎ ፡ ተስፋ ፡ አለበት ፡ አለ ፤ ድል ፡ አደርጋለሁ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፤ ድል ፡ እሁናለሁ ፡ አይልም ።

ወወሂአሰ ፡ እምኔሃ ፡ ይከውን ፡ ምስለ ፡ ምትረተ ፡ ተስፋ ።

ከበዓት ፡ መውጣት ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ከመቍረጥ ፡ ጋራ ፡ ይሆናል ፡ አለ ፤ ድል ፡ አሆናለሁ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፤ ድል ፡ አደርጋለሁ ፡ አይልም ።

ወአምጣነ ፡ ሀሎ ፡ ዘልፈ ፡ ውስተ ፡ በዓቱ ።

በበዓቱ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረ ፡ ያህል ።

ይመውኢ ፡ ውእቱ ፡ ለሰ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምሕግግት ፡ በጸጋ ፡ ረድኤቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ።

በክርስቶስ ፡ ቸርነት ፡ እያንዳንዱ ፡ ጸሩን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ይነሣል ።

ወለእመሰ ፡ ተህክየ ፡ ወወፅአ ፡ ይቤጥል ፡ እምነ ፡ ምግባር ።

በጎቱን ፡ ጥሎ ፡ ቢወጣ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ይፈርስበታል ።

ተስእሎ ፡ ፶፫ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ አባ ፡ ታድራ ፡ ወአባ ፡ ሉቃ ፡ አዝለፉ ፡ ጎምሳ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይደፍዑ ፡ ሕሊናቲሆሙ ።

አባ ፡ ታድራና ፡ አባ ፡ ሉቃ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ምሉ ፡ ኅሊናቸውን ፡ ሲጨቁኑ ፤ ሲያመላልሱ ፡ ኖሩ ።

እስመ ፡ ኮኑ ፡ ይፈቅዱ ፡ ፈቢሰ ፡ እመክኖሙ ።

በዓታቸውን ፡ ጥሎ ፡ መውጣት ፡ ይወዱ ፡ ነበርና ፤ ወይው ፡ አይደለም ፤ መስለው ፡ ስለ ፡ ታዩ ፡ ነው ።

ወኮኑ ፡ ይዛቡ ፡ እስክ ፡ ክረምት ፡ ነሐውር ።

በጋ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ ክረምት ፡ ኑረን ፡ በክረምት ፡ እንሄዳለን ፡ እንጂ ፤ ዛሬማ ፡ ላዩ ፡ እሳት ፤ ታቹ ፡ እሳት ፡ በበጋ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንሄዳለን ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ዖበኒ ፡ ይበጽሕ ፡ ክረምት ፡ ይብሉ ፤ እስክ ፡ ሐጋይ ፡ ነሐውር ።

ክረምት ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ክርመን ፡ በበጋ ፡ እንሄዳለን ፡ እንጂ ፤ ዛሬማ ፡ ላዩ ፡ ባሕር ፤ ታቹ ፡ ባሕር ፡ በክረምት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንሄዳለን ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ወንበሩ ፡ ክመዝ ፡ እስክነ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሕይወቶሙ ።

እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ኖሩ ፤ ይህ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ አሉ ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ ይትቃተልዎሙ ፡ ሰይጣናት ፡ ለአበው ፡ ብዙኃን ፡ በእንተ ፡ ወኒኦ ፡ እምጽሙና ፤ ወበእንተ ፡ አእምሮቶሙ ፡ ፍድድና ፡ ረባሑ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሰይጣናት ፡ አበውን ፡ በበዓት ፡ ቢጸኑ ፡ የሚያገኙትን ፡ ረብሕ ፡ ጥቅም ፡ ስላወቁ ፡ ከበዓታቸው ፡ ለማውጣት ፡ መላልሰው ፡ ይዋጓቸዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ።

ወመንፈቀ ፡ አበውሰ ፡ ይትዋነይዎሙ ፡ ለሕሊናተ ፡ ሰይጣናት ። እሉሌቶቹ ፡ አበው ፡ ክፉ ፡ ሕሊና ፡ የሚያሳስቧቸው ፡ ሰይጣናትን ፡ ይዘብቱባቸዋል ።

ከመ ፡ እሉ ፡ ክልኤቱ ፡ ቅዱሳን ። እንደ ፡ አባ ፡ ታድራ ፡ እንደ ፡ ሉቃ ፡ ያሉት ።

ወለብዙኃንሰ ፡ እምኔሆሙ ፡ ተሳለቅዎሙ ፡ ሰይጣናት ። ከነዚህም ፡ ወገን ፡ ብዙዎቹን ፡ ሰይጣናት ፡ ዘበቱባቸው ። ።

እስከን ፡ ወዕኩ ፡ እምበዓታቲሆሙ ፡ ወእንጎገዉ ። ከበዓታቸው ፡ ወጥተው ፡ እስኪባክኑ ፡ ድረስ ።

በከመ ፡ ኮነ ፡ በመዋዕሊኑ ፡ ለአሐዱ ፡ ዘኮነ ፡ ፍሉመ ፡ በሥርዓት ፡ አምላካዊ ፤ ወተጸገወ ፡ ሀብተ ፡ ለአውዳኦት ፡ ሰይጣናት ። በዘመናችን ፡ ጋኔን ፡ የማውጣት ፡ ሀብት ፡ በተሰጠው ፡ በሥራ ፡ ፍጹም ፡ በነበረ ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ተደረገበት ።

እስመ ፡ ተጎየለ ፡ ጎዐሌሁ ፡ ጸብአ ፡ ፍልሰት ፡ እስክነ ፡ ኮነ ፡ ዘኢያስተርኢ ፡ ውስተ ፡ በዓቱ ፡ ፈድፋደ ፡ እምሰቡዕ ፡ መዋዕል ፡ እስክነ ፡ ሐነጹ ፡ ሎቱ ፡ አርድእቲሁ ፡ መክናተ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ። በበዓቱ ፡ ከሰባት ፡ ቀን ፡ አትርፎ ፡ የማይታይ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ አርድእቶቹ ፡ በየገዳሙ ፡ ቤት ፡ እስክ ፡ መሥራት ፡ ደርሰው ፡ ጸብአ ፡ ፍልሰት ፡ ሠልጥኖበት ፡ ነበርና ።

ወኮነ ፡ ይፈልስ ፡ እምበዓት ፡ ኀበ ፡ በዓት ። ካንዱ ፡ ዋሻ ፡ ወዳንዱ ፡ ዋሻ ፤ ካንዱ ፡ ገዳም ፡ ወዳንዱ ፡ ገዳም ፡ ይዞር ፡ ነበር ።

ወዐቀበቶ ፡ ጸጋ ፡ እምዐዊድ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ። ነገር ፡ ጣን ፡ ወዳገር ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ከመጣባት ፡ ጸጋ ፡ ጠበቀችው ።

ወዝ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ኢይዘንር ። እንዲህም ፡ መሆኑ ፡ እንዳይታበይ ፡ ነው ።

ወፍዳየ ፡ ዐሊያቱ ፡ ለትእዛዘ ፡ አረጋዊ ። የመምሩን ፡ ትእዛዝ ፡ የማፍረሱ ፡ ብድራት ፡ ሁኖ ፡ ተደረገበት ።

እስመ ፡ ይቤሎ ፡ መምህሩ ፤ ለእመ ፡ ኢትነብር ፡ ውስተ ፡ ቤክዝየ ፡ እምድኅረ ፡ ፍልሰትየ ፡ ትጌብል ፡ እንከ ፡ ኅፅሌክ ፡ ፍልሰት ፡ እስክ ፡ ጊዜ ፡ ፍልሰትክ ፡ ወንግደትክ ።

መምሩ ፡ እኔ ፡ ከሞትሁ ፡ በኋላ ፡ በበዓቴ ፡ ጸንተህ ፡ ክልኖርህ ፡ እስክትሞት ፡ ድረስ ፡ ጸብአ ፡ ፍልሰት ፡ ትሰለጥንብሃለች ፡ ብሎት ፡ ነበርና ።

ወከማሁ ፡ ኮነ ፤ ወኮነ ፡ ሎቱ ፡ ተስዓ ፡ ዓመት ። እንዲህ ፡ ሲያደርግ ፡ ዘጠና ፡ ዓመት ፡ ሁኖት ፡ ነበር ።

ወኮነ ፡ ይዜዐን ፡ አድገ ፡ ወያየውድዎ ፡ አርድእቲሁ ፡ በኀቱተ ። ባህያ ፡ ተጭኖ ፡ አርድእቶቹ ፡ ካንዱ ፡ ገዳም ፡ ወዳንዱ ፡ ገዳም ፡ ያዘሩት ፡ ነበር ።

እስክነ ፡ ኮኑ ፡ ያነክሩ ፡ እምኔሁ ፡ አበው ፡ ወይትጌመጹ ፡ አኃው ፡ ቦቱ ። ከእሱ ፡ የተነሣ ፡ አበው ፡ በእርግናም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጸር ፡ ይነሣልን ፡ ብለው ፤ አኃውም ፡ ያበትን ፡ ትእዛዝ ፡ ቢያፈርሱ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጸር ፡ ይነሣልን ፡ ብለው ፡ እስኪያነክሩ ፡ ድረስ ።

ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ አባ ፡ መቃርስኒ ፡ ዘየዐቢ ፡ ዕበ ፡ ኀለየ ፡ ከመ ፡ ይር አይ ፡ ገዳማውያን ። (ተስፎዮ) ። ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ አባ ፡ መቃርስም ፡ ገዳማውያንን ፡ ይገናኝ ፡ ዘንድ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ።

ፈርሀ ፡ እምተቃትሎተ ፡ ፍልሰት ። ጸብአ ፡ ፍልሰት ፡ እንዳይሠለጥንበት ፡ ፈራና ።

ወተጋደለ ፡ እንከ ፡ ኅሊናቲሁ ፡ ሐምስተ ፡ ዓመታተ ። አምስት ፡ ዓመት ፡ ምሉ ፡ ኅሊናውን ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ሲጨቀጭን ፡ ኖረ ።

ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ይጸሊ ፡ ወየኀሥሥ ፡ እምእግዚአብሔር ፤ ቦኑ ፡ ውእቱ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ አው ፡ እምሰይጣን ። ይኸውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሰይጣንም ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግለጽልኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ እያመለከተ ፡ ነው ።

ወእምድኅረዝ ፡ ሖረ ፡ ኀቤሆሙ ። ኋላ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቆ ፡ ሄደ ።

ተስእሎ ፡ ፱፯ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ እንጦንዮስ ። እንጦንዮስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

እስመ ፡ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወይጸሙ ። በገዳም ፡ የሚኖር ፡ በትሩፋት ፡ የሚደክም ፡ ሰው ።

ይድኅን ፡ እምሠለስቱ ፡ አጽባኣ ። ከሦስት ፡ ጸር ፡ ይድናል ።

እምኔሃ ፡ ነገር ፡ ወርእይ ፡ ወሰሚዕ ። አንዱ ፡ ጨዋታ ፤ ሁለተኛው ፡ ማየት ፤ ሦስተኛው ፡ መስማት ፡ ነው ።

ወተርፈ ፡ ሎቱ ፡ ጸብአ ፡ ልብ ።

ጸብአ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ ቀረለት ። ተርፈ ፡ ያለው ፤ ጸብአ ፡ ልብ ፡ ያለው ፡ ምንድር ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ በክመ ፡ እንክ ፡ ውዑኣውያን ፡ እምጽሙና ፡ ዖበ ፡ ተወሰኩ ፡ ዲበ ፡ ቀትሳተ ፡ ሕዋሳት ፡ ቀትሳተ ፡ ልብ ፡ ይወድቁ ።

ከተባሕትዎ ፡ አፍአ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ በአፍአ ፡ ጸር ፡ ላይ ፡ የውሥጥ ፡ ጸር ፡ በተጨመረ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰነ ካከሉ ።

ከማሁ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ እምክመ ፡ ተወሰኩ ፡ ላዕለ ፡ ቀትሳተ ፡ ልብ ፡ ቀትሳተ ፡ ሕዋሳት ፡ እምወድቁ ።

በተባሕትዎ ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡ በውሥጥ ፡ ጸር ፡ ላይ ፡ የአፍአ ፡ ጸር ፡ ቢጨመርባቸው ፡ ይሰነካከላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በክመ ፡ አኃው ፡ እለ ፡ ቦኑ ፡ ኀቤሆሙ ፡ አንስት ፡ ዖበ ፡ ተወሰኩ ፡ ዲበ ፡ ቀትሳተ ፡ ልብ ፡ ሬእየ ፡ ዐይን ፡ ለመልክዐ ፡ ገጽ ፡ ተመውኡ ። አንስት ፡ ሊጠይቋቸው ፡ የመጡ ፡ አኃው ፡ በውሥጥ ፡ ጸር ፡ ላይ ፡ የአፍአ ፡ ጸር ፡ የሚሆን ፡ መልክዐ ፡ አንስትን ፡ ማየት ፡ ቢጨመርባቸው ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ተነሡ ። እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ዘግተው ፡ በተባሕትዎ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። ሳይለያዩ ፡ ባንድ ፡ እየ ፡ ሆኑ ፡ የሚጠይቋቸው ፡ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ አሉ ። ከዕለታት ፡ በንድ ፡ ዕለት ፡ ሳይጠይቋቸው ፡ ጊዜው ፡ መሸ ። ዛሬስ ፡ ሳንጠይቃቸው ፡ መሸብን ፤ ወይም ፡ እንጂ ፡ በረከት ፡ የምናገኝበት ፡ ቀን ፡ ይሆናል ፤ አንቺም ፡ ከአባ ፡ እገሌ ፤ እኔም ፡ ከአባ ፡ እገሌ ፡ ሂደን ፡ በረከት ፡ ተቀብለን ፡ እንምጣ ፡ ብለው ፡ ሄዱ ። ሁሉም ፡ ተሰነካክለዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ወተቃትሎ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ የዐፅብ ። በተባሕትዎ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ የሰይጣን ፡ ጸር ፡ ጭንቅ ፡ ይሆንባቸዋል ። አንድም ፤ የዐቅብ ፤ ሰይጣን ፡ ጸሩን ፡ ያበጋጅባቸዋል ።

በክመ ፡ ይቤ ፡ ወቅሪስ ። ወቅሪስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ።

እስመ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ ብሕትውና ፡ ይትቃተልዎሙ ፡ ሰይጣናት ፡ በርእሶሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በማእከል ። ከሰው ፡ ተለይተው ፤ በበዓት ፡ ተከተው ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰይጣናት ፡ አኃውን ፡ ጋሻ ፤ መከታ ፤ መረገላ ፡ ሳያደርጉ ፡ ራሳቸው ፡ ተገልጸው ፡ ይዋጓቸዋል ።

ወለእለሰ ፡ ውስተ ፡ ማኅበር ፡ ወይፈቅዱ ፡ ይፈጽሙ ፡ ሥርዓተ ፡ ትሩፋት ፡ ይትቃተልዎሙ ፡ ምስለ ፡ ተደምሮ ፡ አኃው ፡ ልሕሱሓን ። በማኅበር ፡ ሁነው ፡ ፍጹም ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ የሚወዱትን ፡ ግን ፡ ድኩማን ፡ አኃውን ፡ ጋሻ ፤ መከታ ፤ መረገላ ፡ አድርገው ፡ ይዋጓቸዋል ።

ወብዙኃን ፡ ቀትሳት ፡ በትፍገዕታተ ፡ ሕዋሳት ፡ ዘበጎቡእ ። በሕዋሳተ ፡ አፍአ ፡ የሚጨመር ፡ ብዙ ፡ የውስጥ ፡ ጸር ፡ አለ ።

ወማእከለ ፡ ተቃትሎታት ፡ ይደመር ፡ ክልእኒ ፡ ውስተ ፡ ሕዋስ ፡ ግሁድ ። በሕዋሳተ ፡ ውስጥም ፡ የሚጨመር ፡ ብዙ ፡ የአፍአ ፡ ጸር ፡ አለ ።

ተስእሎ ፡ ፱፰ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ሚ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለቃለ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፤ እስመ ፡ በዓቱ ፡ ለመነኩስ ፡ ከመ ፡ እቶን ፡ ባቢሎን ፡ ዘሠለስቱ ፡ ደቂቅ ።

የመነኰሴ ፡ በዓቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ እንደ ፡ ወረዱበት ፡ እንደ ፡ እቶን ፡ ባቢሎን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንጦንዮስ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ትርጓሜው ፡ ምንድር ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ በክመ ፡ ለእሳት ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሃ ፡ ላቲ ፡ ክልኤቲ ፡ ግብር ።

ለእሳት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሚሆን ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ እንዳላት ።

አሐቲ ፡ ኃይል ፡ መውዕዪት ፤ ወካዕቢት ፡ ብርሃን ። አንዱ ፡ መተኰስ ፤ ሁለተኛው ፡ ማብራት ፡ ነው ።

ከመዝ ፡ ለእዝልፎተ ፡ በዓትኒ ፡ ላቲ ፡ ክልኤ ፡ ግብር ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሃ ። በበዓት ፡ ጸንቶ ፡ ለመኖርም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሚሆን ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ አላት ።

ቀዳሚት ፡ ዋዕየ ፡ ጸብአ ፡ ተቃትሎተ ፡ ሰይጣናት ፡ በውጣኔ ፡ በብዝኀ ፡ ሀኬት ፡ ወውልዋሌ ፡ ወአፍርሆ ። አንዲቱ ፡ በወጣኒነት ፡ ሀኬት ፡ በማብዛት ፤ በማጠራጠር ፤ በማስፈራራት ፡ የሚሆን ፡ የሰይጣንን ፡ ጸር ፡ ጸንቶ ፡ መዋጋት ፡ ነው ።

ወካዕቢት ፡ ላሕት ፡ ወፍጹም ። ሁለተኛዪቱም ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ማረፍ ፡ ፍጹምነት ።

ወብርሃን ፡ ልብ ፡ ምስለ ፡ ነጺሕ ፡ እምሕግማት ፡ ዘቦቱ ፡ ይበጽሕ ፡ ኀበ ፡ ራእያተ ፡ ብርሃን ። ከኃጣውእ ፡ ከመንጻት ፡ ጋራ ፡ ብርሃንን ፡ ወደ ፡ ማየት ፡ የሚደርስበት ፡ ለልቡና ፡ የሚሰጥ ፡ ብርሃን ፡ ነው ።

ወበከመ ፡ ፈነወ ፡ ለመለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ መልአከ ፡ ጠል ። ጌታ ፡ መልአክ ፡ ጠል ፡ እንዳዘዘላቸው ።

ወፈትሐ ፡ ማእዶሆሙ ፡ እምእቶን ፡ እሳት ።

www.ethiopianorthodox.org

ማሰሪያቸውን ፡ እንደ ፡ ፈታላቸው ፤ የፈታውስ ፡ እሳቱ ፡ ነው ፤ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ዖበ ፡ ተዐገሡ ፡ ክመ ፡ ይትአሰሩ ።

ወደው ፡ በታሰሩ ፡ ጊዜ ።

ወይትወደዩ ፡ ውስተ ፡ እቶን ።

ከእቶን ፡ እሳቱ ፡ በተጣሉ ፡ ጊዜ ።

ወተቃወምዎ ፡ ለንጉሥ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ። (ዳን፪ ፡ ፭-፰፯) ።

አምላክከሂ ፡ ኢናመልክ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሡን ፡ በተቃወሙት ፡ ጊዜ ፡ እንዳዘዘላቸው ።

ከማሁ ፡ ለእንሂ ፡ ወጣኒ ፡ ይፈኑ ፡ ነቢሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድኤት ።

ለወጣኂውም ፡ መነሱሴ ፡ ረድኤት ፡ ያገለለታል ።

ለእመ ፡ ተዐገሠ ፡ በእንተ ፡ ተቃትሎ ፡ ብሕትውና ፡ ወተቃትሎተ ፡ ሰይጣናት ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ።

በተባሕትዎ ፡ ሁኖ ፡ ጸሩን ፡ ለመዋጋት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ሰይጣናትን ፡ ለመቃወም ፡ ቢጸና ።

ወይፌበዮ ፡ ድልወ ፡ ለብዕለ ፡ ፍቅሩ ፡ ፍጽምት ፡ ወርእየ ፡ ብርሃኑ ፡ በቡሕ ።

ለፍጹም ፡ ፍቅሩ ፡ ክቡር ፡ ብርሃኑን ፡ ለማየት ፡ የበቃ ፡ ያደርገዋል ።

«ቅኔ ፤ አሐዱ ፡ እኁ ፡ ተናገሮ ፡ ለአድልፍዩስ ፡ ቃለ ፡ ጽርፈት ፡ ወኢያውሥአ ፤ ወሰበ ፡ ፈጸመ ፡ ይቤሎ ፡ ሞገሰ ፡ ቃል ፡ ይትከዐው ፡ እምከናፍረከ ። ወይቤሎ ፡ ካልእ ፡ ዓለማዊ ፤ አመነኰሳት ፡ ምንትኑ ፡ ያጸንዐከሙ ፡ ለዘከመዝ ፡ ጸዕቀ ፡ መከራት» ።

(፳) ይቤ ፡ አረጋዊ ፤ ኢንፈኢኑ ፡ ኀበ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘኮነ ፡ ለነ ፡ ጥንተ ፡ ለትዕግሥት ።

ለትዕግሥት ፡ በነሮ ፡ የሆነልን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አብነት ፡ አናደርግምን ። አንድም ፡ አከኑ ፡ ንፈኢ ፤ እናደርግ ፡ የለምን ። አንድም ፡ ንፈኢ ፡ አብነት ፡ እናደርጋለን ።

ወለእመ ፡ ኀሕነ ፡ ሐመምነ ፡ ከማሁ ፡ ኀሴባሕ ፡ ኀሕነኒ ፡ ምስሉሁ ።

እኛ ፡ እሱን ፡ መስለን ፡ መከራ ፡ ብንቀበል ፡ ከእሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ እንከብራለን ።

ወለእመ ፡ ተዐገሥነ ፡ ከማሁ ፡ ኀሕነኒ ፡ ንንግሥ ፡ ምስሉሁ ።

እሱን ፡ መስለን ፡ ስድቡን ፡ ብንታገሥ ፡ ከእሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ እንሠለጥናለን ።

በክመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ።

ለእመ ፡ ዐረይኑ ፡ ሕማመ ፡ ንዜሪ ፡ ክብረ ፡ ምስሉሁ ፡ እንዳለ ። (ሮሜ፰፡ ፲፯ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፩ናኒ፪) ።

ኀሙ ፡ በጸሎት ፡ ሥርየተ ፡ ለእለ ፡ ያጠውቁክሙ ። (ሮሜ፲፪ ፡ ፲፬-፳) ።

ሥቃይ ፡ ለሚያጸኑባችሁ ፡ ሰዎች ፡ ሥርየት ፡ ለምኑላቸው ።

በክመ ፡ ገብረ ፡ እግዚእነ ። (ማቴ፭፪ ፡ ፭ ፡ ፭፫ ፡ ፭፬) ።

ጌታ ፡ አባ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ እንዳለ ።

ወበክመ ፡ ገብረ ፡ እስጢፋኖስ ። (ግብሄ ፡ ፯፱) ።

እስጢፋኖስ ፡ ሥረይ ፡ ወኢትረሲ ፡ ሎሙ ፡ ጌጋየ ፡ እንዳለ ።

ወለእመ ፡ ኀሰየ ፡ ብሑት ፡ ውስተ ፡ ዝ ፡ ግብራት ።

መነሱሴ ፡ የጌታን ፡ የእስጢፋኖስን ፡ ነገር ፡ ቢያስብ ፡ ትዕግሥትን ፡ ቢወድ ።

ውእቱኒ ፡ ይመውኒ ፡ ሕማማተ ።

ጦሩን ፡ ድል ፡ ይነሣል ።

ወእኮመ ፡ ከመ ፡ ኢይፍዲ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ እኪተ ፡ ሀየንተ ፡ እኪት ።

እንደ ፡ በደሉኝ ፡ ልበድል ፡ አለማለት ፡ ብቻ ።

ወኢይትቀየም ።

አለመቀየም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

አላ ፡ ይደልዎሂ ፡ ከመ ፡ ይትፈሣሕ ፡ ዖበ ፡ ዘርክቦ ፡ ብእሲ ።

በሰደበት ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ሊለው ።

ወይጸሊ ፡ በእንቲኣሁ ።

ለሰደበውም ፡ ሰው ፡ ሥርየት ፡ ሊለምንለት ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ።

ተስእሎ ፡ ፶፱ ።

ይቤሱ ፡ አኃው ፤ እፈሙ ፡ ዖበ ፡ ዘርክይዎ ፡ አኃው ፡ ለአባ ፡ ሙሴ ፡ ተብህለ ፡ ሎቱ ፡ ኢተሀክክኑ ፡ ልብክ ።

አባ ፡ ሙሴን ፡ አንተ ፡ ሽንቅላ ፡ ብለው ፡ በሰደቡት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አለ ፤ አሁን ፡ ዝም ፡ ማለትህ ፡ ልቡናህ ፡ አላዘነምን ፡ አሉት ።

ወይቤ ፡ ተሀክነ ፤ ወባሕቱ ፡ ኢተናገርኩ ።

ማዘኑንስ ፡ አዘንሁ ፡ አልተናገርሁም ፡ እንጂ ፡ አለ ።

እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ አበ ፡ ምኔቱ ፡ ገብተህ ፡ ቀድስ ፡ ብሎ ፡ ላካበት ። እሺ ፡ ብሎ ፡ ሊቀድስ ፡ ልብሰ ፡ ቆክኖውን ፡ ለብሶ ፡ መጻፉን ፡ ይዳሞ ፡ ሲጨርስ ፡ ከምን ፡ ደረሰ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ይሽው ፡ ሊገባ ፡ ነው ፤ ይዳሞ ፡ ጨርሷል ፡ አለ ። ሂድና ፡ አንት ፡ ሽንቅላ ፡ ይዳሞ ፡ አንተን ፡ ከሥጋው ፡ ከደሙ ፡ ማን ፡ አቅርቦህ ፡ ብለህ ፡ በጥፊ ፡ መትተህ ፡ አስወጣው ፡ አለው ።

እንዳዘዘው ፡ አድርጎ ፡ አስወጣው ። ምን ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ዝም ፡ አለ ፡ አለው ። በል ፡ ግባና ፡ ቀድስ ፡ በለው ፡ ብሎታል ። ሂዶ ፡ ቢነግረው ፡ ገብቶ ፡ ቀድሷልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ በክመ ፡ ለብሕትውና ፡ ቦ ፡ ክልኤ ፡ ፍና ።

ለተባሕትዎ ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ እንዳለው ፡ መጠን ።

ክመ ፡ ኢይትወክ ፡ ሕዋስ ፡ ሥጋ ፡ ወኢ ፡ ሕዋስ ፡ ነፍስ ።

ሕዋሳተ ፡ አፍኣ ፡ ሕዋሳተ ፡ ውስጥ ፡ እንዳያዝን ፡ መሆን ፡ ነው ። አንድም ፡ ከመን ፡ ሳትሻ ፤ ሕዋሳተ ፡ ሥጋ ፡ ሕዋሳተ ፡ ነፍስ ፡ እንዳያዝን ፡ መጠን ፡ ለተባሕትዎ ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ አለው ።

ቀዳሚስ ፡ ዘከመ ፡ ኢይትቄጣዕ ፡ በኀሊና ፡ ወኢይፍጻ ፡ በልሳን ።

አንዱ ፡ በኀሊናው ፡ እንዳያዝን ፤ ባንደበቱ ፡ እንዳይናገር ፡ መሆን ፡ ነው ።

በክመ ፡ ገብረ ፡ አባ ፡ ሙሴ ።

አባ ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፤ ተሀከኩ ፡ በሕቱ ፡ ኢተናገርኩ ፡ እንዳለ ።

ወክዕባይ ፡ ዘፍጹም ።

ሁለተኛው ፡ የፍጹም ፡ ነው ።

ውእቱኒ ፡ ክመ ፡ ኢይትቄጣዕ ፡ በልቡ ፡ ወኢይፍጻ ፡ በልሳን ።

ይሽውም ፡ በልቡናው ፡ እንዳያዝን ፡ መሆን ፡ ነው ፤ ባንደበቱም ፡ እንዳይናገር ፡ መሆን ፡ ነው ። አንድም ፡ ባንደበቱ ፡ እንዳይናገር ፡ መጠን ፤ በልቡናው ፡ እንዳያዝን ፡ መሆን ፡ ነው ።

በክመ ፡ ኮነ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዊር ፡ ወዘአምሳሊሁ ።

ዮሐንስ ፡ ሐዊር ፤ እሱን ፡ የመሰለም ፡ ሌላው ፡ እንዳደረገው ።

እስመ ፡ ዘርክቦ ፡ አሐዱ ፡ ወዘንጉላ ፡ ወውእቱ ፡ ነቢሮ ፡ ማእከለ ፡ አኃው ።

ይሽውም ፡ ከአኃው ፡ መካከል ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ነው ። ከማኅበር ፡ አንዱ ፡ በሰደበው ፡ ጊዜ ፤ አንት ፡ ድንክ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ።

ኢደመነ ፡ ገጹ ።

አላዘነምና ።

ወይቤልዎ ፡ ኢተምዐኑ ፡ ልብክ ፡ ዖበ ፡ ጸዐለክ ።

በሰደበህ ፡ ጊዜ ፡ ልቡናህ ፡ አላዘነምን ፡ አሉት ።

ወይቤሎሙ ፡ በክመ ፡ ርኢክሙኒ ፡ ጎዳአ ፡ እምአፍኣ ፡ ከማሁ ፡ እም ውሥጥኒ ።

በአፍኣ ፡ ጸጥ ፡ ብዬ ፡ እንዳያችሁኝ ፡ በውሥጥም ፡ ያው ፡ ነኝ ፡ አላቸው ።

ዝኩ ፡ ውእቱ ፡ ተዐድዎታ ፡ ለሕግግት ።

ጸሩን ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ወአባ ፡ ሙሴ ፡ ተአመነ ፡ ክመ ፡ ኢበጽሐ ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ።

አባ ፡ ሙሴ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ፍጹምነት ፡ እንዳልደረሰ ፡ ተናገረ ።

ወባሕቱ ፡ አኀዘ ፡ ኀሊናቲሁ ፡ ወአርመመ ።

ሕዋሳቱን ፡ ከመናገር ፡ ወስኖ ፡ ገቶ ፡ ያዘ ፤ ከመናገር ፡ ተከለከለ ፡ እንጂ ።

ወእርአየ ፡ ዝክተ ፡ በእንተ ፡ ፍና ፡ ትሕትና ።

ትሑት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ተሀከኩ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢተናገርኩ ፡ አለ ።

ሙሴስ ፡ ነቢይ ፡ ዖበ ፡ ተዘርክየ ፡ ውእቱ ፡ እምእኁቱ ።

ሙሴሰ ፡ ቢል ፡ ለሙሴ ፡ ጸሊም ፤ ሙሴኒ ፡ ቢል ፡ ለዮሐንስ ፡ ሐዊር ። ነቢዩ ፡ ሙሴ ፡ ጳን ፡ እኅቱ ፡ በማችው ፡ በነቀፈችው ፡ ጊዜ ።

ጎሠሠ ፡ ኅቴ ፡ ስርየተ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወፈወሳ ፡ እምተግሣጾ ። (ዘኍ፲፪ ፡ ፩—፲፫) ።

ከእግዚአብሔር ፡ ስርየት ፡ ለምኖ ፡ ከተፈረደበት ፡ ደዌ ፡ አዳናት ። እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ማርያም ፤ እኅተ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ካንድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ሙሴን ፡ ከደብተራ ፡ አረት ፡ ሲገባ ፡ አይተው ፡ እኛን ፡ ከሚስቶቻቸው ፡ አድራችሁ ፡ አትግቡ ፡ ይላል ፤ እሱ ፡ ከሚስቱ ፡ እያደረ ፡ ይገባል ። ሌላውን ፡ ከአሕዛብ ፡ አትጋቡ ፡ ብሎ ፡ ይላል ፤ እሱ ፡ ከአሕዛብ ፡ ተጋብቷል ፡ ብለው ፡ አሙት ። እሺ ፡ እሱሴታ ፡ አኀኗን ፡ ወንድሟን ፡ አምታለችና ፡ እሱሴታ ፡ ሰው ፡ ነች ፡ ለምጽ ፡ ሆነ ። እሱ ፡ ግን ፡ ሊቀ ፡ ክህናት ፡ ነውና ፡ አልገለጸበትም ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሂዳ ፡ እንዲህ ፡ እንጂ ፡ ሆንሁ ፡ አለችው ። ምነው ፡ አላት ፤ አንተን ፡ አምቼ ፡ አለችው ። ጕዞ ፡ የነበረ ፡ ውሎ ፡ አድርጎ ፡ ለምኖ ፡ አድኑዋታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ተስእሎ ፡ ፷ ።

ይቤሱ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ አበው ፡ ይኤዝዙ ፡ ዖእንተ ፡ ትምህርት ፡ እምአዕፋግ ።

አበው ፡ ከአዕፋግ ፡ ተማሩ ፡ ብለው ፡ ያዘሉ ።

ዘእንበለ ፡ ዘይቤ ፡ ለአሐዱ ፡ እምነ ፡ አኃው ፡ ሑር ፡ ወንበር ፡ ውስተ ፡ በዓትክ ፡ ወይእቲ ፡ ትጌህረክ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከአኃው ፡ አንዱን ፡ ከሰው ፡ ተለይተህ ፡ በበዓት ፡ ተ
ከተህ ፡ ኑር ፤ ሁሉንም ፡ በዓትህ ፡ ታስተምርሃለች ፡
ከለው ፡ ሰው ፡ በቀር ፤ ይህ ፡ አይለያይምን ፡ ብለው ፡
ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እስመ ፡ እሙንቱስ ፡ ኢተፃረሩ ።

እነሱስ ፡ አይለያዩም ።

እስመ ፡ አባ ፡ መቃራኒ ፡ ወቢይ ፡ ይቤ ፤ በጊዜ ፡ በእትክ ፡ ኀበ ፡ በኣትክ ፡
ኀበር ፡ በከመ ፡ ኮንክ ፡ ትገብር ፡ ውስተ ፡ ሥርዓት ፡ ማኅበር ፡ አዝማ
ን ፡ ዕውቀ ።

አባ ፡ መቃራ ፡ ወደ ፡ በኣትህ ፡ በገባህ ፡ ጊዜ ፡ የታወ
ቀውን ፡ ዘመን ፡ ያህል ፡ በማኅበር ፡ ትሠራው ፡ እን
ደ ፡ ነበር ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ሥራ ።

ውስተ ፡ ጸሎት ፡ ወጸም ፡ ወአንብዖ ።

ጸምን ፡ ጸሎትን ፡ መጽሐፍ ፡ መመልከትን ።

ካልእኒ ፡ እምውእቱ ።

ከዚህ ፡ ሌላም ፡ ሰጊድን ፡ ቁመትን ።

ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ትውብ ፡ ለክ ፡ ሥርዓተ ፡ ዘይሰነዐው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚሰማማ ፡ ሥራን ፡ ታስተምርሃለ
ች ።

ዘከማሃ ።

ዘከማሁም ፡ ይላል ፤ እንደ ፡ ቀደመው ፡ ያለ ። ዘከማ
ከ ፡ ቢል ፡ ቀድሞ ፡ ትሠራው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያለ ።

እምተውላክ ፡ ወሕጸጽ ።

ከመጨመር ፡ ከማሳነስ ፡ ወገን ፡ ትገልጽልሃለች ።

ዘውእቱ ፡ በእምጣን ፡ ዘያስተርኢ ፡ ሎሙ ፡ እምኔሁ ፡ ውስተ ፡ ጽሙ
ና ፡ በኅት ።

ይኸውም ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ በበዓት ፡ ተከተው ፡
የተገለጸላቸውን ፡ ያህል ፡ ነው ። አንድም ፡ እንደ ፡ ተ
ገለጸላቸው ፡ መጠን ።

ይሠርዕዎ ፡ ከማሁ ፡ እምወስኑ ፡ ዲበ ፡ ዝኮን ፡ ይገብሮ ፡ ውስተ ፡ ማኅ
በር ፡ አው ፡ ያሕጽጽ ፡ እምኔሁ ።

በማኅበር ፡ ይሠራው ፡ በነበረ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከመጨ
መር ፡ ከማሳነስ ፡ ወገን ፡ ይጨምር ፡ ያሳንስ ፡ ዘንድ ፡
ያዙታል ። ሐተታ ፤ እንግዲህ ፡ ረድቶ ፡ ተባሕትዎ ፡
ሲይዝ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጹም ፡ ጸልይ ፡ ይሉታል ፤ ሁ
ለት ፡ ሶስት ፡ ሱባዔ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ሂደው ፡ እንደ
ምን ፡ ሆንህ ፡ ተስማማህን ፡ አልተስማማህም ፡ ብለ
ው ፡ ይጠይቁታል ፤ ተስማምቶኛል ፡ ቢል ፡ ይጨምሩ
ለታል ፤ አልተስማማኝም ፡ ቢል ፡ ይከፍሉለታልና ፡ እ
ንዲህ ፡ አለ ።

ወዝኬ ፡ ውእቱ ፡ ፈቂደ ፡ ታሉ ፡ ኀበር ፡ ውስተ ፡ በዓትክ ፡ ወይእቲ ፡ ት
ሜህረክ ፡ ኮሎ ።

ትሜህረክ ፡ ያለው ፡ ትርጓሜ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፶፩ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ አባ ፡ አጋቶን ፡ ወደየ ፡ ውስተ ፡ አፋው ፡ ኖ
ኅ ፡ እብን ፡ ኑኃ ፡ ፴ ፡ ዓመታት ፡ ክመ ፡ ኢይትናገር ።

አባ ፡ አጋቶን ፡ በንደበቱ ፡ እንዳይናገር ፡ ሠላሳ ፡ ዓ
መት ፡ ሙሉ ፡ ጠጠር ፡ ጕርሶ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ጊዜ
ን ፡ አለው ፡ ሁለጊዜ ፡ ነውን ፤ ትሩፋቱስ ፡ ይህ ፡ ብ
ቻ ፡ ነውን ፡ ሌላም ፡ አለ ፤ እንዲህ ፡ ማድረጉስ ፡ ስለ
ምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ በኦሶ ፡ ጊዜ ፡ ዘኮነ ፡ ይወጽእ ፡ እምበኅቱ ፡ ኀበ ፡
ማኅበረ ፡ አኃው ።

ከበዓቱ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ማኅበር ፡ በሚኼድበት ፡
ጊዜ ።

ወይንብር ፡ ለሰሚዐ ፡ አንብዐ ።

የሚነበበውን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመስማት ፡ በሚቀመጥበ
ት ፡ ጊዜ ።

ኮነ ፡ ይወዲ ፡ ጭየ ፡ ኀበቲተ ፡ ውስተ ፡ አፋው ፡ ከመ ፡ ኢይደቅ ፡ በል
ሳኑ ፡ በአሐቲኒ ፡ ቃል ።

አንድ ፡ ነገር ፡ ተናግሮ ፡ በንደበቱ ፡ እንዳይሰነካከል ፡
ታናሽ ፡ ጠጠር ፡ አንሥቶ ፡ ይጕርስ ፡ ነበር ።

ወኮነት ፡ እንከ ፡ ሎቱ ፡ አሐቲኒ ፡ ተዝካር ።

ስሙን ፡ የምታስጠራው ፡ አንዲት ፡ ግብር ፡ ነበረች
ው ፤ ምክር ፡ አዋቂ ፡ ነበር ።

ወለእመ ፡ ረክበ ፡ እንከ ፡ በዘይትግር ፡ ነገረ ፡ በቍጐት ።

መንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ የሚመክረው ፡ ሰው ፡ ቢያገኝ ።

ይነሥኢ ፡ ኪያሃ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ።

ካፉ ፡ አውጥቶ ፡ በጁ ፡ ይይዛት ፡ ነበር ።

ወከማሁመ ፡ ሶበኒ ፡ ቆመ ፡ ምስለ ፡ አኃው ፡ ውስተ ፡ ጸሎት ።

ከአኃው ፡ ጋራ ፡ ለጸሎት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ።

ወሶበኒ ፡ ነበረ ፡ ኅዕለ ፡ ማዕድ ።

ከማዕድ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ።

ያወጽኣ ፡ እምአፋው ።

አውጥቶ ፡ ይይዛታል ።

ወሶበ ፡ ወዕአ ፡ እመብልዕ ፡ ያገብኣ ፡ ውስተ ፡ አፋው ።

ከማዕድ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ መልሶ ፡ ያገባታል ።

ወሶበ ፡ ርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተዐቅቦቶ ፡ ወሀበ ፡ መዊዐ ፡ ኅዕለ ፡ ልሳኑ ።

ጌታም ፡ ተዓቅቦውን ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ አንደበቱን ፡ እን
ዲያሸንፍ ፡ አደረገው ።

ወሶበ ፡ ስምው ፡ አበው ፡ ተመሰሉ ፡ ኪያሁ ።

አበውም ፡ ገድሉን ፡ ሰምተው ፡ መሰሉት ።

በ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘወደየ ፡ መስቀለ ፡ ኀኤሰ ፡ ውስተ ፡ አፋው ።

አጭር ፡ መስቀል ፡ ጕርሶ ፡ የኖረ ፡ አለ ።

ወበ ፡ ዘወደየ ፡ ኅልቀተ ።

ቀለበትም ፡ ጕርሶ ፡ የኖረ ፡ አለ ።

ወበ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይትሐሰባ ፡ ለንፍሱ ፡ በጊዜ ፡ በዊኦቱ ፡ ኀበ ፡ በኣ
ቱ ፡ በእንተ ፡ ድቁታተ ፡ ልሳኑ ።

ወደ ፡ በዓቱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ባንደበቱ ፡ የመሰነካከል
ን ፡ ነገር ፡ ሰውነቱን ፡ የሚቆጣጠራት ፡ አለ ፤ ማነን ፡ ተ
ናግሬ ፡ ይሆን ፤ ማነን ፡ አስቀይሜ ፡ ይሆን ፡ እያለ ።

ወያስተበቍዕ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲኣሃ ።

ስለሷ ፡ ተዓቅቦ ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ይለምናል ።

ወይገብእ ፡ እንከ ፡ ኀበ ፡ ተዓቅቦቱ ።

ወደ ፡ ተዓቅቦው ፡ ይመለሳል ።

ወእምድኅረዝ ፡ የዳርፍ ፡ እምተቃትሎታት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከያሩ ፡ ያርፋል ።

ወተዓቅቦት ።

ከተዓቅቦ ፡ በላይ ፡ ይሆናል ።

ወይሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግናል ።

ክፍል ፡ ሐምስ ።

በእንተ ፡ ምሳሌ ።

የኛን ፡ ጸም ፡ የሚመስል ፡ የጌታን ፡ ጸም ፡ ነገር ፡ የ
ሚናገር ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፶፪ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ በእንተ ፡ ምጣኑ ፡ የዐፅብ ፡ ላዕለ ፡ ክርስቲያን ።

በምእመናን ፡ ላይ ።

ወብሑታን ።

በባሕታውያን ።

ወክልኣሆሙ ።

በናዝራውያን ፤ እንድም ፡ በፍጹማን ፡ በወጣንያን ።

ተቃትሎተ ፡ ሰይጣናት ፡ በጸም ፡ ወቢይ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዘተርፉ ፡ መዋ
ዕላት ።

ከቀሩት ፡ አጽዋማት ፡ ይልቅ ፡ በዓቢይ ፡ ጸም ፡ የሰይ
ጣን ፡ ያር ፡ ጭንቅ ፡ የሚሆንብቸው ፡ ስለምን ፡ ነው ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ በእንተ ፡ ሠላስ ፡ ፍናዋት ።

ስለ ፡ ሶስት ፡ ነገር ፡ ነው ።

ቀዳሚ ።

መጀመሪያው ፡ እንዱ ።

እስመ ፡ በእምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ጸም ፡ ኮነ ፡ ተቃትሎተ ፡ ሰይጣን ፡ ምስለ ፡
መድኃኒነ ። (ማቴ፬ ፤ ፩-፲፩) ።

የኛን ፡ ጸም ፡ በሚመስል ፡ በጌታ ፡ ጸም ፡ ሰይጣን ፡
ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ነበርና ።

ወወሀበነ ፡ እግዚእነ ፡ ረባሐ ፡ መዊያቱ ፡ ሎቱ ።

ጌታም ፡ እሱን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ያመጣውን ፡ ክብር ፡
ሰጥቶናልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ካዕበኒ ፡ እስመ ፡ ዘውስቴታ ፡ ያጠብው ፡ ክርስቲያን ፡ ለተዐግሦ ፡ እም
ፍትወታት ፡ ወተቃትሎተ ፡ ሕማማት ።

ሁለተኛም ፡ ምዕመናን ፡ በዓቢይ ፡ ጸም ፡ ከፈቃደ ፡ ሥ
ጋ ፡ ከፈቲው ፡ ያር ፡ ለመጠበቅ ፡ ኃጣውእን ፡ አጋን
ንትን ፡ ለመዋጋት ፡ ይጸናሉና ።

በእንተ ፡ ዝኬ ፡ ያልሕሙ ፡ ሰይጣናት ፡ በእንተ ፡ ተቃትሎቶሙ ።

ስለዚህ ፡ ሰይጣናትም ፡ ያሩን ፡ ያጸኑብቸዋል ።

ሣልስኒ ፡ እስመ ፡ በጸም ፡ ዘበበ ፡ ኅሙት ፡ ይውጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸ
ጋ ፡ ረድኤት ፡ በእንተ ፡ ምግባር ፡ ዘየኀብር ፡ ለጸም ፡ እምነ ፡ ጽድቅ ።

ሶስተኛም ፡ ባመት ፡ በመት ፡ በሚሆን ፡ በጌታ ፡ ጸም ፡
ከትሩፋቱ ፡ ወገን ፡ ለጸም ፡ የሚስማማ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡
ሠሩ ፡ ጌታ ፡ ጸጋ ፡ ረድኤት ፡ ይሰጣልና ፡ ስለዚህ ።

ወበእምጣነ ፡ ረድኤትኪ ፡ ይትዌሰክ ፡ ተቃትሎቶሙኒ ።

ያሩ ፡ እየተጨመረ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ይጨመርላቸዋል ።

ወዛቲ ፡ ልማደሙ ።

ያር ፡ እየተጨመረ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ መጨመር ፡ ልማ
ድ ፡ ነው ።

«ቅኔ ፤ ይቤሎ ፡ አረጋዊ ፡ ለእኁ ፡ ኢትትህክይ ፡ ሶ
በ ፡ ተቃተለከ ፡ ሰይጣን ፡ በአዝልፎቱ ፡ ወዕዕበቱ ፡
ወጥውቀቱ ፡ ወተመውአቱ ፡ ወመዊአትኒ ፤ ወእምዝ ፡
ትመውእ ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር» ።

www.ethiopianorthodox.org

ተስእሎ ፡ ፲፫ ፡

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ አይኑ ፡ ውእቱ ፡ ፈሊጥ ፡ ማእክለ ፡ ተቃትሎት ፡ ወእዝልፎቱ ፡ ወዕዕበቱ ፡ ወጥውቀቱ ፡ ወተመውኦቱ ፡ ወመዊእትኒ ፡ ዘበእንቲኣሁ ፡

በተቃትሎትና ፡ በአዝልፎ ፤ በዕዕበትና ፡ በጥውቀት ፤ በተመውኦትና ፡ በመዊእት ፡ መከከል ፡ ያለው ፡ መ ለያየት ፡ ምንድር ፡ ነው ፡

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ተቃትሎትስ ፡ ውእቱኬ ፡

ተቃትሎ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ፡

ዕበ ፡ የሀውክ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ብሑት ፡ ተዘክሮ ፡ ዘኮነ ፡ እ ምሕማማት ፡

ሰይጣን ፡ በመነሥኡው ፡ ልቡና ፡ ከዓበይት ፡ ኃጣው እ ፡ ወገን ፡ የሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ ክፉ ፡ ሐሊና ፡ ቢያሳስብ ፡

ዘክመ ፡ ዝሙት ፡ ወመግት ፡ ወስብሓት ፡ ጽሩዕ ፡

ይኸውም ፡ እንደ ፡ ዝሙት ፡ እንደ ፡ ቍጣ ፤ እንደ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ቢያሳስበው ፡

ኢይኅድን ፡ እንክ ፡ ብሑት ፡ ይጕንዲ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡

በልቡናው ፡ ይውል ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ እንዳይተወው ፡ መሆን ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ባይተወው ፡ ተቃትሎ ፡ ያ ለው ፡ ይህ ፡ ነው ፡

አላ ፡ ይትመየዕ ፡ ኅዕሌሁ ፡ በእንቲኣሁ ፡

ስለ ፡ ታሰበው ፡ ራሱን ፡ ይገሥጻል ፡ እንጂ ፡

ወይስድዶ ፡ በሰኀቱ ፡ በጸሎት ፡

ፈጥኖ ፡ በጸሎት ፡ ያርቀዋል ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡ ይ ገሥጽ ፡ እንጂ ፤ ያርቅ ፡ እንጂ ፡

ወእመሰ ፡ ኀደጎ ፡ ይጕንዲ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡

በልቡናው ፡ ይውል ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ ቢተወው ፡ ግ ን ፡

ወኢይተመየዕ ፡ ኅዕሉ ፡ ርእሱ ፡ በእንቲኣሁ ፡

ስለ ፡ ታሰበው ፡ ራሱን ፡ ባያገሥጽ ፡

ወኢይሰድዶ ፡ በጸሎት ፡

ፈጥኖ ፡ በጸሎት ፡ ባያርቀው ፡

ወገዝኬ ፡ ውእቱ ፡ ልሕልሕና ፡

ይኸም ፡ ደክምነት ፡ ነው ፤ ትች ፡

ወአኮ ፡ ተቃትሎ ፡

ጸርነት ፡ አይባልም ፡

እስመ ፡ ለኣመ ፡ ጕንደየ ፡ ኅሊና ፡ ውስተ ፡ ልብ ፡

ተዘክሮ ፡ ፍጹም ፡ ጥበብ ፡ ነው ፤ ፍጹም ፡ ጥበብ ፡ ተዘክሮ ፡ ነው ፡ እንዳለ ።

ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢትምትር ፡ ዘክርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምሕሊናከ ።

ይኸውም ፡ ተዘክሮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከልቡናህ ፡ እንዳትለይ ፡ መሆን ፡ ነው ።

ወስለ ፡ ኑሱኒ ፡ ዘተመትረ ፡ ቍጽሮ ።

የተለየውን ፡ ሕሊናህን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አድርገው ።

ወባሕቱ ፡ ዘትከውን ፡ ሎቱ ፡ ዛቲ ፡ ትርፍት ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህች ፡ ፍጹምነት ፡ የምትሰጠው ።

እምድኅረ ፡ ተዐደወ ፡ ኑሱ ፡ አጽባእ፡ ወክልኣታት ።

ያሩን ፡ አሸክላውን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ከነሡ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

እንተ ፡ ትከውን ፡ እምሰይጣናት ።

ከሰይጣናት ፡ ወገን ።

ወእምን ፡ አኃው ፡ እኩያን ።

ከእኩያን ፡ አኃው ፡ ወገን ።

ወእምን ፡ ሕማማተ ፡ ልማድ ፡ ወፍጥረት ።

በልማድ ፡ በባሕርይ ፡ ከሚሠሩ ፡ ኀጣውኣ ፡ ወገን ፡ የሚመጣ ፡ አለ ።

እስመ ፡ ሰይጣናት ፡ ያኅርግዎሙ ፡ ለውሑናን ፡ ለኀበ ፡ ልዕልና ፡ ዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ።

ሰይጣናት ፡ ወጣንያንን ፡ ልዑል ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡ ተዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያወጧቸዋል ።

እምቅድመ ፡ ፍጹም ፡ ዘምግባራት ፡ ወገድላት ።

ትሩፋት ፡ ሠርተው ፡ መከራ ፡ ተቀብለው ፡ ፍጹማን ፡ ከመሆን ፡ አስቀድሞ ።

ወበደኃሪ ፡ ያንብርዎሙ ፡ ኀበ ፡ ማዕምቅተ ፡ ኀጕል ።

ኋላ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ያወርዷቸዋል ።

ዘውኅቱ ፡ ድቀተ ፡ ትዝኅርት ።

ይኸውም ፡ ትዕቢት ፡ ነው ።

ወይደሉ ፡ ለውሑናን ፡ ከመ ፡ ያብዝኑ ፡ አጸንግሎ ፡ ቅድመ ፡ ውስተ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚእን ።

ወጣንያንስ ፡ አስቀድሞ ፡ ጌታ ፡ ያዘዘዉን ፡ ነገር ፡ መ ዘከር ።

ወውስተ ፡ ትፍፋት ።

ትሩፋት ፡ መሥራት ፡ ይገበቸዋል ።

ወኢይኅድኑ ፡ ዘክሮ ፡ ኀጣውኢሆሙ ።

ኀጢአታቸውን ፡ መዘከር ፡ እንዳይተዉ ፡ መሆን ።

ወአእምሮ ፡ ሕማማቲሆሙ ።

ያሩን ፡ ማወቅ ፡ እንዳይተዉ ፡ መሆን ፡ ይገበቸዋል ።

ወያስተባጽሑ ፡ ልቡናቲሆሙ ፡ ምስለ ፡ ተዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርዓት ።

ልቡናቸውን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከተዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያድርጉ ።

ከመ ፡ ለእመ ፡ ኢይክሉ ፡ ያሕሥኡ ፡ አጽባእ ፡ ዕውኣተ ፡ እንተ ፡ ትፃረር ፡ ዘክሮተ ።

ተዘክሮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያፈርስ ፡ የሕሊናን ፡ ያር ፡ ጸጥ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ባይቻላቸው ።

ወበእንተ ፡ ዝንቱኬ ፡ አመረ ፡ አረጋዊ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አረጋዊ ፡ እምዝሰ ፡ የዐቢ ፡ ከመ ፡ ትርአይ ፡ ሕሊናከ ፡ መትሕተ ፡ እምኑሉ ፡ ፍጥረት ፡ ብሎ ፡ መከረው ።

ወናሁ ፡ ይቤ ፡ አረጋዊ ፡ ካልእኒ ።

ሌላውም ፡ አረጋዊ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ዐ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ ንፉኢ ፡ መላእክተ ።

እነሆ ፡ መላእክትን ፡ አየን ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ።

ብፁዕሰ ፡ ዘርእየ ፡ ኀጣውኢሁ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ኀጢአቱን ፡ የሚዘከር ፡ ሰው ፡ ይበልጣል ።

ወኢኮነ ፡ ካዕበ ፡ ርእየተ ፡ መላእክት ፡ ዘያንትግ ፡ ርእየተ ፡ ኀጣይእ ።

ኀጢአቱንም ፡ መዘከር ፡ መላእክትን ፡ ማየት ፡ የሚከለክል ፡ አይደለም ።

ወባሕቱ ፡ አዘዘ ፡ ይትዐቀቡ ፡ ካዕበ ፡ እምስፍጠተ ፡ ሰይጣናት ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከሰይጣናት ፡ ሽንገላ ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

እስመ ፡ ይትሜሰሉ ፡ መላእክተ ፡ ክመ ፡ ያስሕትዎሙ ፡ ለወጣንያን ።

ወጣንያንን ፡ ያስታቸው ፡ ዘንድ ፡ መላእክትን ፡ መስለው ፡ ይታያሉና ። (፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬) ።

(፲፯) ወይቤ ፡ አረጋይ ፤ እስመ ፡ እኁ ፡ ኮነ ፡ መስተጋድለ ፡ በእንተ ፡ ፈጽሞ ፡ ቀኖናው ።

አንድ ፡ መነሥሴ ፡ የተወሰነለትን ፡ የምንዅስና ፡ ሥርዓት ፡ ለመፈጸም ።

ውስተ ፡ ገቢር ።

ትሩፋት ፡ በመሥራት ።

ወጸሎት ።

በጸም ፡ በጸሎት ።

ወሐዘን ፡ ወሐሚም ።

በሐዘን ፡ በልቅሶ ፡ የሚጋደል ፡ ነበረ ።

ወበእንተ ፡ ትሕትናሁ ፡ ኢፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይትቀበል ፡ ኑዛዜ ።

ትሑት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በሥራው ፡ ጸጋ ፡ ላግኝ ፡ አላለም ። አንድም ፤ በእንተ ፡ ልቡናሁ ፤ ልቡናው ፡ ትሑት ፡ ስለ ፡ ሆነ ። አንድም ፤ ዘለልቡ ፤ ለልቡናው ፡ ትሕትና ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ ጸጋ ፡ ላግኝ ፡ አላለም ።

አላ ፡ ኮነ ፡ ይጸንሕ ፡ ጸጋ ፡ ሥርዓተ ፡ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ። አንድም ፡ በትሕትና ፤ አንድም ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ በሰራው ፡ ሥራ ። አንድም ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ መከራ ፡ ተቀብሎ ፡ ያመጣውን ፡ ጸጋ ፡ አገኛለሁ ፡ ይል ፡ ነበር ።

ወሶበ ፡ ክሠተ ፡ ዘንተ ፡ ለአረጋዊ ።

ለአረጋዊ ፡ ይህን ፡ ቢነግረው ።

ይቤሎ ፤ በእንተ ፡ ኩነትክ ፡ ዘኢትቀበልክ ፡ ኑዛዜ ፡ በእንተ ፡ ምግባሪቲክ ።

ትሩፋት ፡ ሠርተህ ፡ ጸጋ ፡ አላገኝም ፡ ማለትህ ፤ በሥ

www.ethiopianorthodox.org

ራዬ ፣ ጸጋ ፣ ላግኝ ፣ አለማለትህ ።

ያጌጹ ፣ በእንተ ፣ ትሕትናህ ፣ ቅድመ ፣ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ፣ ፊት ፣ ትሕትናህን ፣ ያስረዳል ።

ወአፍቅሮትክ ፣ ሎቱ ።

ጌታን ፣ መውደድህን ፣ ያጠይቃል ።

እስመ ፣ ዘያፈቅር ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ዘበአማን ።

ጌታን ፣ በውነት ፣ የሚወድ ፣ ሰው ።

ኢይሬኢ ፣ ክመ ፣ ውእቱ ፣ ገብረ ፣ ምንተኒ ፣ ዘይደሉ ፣ ለአፍቅሮ ፣ እግዚአብሔር ።

ምንም ፣ ምን ፣ ለፍቅረ ፣ እግዚአብሔር ፣ የሚገባ ፣ ሥራ ፣ የሠራው ፣ አይመስለውምና ።

ወበእንተ ፣ ዝንቱ ፣ ይቤ ፣ ብፁዕ ፣ ዳዊት ፤ ምንተ ፣ አዐሥዮ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ በእንተ ፣ ኵሉ ፣ ዘገብረ ፣ ሊተ ። (መዝ፻፲፭) ።

ይህን ፣ የሚያስረዳ ፣ ነገር ፤ ዳዊት ፣ ስለ ፣ ሠራልኝ ፣ ሥራ ፣ ሁሉ ፣ ምን ፣ ዋጋ ፣ እመልስለታለሁ ፣ አለ ።

ወትሑት ፣ ካዕበ ፣ ይሬኢ ፣ ክመ ፣ ርእሱ ፣ ወምግባራቲሁ ፣ ንጹሉ ።

ዳግመኛም ፣ ትሑት ፣ ሰው ፣ ጎዮአ ፣ ነኝ ፣ ይላል ። ትፍቶት ፣ የለኝም ፣ ይላል ። አንድም ፣ ሥራ ፣ እንደ ፣ ሌለው ፣ ያስባል ፣ ይናገራል ፤ ሥራውም ፣ ለጸጋ ፣ እንዳያበቃው ፣ ያስባል ።

ተስእሎ ፤ ፲፭፩ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ እስመ ፣ ይቤ ፣ አባ ፣ አርሳንዮስ ፣ ለአርዳኢሁ ፤ ኢትግበሩ ፣ ሊተ ፣ ተገዝኅረ ፣ ዘእንበለ ፣ ቍርባን ።

አርሳንዮስ ፣ አርድእቶቹን ፣ ከቍርባን ፣ በቀር ፣ ተገዝኅር ፣ አታውጡልኝ ።

ካልእሰ ፣ አልዮ ።

ሌላው ፣ ግን ፣ አይሆንም ፣ አላቸው ።

አይኬ ፣ ፍልጠት ፣ ማእክለ ፣ ተገዝኅረ ፣ ወቍርባን ።

በቍርባንና ፣ በተገዝኅር ፣ መካከል ፣ ያለው ፣ መለያየት ፣ ምንድር ፣ ነው ።

ይቤ ፣ መተርጕም ፤ ይተረጕም ፣ በእንተ ፣ ተገዝኅር ።

ተገዝኅር ፣ ያለው ።

ኢትሕንጹ ፣ ለሥጋየ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ዘይሰማዕ ፣ ባቲ ፣ ተገዝኅርየ ።

በሥጋ ፣ ስሜ ፣ የሚጸራበት ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ አትነጹልኝ ፣ ማለቱ ፣ ነው ።

በክመ ፣ ይቤ ፣ በጊዜ ፣ ሞቱ ፤ እንሰ ፣ እቀምው ፣ ምስሌክሙ ፣ ቅድመ ፣ መንበሩ ፣ ለክርስቶስ ፣ ለእመ ፣ ወሀብክሙ ፣ አዕዕምትየ ፣ ለሰብእ ።

በሞቱ ፣ ጊዜ ፣ መሬቴን ፣ ለሰው ፣ ብትሰጡ ፣ ከናንተ ጋራ ፣ በክርስቶስ ፣ ዘፋን ፣ ፊት ፣ እቆማለሁ ፣ እንዳለ ።

ዘውእቱ ፣ እን ፣ እቀውም ፣ ምስሌክሙ ፣ ውስተ ፣ ተፋትሖ ።

ይኸውም ፣ ከዙፋኑ ፣ ፊት ፣ ቁሜ ፣ እበባላችኋለሁ ፤ እፈራረዳችኋለሁ ፣ ማለቱ ፣ ነው ።

ለእመ ፣ ወሀብክሙ ፣ አዕዕምትየ ፣ ለዘይፌስያ ፣ ምክንያተ ፣ በእንተ ፣ ስሙዓተ ፣ ተገዝኅርየ ።

ስሜ ፣ የሚጸራበት ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ መሬቴን ፣ በሥጋ ፣ መናገጃ ፣ ለሚያደርጋት ፣ ሰው ፣ ብትሰጧት ።

ወይተረጕም ፣ በእንተ ፣ ቍርባንሂ ፣ ተዘክሮተ ፣ ስሙ ፣ በላዕለ ፣ ምሥዋዕ ፣ በጊዜያተ ፣ ቅዳሴያት ።

ቍርባንም ፣ ያለው ፣ በቅዳሴ ፣ ጊዜ ፣ ከመንበሩ ፣ ላይ ፣ ስትቀድሱ ፣ ስሜን ፣ ጽሩኝ ፣ ሲል ፣ ነው ።

እስመ ፣ ቍርባን ፣ ውእቱ ፣ ተዝክረ ፣ ሞቱ ፣ ለክርስቶስ ።

ቍርባን ፣ የክርስቶስ ፣ የሞቱ ፣ መታሰቢያ ፣ ነውና ።

በእንተ ፣ ስርየተ ፣ ኃጣውኢን ።

ኀጢአታችንን ፣ ለማስተስረይ ።

ወውእቱ ፣ ይትሐተም ፣ ለኃጸፊያቲነ ፣ ትርጓሜው ፣ ሰቃል ፣ ዘሰማዕኖ ፣ በእዘኒነ ፤ ዝንቱ ፣ ውእቱ ፣ በግዑ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ዘያሳትት ፣ ኃጢአተ ፣ ዓለም ። (ዮሐ፩ ፣ ፴፮) ።

በወንጌል ፣ ሲነገር ፣ የሰማነው ፣ እንዲህ ፣ ያለው ፣ ትርጓሜ ፣ ለዓይነ ፣ ልቡናችን ፣ ይረዳል ።

ወዝነኒ ፣ ሥጋየ ፣ ዘይትፈተት ፣ በእንቲኣክሙ ። ወዝነኒ ፣ ደምየ ፣ ውእቱ ፣ ዘይትከወው ፣ በእንተ ፣ ስርየተ ፣ ኃጣውኢክሙ ። (ሉቃ፳፪ ፣ ፲፱ና ፳) ።

እንዲህ ፣ ያለው ።

(፲፱) ወይቤ ፣ አረጋይ ፤ እስመ ፣ ዘተብህለ ፣ በእንተ ፣ ሐምሳ ፣ ጸሎት ፣ ወሐምስቱ ፣ ምእት ፣ ጸሎት ፤ እሙንቱኒ ፣ ስግደታት ።

በአስቂጥስ ፣ ሥርዓት ፣ አምሳ ፣ ጸሎት ፤ አምስት ፣ መቶ ፣ ጸሎት ፣ የተባለው ፤ ሁሉም ፣ ስግደት ፣ ነው ። ሁለት ፣ መቶ ፣ ያመነሪ ፤ ሦስት ፣ መቶ ፣ ሃምሳ ፣ የመነኮሴ ፤ አምስት ፣ መቶ ፣ የባሕ ፣ አስኬማ ። አንድም ፣ አምሳ ፣ ጸሎት ፣ ያለው ፣ በቁመ ፣ ጸሎት ፣ አቀጣጥሮ ፤ ስብዐ ፣ በጠ ፣ ስብዕ ፣ ያለውን ፣ ይዘው ፣ የመጸብሐዊን ፣ ጸሎት ፣ በሰባቱ ፣ ጊዜያት ፣ ሁሉ ፤ ስረይ ፣ ሊተ ፣ ለኀጥእ ፣ እግዚኦ ፣ እያሉ ፣ አምሳ ፣ አምሳ ፣ ጊዜ ፣ ያደርሱታል ። (ሉቃ፲፰ ፣ ፲፫) ።)ተስእሎ ፤ ፲፲፩) ። አምስት ፣ መቶ ፣ ጸሎት ፣ ያለው ፣ ግን ፣ ስግደት ፣ እንጂ ፣ በቁመ ፣ ጸሎት ፣ አይደለም ። የሚሰግዱ ፣ እየ ፣ ጸለዩ ፣ ነውና ፣ ስግደታቸው ፣ ከጸሎት ፣ ጋራ ፣ ስለ ፣

ሆነ ፤ የስግደቱን ፣ ቁጥር ፣ ለጸሎት ፣ ሰጥቶ ፣ ተናገረ ። ሁለት ፣ መቶው ፣ ያመነሪ ፤ ሦስት ፣ መቶው ፣ የመነኮሴ ፤ አምስት ፣ መቶው ፣ የባሕታዊ ። ይህ ፣ የማይቀር ፣ የማይታመል ፣ የማኅበር ፣ ግብር ፣ ነው ፤ ትሩፋት ፣ ቢፈልግ ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ እንደ ፣ ተጽለው ፣ ይጨምራል ።

ወደጊሞትኒ ፣ ጸሎት ፣ እንተ ፣ መሀረን ፣ እግዚእን ፤ ዘውእቱ ፣ አቡን ፣ ዘበሰማያት ።

ኒ ፣ አምሳ ፣ ጸሎት ፣ ላለው ፤ ደጊሞት ፣ ያለውም ፤ ጌታ ፣ ያስተማረን ፣ ጸሎት ፣ ነው ። ጸሎተ ፣ ቢል ፤ መላልሶ ፣ መድገምም ፣ አቡነ ፣ ዘበሰማያትን ፣ ነው ። ሥርዓተ ፣ ሲኖዳ ፣ በየጊዜው ፣ ዓሥራ ፣ ሁለት ፣ ያዘል ፤ መላው ፣ ሰማንያ ፣ አራት ።

ተስእሎ ፤ ፲፭፪ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ ይቤ ፣ አባ ፣ ማሚጦስ ፤ በደቂቅናየ ፣ ኮንኩ ፣ እትሐዘብ ፣ ክመ ፣ ሠናየ ፣ ግብረ ፣ ዘኮንኩ ፣ እገብር ።

በወጣኒነቱ ፣ በጎ ፣ ሥራ ፣ የሠራው ፣ ይመስለኝ ፣ ነበር ።

ወዖበ ፣ ረኅዕኩስ ፣ ርኢኩ ፣ ክመ ፣ አነ ፣ ወኢ ፣ አሐደ ፣ ግብረ ፣ ሠናየ ፣ ኢገበርኩ ።

ወደ ፣ ዕርግና ፣ በደረስሁ ፣ ጊዜ ፣ ግን ፣ ጥቂት ፣ ስንኳ ፣ በጎ ፣ ሥራ ፣ እንዳልሠራሁ ፣ ታወቀኝ ፣ አለ ።

ዖኑ ፣ አማንኒጥዩቅ ፤ አው ፣ ይቤ ፣ ዘንተ ፣ በእንተ ፣ ተግባጸ ፣ ትሕትና ።

እንዲህ ፣ ማለቱ ፣ በውነትን ፣ ነው ፤ ወይስ ፣ ለኛ ፣ ትሕትናን ፣ ያስተምረን ፣ ዘንድ ፣ ነው ።

ይቤ ፣ መተርጕም ፤ እመኑን ፣ ውእቱ ።

እውነት ፣ ነው ።

እስመ ፣ ፍጹማንሰ ፣ ለለ ፣ ኵሉ ፣ ዘቀርቡ ፣ ኀበ ፣ እግዚአብሔር ።

ፍጹማን ፣ ወደ ፣ ጌታ ፣ እየ ፣ ቀረቡ ፣ ባለሟል ፣ እየ ፣ ሆኑ ።

ወደለዖሙ ፣ ርእየቱ ፣ በውስተ ፣ ራእየ ፣ ብርሃን ።

በዓይነ ፣ ነፍስ ፣ ጌታን ፣ ማየት ፣ እየ ፣ ተሰጣቸው ።

ይሬእዩ ፣ ክመ ፣ ውእቶሙ ፣ ጕደላውያን ።

ሥራ ፣ ያልሠሩ ፣ ይመስላቸዋልና ።

(፳) ይቤ ፣ አረጋይ ፤ አበው ፣ ናሁ ፣ ዓለሙ ።

ጸሐፉ ፤ መሀሩ ፣ ሲል ፣ ነው ።

ወስመዩ ፣ ትሕትና ፣ በእስማት ፣ ወናያን ።

ትሕትናን ፣ በበጎ ፣ በበጎ ፣ ስም ፣ ጸሩት ።

ወትእምርት ፣ ትርፍት ።

በብዙ ፣ ምሳሌ ፣ መሰሉት ።

ወቅዱስ ፣ እንጦንዮስ ፣ ይቤ ፤ ውእቱ ፣ መርሕቅኒ ፣ ወመድኅንኒ ፣ እመ ሥገርተ ፣ ሰይጣን ።

እንጦንዮስ ፣ መርሕቅ ፣ መድኅን ፣ አለው ። መርሕቅ ፤ አስቀድሞ ፣ ሳይሠሩ ። መድኅን ፤ ከሠሩ ፣ ከተያዙ ፣ በኋላ ፣ ከሰይጣን ፣ አሸክላ ፣ የሚያርቅ ፤ ከዚያ ፣ የሚያድን ፣ አለው ።

ወአባ ፣ መቃርስኒ ፣ ይቤ ፤ ውእቱ ፣ ክትመተ ፣ ሐራዊ ፣ ክርስቶስ ።

መቃርስም ፣ የክርስቶስ ፣ ጭውነት ፣ መለያ ፣ ምልክት ፣ አለው ። (ተረት) ፤ መነኮሴ ፣ በቆቡ ፤ ወንበር ፣ በክታቡ ፣ እንዲሉ ።

ወአባ ፣ አሞንኒ ፣ ስመዮ ፣ ዕበይ ፣ ለሰብእ ።

አሞንም ፣ የሰው ፣ ዘውድ ፣ አለው ።

ወአርሳንዮስኒ ፣ ይቤ ፤ ውእቱ ፣ ምድር ፣ እንተ ፣ ኢትወድቅ ።

አርሳንዮስም ፣ የማይናድ ፣ ይልዳላ ፣ መሬት ፣ አለው ።

ወአባ ፣ ባዖዊኒ ፣ ይቤ ፤ ውእቱ ፣ ልዑል ፣ እምኵሉ ፣ ትፍፋት ።

በምዋም ፣ ከትፍፋት ፣ ሁሉ ፣ የሚበልጥ ፣ አለው ።

ወአባ ፣ ታድራኒ ፣ ስመዮ ፣ መፍርሂ ፣ ሰይጣናት ።

አባ ፣ ታድራም ፣ መስቀል ፣ አለው ።

ወተብያሳዊኒ ፣ ስመዮ ፣ ጎዮየ ፣ ሐቅል ፣ ዘብሕትውና ።

ሲሶይም ፣ የተባሕትዎ ፣ ፀብት ፤ ጋሻ ፣ ጦር ፣ አለው ።

ወበዓሰ ፣ ኩሉሕኒ ፣ አመርዐም ፣ አረፍተ ፣ ትፍፋት ።

አባ ፣ አጋቶንም ፤ ሰመዮ ፣ ሲል ፣ ነው ፤ የትሩፋት ፣ ግድግዳ ፣ አለው ። አንድም ፤ አመርዕም ፣ አረፍተ ፣ ትሩፋት ፤ ግድግዳን ፣ የሚያስጌጥ ፣ ያፈር ፣ ወይዘሮ ፣ አለው ።

ወጳኩሚስኒ ፣ ዘየዐቢ ፣ አመሮ ፣ ፍጹመ ፣ ባሕታውያን ።

ጳኩሚስም ፣ የባሕታውያን ፣ ፍጹምነት ፣ አለው ።

ወቍርብዝማዊኒ ፣ ስመዮ ፣ ሰዋስው ፣ ወእንቀጸ ፣ መንግሥት ፣ ስማያት ።

አባ ፣ ሚልኪም ፣ የመንግሥተ ፣ ሰማይ ፣ መመላለሻ ፣ በር ፣ መግቢያ ፣ አለው ።

ወአባ ፣ ጵርዩኒ ፣ ስመዮ ፣ ክመ ፣ ውእቱ ፣ ሥዕል ፣ እንተ ፣ ታሬኢ ፣ ንትጋተ ።

አባ ፣ ጵርዮም ፣ ሕጸጽን ፣ ሁሉ ፣ የሚያሳይ ፣ የሚያስታውቅ ፣ መስተዋት ፤ አንድም ፣ በቁመ ፣ ስዕል ፣ አለው ።

፩ ፣ ፈላስፋ ፣ ነበር ። ክሌሳ ፣ አገር ፣ እንግዳ ፣ ፈላስፋ ፣ ቢመጣ ፣ መልኩን ፣ ስለ ፣ ወስዳችሁ ፣ አሳዩት ፣ እውነት ፣ ፈላስፋ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ በዚህ ፣ አውቀዋለሁ ፣ ብሎ ፣ አርድእቶቹን ፣ አሲዘ ፣ ሰደደ ። ወስደው ፣

www.ethiopianorthodox.org

ቢሰጡት ፡ ተቀብሎ ፡ አይቶ ፡ መምራችሁ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አቸላው ። አዎን ፡ ቢሉት ፤ ቀኑጡ ፡ ነው ፡ ሴሰኛ ፡ ነውሳ ፡ አላቸው ። የማናውቅበትን ፡ ብለው ፡ ነቅፈው ፡ ተመለሱ ። ምን ፡ አላችኑ ፡ ቢላቸው ፤ እረ ፡ ፍልስፍናም ፡ የለው ፤ የማናውቅብህን ፡ እንዲህ ፡ አለን ፡ አሉት ። እውነተኛ ፡ ፈላስፋ ፡ እንጂ ፤ ቀኑጣዉን ፡ በትዕግሥት ፤ ዝሙቱን ፡ በንጽሕና ፡ ገትቹው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እንደኔ ፡ የሚቃወመው ፡ የለም ፡ ብሏቸዋል ።

ወዮሐንስኒ ፡ ነቢይ ፡ ስመዮ ፡ መርዶ ፡ ነፍሳት ።

ዮሐንስም ፡ የነፍሳት ፡ ወደብ ፡ አለው ።

ወአባ ፡ ሰራብዮንኒ ፡ ይቤ ፤ ውእቱ ፡ ፍጹመ ፡ ጽድቅ ።

አባ ፡ ሰራብዮንም ፡ የትሩፋት ፡ ሁሉ ፡ መፈጸሚያ ፡ አለው ።

ወዮሐንስኒ ፡ ሐዊር ፡ ይቤ ፤ ውእቱ ፡ ቀዳሜ ፡ ትእዛዛት ፡ ብዕዕት ።

ዮሐንስ ፡ ሐዊርም ፡ የወንጌል ፡ ትእዛዝ ፡ መጀመሪያ ፡ ደገኛ ፡ አለው ።

ያኤምር ፡ ኀበ ፡ ቃለ ፡ እግዚእን ፡ ዘውስተ ፡ ወንጌል ፤ ብፁዓን ፡ ነዳያን ፡ በመንፈስ ፤ እስመ ፡ ሎሙ ፡ ይእቲ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

ይኸውም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ።

ወአባ ፡ ወቅሪስኒ ፡ ይቤ ፤ እስመ ፡ ትሕትና ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ እንተ ፡ ታዓርግ ፡ ኀበ ፡ ሱባሌ ።

ወቅሪስም ፡ ወደ ፡ ንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ሰገነት ፡ የሚወጡባት ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ አለው ።

ወአባ ፡ በጥራኒ ፡ ይቤ ፤ ውእቱ ፡ መሠረተ ፡ ትሩፋት ።

አባ ፡ በጥራም ፡ የትሩፋት ፡ መጽኛ ፡ መሠረት ፡ አለው ።

ወአባ ፡ ኢሳይያስኒ ፡ ሰመዮ ፡ እምንተ ፡ ትሩፋት ።

አባ ፡ ኢሳይያስም ፡ የትሩፋት ፡ መታመኛ ፡ አለው ።

ወብዑዊኒ ፡ ዳዊት ፡ ሰመዮ ፡ ነፍስ ፡ የዋህ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ለእግዚአብሔር ። (መዝሙር፶) ።

ዳዊትም ፡ መሥዋዕት ፡ አለው ።

እስመ ፡ ዘይትሌዐል ፡ ወይዜነር ፡ ውእቱኬ ፡ ይወድቅ ፡ ከመ ፡ ሰይጣን ።

የሚኮራ ፡ የሚታበይ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሰይጣን ፡ ይወርዳልና ።

ወዘበ ፡ ይቴሐት ፡ ይትሌዐል ፡ ምስለ ፡ እግዚእን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለማት ፡ አሜን ።

የትሕትና ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ግን ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፤ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይወጣል ።

ሥርዓተ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእን ፡ ናሁ ፡ አስፈወ ፡ ለትሑታን ።

ጌታ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ያስተማረው ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ ብዕዓን ፡ ሰጠ ።

ከመ ፡ ሎሙ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወመንግሥተ ፡ ምድር ።

መንግሥተ ፡ ሰማያት ፤ መንግሥተ ፡ ምድርም ፡ ገንዘባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተናገረ ።

በብሂሎቱ ፤ ብፁዓን ፡ ነዳያን ፡ በመንፈስ ፤ ወብፁዓን ፡ ትሑታን ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይወርስዋ ፡ ለምድር ። (ማቴ፭ ፣ ፫) ።

እንዲህ ፡ ብሎ ።

ክፍል ፡ ዓሥር ።

ቃል ፡ በእንተ ፡ ተቃትሎተ ፡ ዝሙት ።

የዝሙትን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ተስእሎ ፡ ፪፭፮ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ኮነ ፡ ቀትሰ ፡ ዝሙት ፡ ኀበ ፡ አሐዱ ፡ እምባሕታውያን ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ እንብልብልት ፡ በመዓልት ፡ ወበሌሊት ።

ከባሕታውያን ፡ ባንዱ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ የሚቃጠል ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ የማይበርድ ፡ የዝሙት ፡ ፍሬ ፡ ተነሣበት ።

ወኮነ ፡ ይትዔገሥ ።

እሱ ፡ ሻን ፡ ያሩን ፡ ይታገሠው ፡ ነበር ።

ወኢየኀድግ ፡ ሕሊናሁ ።

ዝሙትን ፡ ያስብ ፡ ዘንድ ፡ ሕሊናውን ፡ አያሰናብተውም ፡ ነበረ ።

ወእምድኅረ ፡ አዝማን ፡ ሕቅ ፡ ተወደወ ፡ እምኔሁ ፡ ቀትል ።

ጥቂት ፡ ወራት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ያሩ ፡ ጠፋለት ።

ወበርሀ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ልቡ ።

ንጽሕና ፡ ተሰጠው ፤ ብርሃን ፡ ተሳለበት ። ኢየኀድግ ፡ ያለው ፤ በርሀ ፡ ያለው ፤ ምንድር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ብሂሎቱ ፡ ኢኮነት ፡ ሕሊናሁ ፡ ትወርድ ።

ኢየኀድግ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘውእቱ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ የኀድግ ፡ ዘክሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ወጸሎተ ፡ ኀብዕተ ።

ተዘክሮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጸሎተ ፡ ልብን ፡ ትቶ ።

ወኢይወርድ ፡ ኀበ ፡ ነቢብ ፡ ውስተ ፡ ሕሊና ፡ ዝሙት ።

ተዋርዶ ፡ ዝሙትን ፡ አያስብም ፡ ነበር ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

አላ ፡ ኮነ ፡ ይትመዐዕ ፡ ነፍሶ ፡ ለመቲረ ፡ ፍትወቱ ፡ በፍትወተ ፡ አፍቅሮ ፡ እግዚአብሔር ።

ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመሻት ፡ ፈቲውን ፡ ለማራቅ ፡ ለማጥፋት ፡ ራሱን ፡ ይገሥጽ ፡ ነበር ፡ እንጂ ።

ወያበተኣኪ ፡ ፍትወተ ፡ ሥጋ ፡ በፍትወተ ፡ መንፈስ ።

መንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ በመሻት ። አንድም ፡ በፈቃደ ፡ ነፍስ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ይጸላ ፡ ነበር ።

ወአፍቅሮቶ ፡ ለእግዝእ ፡ በአፍቅሮ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ በመውደድ ፡ ኀጢአትን ፡ መውደድን ፡ ያርቅ ፡ ነበር ።

ወብሂሎቱ ፡ ሶበ ፡ ሞአ ፡ ሕማማተ ፡ ሠረቀ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ልቡ ።

ያሩን ፡ ድል ፡ ከነሣ ፡ በኋላ ፡ በልቡ ፡ ብርሃን ፡ ተሳለበት ፡ ያለውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ዘቲኬ ፡ ጽድቅ ።

በሕታዊ ፡ የሚሠራው ፡ ትሩፋት ፤ የሚያገኘው ፡ ክብር ፡ ነው ።

ዘውእቱ ፡ ንጽሕ ፡ ወትሕትና ።

ይኸውም ፡ ንጽሕና ፡ ትሕትና ፡ ነው ።

ወበእንተ ፡ ገ ።

ብርሃን ፡ ንጽሕና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ለመዮ ፡ አባ ፡ ወቅሪስኒ ፡ ብርሃነ ፡ ቅዱስ ።

አባ ፡ ወቅሪስም ፡ ንጽሕናን ፡ ብርሃን ፡ አለው ።

ወይቤሉ ፡ አበውሂ ፤ እምከመ ፡ ሞአ ፡ ባሕታዊ ፡ ስብሐተ ፡ ዕፍቀ ።

መነኰሲ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

ወወርገ ፡ ኀበ ፡ ሱባሌ ፡ ትሕትና ።

ወደ ፡ ፍጹም ፡ ትሕትና ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

ይሠርቅ ፡ ላዕሌ ፡ ልቡ ፡ ብርሃን ፡ እምላካዊ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ።

በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ በልቡናው ፡ የጌታ ፡ ብርሃን ፡ ይሳለበታል ።

ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ብርሃነ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእን ።

የጌታን ፡ ብርሃን ፡ ማየት ፡ ይሰጠዋል ፤ ለማየት ፡ ይበቃል ።

ተስእሎ ፡ ፪፭፯ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ኮነ ፡ ቀትሰ ፡ ዝሙት ፡ ምስለ ፡ ክልእኒ ፡ እጉ

በሌላውም ፡ መነኰሴ ፡ የገሙት ፡ ያር ፡ ተነሣበት ።

ወተወገሠ ፡ ሎቱ ፡ ምስለ ፡ ትሕርምት ፡ ብዙኅ ፡ ኅሠርተ ፡ ወአርባዕተ ፡ ዓመተ ።

በብዙ ፡ ትሕርምት ፡ ሁኖ ፡ ዓሥራራት ፡ ዓመት ፡ ታገሠው ።

ወኮነ ፡ የዐቅብ ፡ ሕሊናው ።

ዝሙት ፡ እንዳይታሰበው ፡ ሕሊናውን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ።

ወኢይወርድ ፡ ኀበ ፡ ፍትወት ።

ተዋርዶ ፡ ፈቲውን ፡ አያስብም ፡ ነበር ።

ወበደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ መጽአ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ኋላ ፡ ግን ፡ ኑሮ ፡ ኑሮ ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መጣ ።

ወከመት ፡ ቀትሎ ፡ ለሰሎ ፡ ማኅበረ ፡ ምኔት ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ያር ፡ ተነሥቶብኛልና ፡ እዘኑልኝ ፡ ብሎ ፡ ለማኅበሩ ፡ ነገረ ።

ወሐሙ ፡ እንከ ፡ ምስሌሁ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ።

ሰባት ፡ ቀን ፡ ግብር ፡ ገብተው ፡ አዘኑለት ።

ወኮኑ ፡ ይጼልዩ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲኣሁ ።

ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለዩለት ።

ወበጠለ ፡ እንከ ፡ እምኔሁ ፡ ተቃትሎ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ያር ፡ ጠፋለት ። (ታሪክ) ፤ ይኸም ፡ ቢሉ ፤ ሌላም ፡ ቢሉ ፤ አንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያር ፡ ተነሥቶበት ፡ ሳለ ፡ ቀድሰህ ፡ አቍርበን ፡ አሉት ። ዛሬስ ፡ ተዉኝ ፡ አልተቻለኝም ፡ ቢላቸው ፡ ግድ ፡ አሉት ። ግድማ ፡ ካላችሁኝ ፡ ቀድሼ ፡ አቍርቤያችሁ ፡ ሳበቃ ፡ ያልኋችሁን ፡ ታደርጋላችሁ ፡ አላቸው ፤ አምን ፡ አሉት ። እንኪያስ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ቀድሶ ፡ አቍርቧቸው ፡ ሲያበቃ ፡ እንግዴህ ፡ እኔ ፡ ሳላሰናብታችሁ ፡ ሰው ፡ አይውጣ ፡ ብሎ ፡ አስጠበቃቸው ። ኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ ፈጽሞ ፡ ወጥቶ ፡ ከመድረኩ ፡ ላይ ፡ በልቡ ፡ ተኝቶ ፤ በሉ ፡ እያንዳንዳችሁ ፤ አ እግዚኦ ፡ ስረይ ፡ ሎቱ ፡ ኀጢአቶ ፡ እያላችኑ ፡ እየ ፡ ረገጣችሁኝ ፡ ውጡ ፡ አላቸው ። እየ ፡ ረገጡት ፡ ሲወጡ ፡ ሰረይኩ ፡ ሎቱ ፡ በእንተ ፡ ትሕትናሁ ፡ የሚል ፡ ድምጽ ፡ ተሰምቶለታል ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ጸንዐ ፡ ምስሌሁ ፡ ተቃትሎ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ቀዳሚሁሰ ፡ ውኩሰ ፡ ዲበ ፡ ምግባሩ ።

ቀድሞ ፡ ያሩ ፡ የጸናበት ፡ በትሩፋቱ ፡ ይመካ ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ወድኅነ ፡ እምኔሁ ፡ ሶበ ፡ አምነ ፡ ኪያሁ ፡ ለማኅበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ኋላ ፣ ግን ፣ መዳኑ ፣ ያሩን ፣ ለማሳበሩ ፣ ቢነግር ፣ ነው ።

ወጸለዩ ፣ በእንቲኣሁ ።

ቢጸልዩለት ፣ ነው ።

እስመ ፣ ውእቱ ፣ ገብረ ፣ ትሕትና ፣ ብዙኀ ።

ፍጹም ፣ ብዙ ፣ የሚሆን ፣ የትሕትና ፣ ሥራ ፣ ሠርታልና ።

(ጸጸ) ወይቤ ፣ አረጋይ ፤ እስመ ፣ ለእጉኒ ፣ ካልእ ፣ ኮነ ፣ ምስሌሁ ፣ ቀትለ ፣ ዝሙት ።

ሌሳም ፣ አንድ ፣ መነሰሴ ፣ የዝሙት ፣ ያር ፣ ተነሣበት ።

ወተገባብአ ፣ ኀበ ፣ አረጋዊ ፣ በአሐቲ ፣ ሌሊት ፣ ኅሥርተ ፣ ወአሐደ ፣ ጊዜ ።

ወደ ፣ አረጋዊ ፣ ባንድ ፣ ሌሊት ፣ ዓሥራንድ ፣ ጊዜ ፣ ተመላለሰ ።

ወለለ ፣ ኵሉ ፣ ምዕር ፣ ዘይመጽእ ፣ ኮነ ፣ ሰይጣን ፣ ይጕይይ ፣ እምኔሁ ።

ወደ ፣ አረጋዊ ፣ ሲመጣ ፣ ሲመጣ ፣ ሰይጣን ፣ ዝሙት ፣ ይርቅለት ፣ ነበር ።

ወይበጥል ፣ እምኔሁ ፣ ቀትል ።

ያሩም ፣ ይጠፋለት ፣ ነበር ።

እምኀይለ ፣ ጸሎቱ ፣ ለአረጋዊ ።

ከአረጋዊ ፣ ጸሎት ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ።

ወነገሩ ፣ ዘምስሌሁ ።

ከሱ ፣ ጋራ ፣ ከመነጋገሩ ፣ የተነሣ ። አንድም ፤ ወነገሩ ሰ ፣ ይላል ፤ ፈጽሞ ፣ ሣን ፣ ሰይጣነ ፣ ዝሙት ፣ አልተለየውም ፤ ያሩ ፣ አልጠፋለትም ፣ ነበር ።

ወዖበ ፣ ተመይጠ ፣ እጉ ፣ ኀበ ፣ በዓቱ ፣ ይገብእ ፣ ኀቤሁ ፣ ተቃትሎቱ ።

ወደ ፣ በዓቱ ፣ ሲመለስ ፣ ያሩ ፣ ይመለስበት ፣ ነበር ።

ወዝንቱስኬ ።

እንዲህ ፣ መሆኑ ።

እስመ ፣ አረጋዊ ፣ ይደክም ፣ ምስሌሁ ፣ ዖበ ፣ ይመጽእ ፣ ባሕቲቱ ፣ እጉ ፣ ኀቤሁ ።

ወደሱ ፣ ወደሱ ፣ ሲመጣ ፣ ብቻ ፣ ይደክምለት ፣ ነበር ና ።

ወዖበ ፣ የሐውር ፣ እምኀቤሁ ።

ወደ ፣ በዓቱ ፣ ሲሄድ ፣ ግን ።

ያስተሐምም ፣ በእንተ ፣ ነፍሱ ፣ አረጋዊ ።

ለራሱ ፣ ያስብ ፣ ነበርና ፣ ስለዚህ ፣ ነው ።

ወዖበ ፣ አመሮ ፣ እጉ ፣ ለአረጋዊ ።

ኋላ ፣ ግን ፣ ይህ ፣ ያር ፣ አልተወኝም ፣ ብሎ ፣ ቢነግረው ።

ሐለየ ፣ እንክ ፣ ከመ ፣ ምክንያት ፣ እምኀቤሁ ፣ ውእቱ ።

ምክንያቱ ፣ ከሱ ፣ ወገን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ አወቀ ።

ወይቤ ፣ እንኪ ፣ ዘተሀየይኩ ።

ቸል ፣ ያልኩህ ፣ እኔ ፣ ነኝ ፣ አለ ።

እስመ ፣ አነ ፣ ኮንኩ ፣ ዘኢያስተሐምም ፣ በእንቲኣክ ፤ ወኢየሐምም ፣ ወኢይጼኢ ፣ በእንቲኣክ ፣ ዖበ ፣ ሖርክ ፤ በከመ ፣ ኮንኩ ፣ አስተሐምም ፣ በእንቲኣክ ፣ ወአሐምም ፣ ወእጼኢ ፣ በእንቲኣክ ፣ ዖበ ፣ መጸእክ ።

ወደኔ ፣ በመጣህ ፣ ጊዜ ፣ እንደማዝንልህ ፤ በሄድህ ጊዜ ፣ የማላዝንልህ ፣ ሁኛለሁና ።

ወዖበ ፣ ተትሕተ ፣ አረጋዊ ።

የትሕትና ፣ ሥራ ፣ ቢሠራ ።

ወእንወረ ፣ ርእሶ ።

ጥፋተኛው ፣ እኔ ፣ ነኝ ፣ ብሎ ፣ ራሱን ፣ ቢነቅፍ ።

አብጠለ ፣ እግዚአብሔር ፣ ቀትለ ፣ እምእጉ ፣ በምሕረቱ ።

ጌታ ፣ በቸርነቱ ፣ ከዚያ ፣ መነሰሴ ፣ ያሩን ፣ አጠፋላት ።

ወተሰብሐ ፣ እግዚአብሔር ።

እሱም ፣ ተመሰገነ ።

ወይቤ ፣ ካዕበ ፣ አረጋዊ ፤ እስመ ፣ ለዮሱ ፣ ሰብእ ፣ በከመ ፣ አምጣነ ፣ ወቅመ ፣ ሥርዓቱ ፣ ይትጎደግ ፣ ላዕሌሁ ፣ ሰይጣነ ፣ ዝሙት ።

ሰው ፣ ሁሉ ፣ እንደ ፣ ሥራው ፣ መጠን ፣ ሰይጣነ ፣ ዝሙት ፣ ይታዘዝበታል ።

ወዘሰ ፣ ይከውን ፣ ምስሌሁ ፣ ተቃትሎት ፣ ውስተ ፣ ሕሊናት ፣ አዝማኖ ፣ ጕንፉኖ ።

ብዙ ፣ ዘመን ፣ የዝሙት ፣ ያር ፣ በሕሊና ፣ የሚዋጋው ፣ ሰው ።

ለእመ ፣ ኮነ ፣ ይትጋደል ፣ በምግባር ፣ ወጸሎት ።

በጸሎት ፣ በትሩፋት ፣ ቢጋደል ።

ይመውኦ ፣ ተቃትሎተ ፣ ሕሊናት ።

የሕሊናን ፣ ያር ፣ ድል ፣ ይነሣል ።

ወዖቤሃ ፣ ይትቃተሎ ፣ ሰይጣን ፣ ገሃደኒ ፣ በተዐውቆት ።

ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ታይዮ ፤ ተገልጾ ፤ አስታውቆ ፣ ይዋጋዋል ።

ወገሚሦ ፣ አባል ፣ ዘእንበለ ፣ ፈቃዱ ።

ሳይወድ ፣ አካልን ፣ በመዳሰስ ።

ወይገብሩ ፣ በትድሜሁ ፣ ምትሓተ ፣ ተባዕተ ፣ ወእንስተ ።

ወንድና ፣ ሴት ፣ እየ ፣ ሆኑ ፣ በፊቱ ፣ ምትሓት ፣ ያሰዩታል ።

እምነ ፣ እንስሳ ።

ከእንስሳ ፣ ወገን ፣ አለሌና ፣ ባዝራ ።

ወሰብእ ።

ከሰውም ፣ ወገን ፣ ቆንጆና ፣ ጕልማሳ ፣ እየ ፣ ሆኑ ።

ከመ ፣ ዘይደሜንሩ ።

የሚጨዋወቱ ፤ የሚደራረጉ ፣ መስለው ፣ ይታዮታል ።

ወናሁ ፣ ያስሕትዎሙ ፣ በአገብሮ ፣ በአሕላመ ፣ ሌሊት ፣ በሕማም ።

እንዲህ ፣ እያሉ ፣ ሌት ፣ በሕልም ፣ ዝሙትን ፣ በማሳሰብ ፣ ያስታቸዋል ።

ወዖበ ፣ ጸንሁ ፣ ከመዝ ፣ ርኁቅኬ ፣ እንክስ ።

ጸንቶው ፣ ቢዋጉ ፣ ግን ፣ ያሩ ፣ ይርቅላቸዋል ። አንድም ፣ አጋንንት ፣ እንዲህ ፣ አድርገው ፣ ያሩን ፣ ያጸኑባቸው ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ መለየቱ ፣ ያስቸግራል ። አንድም ፤ ርኁቅኬ ፤ ከሰው ፣ ተለይቶ ፣ ከበዓት ፣ ተከቶ ፣ ወደሚኖር ፣ ሰው ፣ መሄድ ፣ ያሻል ።

ከመ ፣ ይትገኝሥ ።

ያሩ ፣ ይርቅለት ፣ ዘንድ ።

ወእባ ፣ ሙሴ ፣ ርእየ ፣ ምትሓታተ ፣ ሕሙማተ ።

አባ ፣ ሙሴም ፣ ምትሓተ ፣ አጋንንትን ፣ አየ ፣

ወጸንዐ ፣ ላዕሌሁ ፣ ተቃትሎት ።

የዝሙት ፣ ያር ፣ ጸናበት ።

ወኢክህለ ፣ ይትዐገሥ ፣ ውስተ ፣ በዓቱ ።

በበዓቱ ፣ ሆኖ ፣ መታገሥ ፣ ባይቻለው ።

ወሖረ ፣ ኀበ ፣ አባ ፣ ኤስድሮስ ።

ወደ ፣ አባ ፣ ኤስድሮስ ፣ ሄደ ።

ወዐርገ ፣ ምስሌሁ ፣ መልዕልተ ፣ ናሕስ ።

ከሰገነት ፣ ላይ ፣ ይዞት ፣ ወጣ ።

ወአርአዮ ፣ ትዕይንተ ፣ ሰይጣናት ፣ ውስተ ፣ ዓረብ ፣ እንዘ ፣ ይትቃተሎ ።

ሠራዊተ ፣ አጋንንት ፣ በምዕራብ ፣ በኩል ፣ ተሰልፈው ፣ ሲዋጉት ፣ አሳየው ።

ወትዕይንት ፣ መላእክት ፣ ቅዱሳን ፣ እምሥራቅ ፣ እንዘ ፣ ይትራድኡ ።

ሠራዊተ ፣ መላእክት ፣ በምሥራቅ ፣ በኩል ፣ ሁነው ፣ ሲረዱት ፣ አሳየው ። (ሐተታ) ፣ መላእክት ፣ በምሥራቅ ፤ አጋንንት ፣ በምዕራብ ፣ ተሰላልፈው ፣ አይቶ ፣ ምንድር ፣ ናቸው ፣ አለው ። በሥራዊ ፣ በጕልበቱ ፣ ብትል ፣ እሊያ ፣ ይዋጉሃል ። በእግዚአብሔር ፣ ቸርነት ፣ ብትል ፣ እሊህ ፣ ይረዱሃል ፣ ብሎታል ።

ወተናዘዘ ፣ እንክ ።

ይህን ፣ ሰምቶ ፣ ደስ ፣ አለው ።

ወተጸንዐ ።

ጸና ፣ ማለት ፤ በረድኤተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ድል ፣ እነሣለሁ ፣ አለ ።

ወገብአ ፣ ኀበ ፣ በዓቱ ።

ተመልሶ ፣ ወደ ፣ በዓቱ ፣ ገባ ።

ወተጋደለ ፣ ምስለ ፣ ትፍሥሕት ፣ ወጥብዓት ።

ደስ ፣ እያለው ፣ ጸንቶ ፣ ተዋጋ ። (ተስእሎ ፸)

ተስእሎ ፣ ፸፰ ።

ይቤሉ ፣ ኦኃው ፤ እስመ ፣ ይቤሉ ፣ አዕሩግ ፤ ለእመ ፣ ኮነት ፣ ሕሊናተ ፣ ዝሙት ፣ ውስተ ፣ ልበ ፣ ብእሲ ።

በሰው ፣ ልቡና ፣ ዝሙት ፣ ብትታሰበው ።

ወኢይፈጽማ ፣ በገቢር ።

በገቢር ፣ ባይፈጽማት ።

ውእቱኬ ፣ ክሙ ፣ ዘያልሕት ፣ ኀፀደ ፣ ወይን ፣ ወይፈቱ ፣ ክሙ ፣ ይብላዕ ፣ እምወይን ።

ወይን ፣ ተክዬ ፣ አሳደጌ ፣ ሲደርስልኝ ፣ ፍሬውን ፣ እበላለሁ ፣ ብሎ ።

ወኢቦአ ፣ ኀበ ፣ ኀፀደ ፣ ወይን ፤ ወኢበልዐ ፣ እምወይን ።

ደርሶለት ፣ ያልበላ ። አንድም ፤ ዘይሰርቅ ፣ ይላል ፤ ወይን ፣ ሰርቄ ፣ እበላለሁ ፣ ብሎ ፣ አስቦ ፣ ሳያገኝ ፣ የቀረን ፣ ይመስላል ።

ለውእቱኬ ፣ ይደልዎ ፣ ዝብጠት ፤ ወአኮሰ ፣ ሞት ።

ለዚህ ፣ ግርፋት ፣ እንጂ ፣ ሞት ፣ አይገባውም ፣ አሉ ። ዝብጠት ፣ ያለው ፣ ምንድር ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፣ መቶርጦም ፤ እስመ ፣ አበው ፣ ይፈእዩ ፣ ክመ ፣ ዝሙት ፣ ዘየወውድ ፣ ውስተ ፣ ሕሊናት ።

በሕሊና ፣ የሚወጣ ፣ የሚወርድ ።

ወይጕንዲ ፣ ውስቴታ ።

በልቡና ፣ የሚውል ፣ የሚያድር ፣ ዝሙትን ።

ወይትቄበሎ ፣ ምስለ ፣ ተፈገፃ ።

ደስ ፣ ብሎት ፣ ቢሰማማው ።

ወኢይመጽእ ፣ ኀበ ፣ ገቢር ።

ከገቢር ፣ ባያደርሰው ።

ኢትመውት ፣ ነፍስ ፣ በእንቲኣሁ ፣ እምነ ፣ ሕይወት ፣ እንተ ፣ እግዚአብሔር ።

በዚህ ፣ ምክንያት ፣ ነፍስ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ አንድነት ፣ አትለይም ።

ወኢትትኄመዕ ፣ ፍጹመ ።

ፈጽማ ፣ በደለኛ ፣ አትባልምና ።

ወባሕቱ ፣ ይርኅት ፣ እምንጽሐ ፣ ልብ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ እምኔሆሙ ።
ይኸውም ፡ ትዕግሥቱ ፡ የሚገኘው ፡ ከሰዎቹ ፡ አይደ
ለም ።
አላ ፡ እምን ፡ ዘየእምር ፡ ሕሊናን ።
ሕሊናችንን ፡ መርምሮ ፡ ከሚያውቅ ።
ወይረድኦ ።
አውቆ ፡ ከሚረዳን ፡ ከጌታ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
አኮሰ ፡ እምተዘክሮ ፡ ገሃነም ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘይትከላእ ፡ ሰብእ ፡ እምኀጣ
ውእ ።
ሰው ፡ ኀጢአት ፡ ከመሥራት ፡ የሚከለክል ፡ ገሃነም
ን ፡ በመዘከር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
ወኢ ፡ እምተዘክሮ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይትቄለው ፡ በእንተ ፡ ም
ግባራት ።
ትሩፋት ፡ ለመሥራት ፡ የሚናደድ ፡ መንግሥተ ፡ ሰ
ማያትን ፡ በመዘከር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
እስመ ፡ ለዮስኒ ፡ አሐዱ ፡ ቦቱ ፡ ዝንቱ ፡ ተዘክሮት ።
ለሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ተዘክሮ ፡ ኦለውና ።
ወባሕቱ ፡ ኢኮነ ፡ ለሮሱ ፡ አሐዱ ፡ ሕሊና ።
አእምሮ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሳን ፡ ለሁሉ ፡ የሚሰጥ ፡ አይደ
ለም ።
እንተ ፡ ትትሜሰል ፡ ምስለ ፡ ኃይለ ፡ ረድኤት ፡ ዘእምሀብታተ ፡ እግዚ
እነ ።
በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ የሚገኝ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ የሚያስረዳ ፡ የሚመስል ፤ አእምሮ ፡ መን
ፈሳዊን ፡ የሚመስል ፡ አለ ፤ አእምሮም ፡ ረድኤትም ፡
ሥራ ፡ ያሠራሉና ።
(፳፱) ወይቤ ፡ አረጋዊ ፤ እስመ ፡ እኁኑ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ እባ ፡ ጲሜ
ን ፡ ወይቤሎ ፡ እንሰ ፡ ፈራህኩ ፡ ቀዳሚው ፡ እምደዊያት ፡ ወሕማማት ፡
ፍጥረታዊት ።
እኔስ ፡ አስቀድሚ ፡ ደዌ ፡ ይወድቅብኛል ፤ የባሕርይ ፡
ያር ፡ ይነሣብኛል ፡ ብዬ ፡ ፈርቼ ።
ወተወየይኩ ፡ እንከ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ።
ትሩፋት ፡ መሥራትን ፡ ቸል ፡ አልሁ ።
ወይቤሎ ፡ ዖበስ ፡ ኮንከ ፡ ጻመውክ ፡ በእንተ ፡ ትርፍት ።
ትሩፋት ፡ ለመሥራት ፡ ብትደክም ።
እምኮንከ ፡ ትድኀን ፡ እምደዊያት ፡ ፍጥረታዊት ።
ከደዌም ፡ ከባሕርይ ፡ ያርም ፡ በዳንኸ ፡ ነበር ።
በእንተ ፡ ምግባራቲከ ፡ በበይነ ፡ አፍቅሮተ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን ፡ ወይሀ ፡ በምትሠራው ፡ ሥራ ።
ከመ ፡ መንፈቀ ፡ አበው ፡ ባሕታውያን ።
እንደ ፡ እሉሱቶቹ ፡ ባሕታውያን ።

እምኮነት ፡ ትትሐሰብ ፡ ለክ ፡ ስምዕ ፡ በእንተ ፡ ምግባራቲክ ፡ ወመዊእ
ትክ ፡ በእንተ ፡ ሕማማተ ፡ ጎጢአት ።
በትድንም ፡ ትሩፋት ፡ ሠርተሀ ፡ የኀጢአትን ፡ ያር ፡
ድል ፡ መንግት ፡ ሰማዕትነት ፡ ትቄጸርልሀ ፡ ነበር ።
ወስምዕ ፡ በእንተ ፡ ትዕግሥትክ ፡ ወአዕዮቶትክ ፡ በውስተ ፡ ደዌያት ፡
ፍጥረታዊት ።
ደዊሀን ፡ ታግሠሀ ፡ ጌታን ፡ ማመስገንህም ፡ ሰማዕትነ
ት ፡ በተቄጠረልሀ ፡ ነበር ።

ተስእሎ ፡ ፲፬፭ ።

ይቤሎ ፡ አኃው ፤ ተስእሎ ፡ እጕ ፡ ለአባ ፡ ጲሜን ፡ በእንተ ፡ ዝሙት ።
አንድ ፡ መነኰሰ ፡ አባ ፡ ጲሜንን ፡ የገሙቱን ፡ ነገር ፡
ጠየቀው ፤ የገመዉቱን ፡ ያር ፡ ድል ፡ መንግት ፡ እንደ
ምን ፡ ነው ፡ ብሎታል ።
ወይቤሎ ፤ ዕቀብ ፡ ልሳንክ ።
አንደበትህን ፡ ጠብቅ ።
ወክርሠክ ።
ሆድህን ፡ ጠብቅ ።
ወንግደተክ ።
እንግድኒትህንም ፡ ተው ፡ አለው ።
ምንት ፡ ይእቲ ፡ ንግድና ።
ንግድና ፡ ያላት ፡ ምንድር ፡ ናት ።
ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ይእቲኬ ፡ ክመ ፡ ኢትኩን ፡ እሙረ ።
ይኸውም ፡ ሰው ፡ ይወቀኝ ፡ ልታወቅ ፤ አትበል ።
ወኢ ፡ ማእምረ ፡ አሐደኒ ።
እኔም ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ልወቅ ፡ አትበል ፡ ማለቱ ፡
ነው ።
በውስተ ፡ መክን ፡ ዘትሄሉ ፡ ውስቴታ ፤ አላ ፡ ክመ ፡ ፈላሲ ።
ባለህበት ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ፈላሲ ፡ ሁነህ ፡ በበዓትህ ፡ ጸ
ንተህ ፡ ኑር ፡ እንጂ ።
ክመ ፡ ይዕቀብ ፡ ልቦ ፡ እምትዝኀርት ፡ ወይይኖታት ።
ከትዕቢት ፡ በሰው ፡ ከመፍረድ ፡ ልቡናውን ፡ ይጠብ
ቅ ፡ ዘንድ ።
እስመ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ወይቁ ፡ ብዙኃን ፡ ውስተ ፡ ዝሙት ።
በነዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በገዝሙት ፡ ተሰነ
ካክለዋልና ።
ወዘበእንተ ፡ ተሞግሶ ፡ ተዐንሱ ።
አቦ ፡ አቦ ፡ መባልን ፡ ስለወደዱ ፡ ከጸጋ ፡ ከክብር ፡ ተ

ንጽሐ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ የለውም ፤ አልተሰጠውም ።
ወይትመተር ፡ እምዝክረ ፡ እግዚአብሔር ።
ከተዘከሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይለያል ።
ወዝ ፡ ውእቱ ፡ ዘአመሩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ዝብጠተ ።
ግርፋት ፡ ይገባዋል ፡ ያሉት ፡ ይህ ፡ ነው ።
ዘእንበለ ፡ ሞት ።
ሞት ፡ ያይደለ ።
ወለዝሙትሰ ፡ ሥጋዊ ፡ ዘበገቢር ፡ ይሰምይዎ ፡ አበው ፡ ሞተ ፡ ፍጥረ
ታዊ ፡ ለነፍ ።
በገቢር ፡ የሚፈጸም ፡ ዝሙትን ፡ ሳን ፡ አበው ፡ ለነፍ
ስ ፡ የባሕርይ ፡ ሞት ፡ ይሉታል ።
እስመ ፡ ለብእሲ ፡ ዘይገብሮ ፡ ይጸለምት ፡ ልቡ ።
የሚሠራው ፡ ሰው ፡ አእምሮው ፡ ይለወጣልና ።
ወይረስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን ፡ ይዘነጋዋል ።
ወይትኀፈር ፡ እምልቡ ።
ከልቡናው ፡ ያፍራል ።
ወየኀጥእ ፡ ሞገስ ፡ እንተ ፡ ሎቱ ፡ ዘኀበ ፡ እግዚአብሔር ።
እንግዴህ ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ ባለሟልነት ፡ አላገኝም ፡
ይላል ።
ወይፌኢ ፡ ክመ ፡ ውእቱ ፡ ፈጸመ ፡ ፈቃደ ፡ እላሚ ።
የሰይጣንን ፡ ፈቃድ ፡ ፈጸምኁ ፡ ይላል ።
ወይትመተር ፡ እንክ ፡ ተስፋሁ ።
ተስፋ ፡ ይቄርጣል ።
ወዝኬ ፡ ውእቱ ፡ ሞት ።
ሞት ፡ ያሉት ፡ ይህ ፡ ነው ።
ወአኮ ፡ ዝብጠት ።
ግርፋት ፡ ያይደለ ።

ተስእሎ ፡ ፲፬ ።

ይቤሎ ፡ አኃው ፤ ምንትኑ ፡ ውእቱ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለቃለ ፡ እም ፡ ሳራ ።
ሳራ ፡ የተናገረችው ፡ ነገር ፡ ትርጓሜው ፡ ምንድር ፡
ነው ።
አንሰ ፡ እንዘ ፡ እፈቅድ ፡ አንብር ፡ እገርየ ፡ ዲበ ፡ ሰዋስው ፤ እንዘ ፡ እ
ፈቅድ ፡ እዕርግ ፡ ኀበ ፡ ናሕስ ፡ አስተዳሎ ፡ ሞትየ ፡ ቅድመ ፡ ገጽየ ።
እኔ ፡ ወደ ፡ ሰገነት ፡ እወጣለሁ ፡ ብዬ ፡ መጀመሪያው
ን ፡ እርከን ፡ ስረግጥ ፡ ሞቴን ፡ አስባለሁ ።
እምቅድመ ፡ አንሥኦ ፡ ክልኦ ።
ሁለተኛውን ፡ ሳልረግጥ ።
ወአብኒ ፡ ክልኦ ፡ ይቤ ።
ሌላውም ፡ አረጋዊ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
ዖበ ፡ እሰፊ ፡ አስፈሬዳ ።
እንቅብ ፡ ልሰፋ ፡ ብቀረብኁ ፡ ጊዜ ።
ወለለ ፡ ሎሱ ፡ ዐዲዎታ ፡ ስመስፈ ።
በወጋህ ፡ ቁጥር ።
አስተዳሉ ፡ ሞትየ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንትየ ።
ሞቴን ፡ ከፊቴ ፡ አዘጋጃለሁ ፡ አለ ።
እምቅድመ ፡ እግበር ፡ ዳግሚተ ።
ሁለተኛ ፡ ሳልወጋ ።
ወበአይኑኬ ፡ ሥርዓት ፡ ይነብር ፡ ዘክሮ ፡ ሞት ፡ ለገሡፉ ፡ ምስለ ፡ ስ
ብእ ።
ለሰው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሞትን ፡ መዘከር ፡ እንደ ፡ ምን ፡
ይሆንለታል ።
ይቤ ፡ መተርጕም ፤ በወብት ፡ እምድኅረ ፡ ገቢር ።
በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ የሚገኝ ፡ ጸጋ ፡ ነው ። አን
ድም ፡ ሥራ ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚ
ሰጥ ፡ ሀብት ፡ ነው ።
አበውኒ ፡ ይጸምዉ ፡ ቅድመ ።
አበው ፡ አስቀድመው ፡ በትሩፋት ፡ ይደክማሉ ።
ወያዴብሩ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ በእንተ ፡ ተዘክሮ ፡ ፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ።
ሰውነታቸውን ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመዘከር ፡
ያገብሩታል ።
በዘክሮ ፡ ሞት ፡ ለዓለም ፤ ወደይን ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ትኩን ፤ ወሥጋ
ይ ፡ ዘውስተ ፡ ገሃነም ።
ሞትን ፤ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያላት ፡ ፍዳን ፤ ሥቃየ ፡ ገሃ
ነምን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በማሰብ ።
ወሶቤሃኬ ፡ ይነሥኡ ፡ ረድኤተ ፡ ኃይል ፡ እምሀብተ ፡ ክርስቶስ ፡ እግ
ዚእነ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ በክርስቶስ ፡ ቸርነት ፡ ኃይል ፡ የሚሆና
ቸውን ፡ ረድኤት ፡ ያገኛሉ ።
በክመ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓዊ ፡ ማርቆስ ።
ንዕድና ፡ ያለው ፡ ማርቆስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ።
እስመ ፡ ፍርሃተ ፡ ገሃነም ።
ገሃነምን ፡ መፍራት ።
ወአፍቅሮተ ፡ ገነት ።
ገነትን ፡ መሻት ።
ይሁባ ፡ ለነፍስ ፡ ትዕግሦተ ፡ በውስተ ፡ ምንዳቤያት ።
ነፍስን ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ እንድትታገሥ ፡ ያደርጋታ
ል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለይተዋልና ።

«ቅኔ ፤ ይቤሎ ፣ እጉ ፣ ለአረጋዊ ፤ አንሰ ፣ ኢይክል ፣ እትዐቀብ ፣ እምሕሊና ፣ ዝሙት ፣ በልብየ ፤ ባሕቱ ፣ እመ ፣ ኢገበርኩ ፣ ምንት ፣ ያኅሥመኒ» ።

(ፍኖ) ወይቤ ፣ አረጋይ ፤ እመሰ ፣ ኮን ፣ መስተጋሥሣን ፣ በእንተ ፣ ንጽሐ ፣ ሥጋ ፣ ባሕቲቱ ።

ንጽሐ ፣ ሥጋን ፣ ብእ ፣ የምንሽ ፣ ብንሆን ።

እምኢኮነት ፣ ሕሊና ፣ ዝሙት ፣ ታኅሥመን ።

ዝሙትን ፣ ማሰብ ፣ በልገዳችን ፣ ነበር ።

ወበእመሰኬ ፣ ኮነ ፣ ንኅሥሥ ፣ ንጽሐ ፣ ልብ ፣ እንተ ፣ ባቲ ፣ ንፌእዮ ፣ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፣ የምናይበት ፣ ንጽሐ ፣ ልብን ፣ የምንሽ ፣ ከሆነ ፣ ግን ።

ድልወትኬ ፣ ክመ ፣ ናስተሐምም ፣ በእንተ ፣ ሰዲደ ፣ ሕሊናት ፣ ክዕበ ።

ሐልዮ ፣ ኅጢአትን ፣ ለማራቅ ፣ መፃር ፤ መከራ ፣ መቀበል ፣ ይገባናል ።

ተስእሎ ፣ ፪፬፪ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ እስመ ፣ መንፈቀ ፣ አበው ፣ አዘዙ ፣ ዖበ ፣ ተሀውክት ፣ ውስቴትን ፣ ሕማመ ፣ ዝሙት ።

እሶሴቶቹ ፣ አበው ፣ የገመሙት ፣ ያር ፣ በተነሣችብን ፣ ጊዜ ።

እምን ፣ ሰይጣናት ።

ሰይጣናት ፣ ባሳሰቡን ፣ ጊዜ ።

ንጸቢ ፣ በእንተ ፣ አብጥሎታ ።

ክፉ ፣ ሕሊናን ፣ ለማራቅ ፣ እንጸልይ ፣ ዘንድ ፣ አዘዋል ።

ወመንፈቆሙሰ ፣ አዘዙ ፣ ክመ ፣ ንትመዐዕ ፣ በቅድሜሁ ፣ በእንተ ፣ ሕሊናት ፣ ወንዘርክዮሙ ፣ ለሰይጣናት ።

እሶሴቶቹ ፣ ግን ፣ ዝሙት ፣ ስለ ፣ ታሰበችን ፣ አስቀድመን ፣ እንገሥጻቸው ፣ ዘንድ ፤ ሰይጣናትን ፣ ዕሩቃን ፣ ውዱቃን ፣ እንላቸው ፣ ዘንድ ፣ አዘዋል ።

ወዖቤሃ ፣ ንጸቢ ።

ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ጸልዩ ፣ ብለዋል ፤ አይለያዩምን ።

ወአሐዱኒ ፣ ይቤ ፤ ዖበ ፣ ተሐለየት ፣ ሕሊና ፣ ዝሙት ፣ ውስቴትክ ።

ከአበውም ፣ አንዱ ፤ ዝሙት ፣ ብትታሰብህ ።

አልዕል ፣ እንክ ፣ ሕሊናክ ፣ ፍጡን ፣ ኀበ ፣ እግዚአብሔር ።

ሕሊናህን ፣ ፈጥነህ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ስቀለው ።

ውስተ ፣ ጸሎት ።

በጸሎተ ፣ ልብ ፣ በተዘክሮ ።

ወኢትደነር ።

ከጸሎት ፤ አንድም ፣ ከመስቀል ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ አትበል ፣ አለ ።

ወአባ ፣ ወቅሪስኒ ፣ ይቤ ፤ ኢትጸሊ ፣ በቀዳሚሁ ፣ ለመክራክ

አባ ፣ ወቅሪስም ፤ ያር ፣ በተነሣብህ ፣ ጊዜ ፣ አስቀድመህ ፣ ጸሎት ፣ አትጅምር ።

እስኪ ፣ ትብል ፣ ነገረ ፣ መዓት ፣ ላዕለ ፣ ሰይጣናት ፣ ዘያወውቁክ ።

የሚዋጉህ ፣ ሰይጣናትን ፣ ዕሩቃን ፣ ውዱቃን ፣ ብለህ ፣ እስከ ፣ መገሠጽ ፣ ደርሰህ ።

እስመ ፣ ለእመሰ ፣ ኢተምዕዐት ፣ ነፍስክ ፣ ውስተ ፣ ሕሊናት ።

ነፍስህ ፣ በሐልዮ ፣ ኅጢአት ፣ ብትያዝ ።

ትክውን ፣ ጸሎትክ ፣ ዘኢንጽሕት ።

ጸሎትህ ፣ ከመበከን ፣ ያልዳንች ፣ ትሆናለች ።

ወበእንተ ፣ ተምዕያትክሰ ፣ ላዕለ ፣ ጸላዕት ።

ሰይጣናትን ፣ ዕሩቃን ፣ ውዱቃን ፣ ብለህ ፣ የተቈጣህ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ግን ።

ትመይጥ ፣ ሕሊናቲሆሙ ።

የሚያሳስቡህ ፣ ክፉ ፣ ሕሊናን ፣ ታጠፋለህና ።

ይቤ ፣ መቶርጕም ፤ እስመ ፣ አበው ፣ በክመ ፣ አምጣነ ፣ ሥርዓቱ ፣ ለእጉ ፣ ይሜህርዎ ።

አበው ፣ ለሰው ፣ ሁሉ ፣ እንደ ፣ ያር ፣ እንደ ፣ ያሩ ፣ ያስተምሩታል ።

ዘምሁርስ ፣ ውስተ ፣ ተቃትሎተ ፣ ሕሊናት ።

የሕሊናን ፣ ያር ፣ ለተማረ ።

ወያዘልፍ ፣ ጸሎተ ፣ ልባዊተ ።

ሁል ፣ ጊዜ ፣ የልቡና ፣ ጸሎትን ፣ ለሚጸልይ ፣ ሰው ።

ይደልዎ ፣ ክመ ፣ ይሚጥ ፣ ሕሊና ፣ ድኃስተ ፣ በጸሎት ፣ እምቀዳሚ ፣ ሁከታ ።

ክፉ ፣ ሕሊናን ፣ መጀመሪያ ፣ እንደ ፣ ታሰበች ፣ በጸሎት ፣ ያርቅ ፣ ዘንድ ፣ ይገባዋል ።

ወውጡኒሂ ፣ ዘኢበጽሐ ፣ ዓዲሁ ፣ ኀበ ፣ ጸሎት ፣ ልባዊት ፣ ዘለዓለማዊት ።

ከጸሎተ ፣ ልቡና ፣ ገና ፣ ያልደረሰ ፣ ወጣኒ ፣ የሆነ ፣ እደ ፣ ሆነ ፤ (ሐተታ) ፤ ጸሎተ ፣ ልብን ፣ ሁል ፣ ጊዜ ፣ የምትደረግ ፣ አላት ፤ ሀኬት ፣ የለባትምና ።

ይኄይሶ ፣ አቅድሞተ ፣ መዓት ፣ ወጽአስት ፣ ላዕለ ፣ ጸላዒ ።

አስቀድሞ ፣ ሰይጣንን ፣ ዕሩቅ ፣ ውዱቅ ፣ ብሎ ፣ መገሠጽ ።

ወዖቤሃ ፣ ይጸሊ ።

ከዚያ ፣ በኋላ ፣ መጸለይ ፣ ይገባዋል ።

ወጸሎተኒ ፣ ከመዝ ፣ ይበል ።

ጸሎቴንም ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ ይጸልይ ።

ኦ እግዚእን ፣ ብከ ፣ ናኅሥሮሙ ፣ ለፀርነ ።

ጌታችን ፣ ሆይ ፤ በንተ ፣ አምነን ፣ አጋንንትን ፣ እና ዋርዳቸዋለን ።

ወበኃይለ ፣ መስቀልክ ፣ ንክይደሙ ፣ ለጸላዕትን ።

በመስቀልህ ፣ ድል ፣ እንነሣቸዋለን ።

ወኢኮነ ፣ ትውክልትነ ፣ ላዕለ ፣ ኃይልነ ።

የምንታመን ፣ በጕልበታችን ፣ አይደለም ።

ወተበውሖትነ ፣ ውስተ ፣ መድኃኒትነ ።

የዳነውም ፣ በሥራችን ፣ በትሩፋታችን ፣ አይደለም ።

አላ ፣ አንተ ፣ ዘአድኀንከነ ።

አንተ ፣ አዳንኸን ፣ እንጂ ።

ወአስተኃፈርኮሙ ፣ ለሰይጣናት ፣ ዕድዋኒነ ።

ባለጋሮቻችን ፣ አጋንንትንም ፣ አሳፈርኻቸው ።

ወጸንከነ ።

መዊእን ፣ ሰጠኸን ።

ክመ ፣ ንሰብሕክ ፣ ወንግነይ ፣ ለክ ፣ በእንተ ፣ ኃይልክ ፣ ወመድኀኒትክ ።

ኃይልህን ፣ ስላደረግህልን ፣ እንገዛልህ ፣ ዘንድ ፤ ድኅነትህ ፣ ስለ ፣ ተደረገልን ፣ እናመሰግንህ ፣ ዘንድ ።

ተስእሎ ፣ ፪፬፫ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፤ እስመ ፣ ይቤ ፣ አረጋዊ ፤ እስመ ፣ ይቤ ፣ ጸላኒ ፣ ለእግዚእን ፤ አንሰ ፣ እፈኑ ፣ ዘሊተ ፣ ላዕለ ፣ እለ ፣ ዘለክ ።

ሰይጣን ፣ ጌታን ፣ የኔን ፣ ወገኖች ፣ አጋንንትን ፤ ባንተ ፣ ወገኖች ፣ ላይ ፣ አሠለጥናቸዋለሁ ።

ወኢይክልዎሙ ፣ እንክ ።

ነገር ፣ ግን ፣ የኔ ፣ ወገኖች ፣ ያንተን ፣ ወገኖች ፣ አይችሏቸውም ፤ ድል ፣ ይነሣሉ ።

ወለእመሰ ፣ ኢይክሉ ።

ምንም ፣ ባይችሏቸው ።

አንሰ ፣ በሕልመ ፣ ሌሊት ፣ አስሕቶሙ ።

እኔ ፣ በሕልመ ፣ ሌሊት ፣ አስታቸዋለሁ ።

ወይቤሎ ፣ እግዚእን ፤ ለእመሰ ፣ ኮን ፣ ድቀት ፣ ይወርስ ፣ አባው ።

ጌታም ፣ ሲመልስለት ፤ ጭንጋፍ ፣ አባቱን ፣ ይወርስ ፣ እንደ ፣ ሆነ ።

ዛቲኒ ፣ ትትሐሰብ ፣ ኀጢአተ ፣ ላዕለ ፣ እሊኣየ ።

ይህችም ፣ ሕልመ ፣ ሌሊት ፣ በኔ ፣ ወገኖች ፣ ዕዳ ፣ ሁና ፣ ትቈጠርባቸዋለች ፣ አለው ፣ አለ ። ሰይጣን ፣ እውነት ፣ ደፍሮ ፣ ጠይቆት ፣ ነውን ፤ ጌታስ ፣ ተዋርዶ ፣ መልሶለትን ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፣ መተርጕም ፤ ኢይቤ ፣ ሰይጣን ፣ ዘንተ ፣ ለእግዚእን ።

ሰይጣን ፣ ጌታን ፣ ደፍሮ ፣ አልጠየቀውም ።

ወኢያውሥኣ ፣ እግዚእነኒ ፣ ዘንተ ።

ጌታም ፣ ተዋርዶ ፣ አልመለሰለትም ።

ወባሕቱ ፣ ዝንቱ ፣ አረጋዊ ፣ ፈቀደ ፣ የአምረነ ፣ ፈቃዳቲሆሙ ፣ በዝንቱ ፣ ገጽ ።

እንዲህ ፣ በማለቱ ፣ አረጋዊ ፣ የሰይጣንን ፣ ፈቃድና ፣ የጌታን ፣ ፈቃድ ፣ ሊያስረዳን ፣ ወዶ ፣ ነው ፣ እንጂ ።

እስመ ፣ ለባሕቃዊ ፣ ሥራ ፣ በጀመረ ፣ ጊዜ ።

ይትቃተልዎ ፣ ሰይጣናት ፣ በመዓልት ፣ በሕሊናት ፣ እኩያት ።

ቀን ፣ ክፉ ፣ ሕሊና ፣ በማሳሰብ ።

ወበሌሊትኒ ፣ በአሕላማት ፣ ጎሠማት ።

ሌትም ፣ ክፉ ፣ ሕልም ፣ በማሳየት ፣ ይዋጉታልና ።

ወዶበ ፣ አንጽሐ ፣ ልቦ ፣ በውስተ ፣ ጸብኦ ።

የሕሊናን ፣ ያር ፣ ድል ፣ ነሥቶ ፣ ልቡናውን ፣ ንጹሕ ፣ ቢያደርግ ።

ወበርሀ ፣ ልቡ ፣ በብርሃነ ፣ ጸጋው ፣ ለክርስቶስ ።

በክርስቶስ ፣ ብርሃንነት ፤ በክርስቶስ ፣ ቸርነት ፣ ልቡናው ፣ ብሩህ ፣ ቢሆን ።

ዖቤሃ ፣ ይደልዎ ፣ ክመ ፣ ይትመጠ ፣ በመዓልትኒ ፣ ሕሊናተ ፣ ጎድአተ ፣ ወንጽሕተ ።

በመዓልት ፣ በጎ ፣ በጎ ፣ ሕሊና ፣ ያስብ ፣ ዘንድ ፣ ይሰጠዋል ።

ወበሌሊትኒ ፣ አሕላማተ ፣ ንጽሕተ ፣ ወጽሬተ ።

ሌትም ፣ በጎ ፣ በጎ ፣ ሕልም ፣ ያያል ።

በክመ ፣ ይቤ ፣ ወቅሪስ ፣ ጠቢብ ።

ወቅሪስ ፣ እንደ ፣ ተናገረ ።

ለእመ ፣ ፈቀድክ ፣ ታእምር ፣ ክመ ፣ አንተ ፣ ቀረብክ ፣ እምዝትዐደው ፣ ሕማማተ ።

ያሩን ፣ ድል ፣ ወደ ፣ መንግሥት ፣ እንደ ፣ ቀረብህ ፣ ልታውቅ ፣ ብትወድ ።

ለቡ ፣ እንክ ፣ ዘንተ ፣ በውስተ ፣ ሕሊናቲክ ፣ ዘመዓልት ።

ይህን ፣ ቀን ፣ በምታስበው ፣ ሕሊና ።

ወኢሕላማቲክኒ ፣ ዘውስተ ፣ ሌሊት ።

ሌት ፣ በምታየው ፣ ሕልም ፣ ዕወቀው ፣ እንዳለ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወዘውጡን ፣ እንክ ፣ ዘይመጽእ ፣ እምዓለም ።
ከዓለም ፡ ወደ ገዳም ፡ የሚመጣ ፡ ወጣኒ ።

ወኢይጸሙ ፡ ውስተ ፡ ኀቡሓ ።
በምንዅስና ፡ ሥራ ፡ የማይደክም ።

ወኢየኀሥሥ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ስርየተ ፡ አበሳቲሁ ፡ ዘቀዳሚ ።
በቀደመው ፡ ኀጢአቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይቅር ፡ በ
ለኝ ፡ የማይል ።

ወለዝንቱኒ ፡ አሕላማቲሁ ፡ መስቄርርት ።
የዚህ ፡ የምታጸይፍ ፡ ሕልም ።

ትትሐሰብ ፡ ሶቱ ፡ ኀጢአተ ።
ዕዳ ፡ ሁና ፡ ትቄጠርበታለች ።

ወዘምኀስው ፡ ማእከለ ፡ አኃው ።
ከአኃው ፡ መካከል ፡ ደካማ ፡ የሚሆን ።

ዘይትቄበል ፡ በመዓልት ፡ ስሕተታተ ፡ ፍትወት ፡ ውስተ ፡ ልቡ ።
በመዓልት ፡ ሐልዮ ፡ ኀጢአትን ፡ በልቡናው ፡ ወዶ ፡
የሚሰማማ ።

ወኢይክሥታ ።
ገልጾ ፡ የማይናገራት ።

ወለዝንቱ ፡ ሕሊናቲሁ ፡ ወአሕላማቲሁ ፡ ወፍትወቶቲሁ ፡ ርኩስት ፡ ት
ትሐሰብ ፡ ሶቱ ፡ ኀጢአተ ፡ ኅዕዐ ።
የዚህም ፡ ክፉ ፡ ሕሊናው ፤ የምታጸይፍ ፡ ሕሊናው ፤
የምታጸይፍ ፡ ሕልመ ፡ ዕዳ ፡ ሁና ፡ ትቄጠርበታለች ።

ወዘበ ፡ ይትጋደል ፡ ሕሊናተ ፡ እንተ ፡ የሀውክዋ ፡ ሰይጣናት ፡ ውስተ ፡
ልቡ ፡ በመዓልት ።
በልቡናው ፡ ሰይጣናት ፡ የሚያሳስቧትን ፡ ክፉ ፡ ሕሊ
ና ፡ በመዓልት ፡ የሚዋጋ ፡ ግን ።

ወለዝኒ ፡ አሕላማቲሁ ፡ መስቄርርት ፡ ዘበሐሊመ ፡ ስዕበት ፡ ኢትትሐሰ
ዝ ፡ ሶቱ ፡ ኀጢአት ።
የዚህ ፡ በተራክቦ ፡ ዘር ፡ በማፍሰስ ፡ የምትታየው ፡
መስቄርርት ፡ ሕልመ ፡ ዕዳ ፡ ተብላ ፡ አትቄጠርበት
ም ።

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ መሓሪ ፡ የአምር ፡ ዝመ ፡ ውእቱ ፡ በ
ጊዜ ፡ ፈቂደቱ ፡ ኢትሰፍጠ ፡ ለፍትወት ።
መሓሪ ፡ ጻድቅ ፡ የሚሆን ፡ ጌታ ፡ ወዶ ፡ ወደ ፡ ፈተ
ው ፡ እንዳልተሰበ ፡ ያውቃልና ።

አላ ፡ ተታተላ ፡ ወሰደጳ ።
ተዋግቶ ፡ አሸናፊት ፡ እንጂ ።

ወለእመኒ ፡ ወረደት ፡ ላዕሌሁ ፡ በጊዜ ፡ ንሞሙ ፡ ኢያሐስባ ፡ ላዕሌሁ ፡
ኀጢአተ ።
ተኝቶ ፡ አንቀላፍቶ ፡ ሳለም ፡ ዘሩ ፡ ቢወርድ ፡ ሰዳ ፡
አይልበትም ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢተቀበላ ፡ በፈቃዱ ።
ወዶ ፡ አልተስማማትምና ።

ወኢኮነ ፡ ክሣሌ ፡ ለተጋድሎታ ፡ ወሰዳይታ ፡ ወአርኅቆታ ።
ተዋግቶም ፡ ለማሸነፍ ፡ አልተቻለውምና ።

ወናሁ ፡ ይቤ ፡ አባ ፡ ኢሳይያስ ፤ ስእመ ፡ ወረደት ፡ ላዕሌክ ፡ በሌሊት
ሕልመ ፡ ጽምረት ፡ ኢትገክራ ፡ በመዓልት ።
ሌት ፡ በሕልም ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ የተገናኘሁ ፡ መስለሙ
ህ ፡ ዘሩ ፡ ቢወርድ ፡ በመዓልት ፡ አታስባት ።

ክመ ፡ ኢትትፈገፅ ፡ ባቲ ፡ በሕሊናከ ።
በክፉ ፡ ሕሊናህ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንዳታደርግ ።

ወኢትስሐት ፡ ላቲ ፡ እንከሰ ፡ በልብከ ።
በልብህ ፡ ወደ ፡ ፊቲው ፡ እንዳትሳብ ።

ወትስሕበከ ፡ ኀበ ፡ ገቢሮታ ፡ በሦሱ ።
ያለዚያ ፡ ግን ፡ በገቢርም ፡ በነቢብም ፡ ወደ ፡ መፈጸ
ም ፡ ታደርስሃለች ።

አላ ፡ ተኀሥእ ፡ ፍጡነ ።
ፈጥነህ ፡ ተነሣ ፡ እንጂ ።

ወግድፍ ፡ ነፍሰከ ፡ ቅድመ ፡ መስቀል ፡ ቅዱስ ።
መስቀል ፡ ተክለህ ፡ ስገድ ።

ወኀሥሥ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ምሕረተ ፡ ወመድኃኒቲተ ።
ይቅር ፡ በለኝ ፤ እርዳኝ ፤ አድነኝ ፡ እያልህ ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ ለምን ።

ወእግዚአብሔር ፡ በምሕረቱ ፡ ዘበእንተ ፡ ድካመ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡
ይረድአክ ።
ጌታም ፡ በቸርነቱ ፡ የባሕርይን ፡ ድካም ፡ ስላወቀ ፡
ይረዳሃል ፤ ያድንሃል ።

ወብሂሎቱ ፡ በክመ ፡ ይቀትል ፡ ኢይወርስ ፡ ወላዲሁ ።
ሣጥንጋፍ ፡ አባቱን ፡ እንዳይወርስ ፡ ማለትም ፡ ይኸ
ነው ።

ዘውእቱ ፡ በእንተ ፡ ክዊናቱ ፡ ዘኢፍጹም ፡ ሕይወቱ ።
ተሥዕሶተ ፡ መልክዕ ፡ ያልተፈጸመለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
ነው ።

ወዘይትረከብ ፡ በአምሳሊሁኒ ፡ ኢይወርስ ፡ እንክ ።
ዘሩን ፡ መስሎ ፡ የሚገኝ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ በል ፤ አ
ባቱን ፡ መስሎ ፡ የማይገኝ ፡ ሣጥንጋፍ ፡ የማይወርስ ፡
ከሆነ ።

ወከማሁ ፡ ስዕበተ ፡ ሕልምኒ ፡ ዘኢፍጽምት ።
በገቢር ፡ ያልተፈጸመች ፡ ሕልመ ፡ ሌሊትም ፡ እንደ
ዚህ ፡ ናት ።

እስመ ፡ ይእቲ ፡ ኢተፈጸመት ፡ በፈቃዲ ።

በገቢር ፡ አልተፈጸመችምና ፡ ዕዳ ፡ ተብላ ፡ አትቄጠ
ርም ።

ተስእሎ ፡ ፱፴፬ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ እጐ ፡ ይቤሎ ፡ ለአባ ፡ ጴሜን ፤ ምንተ ፡
እግበር ፡ ኦ አባ ።
አንድ ፡ መነኩሴ ፡ አባ ፡ ጴሜንን ፡ አባቴ ፡ ምን ፡ ላ
ድርግ ፤ እንደ ፡ ምን ፡ ላድርግ ።

እስመ ፡ ትትነሣእ ፡ ላዕሌየ ፡ ሕሊና ፡ ዝሙት ።
የዝሙት ፡ ያር ፡ በሕሊናዬ ፡ ትዋጋኛለችና ፡ አለው ።

ወይቤሎ ፤ በጊዜ ፡ ቀዳሚት ፡ ጕየይ ።
በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ሽሽ ።

ወበዳግሚትኒ ፡ ጕየይ ።
በሁለተኛውም ፡ ሽሽ ።

ወበሣልሲትኒ ፡ ተንሥእ ፡ ለተዓርኮታ ።
በሦስተኛው ፡ ግን ፡ ተነሥተህ ፡ ተዋጋ ።

ክመ ፡ ሰይፍ ፡ በሊኅ ።
ፈጥነህ ።

ይቤ ፡ መቱርጉም ፤ ዘውእቱ ፡ ለእመ ፡ ሐወጸተከ ፡ ጸጋ ።
እንዲህ ፡ ማለት ፤ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብትሰጥህ ።

አው ፡ ኮንከ ፡ ውስተ ፡ ፍሥሓ ፡ ዘበእንተ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚእነ ።
ጌታን ፡ ስለ ፡ ወደድህ ፡ ደስ ፡ እያለህ ፡ በተባሕትዎ ፡
በተዘክሮ ፡ ብትኖር ።

አው ፡ በጽሒቅ ፡ ኀበ ፡ ኀፈት ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ።
መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ለመዘከር ። አንድም ፤ በጽ
ሒቅ ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በመዘከር ፡ ብትኖር ።

አው ፡ ለተናስሖ ፡ በእንተ ፡ ኀጣይኢክ ፡ ወሐሚም ፡ በእንቲኣሃ ።
ስለ ፡ ኀጢአትህ ፡ ንስሓ ፡ ለመግባት ፡ ኀጢአትህን ፡
አስበህ ፡ ለማዘን ፡ ለማልቀስ ። አንድም ፡ በሐዘን ፡
በልቅሶ ፡ ብትኖር ።

ወየሀውክ ፡ ውስቴትክ ፡ ሰይጣን ፡ ዝሙት ፡ ሕሊናተ ፡ ሕስምተ ፡ በመ
ንፈቀ ፡ ዛቲ ፡ ጊዜያት ።
እንዲህ ፡ ሁነህ ፡ ሳለህ ፡ ሰይጣን ፡ ዝሙት ፡ አንዳን
ድ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ሕሊና ፡ ቢያሳስብህ ።

ኢታዕርፅ ፡ ነፍሰከ ፡ እምዛቲ ፡ ግብራት ።
ልብህን ፡ ከዚህ ፡ ከተዘክሮ ፡ አትለይ ።

ለተቃትሎ ፡ ምስሌሁ ።
ከሱ ፡ ጋራ ፡ እዋጋለሁ ፡ ብለህ ።

አላ ፡ ተመየጥ ፡ በልብከ ፡ እምኔሁ ፡ ወእስተሐምም ፡ በእንተ ፡ ረባሕ
ክ ።
በልብህ ፡ ከያሩ ፡ ተመልሰህ ፡ የሚረባህን ፡ ተዘክሮ
ዉን ፡ ያዝ ፡ እንጂ ፤ ኢታዕርዕ ።

ወዝኬ ፡ ውእቱ ፡ ትርጓሜ ፡ ቃሉ ፡ ጕየይ ፡ በጊዜ ፡ ቀዳሚ ።
በጊዜ ፡ ቀዳሚ ፡ ጕየይ ፡ ያለው ፡ ትርጓሜው ፡ ይህ ፡
ነው ።

ወለእመ ፡ ሆክ ፡ ውስቴትክ ፡ ካዕበ ፡ ሕሊና ፡ ሕሙመ ።
ደግሞ ፡ ሁለተኛ ፡ ክፉ ፡ ሕሊና ፡ ቢያሳስብህ ።

ወግበር ፡ ከማሁመ ፡ ካዕበ ።
እንደዚሁ ፡ አድርግ ፤ ማለት ፡ ተዘክሮውን ፡ አትተ
ው ።

ወዘተ ፡ ይእቲ ፡ ጊዜ ፡ ዳግሚት ።
ወበዳግሚት ፡ ጕየይ ፡ ያለውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ወለእመ ፡ ቄረት ፡ ሕሊናከ ።
ከያሩ ፡ የተነሣ ፡ ሕሊናህ ፡ ቢበርድ ።

ወተመስወት ፡ እምእንታክቲ ፡ ግብራት ።
ሰውነትህ ፡ ቢደክም ።

ወኢበጠስት ፡ ተህውኮተ ፡ ሕሊናት ፡ ሕስምት ።
ሐልዮ ፡ ኀጢአት ፡ ባይጠፋልህ ።

ቁም ፡ እንክሰ ፡ ለተዓርኮታ ።
ተነሥተህ ፡ ተዋጋ ።

ወስግድ ፡ ቅድመ ፡ መስቀል ፡ ቅዱስ ።
መስቀል ፡ ተክለህ ፡ ስገድ ።

ወጕዳፅ ፡ ርእስክ ።
ራስህን ፡ ተምትመው ፤ መክነ ፡ አእምሮ ፡ ነውና ።

ምስለ ፡ ትምዕዕት ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
በጌታ ፡ ፊት ፡ ኀጥአ ፡ አባሲ ፡ ብለህ ፡ ራስህን ። አን
ድም ፡ ዕሩቅ ፡ ውዱቅ ፡ ብለህ ፡ ሰይጣንን ፡ ከመገሠ
ጽ ፡ ጋራ ።

ወሐስ ፡ ነፍስክ ።
ሰውነትህን ፡ አነሳሣው ። አንድም ፤ ጎስ ፡ ይላል ፤ ን
ቀፈው ።

ዘምስለ ፡ ኀሠሣ ።
ረድኤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመሻት ፡ ጋራ ።

በገኅር ፡ ወአንብዕ ፡ ወበቆቃው ።
እያዘንህ ፡ እያለቀስህ ።

ወዘምር ፡ መዝሙረ ፡ በአእምሮ ፡ ወበልባዌ ።
ኃይለ ፡ ቃሉን ፡ እያስተዋልህ ፤ ትርጓሜውን ፡ ምሥ
ጢሩን ፡ እየ ፡ መረመርህ ፡ ዳዊት ፡ ድገም ።

www.ethiopianorthodox.org

ወጎረይ ፣ እምኔሃ ፣ መዝሙረ ፣ መጽንዒ ፣ ወመድኃኔ ።
ከዚያውም ፣ ውሥጥ ፣ የሚያጸናውን ፤ የሚያድነውን ፣ ለይተህ ፣ ለይተህ ፣ ድግም ።

ዘከመ ፣ እግዚአብሔር ፣ ያበርህ ፣ ሊተ ፣ ወያድኅንረ ፣ ምንትኑ ፣ ያፈርሀኒ ።
እንደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ያበርህ ፣ ሊተ ፣ ያለውን ፤ እግዚአብሔር ፣ ያበርህ ፣ ሊተ ፣ ያለውን ። እንዲህ ፣ እያልህ ፣ ሂድ ።

ወኀቤከ ፣ እግዚኦ ፣ እንቃዕደኩ ፣ ነፍስየ ፣ አምላኪየ ። ወኢያክ ፣ ተወክልኩ ፣ ወኢይትኀፈር ፣ ለዓለም ።
እንደ ፣ ኀቤከ ፣ ያለውን ፤ ኀቤከን ።

ወእግዚኦ ፣ ነጽር ፣ ውስተ ፣ ረዲኦትየ ።
እንደ ፣ እግዚኦ ፣ ነጽር ፣ ያለውን ፤ እግዚኦ ፣ ነጽርን ።

ወዘይመስል ፣ ዝክተ ።
ይህን ፣ የመሰለውን ።

ወዘከመ ፣ እስከ ፣ ማዕዜኑ ፣ እግዚኦ ፣ ትረስዐኒ ፣ ለግሙራ ።
እንደ ፣ እስከ ፣ ማዕዜኑ ፣ ያለውን ፤ እስከ ፣ ማዕዜኑን ።

ወይትነሣእ ፣ እግዚአብሔር ፣ ወይዘረዉ ፣ ፀሩ ።
እንደ ፣ ይትነሣእ ፣ ያለውን ፤ ይትነሣእን ።

ወእግዚኦ ፣ በመዓትከ ፣ ኢትቅሥፈኒ ።
እንደ ፣ እግዚኦ ፣ በመዓትከ ፣ ያለውን ፤ እግዚኦ ፣ በመዓትከን ።

ወዘይመስል ፣ ዝክተ ፣ አንብቦሙ ፣ በልባቁ ።
ይህን ፣ የመሰለውን ፣ ሁሉ ፣ አስተውለህ ፣ መርምረህ ፣ ድግም ።

ወበውዕየተ ፣ ነፍስ ።
በልቡናህ ፣ እየ ፣ ተናደድህ ።

እስመ ፣ ትመውኦ ፣ እንክ ፣ እኅተሰ ፣ ለሰይጣን ።
እንደዚህ ፣ ያደረግህ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ድል ፣ ትነሣለህ ።

ወታጠፉ ፣ ጸጋ ፣ ንጽሕና ።
ረድኤትን ፣ መዊእን ፣ ገንዘብ ፣ ታደርጋለህ ።

ወያበርህ ፣ ለክ ፣ ብርሃን ፣ ቅዱስ ፣ ውስተ ፣ ልብክ ።
ንጽሐ ፣ ልቡና ፣ ይሰጥሃል ፤ ዕውቀት ፣ ይገለጽልሃል ።

ወትትረግሕ ፣ በክርስቶስ ፣ ተስፋክ ፣ ሎቱ ፣ ስብሓት ፣ እስክ ፣ ለዓለመ ፣ ዓለም ፣ አሜን ።
ፍቅሩን ፣ አግኝተህ ፣ በክርስቶስ ፣ ደስ ፣ ይልሃል ።

ክፍል ፣ ዓሠርቱ ፣ ወአሐዱ ።

በእንተ ፣ ንስሓ ።
የንስሓን ፣ ነገር ፣ የሚናገር ፣ ክፍል ፣ ይህ ፣ ነው ።

ተስእሎ ፣ ፪፬ ።

ይቤሎ ፣ አኃው ፤ እስመ ፣ ክልኤቱ ፣ አኃው ፣ ገብኡ ፣ ውስተ ፣ ዓለሰ ፣ ወአውሰቡ ።
ሁለት ፣ መነኰሳት ፣ ወደ ፣ ዓለም ፣ ተመልሰው ፣ ሚስት ፣ አገቡ ። አንድም ፣ ዓለማዊ ፣ ሥራ ፣ ሠሩ ።

ወእምድኅረ ፣ ውእቱ ፣ ተናስሑ ።
ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ተመልሰው ።

ወነስሑ ።
ንስሓ ፣ ገቡ ።

ወሶበ ፣ ፈጸሙ ፣ ቀኖና ፣ ንስሓሆሙ ፣ ወወፅኡ ፣ እምነ ፣ ተዘግሖቶሙ ።
የተቀበሉትን ፣ ቀኖናቸውን ፣ በፈጸሙ ፣ ጊዜ ፣ ከዘጉበት ፣ ወጡ ፤ በወጡ ፣ ጊዜ ።

ኮነ ፣ ለአሐዱ ፣ ገጹ ፣ ድሙን ።
ያንዱ ፣ ፊቱ ፣ ጠቁሮ ።

ወሕብሩኒ ፣ ጽምፁየ ።
መልኩ ፣ ጸውልኅ ፣ ወጣ ።

ወካልኡኒ ፣ ፍሡሐ ።
አንዱ ፣ ደስ ፣ ብሎት ።

ወራእዩኒ ፣ ሠናየ ።
መልኩ ፣ ብሩህ ፣ ሁኖ ፣ ወጣ ።

እስመ ፣ ቀዳማዊ ፣ ኮነ ፣ ይዜክር ፣ ኀጣይኢሁ ፣ ወውስተ ፣ እላተ ፣ ገሃነም ።
የኋላ ፣ ሰዎች ፣ እንዲህ ፣ ይላሉ ፤ የመጀመሪያው ፣ አንዱ ፣ ኀጢአቱን ፣ አስቦ ፣ ገሃነምን ፣ ይፈራ ፣ ነበርና ፣ አዝኖ ፣ ጠቁሮ ፣ ወጣ ።

ወካልኡሂ ፣ ኮነ ፣ ይዜክር ፣ ውስተ ፣ ምሕረተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ወይቤፍ ፣ ግህሎ ።
ሁለተኛው ፣ ግን ፣ የጌታን ፣ መሐሪነቱን ፣ አስቦ ፣ ይቅርታዉን ፣ ተስፋ ፣ ያደርግ ፣ ነበርና ፣ ፊቱን ፣ ደስ ፣ ብሎት ፣ ወጣ ።

ወአበውኢ ፣ ይቤሉ ፤ እስመ ፣ ንስሓሆሙ ፣ ዕፍያን ፣ በኀበ ፣ እግዚአብሔር ።

አበውም ፣ ንስሓቸው ፣ በጌታ ፣ ዘንድ ፣ ትክክል ፣ ነው ፣ አሉ ። አንዱ ፣ ብሩህ ፣ መሆኑ ፤ አንዱ ፣ መጥቁሩ ፣ ስለ ፣ ምን ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፣ መተርጕም ፤ በከመ ፣ ለእሳት ፣ ባቲ ፣ ዘዚእሃ ፣ ክልኤ ፣ ግብር ።
ለእሳት ፣ ገንዘቧ ፣ የሚሆን ፣ ሁለት ፣ ጳብር ፣ እንዳላት ።

ዋዕይ ፣ ወብርሃን ።
አንዱ ፣ መተኰስ ፤ አንዱ ፣ መብራት ፣ ነው ።

ዋዕይሰ ፣ ይደሉ ፣ ለሰንኒኒ ።
ዋዕይ ፣ የሰነኔ ፣ ምሳሌ ፣ ለመሆን ። አንድም ፣ ሰነኔ ፣ ለመሆን ፣ የሚገባ ፣ ነው ።

ወብርሃን ፣ ይደሉ ፣ ለዕረፍት ።
ብርሃንም ፣ የዕረፍት ፣ ምሳሌ ፣ ለመሆን ። አንድም ፣ ዕረፍት ፣ ለመሆን ፣ የሚገባ ፣ ነው ።

ከማሁኬ ፣ ለንስሓኒ ፣ ባቲ ፣ ክልኤ ፣ ኃይላት ።
ለንስሓም ፣ ሁለት ፣ ጳብር ፣ አሳት ።

ወትትፈጸም ፣ ዘበፍርሃት ፣ ወአፍቅሮት ።
በፈሪሀ ፣ እግዚአብሔርና ፣ በፍቅረ ፣ እግዚአብሔር ፣ ትፈጸማለች ።

ወተዘክሮተ ፣ ፈሪሀ ፣ እግዚአብሔርሰ ፣ ያቴክዝ ።
ፈሪሀ ፣ እግዚአብሔርን ፣ መዘከር ፣ ያሳዝናል ።

ወተዘክሮተ ፣ ተስፋ ፣ ፍቅሩኒ ፣ ያስተፈሥሕ ።
ፍቅሩን ፣ ተስፋ ፣ አድርጎ ፣ መዘከር ፣ ደስ ፣ ያሰኛል ።

ወናሁ ፣ ይቤ ፣ እባ ፣ ወቅሪስ ፣ ግብር ፣ ምስለ ፣ እግዚአብሔር ፣ በእንተ ፣ ፍቅር ።
ወቅሪስም ፣ የፍቅርን ፣ ነገር ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ብለህ ፣ ሥራው ፣ አለ ።

ዘበበይን ፣ አብ ፣ ኀር ፣ ውእቱ ።
አብ ፣ ኄር ፣ ስለ ፣ ሆነ ። ኄር ፣ ነው ፣ ብለህ ፤ ኄር ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ዐውቀህ ።

ወበእንተ ፣ ፍርሃትኒ ፣ እስመ ፣ ውእቱ ፣ ደያኔ ፣ ጽድቅ ።
የፍርሃትንም ፣ ነገር ፣ ኩናኒ ፣ በጽድቅ ፤ ፈታሒ ፣ በርትዕ ፣ ነው ፣ ብለህ ፤ እንደ ፣ ሆነ ፣ ዐውቀህ ፣ አድርገው ።

ተስእሎ ፣ ፪፭ ።

ይቤሉ ፣ አኃው ፣ በእንተ ፣ ምንትኑ ፣ ዘይትይይ ፣ እምኀጢአት ።
በንስሓ ፣ ከኀጢአት ፤ በምናኔ ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ የሚለይ ።

ወይወፅእ ፣ እምዓለም ፣ ወይመጽእ ፣ ውስተ ፣ ሥርዓተ ፣ ምንኵስና ።
ከዓለም ፣ ወጥቶ ፣ የምንኵስና ፣ ሥራ ፣ ወደሚሠራበት ፣ ወደ ፣ ገዳም ፣ የሚመጣ ።

ይደመሮ ፣ ትፍሥሕት ።
ደስ ፣ የሚለው ።

ወዕረፍተ ፣ ትዕግሥት ።
ትዕግሥት ፣ የሚሰጠው ።

ወባሕታዊሰ ፣ ዘይድኅዕ ፣ ወይወድቅ ፣ ውስተ ፣ ኀጢአት ።
ከመነኑ ፣ በኋላ ፣ በኀጢአት ፣ የሚሰነካከል ።

ወይፈቅድ ፣ ክመ ፣ ይነስሕ ።
ንስሓ ፣ ሊገባ ፣ የሚወድ ፣ በሕታዊ ፣ ግን ።

የኀዝን ፣ ወይደበደብ ።
ይህ ፣ የሚያዝን ፣ ስለ ፣ ምን ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፣ መተርጕም ፤ እስመ ፣ ዐኣት ፣ እምዓለም ፣ ዘበእንተ ፣ እግዚአብሔር ።
ስለ ፣ እግዚአብሔር ፣ ብሎ ፣ በምናኔ ፣ ከዓለም ፣ መውጣት ።

ኢይክውን ፣ ዘእንበለ ፣ ምስለ ፣ ጸጋ ፣ እግዚአብሔር ።
በእግዚአብሔር ፣ ቸርነት ፣ ቢሆን ፣ ነው ፣ እንጂ ፤ ያለ ዚያ ፣ አይደረግም ።

በከመ ፣ ለዘይጠመቅ ፣ ይደመሮ ፣ ትፍሥሕተ ፣ ጸጋ ።
አምኖ ፣ የሚጠመቅ ፣ ሰው ፣ በጸጋ ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ሀብተ ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስን ፣ አግኝቶ ፣ ደስ ፣ እንዲለው ። (ግብኟ ፣ ፴፯—፴፯) ።

ወኢይዜክር ፣ ኀጣውኢሁ ፣ ዘቀዳሚ ።
የቀደመውን ፣ ኀጢአቱን ፣ ያስፈርድብኛል ፣ ብሎ ፣ እንዳያስበው ።

ለእመ ፣ ገብአሰ ፣ ወአበሰ ።
ካመነ ፣ ከተጠመቀ ፣ በኋላ ፣ ቢበድል ፣ ግን ።

ወንስሐ ፣ ካዕበ ።
ወደ ፣ ንስሓ ፣ ቢመለስ ።

ይኔስሕ ፣ ምስለ ፣ ኀዘን ፣ በእንተ ፣ ተኀጥኦታ ፣ ለእንትኩ ፣ ጸጋ ።
ጸጋዉን ፣ ስላጣት ፣ እያዘነ ፣ ንስሓ ፣ እንዲገባ ።

ከማሁኬ ፣ ለዘይወፅእ ፣ እምዓለም ፣ በእንተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ትዴመሮ ፣ ዋዕይ ፣ ቅድስት ።
በምናኔ ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ የሚወጣ ፣ ሰውም ፣ በፍቅረ ፣ እግዚአብሔር ፣ መናደድ ፣ ትሰጠዋለች ።

ወኢይዜክር ፣ ኀጣውኢሁ ፣ ቀዳሚት ፣ ዘውስተ ፣ ዓለም ።
በዓለም ፣ ሳለ ፣ ቀድሞ ፣ የሠረውን ፣ ኀጢአት ፣ ያስፈርድብኛል ፣ ብሎ ፣ አያስበውም ።

www.ethiopianorthodox.org

ወለእመሰ ፡ ተባሕትወ ፡ ወወድቀ ፡ ውስተ ፡ ጎጠኣት ።
ተባሕትዎ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በጎጠኢት ፡ ቢሰነካከል ።

ወእምድኅረ ፡ ውኅቱ ፡ ካዕበ ፡ ነስሐ ።
ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንስሓ ፡ ቢመለስ ።

እስመ ፡ ይኄስሕ ፡ ውኅቱ ፡ ዘበጎዘን ።
እያዘነ ፡ ንስሓ ፡ ይገባል ።

ወውኅቱኬ ፡ ሥርዓተ ፡ እግዚአብሔር ።
ይኸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘበት ፡ አዘለት ፡ ነው ።

ከመ ፡ ኢይግባእ ፡ ይደቅ ፡ ዘበተክህኖቱ ።
በአእምሮው ፡ እየ ፡ ወደደ ፡ ይሰነካከል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጎጠኢት ፡ እንዳይመለስ ፡ አዘበት ፡ ነው ።

ወኢይጸራኦ ፡ እምገድሉ ፡ ዘበእንተ ፡ ፍናዊ ፡ ትርፍት ።
ትሩፋት ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ከመጋደል ፡ እንዳይለይ፡ አዘለት ፡ ነው ።

ወባሕታውያን ፡ ይብሉ ፤ እስመ ፡ ዘይድኅፅ ፡ ወይወድቅ ፡ ወይትነሣእ ፡ ለንስሓ ፡ ፍጡን ።
በጎጠኢት ፡ የሚሰነካከል ፤ ፈጥኖ ፡ በንስሓ ፡ የሚመለስ ።

እስመ ፡ ውኅቱ ፡ ይክውን ፡ ፍጹመ ፡ በእንተ ፡ አእምሮ ፡ ወሥርዓት ።
በዕውቀት ፡ በሥርዓት ። አንድም ፡ አናበ ፤ ሥርዓት፡ በማወቅ ፡ ፍጹም ፡ ይሆናል ።

ፈድፋደ ፡ እምን ፡ ዘወጠነ ፡ ውስተ ፡ ገቢረ ፡ ትርፍት ፡ ብሕትውና ።
የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ከጀመረ ፡ ከወጣኂው ፡ ይልቅ ።

እስመ ፡ ቀዳሚሁ ፡ ይመስል ፡ ዘሐነጸ ቤተ ፡ ወያፈርስ ።
ቀዳማዊ ፡ ለጽሕፈት ፡ ነው ፤ በንስሓ ፡ የተመለሰው ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ የፈረሰበት ።

አው ፡ ተሠውጠ ፡ ውስተ ፡ ሐመር ፡ ወተሠጥመ ።
መርከብ ፡ ጭኖ ፡ የሰጠመበትን ፡ ይመስላል ።

እስ ፡ ውኅቱ ፡ ለእመ ፡ ገብአ ፡ ለሐኒጽ ፤ አው ፡ ለንጊድ ።
ተሠልሺ ፡ ቤት ፡ እሠራለሁ ፤ መርከብ ፡ እጭናለሁ ፡ ቢል ።

እስመ ፡ ውኅቱ ፡ የአምር ፡ ግብሬተ ፡ ፍርሰት ፡ ወሥጥመት ።
የሚፈርሰብትን ፡ የሚሰጥምበትን ፡ ያውቃል ።

ወይትዐቀብ ፡ ኅምነሃ ።
ከመፍረሱ ፤ ከመስጠሙ ፡ ይጠበቃል ።

ወየሐንጽ ፡ ዘይኄይሰ ፡ እምቀዳሚ ፡ ሕንጻ ።
ከቀድሞ ፡ የሚበረጥ ፡ ግለት ፤ ይህ ፡ ጠሮ ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ከሌላ ፡ በታ ፡ ይሠራል ። ይህ ፡ ባሕር ፡ ሾተላይ ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ከሌላ ፡ በኩል ፡ ይጭናል ።

ወካልኣዊኒ ፡ ይመስል ፡ ዘወጠነ ፡ ሐኒጸ ወንግደተ ።
ወጣሂው ፡ ቤት ፡ መሥራት ፤ መርከብ ፡ መጫን ፡ የጀመረን ፡ ይመስላል ።

ወይክውን ፡ ዘኢየአምር ፡ ግብራተ ፡ ፍርሰት ፡ ወሥጥመት ።
የሚፈርስበትን ፤ የሚሰጥምበትን ፡ ጓብር ፡ የማያውቅ ፡ ይመስላል ።

ወበእንተዝ ፡ ይደልዎ ፡ ክመ ፡ ትደመሮ ፡ ረድኤት ።
ለዚህ ፡ ረድኤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትሰጠዋለች ።

ወምግባር ።
ትሩፋት ፡ ይሠራል ።

ክመ ፡ ያቅልል ፡ እምኔሁ ፡ ክበዳተ ።
ያሩን ፡ ያቀልለት ፤ መከራውን ፡ ያርቅለት ፡ ዘንድ ።

ተስእሎ ፡ ፲፬፤ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ እጎ ፡ ይቤ ፡ ለአባ ፡ ሲሶይ ።
አንድ ፡ መነኮሴ ፡ አባ ፡ ሲሶይን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።

ምንተ ፡ እገብር ፡ ኦ አቡየ ፡ እስመ ፡ ወደቁ ፡ እን ።
አባቴ ፡ በጎጠኢት ፡ ተሰነካክያለሁና ፡ ምን ፡ ላድርግ፤ እንደ ፡ ምን ፡ ላድርግ ።

ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ።
ንስሓ ፡ ግባ ፡ አለው ።

ወይቤሎ ፡ ምዕራተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወደቁ ፡ ወተንሣእኩ ።
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተሰነካከልኁ ፡ በንስሓ ፡ ተመለስሁ።

ወእስከ ፡ ማእዜኑ ፡ እወድቅ ፡ ወእትነሣእ ።
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ስወድቅ ፡ ስነሣ ፡ እኖራለሁ ።

ወይቤሎ ፤ እስክ ፡ ትበድር ።
እስክትሞት ፡ ድረስ ። አንድም ፡ ሞትን ፡ በንስሓ ። አንድም ፡ ጎጠኢትን ፡ በንስሓ ። አንድም ፡ በሞት ፡ እስክትቀድም ፡ ድረስ ።

እመ ፡ አኮ ፡ ውስተ ፡ ተንሥኦ ።
በንስሓም ፡ ሳለህ ፡ ቢሆን ።

አው ፡ ውስተ ፡ ወዳቅ ።
በጎጠኢትም ፡ ሳለህ ፡ ቢሆን ፤ እስክ ፡ ትበድር ፤ እስክትቀድም ፡ ድረስ ።

እስመ ፡ ምግባር ፡ ዘውስቴቱ ፡ ብእሲ ፡ የሐውር ፡ ቦቱ ።
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ባለበት ፡ ባለበት ፡ ግብር ፡ ይሄዳልና ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ውኅቱ ፡ ይኤምር ፡ ኀበ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘበልዓን ፡ ሕዝቅኤል ።

ይኸ ፡ ነገር ፡ ጌታ ፡ በሕዝቅኤል ፡ አድሮ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ።

እስመ ፡ በዕለት ፡ ዘይትመየጥ ፡ ባቲ ፡ ጻድቅ ፡ እምጽድቁ ፡ ወይገብር ፡ አበሳ ።
ደግ ፡ ሰው ፡ ክበጎ ፡ ሥራው ፡ በሚመለስበት ፤ ጎጠኢት ፡ በሚሠራበት ፡ ቀን ፡ ቢሞት ።

ኢይዜክር ፡ ሎቱ ፡ ጽድቆ ።
የቀድሞ ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡ አላስብለትም ።

አላ ፡ ይመውት ፡ በጎጣውኢሁ ።
ኋላ ፡ በሠራው ፡ ጎጢኢት ፡ ይሞታል ፡ እንጂ ።

ወክግሣሁ ፡ ለእመ ፡ ተመይጠ ፡ ጎጥእኒ ፡ እምአበሳሁ ፤ ወገብረ ፡ ጽድቀ ።
ጎጥእም ፡ ከጎጢኢቱ ፡ ተመልሶ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ቢሠራ ።

ኢይዜክር ፡ አበሳሁ ።
የቀድሞ ፡ ጎጢኢቱን ፡ አላስብበትም ።

አላ ፡ ይመውት ፡ በጽድቁ ።
አላ ፡ የሐዩ ፡ በጽድቁ ፡ ወኢይመውት ፡ ብለህ ፡ አቅና ፤ እናተ ፡ አላ ፡ ይመውት ፡ አይልም ። ኋላ ፡ በሠራው ፡ ጽድቅ ፡ ይድናል ፡ እንጂ ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ አይሞትም ፡ ያለውን ፡ ይመስላል ። (ሕዝ፴፫ ፡ ፲፪—፲፮) ።

ወበእንተዝኬ ፡ ይደሉ ፡ ክመ ፡ ንትዐቀብ ፡ በእንተ ፡ አስተፋጥኖ ፡ ንስሓ ፡ ማእዜኒ ፡ እመ ፡ ወደቅን ።
ሰው ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ ግብሩ ፡ የሚሄድ ፡ ስለ ፡ ሆነ፡ መቼም ፡ መች ፡ በጎጢኢት ፡ በተሰነካከልን ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ ለመመለስ ፡ ንስሓ ፡ ለመግባት ፡ ዝግጁ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ።

ክመ ፡ ኢይርክበን ፡ ሞት ፡ ዘበወዲቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ንስሓ ።
በጎጢኢት ፡ ሳለን ፤ ንስሓ ፡ ሳንገባ ፡ ሞት ፡ እንዳያገኝን ።

ንወፅኦ ፡ እምዓለም ።
ያለዚያ ፡ ግን ፡ በሞት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንለያለን ።

ወንትወሀብ ፡ እንከ ፡ ለሥቃይ ።
ሥቃየ ፡ ገሃነም ፡ ይፈረድብናል ።

ተስእሎ ፡ ፲፬፯ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ ወዝንቱሰ ፡ ያግጎድ ፡ እንከ ፡ ተፃርሮተ ፡ ለቃለ ፡ አባ ፡ ማርቆስ ።
ይኸስ ፡ ከአባ ፡ ማርቆስ ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ የተለያየ ፡ ይመስላል ፤ ልዩ ፡ ነው ።

እስመ ፡ በጊዜ ፡ ወእትን ፡ እምኀለም ።
በሞት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በተለየን ፡ ጊዜ ።

ይደሉ ፡ ረባሕን ፡ ምስለ ፡ ጎጕልን ።
ያለማነው ፡ ከጠፋነው ፡ ጋራ ፡ በፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመዘናል ።

ወንደየን ።
ያለማነው ፡ በልጠ ፡ ቢገኝ ፡ ይፈረድልናል ። ያጠፋነው ፡ በልጠ ፡ ቢገኝ ፡ ይፈረድብናል ፡ ከለው ፡ ጋራ ፡ ይለያያል ፡ አሉት ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፤ እኮ ፡ ማእክሌሆሙ ፡ ተፃርሮት ።
መለያየት ፡ የለባቸውም ።

እስመ ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ አመረ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ የጎጕሉ ፡ ወይብሉ ፤ ንሕነሰ ፡ መስተጋድላን ፡ ወይረብሑ ።
አባ ፡ ማርቆስ ፡ ትሩፋት ፡ ሠርተናል ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ አግኝተን ፡ ተጠቅመናል ፤ ባለ ፡ ምግባር ፡ ነን ፡ የሚሉትን ፡ ተናገረ ።

እንዘ ፡ ውእቶሙ ፡ ውስተ ፡ መፍቅደ ፡ ጸጋ ፡ ዘለንስሓ ፡ ወጽድቅ ፡ እስመ ፡ ውእቶሙ ፡ ይመውቱ ።
ንስሓ ፡ ገብተው ፤ ትሩፋት ፡ ሠርተው ፡ ጸጋ ፡ ማግኘት ፡ ሲያሻቸው ፡ ይሞታሉና ።

ወአባ ፡ ሲሶይ ፡ አመረ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይመውቱ ፡ በጎጠውኢሆሙ ።
ሲሶይም ፡ በጎጢኢት ፡ ሳሉ ፡ የሚሞቱትን ፡ ተናግሯልና ፡ አይለያይም ፤ አንድ ፡ ነው ። አንድም ፡ ማርቆስ ፡ ንስሓ ፡ ገብተን ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ እንሠራለን ፤ ጸጋ ፡ ክብር ፡ አግኝተን ፡ እንጠቀማለን ፡ የሚሉ፡ የወጣንያንን ፡ ተናገረ ። ንስሓ ፡ ገብቶ ፤ ትሩፋት ፡ ሠርቶ ፡ የሚገኝ ፡ ጸጋን ፡ ሲሹ ፡ ይሞታሉና ፤ አባ ፡ ሲሶይ ፡ ግን ።

እንተ ፡ ነበሩ ፡ ባቲ ፡ እስክ ፡ ለሞት ፡ በበ ፡ ፍትወታቲሆሙ ።
እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ በፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ ተስበው ፡ ይሠሯት ፡ በነበረ ፡ በጎጢኢታቸው ፡ ሳሉ ፤ ሳይመለሱ ፡ የሚሞቱትን ፡ ተናግሯልና ፤ ስልቱ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

እስመ ፡ ዐመፁ ፡ እመንቱ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንተ ፡ በእንቲኣሃ ፡ ተሰብአ ።
ጌታ ፡ ሰው ፡ የሆነላት ፡ ንስሓን ፡ በድለዋልና ።

እስመ ፡ እግዚእ ፡ ክርስቶስ ፡ ይቤ ፡ ኢመጻእኩ ፡ እጸውዕ ፡ ጻድቃን ፤ አላ ፡ ኀጥኣን ፡ ለንስሓ ። (ማቴ፱ ፡ ፲፫) ።
ጌታ ፡ በወንጌል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ።

እስመ ፡ ኢኮነኬ ፡ እምኀቤሁ ፡ ጽርኅት ፡ ለበርየተ ፡ ኀጣውኢ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጎጢአትን ፣ ለማስተስረይ ፣ ንስሓን ፣ ያላዘዘበት ፣ ጊዜ ፣ የለምና ።

ወዘሰኬ ፣ ይትሔየይ ፣ በእንተ ፣ ንስሓ ፣ እስከን ፣ ይመውት ።

እስኪሞት ፣ ድረስ ፣ ንስሓን ፣ ቸል ፣ የሚል ፣ ግን ።

ይደየን ፣ ክመ ፣ ዘኢጸድቅ ፣ ወዘኢመሃይምን ።

እንደ ፣ ጎጥእ ፣ እንደ ፣ ኢአማኒ ፣ ይፈረድበታል ።

እስመ ፣ ውእቱ ፣ አጎጥኣ ፣ ለርእሱ ፣ ንስሓ ።

ንስሓ ፣ አልገባምና ።

እንተ ፣ ይእቲ ፣ ሀብት ፣ መንጽሐቶሙ ፣ ለጎጥኣን ፣ እምን ፣ መሃይምናን ።

ይሀችውም ፣ ከምእመናን ፣ ወገን ፣ ጎጥአንን ፣ የምታ ነጻቸው ፣ ሀብት ፣ ናት ።

ተስእሎ ፣ ፪፬፱ ።

ይቤሎ ፣ አኃው ፣ ምንትኑ ፣ ፍልጠት ፣ ማእክለ ፣ ንስሓ ፣ ወጽድቅ ።

አሁን ፣ ዘበንስሓ ፣ ወጽድቅ ፣ ያለውን ፣ ይዘው ፣ ይጠይቃሉ ። በጽድቅና ፣ በንስሓ ፣ መካከል ፣ ያለው ፣ መለያየት ፣ ምንድር ፣ ነው ።

ይቤ ፣ መተርጉም ፣ ንስሓሰኬ ፣ ይእቲ ፣ ጽድቅ ፣ ምስለ ፣ ትሕትና ።

ጽድቅሰኒ ፣ ይእቲ ፣ ንስሓ ፣ ምስለ ፣ ትሕትና ፣ ብለህ ፣ ግጠም ፤ ጽድቅ ፣ ያለው ፣ በትሕትና ፣ የሚሆን ፣ ንስሓ ፣ ነው ።

እስመ ፣ ለንሱስ ፣ ትዝኅርት ፣ ነክር ፣ እምኔሁ ።

ንስሓ ፣ የገባ ፣ ሰው ፣ ትዕቢት ፣ የለበትምና ።

ወለዘሰ ፣ ይገብር ፣ ጽድቀ ፣ ዘትርፍት ፣ እስመ ፣ ኢርኅቅት ፣ እምኔሁ ።

ትሩፋት ፣ የሚሠራን ፣ ግን ፣ ትዕቢት ፣ አትለየውም ።

እስመ ፣ ትዝኅርት ፣ ትተልዋ ፣ ለትርፍት ።

ትሩፋትን ፣ ትዕቢት ፣ ይከተላታልና ።

ብክመ ፣ ትጽሕፈ ፣ በእንተ ፣ ትሕትናሁ ፣ ለመጸብሓዊ ።

ስለይ ፣ ሊተ ፣ ለጎጥእ ፣ ያለው ፣ የመጸብሓዊ ፣ ትሕትና ።

ወጽደቀ ፣ ፈረሳዊ ።

ዘኢረሰይከኒ ፣ ክመ ፣ ዝንቱ ፣ መጸብሓዊ ፣ ያለው ፣ የፈረሳዊም ፣ ትዕቢት ፣ እንደ ፣ ተነገረ ። (ሉቃ፲፰ ፣ ፲—፲፬) ።

ተስእሎ ፣ ፪፻ ።

ይቤሎ ፣ አኃው ፣ እስመ ፣ እጙ ፣ ተስእሎ ፣ ለአባ ፣ ጴሜንን ፣ ተስእሎተ ፣ ወይቤሎ ፣ እንክ ።

አንድ ፣ መነኮሰ ፣ አባ ፣ ጴሜንን ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ ጠየቀው ።

እስመ ፣ ክልኤቱ ፣ ዕደው ፣ ነበሩ ።

ሁለት ፣ ሰዎች ፣ ነበሩ ።

አሐዱ ፣ እምኔሆሙ ፣ ባሕታዊ ።

አንዱ ፣ መነኮሰ ፣ ነው ።

ወአሐዱ ፣ ዓለማዊ ።

አንዱ ፣ ባለ ፣ ሕግ ፣ ነበር ።

ባሕታዊሰ ፣ ሐለየ ፣ በነፍሱ ፣ ሠርክ ፣ ክመ ፣ ውእቱ ፣ ይገድፍ ፣ በጽሕ ፣ አልባሰ ፣ ምንኮስና ።

ባሕታዊ ፣ ማታ ፣ ሲተኛ ፣ በልቡናው ፣ ነገ ፣ ቆቢን ፣ እጥላለሁ ፣ ምንኮስናዬን ፣ አፈርሰለሁ ፣ ብሎ ፣ አሰበ ።

ዓለማዊኒ ፣ ሐለየ ፣ በነፍሱ ፣ በእንተ ፣ ዘከመ ፣ ውእቱ ፣ በጽባሕ ፣ ይ… ብስ ፣ አልባሰ ፣ ምንኮስና ።

ዓለማዊም ፣ ነገ ፣ እመነኮሰለሁ ፣ ብሎ ፣ አሰበ ።

ወደይቀ ፣ ሞቆሙ ፣ በይእቲ ሌሊት ፣ (ሰዓት፲፪ ፣ ፷) ።

በዚያች ፣ ሌሊት ፣ ሁለቱ ፣ ሙተው ፣ አደሩ ።

ምንተ ፣ እንክ ፣ ይትሐሰብ ፣ ሎሙ ።

ምን ፣ ይቄጠርባቸዋል ፣ ምንስ ፣ ይቄጠርላቸዋል ፣ አለው ።

ወይቤሎ ፣ አረጋዊ ፤ እስመ ፣ መነኰስኒ ፣ ሞተ ፣ እንዘ ፣ ውእቱ ፣ መነኰስ ።

ጴሜንም ፤ መነኮሰው ፣ በምንኮስናው ፣ ሳለ ፣ ሞተ ።

ወዓለማዊኒ ፣ ሞተ ፣ እንዘ ፣ ውእቱ ፣ ዓለማዊ ።

ዓለማዊውም ፣ በዓለማዊነቱ ፣ ሳለ ፣ ሞተ ።

ወበክመ ፣ ተረክቡ ፣ ተንሥኡ ።

ሁለቱም ፣ እንዳሉ ፣ እንዳሉ ፣ ሄዱ ።

ይቤሎ ፣ አኃው ፣ ካዕበ ፤ ቦኑኬ ፣ ፍዳ ፣ በክመ ፣ አምጣን ፣ ምግባር ።

ካዕበ ፣ ለመጀመሪያው ፣ ነው ፤ በውኑ ፣ ፍዳ ፣ (ዋጋ) ፣ እንደ ፣ ሥራ ፣ መጠን ፣ ነውን ።

አው ፣ በክመ ፣ አምጣን ፣ ሕሊና ።

ወይስ ፣ እንደ ፣ ሕሊና ፣ መጠን ፣ ነውን ።

ይቤ ፣ መተርጉም ፣ ኢኮን ፣ ዘንረክብ ፣ ምግባራተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ውስተ ፣ ዝንቱ ፣ ዓለም ።

ፍትሐ ፣ እግዚአብሔርን ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ መርምረን ፣ የምናውቅ ፣ አይደለንም ።

እስመ ፣ ጽሑፍ ፣ ውእቱ ፤ ጥበቢሁ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ኢትትነሥሥ ።

የጌታ ፣ ፍርዱ ፣ እትመረመርም ፣ የሚል ፣ ጽሑፍ ፣ አለና ። (ጥበበ ፣ ሲራክ፣ ፸፪ናው፫) ።

ወጥበብከ ፣ ኦ እግዚኦ ፣ ክመ ፣ ቀላይ ፣ ዕምቅት ።

ፍርድህ ፣ ረቂቅ ፣ ነው ፤ ጥልቅ ፣ ነው ፣ ይላልና ። (ሮሜ ፲፩ ፣ ፴፫) ።

ወንሕነሰ ፣ ረሰይነ ፣ ለነ ፣ ተጎሥሦተ ፣ ንጹሓን ፣ ወአዝማደሙ ።

እኛ ፣ ግን ፣ የነጸላድዮስን ፣ ነገር ፣ የጠየቁትን ፣ ጥያቄ ፣ ለመተርጐም ፣ ሳዳጅ ፣ አድርገናል ። አንድም ፣ ቀጠሮ ፣ አድርገናል ።

በክመ ፣ ጸሐፉ ።

እንደ ፣ ጻፉት ፣ አድርገን ፣ ለመተርጐም ።

እስመ ፣ ጎበዕት ፣ ይእቲ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ አምላክነ ።

የጌታ ፣ ግን ፣ ፍርዱ ፣ ረቂቅ ፣ ናት ፣ እትመረመርም ።

አንድም ፤ እስመ ፣ ጎቡዓት ፣ ይላል ፤ ጎቡዓትን ፣ ማወቅ ፣ ለርሱ ፣ ብቻ ፣ ነው ።

ዘረክብናሰ ፣ እምገዝኔ ፣ ዓለም ።

በዚህ ፣ ዓለም ፣ ልንናገረውስ ፣ የሚገባ ፣ ነገር ፣ ይህ ፣ ነው ።

እስመ ፣ አባ ፣ ጴሜን ፣ ዘነ ፣ የአምር ፣ ሕሊናቲሆሙ ፣ ለብዙኃን ፣ እምባሕታውያን ።

አባ ፣ ጴሜን ፣ ከባሕታውያን ፣ ወገን ፣ ብዙዎቹ ፣ የሚያስቡትን ፣ አሳባቸውን ፣ ያውቅ ፣ ነበር ።

ወእምኔሆሙ ፣ ዘይጸንዕ ፣ ላዕሌሁ ፣ ተቃትሎተ ፣ ሰይጣናት ፣ በሌሊት ።

ከነሱ ፣ ወገን ፣ የሰይጣን ፣ ያር ፣ የሚጸናበትንም ፣ የማይጸናበትንም ፣ ለይቶ ፣ ያውቀው ፣ ነበር ።

ወፈድፋደሰ ፣ ሰይጣን ፣ ዝሙት ፣ በሌሊት ።

ይልቁንም ፣ ሰይጣን ፣ ዝሙት ፣ በሌሊት ፣ የሚዋጋውን ፣ ያውቅ ፣ ነበር ።

ከመ ፣ የሐሊ ፣ ውእቱ ፣ ክመ ፣ በሳኒታ ፣ ይግባእ ፣ ኀበ ፣ ዓለም ።

ነገ ፣ ወደ ፣ ዓለም ፣ እመለሳለሁ ፣ ብሎ ፣ እንዲያስብ ፣ መጠን ።

ወየአምር ፣ በእንተኣሆሙ ፣ ለዘኒ ፣ የኀድእ ፣ እምኔሁ ፣ ተቃትሎት ፣ ዘበእንተ ፣ ምንኮስና ።

ስለ ፣ ምንኮስና ፣ የሚመጣው ፣ ያር ፣ የሚጠፋላቸውን ፣ የማይጠፋላቸውን ።

ወፈድፋደሰ ፣ ለእለ ፣ ትሔውጸሙኒ ፣ ጸጋ ፣ ረድኤት ፣ በውስተ ፣ ቀትል ፣ ዕፀብት ።

ይልቁንም ፣ በያሩ ፣ ጊዜ ፣ ጸጋ ፣ እግዚአብሔር ፤ ረድኤት ፣ እግዚአብሔር ፣ የምትሰጣቸውን ፣ ያውቅ ፣ ነበር ።

ወውእቶሙ ፣ ብዙኃን ።

እሊህም ፣ ብዙ ፣ ናቸው ።

ወከማሁ ፣ ለብዙኃን ፣ እምዓለማውያን ፣ ዘይሔልዩ ፣ በእንተ ፣ ወሢአ ፣ እምዓለም ፣ ኀበ ፣ ምንኮስና ።

እንደ ፣ በሕታውያን ፣ ከዓለማውያንም ፣ ብዙዎቹ ፣ ከዓለም ፣ ወጥተው ፣ እንመነኰሳለን ፣ ብለው ፣ እንዲያስቡ ። አንድም ፣ የሚያስቡትን ። አንድም ፣ የሚያስቡ ፣ ብዙ ፣ እንደ ፣ ሆኑ ፣ ያውቅ ፣ ነበር ።

ወይጸርፀው ፣ እምፍናኖት ፣ መክልኢት ።

ትሩፋትን ፣ ከምትከለክል ፣ ከዓለማውያን ፣ ሥራ ፣ በ ብዙ ፣ ወገን ፣ እንዲሰነካከሉ ።

ወትትመሶ ፣ አልባቢሆሙ ።

ሕሊናቸው ፣ ተዳክማባቸው ፣ እንዲቀሩ ። አንድም ፣ የሚሰነካከሉትን ፤ ተዳክመው ፣ የሚቀሩትን ። አንድም ፣ የሚሰነካከሉ ፤ ተዳክመው ፣ የሚቀሩ ፣ ብዙ ፣ እንደ ፣ ሆኑ ፣ ያውቅ ፣ ነበር ።

ወበእንተገ ፣ ይቤ ፤ እስመ ፣ መነኰስኒ ፣ ሞተ ፣ እንዘ ፣ መነኰስ ፤ ወዓለማዊኒ ፣ ሞተ ፣ እንዘ ፣ ዓለማዊ ፣ ውእቱ ።

ስለዚህ ፣ ነገር ፣ መነኮሴው ፣ መነኮሰ ፣ ሳለ ፣ ሞተ ፤ ዓለማዊውም ፣ ዓለማዊ ፣ ሳለ ፣ ሞተ ፣ አለ ። እንደ ፣ ሁለት ፣ መነኰሳት ። ወደ ፣ አባ ፣ እንጦንዮስ ፣ ሲሄዱ ፣ ከበረሃ ፣ የሚኖር ፣ አንድ ፣ ፍጹም ፣ መነኮሴ ፣ አገኙ ። ወዲት ፣ ትሄዳላችሁ ፣ አላቸው ፤ ወደ ፣ አባ ፣ እንጦንዮስ ፣ አሉት ። ይህን ፣ በረሃ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ልትችሉት ፣ ብሎ ፣ እጁን ፣ ቢጸፋ ። ሁለት ፣ አዕዱገ ፣ ገዳም ፣ መጡ ፤ በአግር ፣ አትዘልቁምና ፣ በሊህ ፣ ሁና ችሁ ። ሂዱ ፣ አላቸው ። ተጭነው ፣ ሂደው ፣ ሲደርሱ ፣ መልሰው ፣ ሰደዷቸው ፤ ወዲያው ፣ በነዚያ ፣ ተሰነካከለ ። እንጦንዮስም ፣ ይህን ፣ ዐውቆ ፣ በረሃዉን ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ችላችሁ ፣ መጣችሁ ፣ አላቸው ። አባታችን ፤ አንድ ፣ ደግ ፣ ሰው ፣ አግኝተን ፣ እንዲህ ፣ አድርጎ ፣ ሰደደን ፣ እንጂ ፤ እኛማ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ እንዘልቀው ፣ ነበር ፣ አሉት ። ደግስ ፣ ደግ ፣ ነበረ ፤ ነገር ፣ ግን ፣ መልካክም ፣ ዕቃ ፣ ይዘ ፣ ያለ ፣ ቀዛፊ ፣ ከባሕር ፣ መካከል ፣ የቆመ ፣ መርከብን ፣ ይመስላል ፣ አላቸው ። ወዲያው ፣ ይህን ፣ ነግሯቸው ፣ ፊቱን ፣ እየ ፣ ጸፋ ፤ ጽሕሙን ፣ እየ ፣ ነጨ ፣ ያለቅስ ፣ ጀመረ ። አባታችን ፤ ምንድር ፣ ነው ፣ አሉት ። ሂዱ ፤ አሁን ፣ ከዛፍ ፣ ስር ፣ ቁሞ ፣ ሲያለቅስ ፣ ታገኙታላችኑ ፣ አላቸው ። ቢሄዱ ፣ እንደ ፣ ነገራቸው ፣ ሁኖ ፣ አገኙት ፤ ነገራቸው ። ወዲሁ ፣ ተመልሳችሁ ፣ ሂዱና ፣ ለአረጋዊ ፣ ንገሩልኝ ፤ ዓሥር ፣ ቀን ፣ ዕድሜ ፣ ሰዓተ ፣ ንስሓ ፣ እንዲያስጠኝ ፣ አላቸው ። የዚያ ፣ ምላሽ ፣ ሳይመጣለት ፣ ከመካከል ፣ እርሱ ፣ አርፏል ።

www.ethiopianorthodox.org

እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ ዘግቶ ፡ ትሩፋት ፡ የሠራ ፡ አንድ ፡ ባሕታዊ ፡ ነበር ። ሰይጣን ፡ በ ትዕቢት ፡ እጅ ፡ አደረገው ። ጌታ ፡ ዋጋህን ፡ ልስጥህ ፡ ቢለው ፡ እሺ ፡ ስጠኝ ፡ አለው ። እንደ ፡ ቸርነቱ ፡ ነውን ፡ እንደ ፡ ሥራህ ፡ ቢለው ፤ እንደ ፡ ሥራዬ ፡ ስጠኝ ፡ እንጂ ፡ የቸርነትህንስ ፡ ለሰብአ ፡ ዓለም ፡ አድርገው ፡ አለው ። እንዲህ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተለየው ። የረኃብ ፡ ያር ፡ ተነሣበት ፤ ከ ገቢያ ፡ ገብቶ ፡ ምግብ ፡ የሚሸጡትን ፡ ሂዶ ፡ ስጡኝ ፡ አላቸው ፤ ዋጋ ፡ አምጣ ፡ አሉት ። እኔ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለኝ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ ዘግቼ ፡ ትሩፋት ፡ ሠርቻለሁ ፤ ኻያው ፡ ዘመን ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ፡ አላቸው ። ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስጠርተው ፡ ሰጡት ። ያን ፡ በልቶ ፡ ሲያበቃ ፡ ደግሞ ፡ የጽምዕ ፡ ያር ፡ ተነሣበት ፤ ውሀ ፡ ጠማው ። መጠጥ ፡ የሚሸጡትን ፡ ሂዶ ፡ ስጡኝ ፡ አላቸው ፤ ዋጋ ፡ አምጣ ፡ አሉት ። ዋጋም ፡ የለኝ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ ዘግቼ ፡ ትሩፋት ፡ ሠርቻለሁ ፡ ኻያው ፡ ዘመን ፡ ለናንተ ፡ ይሁናችሁ ፡ አላቸው ። ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስጠርተው ፡ ሰጡት ። ያንንም ፡ ያንንም ፡ ተመግቦ ፡ ሲወጣ ፡ በገዳም ፡ ሳለ ፡ የለመዳት ፡ ቁጽለ ፡ ዕፅ ፡ ነበረች ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ይሂት ፡ ሲገባ ፡ አየ ። ሂዶ ፡ ይህችን ፡ ቅጠል ፡ አባክህ ፡ አለው ፤ ዋጋ ፡ አምጣ ፡ አለው ። ከዚህ ፡ መካከል ፡ መልአኩ ፡ አንተ ፡ ምግባርህን ፡ ሽጠህ ፡ ጨረስህ ፤ ደግሞ ፡ ሃይማኖትህን ፡ ልትሸጠው ፡ ነውን ፡ ብሎ ፡ ገሠጸው ። ደንግጾ ፡ ሂዶ ፡ ከአባ ፡ ዳንኤል ፡ ገዳም ፡ ገባ ። ወዲያው ፡ ቀኖናውን ፡ ዓሥራምስት ፡ ዓመት ፡ ሰጠው ፤ ሳይፈጽመው ፡ ሙታል ። አባ ፡ ዳንኤል ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሁኖ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ ቢያመለክት ፤ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ በጎረ ፡ ገነት ፡ ይኖራል ፤ ኋላ ፡ በምጽአት ፡ ዋጋዉን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ብሎታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ወአእምሮተ ፡ ፍዳስ ፡ በውቀት ።

ይህን ፡ ነገር ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ አይቻልም ።

አእምሮታዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባሕቲቱ ።

ይህንስ ፡ ማወቅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ። አንድም ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ይህን ፡ ፈጽሞ ፡ ማወቅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለሌላ ፡ አይደለም ።

ተስእሎ ፡ ፻፸፩ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፡ ወለውእቱኬ ፡ እጐ ፡ ዘሖረ ፡ ኀበ ፡ ዓለም ።

የዚያሳ ፡ መነሡሲ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ የሄደው ።

ወአውሰበ ፡ ብእሲተ ።

ሚስት ፡ ያገባው ።

ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ አረጋዊ ፡ መምህሩ ።

መምህሩ ፡ አረጋዊ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ።

ጸለየ ፡ በእንቲኣሁ ።

ያዘነለት ፤ የጸለየለት ።

ወጎሠሠ ፡ እምእግዚእነ ።

ከጌታ ፡ የለመነለት ።

እንዘ ፡ ይብል ፤ ኢትጎድን ፡ ለገብርከ ፡ ይርኩስ ።

ባሪያህን ፡ በገቢር ፡ ፈጽሞ ፡ ይበድል ፡ ዘንድ ፡ በረደኤት ፡ አትለየው ፡ ብሎ ።

ወሶበ ፡ ዐእ ፡ ኀበ ፡ መርዓት ።

መጋረጃ ፡ ገልጦ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ።

መጠወ ፡ መንፈሶ ፡ በጊዜሃ ።

ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ተለየች ።

ዐጉ ፡ ሞተ ፡ እንዘ ፡ ባሕታዊ ፤ አው ፡ እንዘ ፡ ዓለማዊ ።

ይኽሳ ፡ ባሕታዊን ፡ ሁኖ ፡ ሞተ ፤ ወይስ ፡ ዓለማዊ ፡ ሁኖ ፤ ይህ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ። (ታሪክ) ፤ ወሬዛ ፡ እስክንድርያዊ ፡ ይለዋል ፤ ከገዳሙ ፡ ሊወጣ ፡ ሲነሣ ፡ አንተ ፡ ተው ፡ እትውጣ ፡ ያር ፡ ይነሣብሃል ፡ አሉት ። እኔ ፡ አባ ፡ ብሎ ፡ ተመክቶ ፡ ወጣ ። ወዲያው ፡ ውሀ ፡ የሚቀዱ ፡ ሴቶች ፡ አግኝቶ ፡ ተስቧል ፡ ይላሉ ። ይህስ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፤ ከመሸተኛ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ በልቶ ፡ ጠጥቶ ፡ ሲያበቃ ፡ ወዲያው ፡ ተስቧል ፤ መጋረጃ ፡ ገልጦ ፡ ሲገባ ፡ እባብ ፡ ነድፋው ፡ ሙታል ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ ወለዛቲኒ ፡ ካዕበ ፡ አእምሮታ ፡ ዕፅብት ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ።

ይህንም ፡ ማወቅ ፡ ለሰው ፡ አይቻልም ፤ ጭንቅ ፡ ነው ።

ወባሕታዊሰ ፡ በአምጣነ ፡ ጎሠሣው ፡ ለብእሲ ፡ ይብል ፡ ሞተ ።

ባሕታዊ ፡ ጴሜን ፡ ግን ። አንድም ፡ ባሕታዊ ፡ መምሩ ፡ ለዚያ ፡ ሰው ። አንድም ፡ ለብእሲ ፡ ባሕታዊ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ባሕታዊ ፡ ረዱ ፤ አረጋዊ ፡ መምሩ ፡ እንደ ፡ ለመነለት ፡ መጠን ።

ዝንቱኒ ፡ እጉ ፡ ካዕበ ፡ ክመ ፡ ገዝኩ ፡ እንዘ ፡ መነኰስ ።

ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ፈት ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ በምን ዅስና ፡ ሞተ ፡ አለ ።

ወባሕቱ ፡ ወሰከ ፡ ሳዕሌሁ ፡ እሳተ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እሳተ ፡ ገሃነምን ፤ ሥቃየ ፡ ፍዳን ። አንድም ፡ ንስሓውን ፡ ቀኖናዉን ፡ ተቀበለ ። አንድም ፡ ሥጋሃ ፡ ለብእሲት ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ እንብልብልት ፡ እንዲል ፤ በያር ፡ ላይ ፡ ያርን ፡ የገላ ፡ ሙቀትን ፡ ጨመረ ፡ አለ ።

በጎሢመ ፡ ፈቃዱ ፡ በእንተ ፡ ፍትወት ፡ ፈድፋደ ።

የፈቲው ፡ ያር ፡ ተነሥቶበት ፡ ፈቃዱን ፡ በገቢር ፡ መፈጸም ፡ ስለ ፡ ወደደ ።

ወለክልኤሆሙ ፡ ረከበቶሙ ፡ ኂሩተ ፡ እግዚአብሔር ።

ለሁለቱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ይቅርታ ፡ ምሕረት ፡ ተሰጠቻቸው ።

ወእጽርዐቶሙ ፡ እምፈጽሞ ፡ ሥጫረ ፡ ምንዅስና ፡ በገቢር ።

ምንዅስናን ፡ በገቢር ፡ ፈጽሞ ፡ ከማፍረስ ፡ ከለከለቻቸው ።

ወአበው ፡ ካልኣንሰ ፡ ለአልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ አርድእቲሆሙ ።

ሌሎቹ ፡ አበው ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አርድእቶቻቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመኑት ።

ክመ ፡ ገ ።

እንደዚህ ፡ አረጋዊ ።

ወኢሰምዐ ፡ እምኔሆሙ ።

ልመናቸውን ፡ አልሰማቸውም ፤ ባይሰማቸው ።

ወፈጸሙ ፡ አርዳኢሆሙ ።

ጎጠአታቸውን ፡ በገቢር ፡ ፈጸሙ ።

ወጎለፉ ፡ በድቀቶሙ ።

በጎጠአታቸው ፡ ተሰነካክለው ፡ ሞቱ ።

ወበእንተዝ ፡ ረከበቶ ፡ ለዝንቱሰ ፡ ኂሩቱ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ለዚህ ፡ ግን ፡ ምሕረት ፡ የተሰጠችው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ውእቱኬ ፡ እመ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ አረጋዊ ፡ መምህሩ ።

ሌላም ፡ ባይሆን ፡ አረጋዊ ፡ መምሩ ፡ ስላዘነለት ፡ ይሆናል ።

እስመ ፡ መፍቅዱ ፡ በውስተ ፡ ስእለቱ ፡ ክመ ፡ ይኩን ፡ ረድኡ ፡ ጕሶቀ ፡ ምስለ ፡ ባሕታውያን ።

በጸሎቱ ፡ የሚሻው ፡ ነገር ፡ ረድኡ ፡ ከባሕታውያን ፡ ጋራ ፡ ይቄጠር ፡ ዘንድ ፡ ነውና ።

ክመ ፡ ይትፈደይ ፡ ክመ ፡ ባሕታዊ ።

ያው ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ባሕታዊ ፡ ዋጋዉን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

አው ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ አእመረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምግእዙ ፡ ክመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ድልወ ፡ ለገዝኑቱ ።

ወይም ፡ ጌታ ፡ ለዚህ ፡ ድሳነት ፡ የበቃ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጠን ፡ ግብሩን ፡ ስላወቀ ፡ ይሆናል ፤ እንደ ፡ ሆነም ፡ እንጂ ።

ወክመ ፡ ውእቱ ፡ ተገበረ ፡ በእንተዝ ፡ ፈቀደ ፡ ኪያሁ ።

ሰይጣን ፡ አገብሮት ፡ ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ስላወቀ ፡ ይሆናል ፤ እንደ ፡ ሆነም ፡ እንጂ ።

አው ፡ በእንተ ፡ ውርዝውናሁ ።

ወይም ፡ ሕጸን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይሆናል ።

አው ፡ በእንተ ፡ መጊኦተ ፡ ሰይጣናት ፡ መስተጋድላን ።

ወይም ፡ በገዘሙት ፡ የሚዋጋው ፡ ሰይጣን ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ነሣው ፡ ስላወቀ ፡ ይሆናል ።

አው ፡ በእንተ ፡ ድካመ ፡ ፍጥረቱ ፡ ወእእምሮቱ ።

ወይም ፡ ባሕርዩ ፡ ደክሞ ፡ አእምሮው ፡ ተነሥቶት ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ስላወቀ ፡ ይሆናል ።

አው ፡ በእንተ ፡ ዘአእመረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኂሩቱ ፡ ዘአቅደመ ፡ እምቅኑሙ ።

ወይም ፡ ከርድና ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ አስቀድሞ ፡ የሠራውን ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡ ስላወቀ ፡ ይሆናል ።

ወትሕትናሁ ።

ከትሕትና ፡ ወገን ፡ ትሕትናውን ።

ወኦሆ ፡ ብሂሎቱ ፡ ለመምህሩ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ፡ መታዘዝ ፡ ይሆንልኛል ፡ ብሎ ፡ ለመምሩ ፡ እሺ ፡ በጎ ፡ ማለቱን ፡ ስላወቀለት ።

እስከነ ፡ ረድኡ ፡ ኢያውዕዐ ።

ረድኡ ፡ እስክለማግባት ፡ ደረሰ ።

ወእፎኒ ፡ ዘኢሐይወ ።

እንኪያ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ያልኖረ ።

ወኢገብአ ፡ ኀቤሁ ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ብሕትውና ፡ ዘበሥምረት ፡ ወገቢር ።

በፈቃድ ፡ ትሩፋት ፡ እየ ፡ ሠራ ፡ በተባሕትዎ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አረጋዊ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ያልተመለሰ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ።

ወእእምሮተ ፡ ዝንቱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአኮ ፡ ለእንዳለ ፡ እመሕያው ፡ በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ።

ይህንንስ ፡ ማወቅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላለ ፡ ለመዋቲ ፡ ሰው ፡ አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

ተስእሎ ፤ ፪፻፪ ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፤ እስመ ፡ አባ ፡ ጲሜን ፡ ይቤ ፤ ሶሎ ፡ ጊዜ ፡ ዘይወድቅ ፡ ብእሲ ፡ በእይኒ ፡ ታሕጸጽ ፡ ወዕበድ ፡ ዘኮነ ።

በማናቸውም ፡ ኀጢአት ፤ በማናቸውም ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ የሚሰነካከል ፡ ሰው ።

ወይብል ፡ በጊዜሃ ፡ አበስኩ ፤ ይትዌከር ፡ እግዚአብሔር ።

ወዲያው ፡ ተመልሶ ፡ በደልሁ ፡ ማረኝ ፡ ቢል ፡ ንስሓውን ፡ ይቀበለዋል ፡ አለ ፤ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ።

ይቤ ፡ መተርጉም ፤ ወኀጣውኦስ ፡ እንተ ፡ እምቅድመ ፡ ጥምቀት ፡ በጥምቀት ፡ ይሰረይ ።

ከጥምቀት ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ኀጣውኡ ፡ በጥምቀት ፡ ይሰረያሉ ።

እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውእቱ ፤ ነስሑ ፡ ወይጠመቅ ፡ ሶሎ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኔክሙ ፡ በስመ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለስርየተ ፡ ኀጣውእ ።

ነስሑ ፡ ወተጠመቁ ፡ ለስርየተ ፡ ኀጣውእ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለና ። (ግብ፲ ፤ ፲፱) ።

ወኀጣውእሰ ፡ እንተ ፡ እምድኅረ ፡ ጥምቀትኒ ፡ ትሰረይ ፡ በምሥጢራተ ፡ ቅድሳት ።

ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ የሚሠሩ ፡ ኀጣውእ ፡ ግን ፡ በሥጋው ፡ በደሙ ፡ ይሰረያሉ ።

እስመ ፡ ይቤ ፡ ክርስቶስ ፤ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋየ ፡ ወደምየ ፡ ዘበእንቲኣ ክሙ ፡ ይትፈተት ፡ ወይትከፀው ፡ ለስርየተ ፡ ኀጣውኡ ።

ጌታ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ። (ማቴ፳፮ ፡ ፳፰—፳፰) ።

ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ኀጢአት ፡ ዓባየ ፡ ዘነመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ ክመ ፡ ይእቲ ፡ ታርኅቅ ፡ እመንግሥት ።

ምንም ፡ ኀጢአት ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታርቃለች ፡ ብሎ ፡ ሐዋርያ ፡ እንደ ፡ ተናገራት ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ኀጢአት ፡ ያለች ፡ ብትሆን ።

ዘቲኒ ።

ይህችም ።

ለእመ ፡ ፈጸመ ፡ ጎጥእ ፡ ቀኖናሁ ፡ እንተ ፡ ይትቄበላ ፡ እመምህራኒሁ ።

ኀጥእ ፡ ከመምህረ ፡ ንስሓው ፡ የተቀበላትን ፡ ቀኖናውን ፡ ቢፈጽም ።

ካዕበ ፡ ለእመ ፡ ተመጠወ ፡ ምሥጢራተ ፡ አምላክነቱ ።

መምህረ ፡ ንስሓው ፡ ያዘዘውን ፡ ሠርቶ ፡ ሥጋዉን ፡ ደሙን ፡ ቢቀበል ።

ወነፍሱ ፡ እንዘ ፡ ምልዕት ፡ ሕማማተ ።

ልቡናው ፡ እያዘነ ።

ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ንሑሕ ፡ በእንተ ፡ ኀጣውኢሁ ።

ይኸውም ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ንስሓ ፡ ገብቶ ፡ ነው ። ትች ፤ ኀጢአቱን ፡ አስቦ ፡ እያዘነ ፡ እየ ፡ ተጸጸተ ፡ ቢሆን ፡ ነው ።

እስመ ፡ ይእቲ ፡ ትሰረይ ፡ ሶቱ ።

ይሰረይለታልና ።

ወለእመ ፡ አብደ ፡ ብእሲ ፡ ዲበ ፡ እጉሁ ፡ በአይኒ ፡ አበድ ፡ ዘኮነ ።

ሰው ፡ ወንድሙን ፡ በማናቸውም ፡ በደል ፡ ቢበድል ።

ወይገብር ፡ ሶቱ ፡ ስግደተ ፡ ዘበትሕትና ፡ ልብ ።

በትሕትና ፡ ልብ ፡ ሁኖ ፡ ከጫማው ፡ ወድቆ ፡ ማረኝ ፡ ቢለው ።

ወይብል ፡ አበስኩ ።

በደልኩ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ቢለው ።

